# የአማራ ክልል
# የመረጃ መጽሐፍ

የ2016 ዓ.ም ህትመት



በመንግስት ኮሙዩኒኬሽን ቢሮ
በሚዲያ ልማት፣
የፖሊስ ጥናትና አብዝሃነት
ዳይሬክቶሬት በመንግስት ፖሊሲ አፈፃፀም
ትንተና ቡድን የተዘጋጀ

የካቲት 2017 ዓ.ም

# የአማራ ክልል የመረጃ መጽሐፍ

## የ2016 ዓ.ም ህትመት

በመንግስት ኮሙዩኒኬሽን ቢሮ በሚዲያ ልማት፣ የፖሊስ ጥናትና አብዝሃነት ዳይሬክቶሬት በመንግስት ፖሊሲ አፈፃፀም ትንተና ቡድን የተዘጋጀ

## የ ኢትዮጵ ራዕይ

በህዝብ ተሳትፎና በህዝቦች መፈቃቀድ ላይ የተመሠረተ ዴሞክራሲያዊ ስርዓትና መልካም አስተዳደር የሰፈነባት፣ ማህበራዊ ፍትህ የነገሠባትና ከድህነት ተላቃ መካከለኛ ገቢ ያላት ኢትዮጵያን እውን ማድረግ ነው!

## የ ክ ል ሉ ራ ዕ ይ

አስተማማኝ ሠላም፣ ዴሞክራሲና መልካም አስተዳደር የሠፈነበት፣ማህበራዊ ፍትህ የነገሰበት፣ ከድህነት የተላቀቀና መካከለኛ ገቢ ያለው ክልል እውን ሆኖ ማየት!

## የ ቢሮው ራ ዕ ይ

በመረጃ የበለገፀ፣ ሁለገብ ተሳትፎ የሚያደርግ፣ በመሠረታዊ ክልላዊና ሀገራዊ ጉዳዮች መግባባት የፈጠረ ህዝብ እውን ሆኖ ማየት!”

የመጀመሪያው ህትመት "ብሔረ አማራ" በሚል መጠሪያ በ1995 ዓ.ም ተዘጋጀ፡፡ ከ2013 ዓ.ም ጀምሮ ደግሞ "የአማራ ክልል የመረጃ መጽሐፍ" በሚል ስያሜ መዘጋጀት ጀመረ፡፡



አቶ አረጋ ከበደ

## የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት

## ርዕሰ መስተዳደር

## የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት መስተዳድር ምክር ቤት ካቢኔ አባላት

| | | |
|---|---|---|
| <br>አቶ አረጋ ከበደ<br>ዕርሰ መስተዳድር | <br>ዶ/ር አብዱ ሁሴን<br>ም/ርዕሰ መስተዳድር | <br>ዶ/ር መንገሻ ፈንታው<br>የመንግስት ኮሙኒኬሽን ቢሮ ሀላፊ |
| <br>አቶ ሀይሌ አበበ<br>የማዕድን ሀብት ቢሮ ሀላፊ | <br>ዶ/ር አሕመዲን ሙሐመድ<br>በምክትል ርዕሰ መስተዳድር ማዕረግ የከተሞች ልማት ዘርፍ አስተባባሪ እና የከተማ እና መሰረተ ልማት ቢሮ ሀላፊ | <br>ዶ/ር ድረስ ሳህሉ<br>በምክትል ርዕሰ መስተዳድር ማዕረግ የገጠር ክላስተር አስተባባሪና የግብርና ቢሮ ሀላፊ |
| <br>አቶ አብየ ካሳሁን<br>የጠቅላይ ፍርድቤት ቢሮ ሀላፊ | <br>ዶ/ር ማማሩ አያሌው<br>ውሃና ኢነርጅ ቢሮ ሀላፊ | <br>ዶ/ር ኢንጅነር ዳኘነት ፈንታ<br>የመስኖና ቆላማ አካባቢዎች ልማት ቢሮ ሀላፊ |

| | | |
|---|---|---|
| <br>ዶ/ር ደመቀ ቦሩ ባህሩ<br>የፕላንና ልማት ቢሮ ሀላፊ | <br>ወ/ሮ ብርቱካን ሲሳይ<br>የሴቶች፤ህፃናትና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ ሀላፊ | <br>አቶ እርዚቅ ኢሳ<br>የወጣቶችና ስፖርት ቢሮ ሀላፊ |
| <br>አቶ ሲሳይ ዳምጤ<br>የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ቢሮ ኃላፊ | <br>አቶ ተስፋሁን አለምነህ<br>የአካባቢና ደን ጥበቃ ባለስልጣን | <br>ዶ/ር ሙልነሽ ደሴ<br>የትምህርት ቢሮ ሀላፊ |
| <br>ዶ/ር ጥላሁን ማህሪ<br>የገንዘብ ቢሮ ሀላፊ | <br>ዶ/ር ጋሻው አወቀ<br>የመንገድ ቢሮ ኃላፊ | <br>አቶ ክብረት ማህሙድ<br>ገቢዎች ቢሮ ኃላፊ |
| <br>አቶ አብዱልከሪም መንግስቱ<br>ጤና ቢሮ ሃላፊ | <br>ዶ/ር ስቡህ ገበየሁ<br>የስራና ስልጠና ቢሮ ሀላፊ | <br>አቶ ብርሃኑ ጎሽም አዘረፍ<br>የፍትህ ቢሮ ሀላፊ |

| | | |
|---|---|---|
| <br>አቶ እንድሪስ አብዱ<br>የኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት<br>ቢሮ ሀላፊ | <br>ወ/ሮ ባንችአምላክ ገ/ማርያም<br>የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን | <br>አቶ መልካሙ ፀጋየ<br>የባህልና ቱሪዝም ቢሮ ሀላፊ |
| <br>ዶ/ር ኢብራሂም መሀመድ<br>የንግድና ገበያ ልማት ቢሮ ሀላፊ | . | . |

## የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት

## ብሔራዊ ዓርማ

<u>የዓርማው ትርጉም</u>

የስንዴ ዘለላ - የእርሻውን ክፍለ ኢኮኖሚ

ጊሩ - የኢንዱስትሪውን ክፍለ ኢኮኖሚ

እርግቧ - ሠላምን

ሚዛኑ - ፍትህና ዲሞክራሲን

የላሊበላና የፋሲል ግንብ - የክልሉን ታሪክ የቅርስ ሃብት

የጭስ ዓባይ ፏፏቴ - የክልሉን የተፈጥሮ ሃብት ያመላክታል፡፡

## የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት

## የሕዝብ መዝሙር



የታታሪ ሕዝቦች - - - የታሪክ ማህደር፣

የአኩሪ ባህል አምባ - - - የድንግል ሀብት አፌር፡፡

የሕዝቦችሽ ተስፋ - - - - ለሚ ክልላችን፣

በሠላም በፍትህ - - - በልማት ጉዟችን፣

ተባብረን በሥራ - - - እንገነባሻለን፡፡

የአማራነትን ክብር - - - ደማቅ አርማ ይዘን፣

ከሌሎች ሕዝቦች ጋር - - - እኩል ተከባብረን፣

በፍቅር በአንድነት - - - አብርን እንዘልቃለን፡፡

## ማውጫ

ርዕስ ጉዳይ ገጽ


- የቢሮ ሀላፊ መልዕክት

I. የአማራ ክልል በጥቂቱ---------------------------------------------------------------------

II. ኢኮኖሚ ዘርፍ

- ግብርና ልማት---------------------------------------------------------------------------
- መንገድ ልማት ----------------------------------------------------------
- ከተማና መሰረተ ልማት
- ህዳሴ ግድብ…………………………………………….
- ህብረት ስራ ማህበራት ማስፋፊያ…………………………..
- ንግድና ገበያ ልማት……………………………………………………………..
- ውሀ እና ኢነርጅ…………………………………………………………………
- እንስሳት እና አሳ ሀብት ልማት……………………………………………..
- ፕላንና ልማት……………………………………………………………………
- አካባቢና ደን ጥበቃ…………………………………………………………
- ኢንዱስትሪናኢንቨስትመንት ልማት…………………………………………………
- ግብርናምርምር……………………………………………………………………
- መስኖ እና ቆላማ አካባቢዎች ልማት………………………………………………
- መሬት ልማት……………………………………………………………………
- ገቢ……………………………………………………
- ማዕድን ሀብትልማት…………………………………………………………………..
- ስራና ስልጠና ……………………………………………………………
- አደጋ መከላከልና ምግብ ዋስትና…………………………………………….
- ገንዘብና ልማት…………………………………………………..

III. ማህበራዊ ዘርፍ

- ትምህርትና ስልጠና-----------------------------------------------------
- ባህልና ቱሪዝም…………………………………………………
- ጤና ……………………………………………………………………………

- ሲቪልሰርቪስና የሰው ሀብትአስተዳደር……………………………………………
- ሴቶች፤ህጻናትና ማህበራዊ ጉዳይ…………………………………………………
- ወጣቶችና ስፖርት ልማት…………………………………………………………..
- አማራ ህዝቦች ሰማዕታት መታሰቢያ ……………………………………………
- ሙያ ብቃት ምዘና ማረጋገጫ……………………………………………………

IV. መልካም አስተዳደር ዘርፍ

- ርዕሰ መስተዳድር…………………………………………………
- ክልል ምክር ቤት…………………………………………………
- የመንግስት ኮሙዩኒኬሽን…………………………………………
- ጠቅላይ ፍርድ ቤት………………………………………………
- ፍትህ……………………………………………………………………
- ስነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና…………………………………………………
- አማራ ሚዲያ ኮርፖሬሽን…………………………………………
- ዋና ኦዲተር……………………………………………………………..

V. አጠቃላይ መረጃ

- በክልል የሚገኙ ልዩ ልዩ መስሪያቤቶች አድራሻ----------------------------------------
  - በክልሉ የሚገኙ የትምህርት፣ የጤና፣ የትምህርት መገናኛ ፤የግብርና ኮሌጆችና ማሰልጠኛ ተቋማት አድራሻ----------------------------------------------------------------
  - በክልሉ የሚገኙ ዞኖችና ሪጅኦ ፖሊታን ከተሞች ……………………………………
  - በክልሉ የሚገኙ ዋና ዋና ወንዞች፣ሐይቆችና ተራሮች ---------------------------
  - በክልሉ የሚገኙ ዋና ዋና የቱሪስት መስብህ ሀብቶች------------------------------
  - ባለኮከብ ሆቴሎች------------------------------
  - በክልሉ የሚገኙ ዞኖችና ወረዳዎች -------------------------------------------------------

## የቢሮ ሀላፊው መልዕክት



የሚዲያ እና ኮሙዩኒኬሽን ዘርፉ የሀገራችን ፖለቲካ ከመጣበት ተናጠላዊ ትርክት ወጥቶ አሰባሳቢ ትርክት እንዲፈጠር በማድረግ ኢትዮጵያ ቀጣይ ለምታሳካዉ የብልጽግና ጉዞ የድርሻውን እንዲወጣ እየተሰራ ነው። የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ህገመንግስታዊ የፌድራል ስርዓትን በመተግበር በክልሉ በኢኮኖሚያዊ፣ፖለቲካዊና ማህበራዊ ዘርፎች የህዝቡን እኩል ተጠቃሚነት እና ፍትሐዊነት ማረጋገጥ የሚያስችል አሰራር ዘርግቶ እየሠራ ይገኛል።

የአማራን ህዝብ በተሳሳተ ትርክት፣ በጥላቻ እና ጥርጣሬ እንዲታይ ያደረገውን የፖለቲካ ሴራና የሀሰት ፕሮፓጋንዳ በመቀልበስ በምትኩ የጋራ ብሔራዊ ትርዕክት እንዲገነባም በቁርጠኝነት በመስራት ላይ ነው። ይሄን በተሟላ ደረጃ ለመተግበር የሚዲያና ኮሙኒኬሽን ዘርፉ ትልቅ ሀላፊነት ወስዶ እየሰራ ሲሆን መንግስታዊ አፈፃፀሞችን ለሕዝብ ተደራሽ በማድረግ፤ ህዝብና መንግስትን በማገናኘት፣ ግልፅና ተአማኒ መረጃዎችን ለህዝብ በመስጠት፤ በህዝብ እና መንግሥት መካከል መልካም መስተጋብር እንዲኖር የማድረግ ሚናውን እየተወጣ ይገኛል።

ህዝባችን ለሀሰት ፕሮፓጋንዳ እና ለተለያዩ አሉቧልታዎች ሰለባ እንዳይሆን አሁናዊ፤ ትክክለኛ እና ታማኝ መረጃዎችን በማሰራጨት በክልላችን አንፃራዊ ሠላም እንዲመጣ የበኩሉን ድርሻ በመወጣት ረገድ ዘርፉ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክቷል። እያበረከተም ይገኛል።በተጨማሪም የሚዲያና ኮሙዩኒኬሽን ዘርፉ የሰላና የተሣለጠ ተግባራትን በማከናወን ዘመኑን የሚመጥን ቴክኖሎጅን በመጠቀም እንደ ትልቅ መሸጋገሪያ ድልድይ ሆኖ እያገለገለ የሚገኝበትን መልካም ጅማሮ በማስቀጠል በቀጣይ በተሟላ ደረጃ ቴክኖሎጂን አሟጦ በመጠቀም ለመስራት እየተጋ ይገኛል።

በክልላችን የተከሰተውን የፀጥታ ችግር ለመቀልበስ በተደረገው ርብርብና የክልሉን አንጻራዊ ሰላም በማስፈን ረገድ የክልላችን የሚዲያና ኮሙኒኬሽን ዘርፍ እየተጫወተ ያለው ሚና በትንሹ የሚተመን አይደለም።ለዚህም ህዝባዊ ውይይቶችን በማደራጀት፣ ወቅታዊ መግለጫዎችን፣ ዜናዎችን፣ መልእክቶችን እና የመሳሰሉትን በህትመትና በኤሌክትሮኒክስ እንዲሁም በማህበራዊ የሚዲያ አማራጮች ለህዝብ ተደራሽ በማድረግ ትልቅ ሚና አበርክቷል። እያበረከተም ይገኛል።በተለይ በተለያዩ ከተሞች በተካሄዱ ሕዝባዊ ውይይቶች እና በተሠሩ የኮሙኒኬሽንና የሚዲያ ስራዎች አሁን ላይ በክልሉ አንጻራዊ ሰላም እንዲሰፍንና ህዝቡ በውሸት ፕሮፖጋንዳ ሳይደናገር የእለት ተእለት ተግባሩን እንዲያከናውን ማድረግ ተችሏል።

በፖለቲካ ልዩነት ብቻ ነፍጥ አንግበው ጫካ የሚንቀሳቀሱና ለክልሉ ሰላም ማጣት ምክንያት የሆኑ ሀይሎች ወደ ሰላም እንዲመጡ ህዝብና መንግስት በተደጋጋሚ ያቀረቡትን የሰላም ጥሪ ተደራሽ በማድረግ ረገድም የሚዲያና ኮሙኒኬሽን ዘርፉ ትልቅ አወንታዊ ሚና ተጫውቷል።በዚህም በክልሉ በተለያዩ አካባቢዎች የመንግስትና የህዝብን የሰላም ጥሪ መነሻ በማድረግ በሁሉም አቅጣጫ የሰላም አማራጭን መርጠው የሚመጡ የታጣቂ ሀይሎች ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እንዲጨምር ያላሰለሰ ጥረት አድርጓል። እያደረገም ይገኛል።

በክልላችን የተፈጠረውን የፀጥታ ችግር እንደ መልካም አጋጣሚ በመቁጠር የህገ ወጥ ነጋዴዎች መበራከት፤ በሸቀጦች ላይ ያልተገባ የዋጋ ጭማሪ በማድረግ እና አጠቃላይ በማህበረሰቡ ላይ የኑሮ ውድነት እንዲፈጠር የሚያደርጉ አካላትን በማጋለጥ ረገድም በውስንም ቢሆን ችግሩ እንዲቀረፍ መረጃዎችን ለህዝብና መንግስት በማድረስ የኮሙኒኬሽን ሚናውን እየተወጣ ይገኛል።

በክልላችን የተረጋጋ የኢኮኖሚ ሥርዓት እንዲዘረጋና የልማት ተደራሽነት እንዲረጋገጥ በግብርናው፣ በጤናው፣ በሠላምና ፀጥታ፣ በትምህርት፣ በአረንጓዴ አሻራ፣ በሌማት ትሩፋት፣ በኮሪደር ልማትና እንዲሁም በቴክኖሎጂው ዘርፍ ከፍተኛ ለውጥ እንዲመጣ እየተሰራ ያለውን ተግባር ለህዝብ አይንና ጆሮ ተደራሽ ከማድረግ አንፃርም ከላይ እስከ ታች ያለው የኮሙኒኬሽን ተቋም የበኩሉን ሚና ተጫውቷል።

በመጨረሻም የኮሙዩኒኬሽን ቢሮ የተሳሳቱና አፍረሽ ዘገባዎችን በመመከት የሀገራችንና የክልላችን ገጽታ ለመገንባት በተለይም በክልሉ በሁሉም ዘርፎች የሚሰሩ የልማት፣ የሰላም እና የመልካም አስተዳደር ተግባራትን በአጠቃላይም በመረጃ የበለፀገ ህዝብና መንግስት እንዲኖር እንደዚህ ቀደሙ ሁሉ የመረጃ ሰጭነት ሀላፊነቱን ሙሉ በሙሉ ይወጣል።

**ሰላም!**

መንገሻ ፈንታው (ዶ/ር)

የአማራ ክልል ኮሙኒኬሽን ቢሮ ኃላፊ

## I. የአማራ ክልል በጥቂቱ

የክልሉ ግብርና ቢሮ መረጃ እንደሚያሳየው የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ከ9-14 ዲግሪ ሰሜን ኬክሮስና ከ36-40 ዲግሪ ምስራቅ ኬንትሮስ ሃሳባዊ መስመሮች መካከል የሚገኝ ሲሆን 161 ሺህ 828.4 ካሬ ኪሎ ሜትር ስፋት አለው፡፡ክልሉ ከጠቅላላው የአገሪቱ የቆዳ ስፋት 15 በመቶ የሚሆነውን ይሸፍናል፡፡ ክልሉ በሰሜን ከትግራይ፣ በምስራቅ ከአፋር፣ በደቡብ ከኦሮሚያ፣ በምዕራብ ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልልና ከሱዳን ጋር ይዋሰናል፡፡

በአገራችን በከፍታው የሚታወቀውና 4,620 ሜትር ከፍታ ያለው የራስ ደጀን ተራራ የሚገኘው በዚሁ ክልል ሲሆን ለተለያዩ ተግባራት ሊውሉ የሚችሉ የበርካታ ወንዞች (አባይ፣ ተከዜ፣ አንገረብ፣ መገጭ) እና ሐይቆችም (የጣና፣ የዘንገና፣ የሎጎና፣ የአርዲቦ ...) ባለቤት ነው፡፡

የክልሉ የአየር ንብረት 2.35 በመቶ ውርጭ፣ 24.15 በመቶ ደጋ፣ 46.61 በመቶ ወይና ደጋና 26.71 በመቶ ቆላ ነው፡፡ ዓመታዊ የዝናብ መጠኑ ከ598.3-1,692 ሚሊ ሜትር ሲሆን በዓመት በአማካይ ከ12.4-27.8 ዲግሪ ሴንቲ ግሬድ የሙቀት መጠን አለው፡፡

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ገንዘብ ቢሮ የስነ-ህዝብ መረጃዎች እንደሚያመላክቱት የክልሉ የህዝብ ብዛት ከ1999 የህዝብ ቆጠራ በመነሳትና በየዓመቱ በአማካይ የሚጨምረውን የ1.7 በመቶ የህዝብ ዕድገት ምጣኔ መነሻ በማድረግ በ2016 ዓ.ም. የተተነበ የህዝብ ብዛት 23,548,999 ነው፡፡ይህም በፆታ ሲተነተን 11,725,424 ወንድና 11,823,575 ሴት እንደሆነ ያመላክታል፡፡የህዝብ ቁጥሩ በአዲስ ተቆጥሮ ያልተረጋገጠ በመሆኑ ከትግራይ ክልል በሀይል ተወስደው የነበሩ ወደ አማራ ክልል የተመለሱ ወልቃይት ጠገዴ ሴቲት ሁመራ እንዲሁም ራያ አላማጣን የህዝብ ቁጥር አይጨምርም፡፡

ክልሉ ከአማራ ብሄር በተጨማሪ የአዊ፣ የኦሮሞ፣ የዋግ ኽምራ፣ የአርጎባና የቅማንት ብሄረሰቦች ይኖሩበታል፡፡ክልሉ በ14 ዞን አስተዳደሮች (ሶስቱ የብሄረሰብ አስተዳደሮች እና ከትግራይ ወደ አማራ ክልል የተመለሰ ወልቃይት ጠገዴ ሰቲት ሁመራ ዞን) የተዋቀረ ነው፡፡ እንዲሁም በ8 ሪጀኦ ፖሊታን ከተሞች፣ በ77 የከተማ አስተዳደሮች፣ በ149 መሪ ማዘጋጃ ቤቶች በ104 ንዑስ ማዘጋጃ ቤቶች በ390 ታዳጊ ከተሞች በአጠቃላይ የወልቃይት ጠገዴ ሰቲት ሁመራ ዞን ከተሞችን ጨማሮ በ728 ከተሞች የተዋቀረ ነው፡፡

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት አመሰራረት ፓርላሜንታዊ ነው። በአሁኑ ወቅት ክልል

ምክር ቤቱ 294 መቀመጫ ወንበሮች ያሉት ሲሆን በተለያዩ ምክንያቶች በተወሰኑ የምርጫ ክልሎች የምክርቤት አባላት ያልተመረጡ በመሆኑ የምክርቤት አባላት ብዛት 256 ሲሆን ከዖታ አንፃር 163 ወንድና 93 ሴት የምክር ቤት አባላት አሉት፡፡ የምክር ቤቱ አባላት የብልፅግና እና የአብን ተወካዮች ሲሆኑ አብላጫውን የምክርቤት መቀመጫ የያዘው የብልፅግና ፓርቲ ነው፡፡ የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የክልሉን አኩሪ ባህል ጠብቆ በማቆየት፣ የዱር እንስሳት ሀብት እንዲጠበቁና ለትውልድ እንዲተላለፉ የማድረግ ሚናውን እየተጫወተ ይገኛል፡፡

እንዲሁም ለባለሀብቶችና የቱሪስት አገልግሎት ሰጭ ተቋማት ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ሰላማዊ ስርዓት በማስፈን ፈጣን ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ለማምጣት የሚደረገውን ጥረት በዋናነት እንዲያግዝ የማድረግ አላማ ይዞ እየሠራ ይገኛል፡፡

ለክልላችን ኢኮኖሚ ማደግ አስተዋጽኦ የሚያደርጉና የቱሪስትን ቀልብ ከሚያማልሉ የመስህብ ሀብቶች መካከል በዓለም አቀፍ ደረጃ እውቅና ካላቸው ኪነ-ህንፃዎች፣ ብርቅየ የዱር አራዊ ቶች፣ታሪካዊ ቦታዎች፣ልዩ ልዩ ድንቃ ድንቅ ቅርሶች፣ የአባይ ምንጭ ፏፏቴ፣ አስገራሚ ዋሻዎችና ፓርኮች እንዲሁም የጣና ደሴቶችና ገዳማት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡ በሀገራችን በዩኔስኮ ከተመዘገቡት የዓለም ቅርሶች መካከል አራቱ በአማራ ክልል ይገኛሉ፡፡ የክልሉ ርዕሰ መዲና ባሕርዳር ናት፡፡

የባሕርዳር ከተማ ከተቆረቆረች ረጅም የሚባል ዘመን ብታስቆጥርም በፈጣን የዕድገት ጐዳና ላይ ትገኛለች፡፡ የከተማዋ ነዋሪ ከመንግስት የከተሞች ልማት ፖሊሲ ጋር በመተዋወቅና ልማታዊ አስተሳሰብን እያዳበረ በመምጣቱ በባሕር ዳር ከተማ አስገራሚ ፈጣንና ሁለንተናዊ ለውጥ እየተመዘገበ ይገኛል፡፡

በከፊል በጣና ሃይቅ የተከበበችው እና የአባይ ወንዝ አካሎ የሚያልፉት ባሕርዳር በተፈጥሮ ሃብት የታደለችና የቱሪስቶች መናኸሪያ ከተማ ከመሆኗም በላይ ለንግድ አገልግሎት፣ለባለ ኮከብ ሆቴሎች መገኛ እና ለተለያዩ አገልግሎት የሚውሉ የኢንቨስትመንት አማራጮች እየተስፋፉ የሚገኙባት ከተማ ሆናለች፡፡

በአማራ ክልል ባሉ ከተሞች ደረጃቸውን የጠበቁ ከ100 በላይ ቱሪስት መጥን ሆቴሎች ሲኖሩ በዋና ከተማዋ በባሕርዳር ከ23 በላይ ደረጃቸውን የጠበቁ ሆቴሎች ወደ ከተማዋ ለሚገቡ እንግዶች አስፈላጊውን መስተንግዶ በመስጠት ይታወቃሉ፡፡

የአማራ ክልል በአገር ውስጥና በውጭ የሚኖሩ ባለሃብቶችን እንደ ልማት ፍላጐታቸው ማስተናገድ የሚያስችሉ የተለያዩ የኢንቨስትመንት አማራጮችን አቅፎ የያዘና ባለሃብቶች

በመረጡት ዘርፍ ቢሠማሩ ትርፋማ ሊሆኑ እንደሚችሉ የሚጠቁሙ መረጃዎችን ለይቶ አደራጅቷል፡፡በዚህ መሠረት ባለሀብቶች ሊሠማሩበት በሚፈልጉት የኢንቨስትመንት መስክ አንፃር መረጃዎችን አገናዝበው መጠቀም እንዲችሉ የተመቸ ዕድል ፈጥሯል፡፡

ክልሉ ለአዝርዕት ተስማሚ የሆነ መሬት፣ የአየር ንብረትና እምቅ የውሃ ሀብት አለው፡፡ ይህም በዝናብም ሆነ በመስኖ የብዕር፣ የጥራጥሬና የቅባት እህሎችን፣ የአትክልትና ፍራፍሬ ሰብሎችን በስፋት ለማልማት ምቹ አድርጎታል፡፡ በክልሉ ከፍተኛ ቁጥር ያለው የእንስሳት ሃብት እንዳለ ቢታወቅም የዘርፉ ልማት የሚካሄደው በተለመደው ኋላቀር አያያዝና የአረባብ ዘዴ በመሆኑ ሊገኝ የሚገባውን የምርት መጠንና ጥቅም ማግኘት ሳይቻል ቆይቷል፡፡ በመሆኑም የግል ባለሃብቶች በመስኩ በመሰማራት በዘመናዊ መልክ በመጠቀም በእንስሳት እርባታ እና በማድለብ፣ በመኖ ልማት፣ በእንስሳት ተዋፅኦ ገበያ ልማትና የእንስሳት ጤና ጥበቃ አገልግሎት ሊሳተፉ የሚችሉባቸው ዕድሎች ናቸው፡፡

በክልሉ ሰፊ የዓሣ ሀብት ይገኛል፡፡ከጣና ሐይቅ ብቻ በዓመት 15 ሺህ ቶን ዓሳ ማምረት ይቻላል፡፡ በተለይም ከሐይቆች ጣና፣ ሎጎና አርዲቦ፣ ከወንዞች አባይ፣ ተከዜና አንገረብ አስተማማኝ የዓሳ ሃብት ምንጮች መሆናቸውን ጥናቶች ያመለክታሉ፡፡ ባለሃብቶች በዚህ ዘርፍ ቢሰማሩ የዓሳ ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪ በማቋቋም ምርቱን ለሀገር ውስጥና ለውጭ ሀገር ገበያ በማቅረብ፣ እንዲሁም ተረፈ ምርቱን ለእንስሳት መኖ በማቀነባበር ያለውን የሃብት ክምችት ጥቅም ላይ ለማዋል ከማስቻሉም በላይ በከፍተኛ ደረጃ ተጠቃሚ እንደሚያደርግ ይታመናል፡፡

ከክልሉ የተፈጥሮ ደን ውስጥ ሙጫና የዕጣን ዛፍ ይገኙበታል፡፡ ይህን ሃብት ለማልማት 604,382 ሄክታር የሚሸፍን መሬት እንደሚኖር ጥናቶች ይጠቁማሉ፡፡ ይሁን እንጂ እስከ አሁን ይህ ዘርፍ በአግባቡ ጥቅም ላይ ያልዋለ የኢንቨስትመንት መስክ ነው፡፡ በክልሉ የዕጣን ሀብት በስፋት የሚገኙባቸው ቆላማ ቦታዎች አዲአርቃይ፣ ታች አርማጭሆ፣ መተማ፣ ደራ፣ደብረ ኤልያስ፣ ባሶሊበን፣ ዳንግላና ጓንጓ ሲሆኑ በአጠቃላይ ወቃይት ጠገደ ስተቲት ሁመራ ዞንን ሳይጨምር በ9 ዞኖች በሚገኙ 39 ወረዳዎች በዓመት 200 ሺህ ቶን ዕጣንና የዱር ሙጫ ማምረት ይቻላል፡፡ ይህም በርካታ ባለሃብቶችን ሊያሳትፍ የሚችል አቅም ያለው መሆኑን ያመላክታል፡፡

በክልሉ ያለው የጤናና የትምህርት ሽፋን እየተሻሻለ የመጣ ቢሆንም ክልሉ ካለው የህዝብ ቁጥር አንፃር ሲታይ ገና ብዙ መሠራት እንዳለበት ያመለክታል፡፡ ስለሆነም ባለሃብቶች የሚታየውን የጤናና የትምህርት ሽፋን ለማሳደግ ጉልህ ድርሻ እንደሚኖራቸው

ይታመናል፡፡ በትምህርቱ ዘርፍ ከአፀደ ህፃናት እስከ ከፍተኛ ትምህርት፣ በጤና አገልግሎት ደግሞ ከክሊኒክ እስከ ሆስፒታል እንዲሁም የጤናና የቴክኒክ እና ሙያ ማሰልጠኛ ተቋማትን፣ የመድሃኒት ማምረቻና የጅምላ ማከፋፈያዎችን በመክፈት ሰፊ የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ ማካሄድና ተጠቃሚ መሆን ይቻላል፡፡

በአገራችን ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ዕድገት እያሳዩ ከመጡት የኢንቨስትመንት ዘርፎች አንዱ የግንባታ (ኮንስትራክሽን) ኢንዱስትሪ ነው፡፡ ለዚህ ዘርፍ መስፋፋት ምክንያቶች ደግሞ የኢንዱስትሪው ኢንቨስትመንት መጨመርና ለንግድ ሥራ የሚውሉ ግንባታዎች ማስፈለጋቸው ነው፡፡ የህዝብ ብዛት ፈጣን ዕድገት እያሳየ መምጣትና የመኖሪያ ቤት እጥረት ሰፊ በመሆኑ እንዲሁም የመሰረተ ልማት አውታሮች በከተሞች ብቻ ሳይወሰኑ ገጠሩንም ማካለላቸው ለዘርፉ አስፈላጊነት ምክንያቶች ሆነዋል፡፡ ስለዚህ ባለሃብቶች በዚህ መስክ የመኖሪያ ቤቶችን ለቢሮና ለተለያዩ አገልግሎቶች የሚውሉ ህንፃዎችን ሰርተው ቢያከራዩና በተለያዩ የህንፃ ግንባታና የመንገድ ሥራዎች ላይ ቢሰማሩ ክልሉን ማልማት የሚችሉ ከመሆኑም በላይ አስተማማኝ የገቢ ምንጭ የሚያገኙበት ነው፡፡

ክልሉ ሰፊ የማዕድን ሐብት ባለቤት ነው፡፡ ይሁን እንጂ በአሁኑ ወቅት ያለው የማዕድን ልማት ተግባራዊ እንቅስቃሴ በአብዛኛው ለግንባታ አገልግሎት የሚውል ድንጋይ በማምረትና በመጠቀም ላይ ያተኮረ ነው፡፡ ይህም የሚያመለክተው ክልሉ ያለውን ያልተነካ የማዕድን ሀብት ጥቅም ላይ ለማዋልና ብሎም ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ለማምጣት የማዕድን ፍለጋና ማምረት የግል ባለሃብቶችን ተሳትፎ የሚጋብዝ መሆኑን ነው፡፡ ስለዚህ ባለሀብቶች የተለያዩ የሐይል ግብአቶችን በመጠቀም ለልማቱ አጋዥ መሆን ይችላሉ፡፡ ከዚህ ባሻገር የነፋስና የፀሐይ ሐይል በተለይ በገጠሩ አካባቢ ከፍተኛ አገልግሎት ሊሰጡ የሚችሉ የሐይል ምንጮች መሆናቸውን በመገንዘብ በዘመኑ ቴክኖሎጂ በመታገዝ ጥቅም ላይ ማዋል ይቻላል፡፡ የክልሉ መንግስት ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋት በሰጠው ልዩ ትኩረት መነሻነት የተለያዩ ርምጃዎችን ሲወስድ ቆይቷል፡፡በፌዴራል መንግስት የተፈቀዱ የኢንቨስትመንት ማበረታቻ ዎችን በመተግበር ለባለሃብቱ ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር ተንቀሳቅሷል፤ ባለሃብቶችን ወደ ክልሉ ለመሳብና ለማበረታታት ለተመረጡ የከተማ ፕሮጀክቶች መሬት በአነስተኛ ክፍያ በማቅረብ ከመስራቱም በላይ ለአርሶ አደር የይዞታ መሬት ካሳ ከፍሎ ከሶስተኛ ወገን ነፃ በማድረግ ለአበባና አትክልት ልማት ኢንቨስትመንት መሬት በነፃ በማቅረብ እያበረታታ ይገኛል፡፡ በጣና ሀይቅ ዙሪያ ሊኖር የሚችለውን የልማት አማራጭ ለማወቅና ጥቅም ላይ እንዲውል ለማድረግ የጣና ሃይቅ አካባቢን

በከፍተኛ ባለሙያዎች አስጠንቶ ያለውን ጥቅም የመለየት ስራ ተሰርቷል፡፡

ከዚህ በተጨማሪም ክልሉ ከጐረቤት ሀገሮች ከሱዳንና ከጅቡቲ ጋር የሚያገናኙ ሀገር አቋራጭ መንገዶች፣ ዓለም-አቀፋዊና የሀገር ውስጥ በረራዎችን የሚያስተናግዱ የአውሮፕላን ማረፊ ያዎች እና የተለያዩ መሠረተ ልማቶች በስፋት የተዘረጉበት ክልል ነው፡፡

በመሆኑም  አጋር አካላትና ባሃብቶች በክልሉ በሚገኙ የተለያዩ ዘርፎች ገብተው እንዲሳተፉ ክልሉ አስፈላጊውን ቅድመ ዝግጅት አሟልቶ እየጠበቀ ነው፡፡ ተሳታፊ እንድትሆኑ ጥሪውን ያስተላልፋል፡፡

## II.ኢኮኖሚ ዘርፍ

## ግብርና ልማት

ክልላችን ለልማት የሚያስፈልጉት የተለያዩ የምርት ግባቶች አሉት፡፡በዚህ ውስጥ በቅድሚያ የሚጠቀሱት ካፒታል፣ጉልበትና መሬት ናቸው፡፡እነዚህን የልማት ግባቶች በላቀ ውጤታማነት በመጠቀም የክልላችን የጀርባ አጥንት የሆነውን የግብርና ክፍለኢኮኖሚ ማሳደግ አስፈላጊ ነው፡፡ይህም ሲባል ከክልሉ ኢኮኖሚ በየአመቱ በአማካይ 164.9 ቢሊየን ብር በላይ የሚሆነው እሴት ጭማሪ በግብርና ሴክተር የሚገኝ ነው፡፡ በሌላ አገላለጽ ግብርና በአማካይ 52.5% የሚሆነውን እሴት ጭማሪ ለክልሉ ኢኮኖሚ በማመንጨት ላይ ያለ ሴክተር ነው፡፡ ከግብርና ሴክተር እሴት ጭማሪ ውስጥ ደግሞ በየዓመቱ በአማካይ 110.98 ቢሊየን ብር ወይም 67% በላይ የሚሆነውን የሚሸፍነው የሰብል ምርት እሴት ጭማሪ ነው፡፡ ከክልሉ አጠቃላይ ኢኮኖሚም ቢሆን የሰብል እሴት ጭማሪ በአማካይ 37.5% ይሸፍናል፡፡ በ2015/16 የምርት ዘመን በግብርና ቢሮ የምርት ትንበያ መሰረት በመደበኛና በኮሞዲቲ የመኸር ሠብሎች የተገኘውን 145,304,384 ኩንታል ምርት በ2016/17 የምርት ዘመን 5,185,468 ሄክታር መሬት በማልማትና ምርቱንም በ16.4% በማሣደግ 169,652,386 ኩንታል ምርት ማምረት፣ ምርታማነቱንም በ2015/16 ምርት ዘመን ከነበረበት 28.2 ኩንታል/ በሄክታር ወደ 32.7 ኩንታል በሄክታር ለማድረስ ታቅዶ ሲተገበር ቆይቷል፡፡

## የግብርና ኤክስቴንሽን

ክልላችን የግብርና ምርቶችን በዓይነት፣ በብዛት እና በጥራት ለማምረት የሚያስችል እምቅ ሀብት እና የተለያዩ ምቹ የሆኑ ተፈጥሮአዊ ስነምህዳር ያለው መሆኑ ይታወቃል፡፡ ይህንን ሀብትም ባግባቡ በመጠቀም ክልሉ ከግብርና ሊያገኝ የሚገባውን ጥቅም ለማግኘት የአርሶ አደሮችን ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎች አጠቃቀም በማዘመን ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ የሚያስችል የኤክስቴሽን ስራ በሰፊው ለመስራት የሚያስችል አሰራር ማስፈን አስፈላጊ ነው፡፡

በመሆኑም አመቱ የግብርና ኤክስቴንሽን አፈፃፀምን በሚመለከት የክልሉን አርሶ አደር በግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎት ተጠቃሚ ማድረግ የሚቻለው በአባወራና እማወራ የግብርና የልማት ቡድን አደረጃጀት በማጠናከር ነው፡፡ ስለሆነም የክልላችን አርሶ አደር አዳዲስ አሰራሮችንና ቴክኖሎጅዎችን በመጠቀም ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ እንዲችሉ የኤክስቴንሽን ተጠቃሚ ለማድረግ በተሰራው ስራ 6,574,946 አርሶ አደሮችን የኤክስቴንሽን ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ 6,461,748 (98%) ማከናወን ተችሏል፡፡ በተመሳሳይ ለአርሶ አደሮች ተገቢውን የኤክስቴንሽን አገልግሎት በመስጠት በሁሉም ግብርና ልማቶች በምክረ ሀሳቡ መሰረት ሙሉ ፓኬጅን ለ2,296,001 አርሶ አደሮች እንዲተገብሩ ለማድረግ ታቅዶ ወንድ 1,532,037 ሴት 310,566 በድምሩ 1,872,202 (82%) አርሶ አደሮች ሙሉ ፓኬጁን እንዲተገብሩ ተደርጓል፡፡

## ሰብል ልማት

የክልሉ መንግስት የግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚ የክልሉ አንቀሳቃሽ ሞተር መሆኑን በመገንዘብ በ2016/17 የምርት ዘመን በመኸር ወቅት የእርሻ ስራ እንቅስቃሴ 5,185,468 ሄክታር መሬት ለማልማት ታቅዶ ወደ ተግባር የተገባ ሲሆን በዚህም በበጀት አመቱ መጨረሻ 4,540,822 (88%) ሄክታር መሬት ማረስ ተችሏል፡፡በባለፈው ዓመት በተመሳሳይ ወቅት ከታረሰው 4,434,242 ሄክታር መሬት ጋር ሲነጻጸር በ106,580 ሄክታር ብልጫ አለው፡፡በበልግ ወቅት 239,509 ሄክታር ማሳ በማልማት 4,260,370 ኩንታል ምርት ለማምረት ታቅዶ በበጀት አመቱ መጨረሻ 247,463.5 ሄክታር (103%) ማሳ ማልማት ተችሏል፡፡



የጤፍ ሰብል -ሽበል በረንታ

## ኮምፖስት ዝግጅት

ኮምፖስት ወይም ብስባሽ በስነ-ህይወታዊ ሂደት የተብላላ ኦርጋኒክ ወይም ካርቦኒክ ቁስ ሲሆን የተፈጥሮ በስነ-ህይወታዊ ሂደትን የማፋጠን ማለትም በቀላሉ ሊብላላ የሚያስችላቸውን ሁኔታዎች በማመቻቸት የዘር ወቅት ከመድረሱ በፊት የሚዘጋጅ ነው፡፡ ኮምፖስት ለእፅዋት የሚያስፈልጉ የተመጣጠኑ ንጥረ-ነገሮችን እና ጠቃሚ ደቂቅ-አካላትን የያዘ ስለሆነ የአፈርን ለአፅዋት ምግብ የማቅረብ አቅም ያሳድጋል፡፡ በተለይም ዝናብ አጠር በሆነ እና የሰው ሰራሽ ኬሚካል ማዳበሪያ ውጤታማነት በዝናብ እጥረት ምክንያት አስተማማኝ ባልሆነበት አካባቢ ጠቀሜታው የላቀ ነው፡፡ስለሆነም በበጀት ዓመቱ 102,031,197 ሜትር ኩብ መደበኛ ኮምፖስት ለማዘጋጀት ታቅዶ 59,503,665 ሜትር ኩብ (58%) ማዘጋጀት ተችሏል፡፡ በተመሳሳይ 2,265,195 ኩንታል ቨርሚ ኮምፖስት ለማዘጋጀት ታቅዶ 369,518 (16%) ኩንታል የተዘጋጀ ሲሆን በዚህም 29,914 አርሶ አደሮች ተሳታፊ ሲሆኑ 369,518 ኩንታል ቨርሚ ኮምፖስት ከአፈር ጋር በማዋሃድ 12,317 ሄክታር ማሳ ማልማት ተችሏል፡፡ እንዲሁም 292,152 ሜትር ኩብ ባዮስለሪ ኮምፖስት ለማዘጋጀት ታቅዶ 147,275 ሜትር ኩብ (50%) የተዘጋጀ ሲሆን በዚህም 5,620 አርሶ አደሮችን በማሳተፍ የተዘጋጀ ሲሆን 18,409 ሄክታር ማሳ ማልማት ተችሏል፡፡



ኮምፖስት ዝግጅት

## አሲዳማ አፈር ልየታ

በክልላችን ለአፈር አሲዳማነት መከሰት ከፍተኛ ድርሻ የሚይዘው ፒ.ኤችን ለማማከል የሚረዱ እንደ ካልሲየም፣ማግኒዝየም እና ፖታሲም ያሉ አስፈላጊ ንጥረ ነገሮች በዝናብ ታጥበው ወይም ሰርገው በመሄዳቸው ሲሆን ሰብሎች ከአፈር የሚወሰዱትን ንጥረ ነገሮች ባለመተካታቸው በሂደት በአፈር የላይኛው ክፍል የንጥረ ነገሮች መመናመን በሚያመጣው ኬሚካላዊ ለውጥ የተነሳ መሆኑ ይታወቃል፡፡ስለሆነም በበጀት አመቱ በክልሉ በተለያዩ ቦታዎች የአሲዳማ አፈርን የልየታ ስራ ለማከናወን በ20,785 ሄክታር መሬት ላይ 103,925 ናሙና ለመሰብሰብ ታቅዶ 4,074 ሄክታር መሬት ላይ 15,511 የአፈር ናሙና በመሰብሰብ 12,149 (78%) ናሙና በላብራቶሪ በማስመርመር የ10,558 ናሙና ውጤት የተገለጸ ሲሆን 5,813 ናሙና (1,324 ሄክታር ማሳ) አሲዳማ ሁኗል፡፡ በዚህም 15,160 አርሶ አደሮች ማሳተፍ ተችሏል፡፡ አፈጻጸሙ ከባለፈው ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻጸር በ1,828 የአሲዳማ አፈር ናሙና (በ366 ሄክታር ማሳ) ያንሳል፡፡

## የዘር ብዜት

በ20 15/16 ምርት ዘመን በተለያዩ ሰብሎችና ዝርያዎች እስከ በጀት አመቱ መጨረሻ ሊሰበሰብ ከታቀደው 315,109 ኩንታል ዘር ብዜት ውስጥ 190,805 ኩንታል (60.6%) ማሰባሰብ ተችሏል፡፡ ይህ አፈጻጸም ከባለፈው አመት ተመሳሳይ ወቅት መሰብሰብ ከተቻለው ዘር 213,704 ኩንታል ጋር ሲነጻጸር በ22,899 ኩንታል ያንሳል፡፡

## ሰብል ጥበቃና ቁጥጥር

በበጀት አመቱ የሰብል ጥበቃና ቁጥጥር ስራ ለመስራት በታቀደው መሰረት በክልሉ የነፍሳት ተባይን 2,060,265 ሄክታር መሬት ለማሰስ ታቅዶ እስከ በጀት አመቱ መጨረሻ 1,628,770 ሄክታር መሬት የታሰሰ ሲሆን በዚህም ወንድ 1,253,782 እና ሴት 165,941 በድምሩ 1,419,723 አርሶአደሮችን ለማሳተፍ ተችሏል፡፡ እንዲሁም በበልግ ሰብል ልማት እና በበጋ መስኖ ስንዴ ልማት በምስራቅ አማራ ቀጠና በሚገኙ 2 ዞኖች (ሰሜንሸዋና ኦሮሞብሄረሰብ) በ6 ወረዳዎች እና በ21 ቀበሌዎች፣ 28 የማደሪያ ቦታዎች ላይ 17.49 ሚሊዮን የግሪሳ ወፍ የተከሰተ ሲሆን በ21 ቀበሌዎች ላይ 175 ሊትር የባቲዮን ፀረ-ወፍ ኬሚካል በመጠቀም በ88.5 ሄክታር መሬት ላይ ርጭት የመከላከል ሥራ ተሰርቷል፡፡

## አትክልትና ፍራፍሬ ልማት

በ2016 ዓ.ም በአትክልትና ፍራፍሬ መስኖ ልማት 333,416 ሄክታር ለማልማት ታቅዶ 301,469 ሄክታር (90%) መሬት ታርሶ 299,764 (90%) ሄክታር በዘር ለመሸፈን የተቻለ ሲሆን በ1ኛ ዙር መስኖ ልማት 25,723,636 ኩንታል ምርት ለማምረት ታቅዶ 29,705,814 (115.5%) ኩንታል ምርት ተሰብስቧል፡፡



አትክልትና ፍራፍሬ-ባህርዳር

## የፍራፍሬ ችግኝ ጣቢያና ተከላ

በበጀት ዓመቱ 15,241 ነባር ችግኝ ጣቢያ ለማካሄድና 373 በአዲስ ለማቋቋም ታቅዶ 2,277 (15%) ነባር ችግኝ ጣቢያ ማካሄድና 21 (5.6%) አዲስ ችግኝ ጣቢያ ማቋቋም ተችሏል፡፡በአጠቃላይ 18.5 ሚሊዮን የቡናና ፍራፍሬ ችግኝ ለተከላ ለማዘጋጀት ታቅዶ 16.5

ሚሊዮን የተዘጋጀ ሲሆን ከዚህም ውስጥ 8.9 ሚሊዮን ቡና፤ 7.03 ሚሊዮን የቆላ ፍራፍሬ እና 0.57 ሚሊዮን የደጋ ፍራፍሬ ተዘጋጅቷል፡፡ በዚህም 466,451 ተሳታፊ አርሶ አደሮችን ለመለየት ታቅዶ 210,509 (45%) የተከናወነ ሲሆን እንደ ክልል ለተከላ ለተዘጋጀው 15.2 ሚሊዮን ችግኝ መትከያ 10.5 (64%) ሚሊየን ጉድጓድ ተቆፍሯል፡፡

2015/16 ምርት ዘመን 386,356 የአቮካዶ ችግኝ በ1,259 ሄክታር መሬት ላይ ለመትከል ታቅዶ በበጀት አመቱ መጨረሻ 121,956 (31%) የአቮካዶ ችግኝ በ313 ሄክታር መሬት ላይ በማልማት 2,868 (231 ሴቶች) አርሶ አደሮች ተሳታፊ ማድረግ ተችሏል፡፡ በምርት ዘመኑ 241,706 የማንጎ ችግኝ በ879 ሄክታር መሬት ላይ ለመትከል በእቅድ ተይዞ በበጀት አመቱ መጨረሻ 106,316 (43%) የማንጎ ችግኝ በ369 ሄክታር በማልማት 4,273 (414 ሴቶች) አርሶ አደሮች ተሳታፊ ማድረግ ተችሏል፡፡ 130,630 የሙዝ ሳከር በ79 ሄክታር መሬት ላይ ለመትከል ታቅዶ በበጀት አመቱ መጨረሻ 73,845 (58%) የሙዝ ሳከር በ46 ሄክታር መሬት በማልማት 2,448 (123 ሴቶች) አርሶ አደሮች ተሳታፊ ማድረግ ተችሏል፡፡በምርት ዘመኑ 64,700 የአፕል ችግኝ በ56 ሄክታር መሬት ላይ ለመትከል ታቅዶ፤ 54,505 (84%) የአፕል ችግኝ በ44 ሄክታር መሬት በማልማት 627 (176 ሴቶች) አርሶ አደሮች ተሳታፊ ማድረግ ተችሏል፡፡ 46,080 የብርቱካን ችግኝ በ138 ሄክታር መሬት ላይ ለመትከል ታቅዶ በበጀት አመቱ መጨረሻ 46,080 (100%) የብርቱካን ችግኝ በ166 ሄክታር መሬት በማልማት ,405 (400 ሴቶች) አርሶ አደሮች ተሳታፊ ማድረግ ተችሏል፡፡

## የግብርና ኢንቨስትመንትና ግብዓት አቅርቦት

በ2016 ዓ.ም የግብርና ኢንቨስትመንትና ግብዓት አቅርቦት ተግባራት ለአርሶ አደሩ የአፈር ማዳበሪያ፤ ዘመናዊ የእርሻ ቴክኖሎጅዎችን እና ሌሎች የግብርና ግብዓቶችን በሚፈለገው ቦታ፣ ወቅት፣ ዓይነትና በተመጣጣኝ ዋጋ በበቂ መጠን ለማቅረብ በዘርፉ የተሰማሩ ባለድርሻ አካላት ሚና ወሳኝ በመሆኑ ከፍተኛ ርብርብ ተደርጓል፡፡የግብርናን ምርትና ምርታማነት የሚያሳድጉ ግብዓቶችን በምክረ ሃሳብ መሰረት መጠቀም ለምግብ፣ ለኢንዳስትሪና ለገበያ የሚሆን ምርት ለማምረት የሚጫወተው ሚና ከፍተኛ ነው፡፡

ለምርት ዘመኑ በአዲስ ተገዝቶ የሚቀርብ 8,057,900 ኩንታል እና የከረመ 219,742 ኩንታል በድምሩ 8,277,642 ኩንታል የአፈር ማዳበሪያ ለማቅረብ ታቅዶ 8,057,900 ኩንታል የተገዛ ሲሆን ከዚህም በአዲስ ከወደብ የቀረበውን 5,805,515 ኩንታል እና ከ2015/16 ምርት ዘመን

ያደረውን 219,742 ኩንታል ጨምሮ በድምሩ 6,025,257 ኩንታል ቀርቧል፡፡ ከአጠቃላይ አቅርቦት ውስጥ በመኸር እና በመስኖ 5,520,429 ኩንታል የአፈር ማዳበሪያ ተሰራጭቷል፡፡ ለ2016/17 ምርት ዘመን ተገዝቶ የቀረበው የአፈር ማዳበሪያ ከባለፈው ምርት ዘመን ከተገዛው 5,296,670 ኩንታል ጋር ሲነጻጸር የዚህ ዓመቱ በ2,761,230 ኩንታል ብልጫ አለው፡፡ እንዲሁም በ2016/17 ምርት ዘመን 312,242 ኩንታል የተለያየ ምርጥ ዘር በማቅረብ ለማሰራጨት ታቅዶ 152,527 ኩንታል ምርጥ ዘር ቀርቦ 125,257 ኩንታል ማሰራጨት ተችሏል፡፡

በ2016/17 ምርት ዘመን 45,400 ኩንታል ኖራ ለማቅረብ ታቅዶ ከደጀን የኖራ ፋብሪካ 24,610 ኩንታል በማቅረብ 23,881 ኩንታል ለአርሶ አደሩ ማሰራጨት ተችሏል፡፡ በተመሳሳይ በ2016/17 ምርት ዘመን 1,372,054 ሊትር ኬሚካል ለማቅረብ ታቅዶ 1,097,011 ሊትር ፈሳሽና 154067 ኪሎ ግራም በዱቄት ማቅረብ ተችሏል፡፡በግብርናው ኢንቨስትመንት ዘርፍ ሜካናይዜሽንን ለማሳደግ በክልሉ መንግስት 20በ80 የመካናይዜሽን መሳሪያዎች የመግዣ ስርዓት መስረት አበዳሪ ባንኮችን በማፈላለግና መነሻ በጀት በመመደብ አርሶ አደሮች፣ በግብርናው ዘርፍ የተሰማሩ ባለሀብቶች፣ ድርጅቶች እና ተቋማት ትራክተር እንዲወስዱ የማድረግ ስራ ተሰርቷል፡፡ ከ2015/16 ምርት ዘመን በክልሉ መንግስት 30 ሚሊዮን ዶላር በማስፈቀድ ለቀረቡት 412 ትራክተሮች ውስጥ ሳይሰራጩ የከረሙትን ለአርሶአደሩ ተደራሽ ለማድረግ ሰፊ ስራ ተሰርቷል፡፡ በ2016 በጀት ዓመት 144 ትራክተሮችን ለአርሶ አደሩ ለማሰራጨት ታቅዶ በበጀት አመቱ መጨረሻ 169 ትራክተሮችን (ከ100% በላይ) ማቅረብና ማሰራጨት የተቻለ ሲሆን በዚህም የክልሉን የትራክተር ቁጥር ወደ 1,950 ማድረስ ተችሏል፡፡ እንዲሁም በክልላችን ከሚታረሰው መሬት ውስጥ 60% የሚሆነው ለመካናይዜሽን ምቹ በመሆኑ 46 የሰብል መውቂያ ኮምባይነር ለማቅረብ ታቅዶ 13 ኮምባይነር በማቅረብ ለማሰራጨት የተቻለ ሲሆን በዚህም የክልሉን የኮምባይነር ቁጥር 54 ማድረስ ተችሏል፡፡ በመሆኑም በክልሉ ያለውን የኮምባይነር ቁጥር 54 ለማድረስ ተችሏል፡፡ በተጨማሪም በበጀት ዓመቱ 23 ከፍተኛ መውቂያ መሳሪያዎችን ለማቅረብ ታቅዶ 13 ኮምባይነሮችን በማቅረብ የክልሉን የኮምባይነር ቁጥር 54 ማድረስ ተችሏል፡፡ እንዲሁም 186 ትሬሸር እና 902 ሸለሮችን ለማቅረብ እና ለማሰራጨት ታቅዶ 102 ትሬሸር እና 885 ሸለሮችን ማሰራጨት ተችሏል፡፡

## የግባት ብድርና አመላለስ

የ2015/16 ምርት ዘመን የብድር አመላለስ በምርት ዘመኑ ከተፈቀደው 29 ቢሊዮን ብር ውስጥ 23,206,753,249.91 ብር ጥቅም ላይ የዋለ ሲሆን ከዚህም 22,137,421,420.63 ብር (93%) የተመለሰ ሲሆን ቀሪው 1,069,331,829.28 ብር በብድር የተሰጠ ገንዘብ እና መንግስት ያደረገውን የድጎማ ገንዘብ ባለመመለሱ ባንክ ላይ ባለው ተጨማሪ ወለድ ምክንያት የተገኘ ብደር ነው፡፡ በምርት ዘመኑ ምርጥ ዘር ለሚያባዙ ዩኒየኖች የሚያጋጥማቸውን የገንዘብ እጥረት ለመፍታት ለጉና፣ ተጉለት እና እድገት ብር 120,000,000.00 እና ለቦርከና፣ ወደራ፣ ከሰም እና ዋቢ ዩኒየን ከመደበኛው በጀት ብር 86,270,400.00 በድምሩ 206,270,400.00 ብር የተመደበ ሲሆን ከዚህም 120,000,000.00 ብር የተመለሰ ሲሆን ቀሪው ገንዘብ ከመደበኛው የብድር አመላለስ ጋር እየተመለሰ ይገኛል፡፡

በ2014/15 ምርት ዘመን በዩኒየኖች ለቀረበ 4,997,245 ኩንታል የአፈር ማዳበሪያ 5,771,806,275.73 ብር ተመላሽ መሆኑን ከግብርና ስራዎች ኮርፖሬሽን ጋር ሂሳብ የማስታረቅ ስራ የተሰራ ሲሆን ከዚህም ከድጎማ በፊት ለተሸጠ 2,122,553 ኩንታል የአፈር ማዳበሪያ ተመላሽ የሚሆን 2,222,075,522.00 ብር ዘግይቶ ለቀረበ ዩሪያ የተከፈለ ገንዘብ ጋር የማስታረቅ ስራ ተሰርቷል፡፡ በኢፌድሪ ግብርና ሚኒስትር በኩል ተፈቅዶ የተመለሰው 1.3 ቢሊዮን ብር ለሁሉም ዞኖች መመሪያ በማዘጋጀት የተላከ ሲሆን ከተለቀቀው ለ6 ዞኖች 650.5 ሚሊየን ብር (48%) የማስተላለፍ ስራ የተሰራ ቢሆንም ሌሎች ዞኖች ወደ ስራ መግባት አልቻሉም፡፡

## ለመድሀኒት ግዥ የሚውል ተዘዋዋሪ በጀት ማስፈቀድ

በበጀት ዓመቱ ለመድሀኒት ግዥ የሚውል 2,140,000 ብር ለማስመደብ ታቅዶ 6,144,859 (100%) ማስመደብ ተችሏል፡፡ እንዲሁም በሚሰጠው የህክምና አገልግሎት 20 ሚሊየን ብር የአገልግሎት ክፍያን ለመሰብሰብ ታቅዶ 7,664,282 (38%) ብር የአገልግሎት ክፍያ መሰብስብ ተችሏል፡፡

## ተፋሰስ ልማት

በ2016 ዓ.ም የተፋሰስ ልማት የትግበራ መርሃ ግብር ማስጀመሪያ ፕሮግራም የለሙና ለቀጣይ እንደ መነሻ ሆነው ሊወሰዱ የሚችሉ የተቀናጀ የተፋሰስ ልማት ስራዎችን በመስክ ጉብኝት

ማድረግ ተችሏል፡፡ በዚህም የተሰሩ የስነ አካላዊ ስራዎች በየአመቱ እያደጉ ወደ ጠረጴዛማነት መቀየራቸውና ከውሀ ጋር መቀናጀታቸው፣ተከልለው እያገገሙ ያሉ ሰፋፊ ተራራማ ቦታወች፤ በጥቅሉ በእንስሳት እና በተፈጥሮ ሀብት መካከል ያለው የመመጋገብ ቅንጅት እንዲሁም በዋናነት እርከኖችን ገቢ በሚያመነጩ ፍራፍሬዎችና የመኖ እጽዋት መበልጸጋቸው እና የአርሶአደሩ ኑሮ እየተሻሻለ መምጠቱ ከጉብኝቱ የተወሰዱ መልካም ተሞክሮዎች ናቸው፡፡በዚህም መሰረት በሁሉም ዞኖች፤ በ164 ወረዳዎች፤ በ3,564 ቀበሌዎችና በ9,060 የማህበረሰብ ተፋሰሶች የትግበራ መርሃ ግብር መሰረት ለመተግበር ታቅዶ በ13 ዞኖች፤ በ6 ከተማ አስተዳደር፤ 141 ወረዳዎች፤ 2,249 ቀበሌዎች እና 5,442 የማህበረሰብ ተፋሰሶች ወደ ተግባር ገብተዋል፡፡ ይሁን እንጂ በተፈጠረው ወቅታዊ የጸጥታ ችግር ምክንያት በሁሉም አካባቢ የዞኖችን ተጨባጭ ሁኔታ መሰረት በማድረግ በቀጣይ እየተከታተሉ ፈጥነው ወደ ተግባር እንዲገቡ በማድረግ ዕቅዱን ለማሳካት በግልና አደረጃጀትን መሰረት በማድረግ ከፍተኛ ርብርብ ማድረግን ይጠይቃል፡፡ጠንካራ የተፋሰስ ተቋም በመገንባት የህብረተሰብ ተጠቃሚነትን ማረጋገጥን በተመለከተ በአጠቃላይ በክልሉ 19,894 ተፋሰሶች ወደ ልማት የገቡ ሲሆን በበጀት ዓመቱ በፌደራል አዋጅ ቁጥር 1223/2012 መሰረት 284 ተፋሰሶች በህብረት ስራ ማህበር ህጋዊ ሰውነት ያገኙ ሲሆን በአጠቃላይ እስካሁን 3,334 ተፋሰሶች ህጋዊ ሰውነት አግኝተዋል፡፡ ከተደራጁ የተፋሰስ ተቋማት ውስጥ ልቅ ግጦሽን ያስቆሙ 971 ቀበሌዎች እና 7,111 ተፋሰሶች ናቸው፡፡



የተፋሰስ ልማት -አርጎባ ልዩ ወረዳ

## በተፋሰስ ልማት የህብረተሰብ ተሳትፎ

እንደ ክልል በአማካይ ሁሉም ተፋሰሶች ለ25 የስራ ቀናት የተቀናጀ ተፋሰስ ልማት በህዝብ ንቅናቄ የተሰሩ ሲሆን ይህም በድግግሞሽ 98,906,280 ሰው በቀን ጥቅም ላይ ለማዋል ታቅዶና ወደ ተግባር ተገብቶ 49,451,761 (45.9%) ሰው በቀን ማሳተፍ ተችሏል፡፡ በዚህም መሰረት ከህዝብ ተሳትፎ አፈፃፀም አኳያ ከፍተኛ የወጣበትን ቀን በመውሰድ እንደ ክልል 41% አፈጻጸም ላይ እንገኛለን፡፡ ይሁን እንጂ የተለያየ የተፋሰስ ልማት አጀማመር መኖሩና በየስራ ቀኑ መገኘት ያለበት የሰው ሀይል ተቀያያሪ በመሆኑ አፈጻጽሙ ዞኖች ከዓመታዊ ዕቅዳቸው አንፃር ያሉበትን ሁኔታ አያሳይም፡፡ በመሆኑም ህብረተሰቡ ለአካባቢ ልማት ያደረገው አስተዋጽኦ በገንዘብ ሲተመን 1,964,116,328 ብር ነው፡፡

## አፈርና ውሃ ጥበቃ ስራ

በ2016 ዓ.ም በ311,784 ሄክታር መሬት ላይ የአፈርና ውሃ ጥበቃ ስራ ለመስራት ታቅዶ 147,675 (47.4%) ሄክታር ማከናወን ተችሏል፡፡ በዚህም ደቡብ ወሎ፣ ዋግኽምራ ብሄረሰብ አስተዳደር፣ ኮምቦልቻ ከተማ፣ ደብረ ታቦር ከተማ እና ደሴ ከተማ አስተዳደር በአንጻራዊነት የተሻለ አፈጻጸም ያላቸው ሲሆኑ ሌሎች ዝቅተኛ አፈጻጸም ላይ ናቸው፡፡በማሳ ላይ የተሰሩ የተለያዩ የአፈርና ውሃ ጥበቃ ስራዎች በሚመለከት 169,675 ሄክታር መሬት እርከን ለመስራት ታቅዶ 86,326 ሄክታር (50.9%) የተሰራ ሲሆን በተጨማሪም 14,212 ሄክታር መሬት የሳር ሰርጥ ለመስራት ታቅዶ 2,183.9 ሄክታር (15.4%) እና 127,896 የማሳ ላይ እርከን ደረጃ ለማሳደግ ታቅዶ 59,165.2 ሄክታር (46.3%) ተሰርቷል፡፡



የእርከን ስራ-ደሴ ዙሪያ ወረዳ

### መጤ አረምን ማስወገድ

በበጀት አመቱ 1,870 ሄክታር የእንቦጭ አረም ለማሰወገድ ታቅዶ 559.9 ሄክታር (35.6%) ማስወገድ ተችሏል፡፡ በዚህም ደቡብ ጎንደር ዞን 945 ሄክታር እና ማዕከላዊ ጎንደር ዞን 500

ሄክታር መሬት ላይ የእንቦጭ አረም ለማስወገድ ታቅዶ 273.9 ሄክታር (28.9%) ደቡብ ጎንደር እና 286 ሄክታር (57.2%) ማዕከላዊ ጎንደር ማስወገድ ተችሏል፡፡ ኦሮሞ ብሄረሰብ አስተዳደር 228 ሄክታር ከላንታና ካማራ ለማጽዳት ታቅዶ 513.9 ሄክታር መሬት (100%) በላይ ለማስወገድ ተችሏል፡፡ በተጨማሪም 17,710 ሄክታር የተለያዩ መጤ አረሞችን ለማስወገድ ታቅዶ 6,681 ሄክታር መሬት (37.7%) ላይ ማስወገድ ተችሏል፡፡

## የተራራ ልማት ስራ

በ2016 ዓ.ም የተራራ ልማት ስራዎችን ለማከናወን በተደረገው የተፋሰስ ጥናት መሰረት ምንም ጥቅም የማይሰጡ ተራሮችን በማልማት ጥቅም እንዲሰጡ ለማድረግ የተለያዩ የፊዚካል ስትራክቸሮችን በመስራት ለተጠቃሚዎች ተጨማሪ መሬትን ለልማት ምቹ በማድረግ ማህበረሰቡን ተጠቃሚ ለማድረግ ስራ ተሰርቷል፡፡ በመሆኑም 52,435 ሄክታር የተራራ ልማት ለመስራት ታቅዶ 29,446.3 ሄክታር የተራራ ልማት (56.2%) ማከናወን ተችሏል፡፡

## የውሀ አያያዝ ስራ

በበጀት ዓመቱ 4,306,159 ሜትር ኩብ የትርፍ ውሃ አያያዝ ማናጅመንት ስትራክቸር ለመስራት ታቅዶ 1,141,181 (26.5%) ሜትር ኩብ ስትራክቸር መስራት ተችሏል፡፡ በዚህም 2,100,128 ሜትር ኩብ የጉርፍ ማፋሰሻ ቦይ ለመስራት ታቀዶ 691,629.1 ሜትር ኩብ (32.9%) መፈጸም የተቻለ ሲሆን ከዚህ በተጨማሪም 2,206,031 ሜትር ኩብ የውሃ ማፋሰሻ ቦይ ለመስራት ታቅዶ 449,552 ሜትር ኩብ (20.4%) መስራት ተችሏል፡፡

## ቦረቦር አፈር ልማት

ቦረቦር የተከሰትበትን አካባቢ በመለየት የተለያዩ ስትራክቸሮችን በመስራት አካባቢን ለማልማት በትኩረት ተይዞ ወደ ተግባር ተገብቷል፡፡ በዚህም መሰረት 11,879 ሄክታር የቦረቦር መሬት በመለየት ለማዳንና ወደ ልማት ለማስገባት ታቅዶ 3,652.2 (30.7%) ሄክታር መሬት የተለያዩ የክትር አይነቶች መስራት ተችሏል፡፡ በአጠቃላይ በበጀት ዓመቱ 376,099 ሄክታር ላይ የአፈርና ውሃ ጥበቃ ስራ ለመስራት ታቅዶ 180,389 ሄክታር (48%) ላይ ማከናወን ተችሏል፡፡ ከዚህም በአዲስ 234,062 ሄክታር መሬት ለመስራት ታቅዶ 115,109 ሄክታር (49.2%) የተሰራ ሲሆን በነባር 142,036 ሄክታር መሬት ለመስራት ታቅዶ 65,280 ሄክታር (46%) መፈጸም ተችሏል፡፡

## ደን ልማትና ጥበቃ

የደን ዘርፍ የአየር ንብረት ለውጥ የሚያደርሰውን አሉታዊ ተፅዕኖ ለመቋቋም ትልቅ ሚና የሚጫወት በመሆኑና በክልላችን በከፍተኛ ደረጃ በደን መመናመን ምክንያት እየተከሰተ ያለውን አካባቢያዊ፣ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮችን ለመግታት ዘላቂ የደን ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም ወሳኝ ሚና አለው፡፡

በ2016 ዓ.ም የደን አግሮፎሬስተሪ ልማትና ጥበቃ ስራዎችን ስንመለከት ችግኝ ከመፈላቱ በፊት በተለያዩ የመትከያ ስልቶች የሚሸፍን የተከላ ቦታ መለየትና ለምን አላማ እንደሚተከል በማወቅ ችግኝ ማዘጋጀት የተቻለ ሲሆን 201,374 ሄክታር የተከላ ቦታ ለመለየት ታቅዶ 167,781.6 (83.3%) ሄክታር መለየት ተችሏል፡፡ በተጨማሪም 102,392 ሄክታር የደን መሬት ለመለየት ታቅዶ 73,254.5 (71.5%) ሄክታር የልየታ ስራ ተሰርቷል፡፡ እንዲሁም 98,982 ሄክታር የጥምር ደን እርሻ ለመለየት ታቅዶ መለየት የተቻለው 94,527.1 (95.5%) ሄክታር ነው፡፡ በተጨማሪም የደን ልማት ስራ ለማዘመን የተለየውን የተከላ ቦታ ኮርዲኔቱን በመውሰድና ካርታ በመስራት ከተጠቃሚው ማህበረሰብ ጋር ስምምነት በመውሰድና የሚያስፈልገውን ችግኝ በወቅቱ በማዘጋጀት ወደ ስራ ለመግባት ሰፊ ስራ ተሰርቷል፡፡ በመሆኑም በበጀት ዓመቱ 62,620 ሄክታር የተከላ ቦታ ካርታ ለመስራት ታቅዶ 31,833 (51%) ሄክታር የተከላ ቦታ ካርታ መስራት ተችሏል፡፡

## የችግኝ ጣቢያ ግባት ዝግጅት

በበጀት አመቱ የችግኝ ጣቢያ ኮምፖስት ዝግጅትን በሚመለከት ጥራት ያለው ችግኝ ለማፍላት ኮምፖስት ማዘጋጀትና መጠቀም አስፈላጊ በመሆኑ  ለደን ችግኝ ጣቢያ የሚውል 202,602 ሜትር ኩብ ኮምፖስት ለማዘጋጀት ታቅዶ 223,760.2 (110%) ሜትር ኩብ ማዘጋጀት ተችሏል፡፡የችግኝ ጣቢያ ግብዓት ዝግጅትን ስናይ የተለያዩ የደን ዝርያዎችን ችግኝ በብዛትና በጥራት ለማፍላት አስፈላጊ ግብዓቶቸን ማሟላት ተገቢ በመሆኑ 1,474 ኩንታል ጥራት ያለው ዘር በለቀማና በግዥ ለማዘጋጀት ታቅዶ 1,270.6 (86.2%) ኩንታል ዘር መሰብሰብ ተችሏል፡፡ ከዚህም ውስጥ 928 ኩንታል የደን ዘር ለመሰብሰብ ታቅዶ 796.6 (85.9%) ኩንታል ዘር የተሰበሰበ ሲሆን በተጨማሪም 546 ኩንታል የተለያዩ የሳርና የመኖ ዘር ለመሰብሰብ ታቅዶ 474 (86.8%) ኩንታል ዘር ተሰብስቧል፡፡በመሆኑም በተለየ የአሰራር ስልት የሚተከሉ ችግኞችን የጽደቀት መጠን ለመጨመር የተለያዩ መጠን ያላቸው ፕላስቲክ ቲዩብ 3,205

ኩንታል ለማቅረብ ታቅዶ 1,988 (62%) ኩንታል ማቅረብ ተችሏል፡፡ እንዲሁም በተለያዩ ስልቶች ችግኝ አፍልቶ ለተከላ ለማዘጋጀት ችግኝ ጣቢያዎችን በነባርና በአዲስ ወደ ስራ ማስገባት ወሳኝ ተግባር ነው፡፡ በዚህም መሰረት በአዲስና በነባር ወደ ስራ መግባት ካለባቸው 84,834 ችግኝ ጣቢያዎች ውስጥ 69,777 (82.2%) ችግኝ ጣቢያዎችን ወደ ስራ ለማስገባት ተችሏል፡፡ ከዚህም ውስጥ 78,883 ነባር ችግኝ ጣቢያ ለማካሄድና 5,951 በአዲስ ለማቋቋም ታቅዶ 65,387 (82.8%) ችግኝ ጣቢያ ማካሄድና 4,390 (73.8%) ማቋቋም ተችሏል፡፡

## የምግብና ስርዓተ ምግብ ተግባራት

በ2016 በጀት ዓመቱ በክልሉ ያለውን የስርዓተ ምግብ መጓደል ችግሮች ለመቅረፍ ወረዳ አቀፍ የስርዓተ ምግብ ተኮር ግብርና ታቅዶ በእንቅስቃሴ ላይ ይገኛል፡፡ለዚህም ተግባር በሰቆጣ ቃልኪዳን ለታቀፉ 62 ወረዳዎች እና ዘጠኝ ዞኖች ከክልል መንግስት፣ ከፌደራል ግብርና ሚኒስቴር እና ከጤና ሚኒስቴር በአጠቃላይ ለስርዓተ ምግብ ተኮር ግብርና የሚውል 90,688,124 ብር ለተለያዩ ግብዓት መግዣ እና የአቅም ግንባታ ተግባራት ለማከናወን ወደ ወረዳዎች እንዲተላለፍ ተደርጓል፡፡ በበጀት ዓመቱ 325,073 እናቶችን የተቀናጀ የጓሮ ዙሪያ ስርዓተ ምግብ ተኮር ግብርና በማካሄድ የተሰባጠረ አመጋገብ እንዲኖራቸው ለማድረግ ታቅዶ 287,958 (89%) እናቶች እንዲጠቀሙ ተደርጓል፡፡

በበጀት ዓመቱ 139,288 ነፍሰጡርና አጥቢ እናቶች የአበሻ ጎመን እንዲያለሙ ለማድረግ ታቅዶ 186,277 (100% በላይ) ተሳታፊ እንዲሆኑ ተደርጓል፡፡ 2,438 ኪሎ ግራም የአበሻ ጎመን ዘር ለማቅረብ ታቅዶ 5,146 (100% በላይ) ኪሎ ግራም ማቅረብ ተችሏል፡፡ በመጨረሻም 348,220 ኩንታል የአበሻ ጎመን ለማምረት ታቅዶ 321,060 (92%) ኩንታል ምርት ተሰብስቧል፡፡ በተመሳሳይ 265,339 ነፍሰጡርና አጥቢ እናቶችን ብርቱካናማ ስኳር ድንች እንዲያለሙ ለማድረግ ታቅዶ 200,457 (76%) ተሳታፊ እንዲሆኑ ተደርጓል፡፡ለዚህም 10,613,560 ቁርጥራጭ ለማቅረብ ታቅዶ 6,013,711 (57%) ቁርጥራጭ ማቅረብ ተችሏል፡፡ በመጨረሻም 19,105 ኩንታል ለማምረት ታቅዶ 15,339 (80%) ኩንታል ምርት ተሰብስቧል፡፡

ከዚሁ ጋር በተገናኘ በበጀት ዓመቱ 310,662 እናቶች አካባቢን መሰረት ያደረገ ሌሎች የጓሮ አትክልት እንዲያለሙ ታቅዶ 312,821 (100% በላይ) ተሳታፊ እንዲሆኑ ተደርጓል፡፡ ለዚህም 7,767 ኪሎ ግራም ዘር ለማቅረብ ታቅዶ 7,571 (97%) ኪሎ ግራም ዘር ማቅረብ ተችሏል፡፡ በመጨረሻም 621,324 ኩንታል አትክልት ለማምረት ታቅዶ 620,232 (100%) ኩንታል

ምርት ተሰብስቧል፡፡ በምርት ዘመኑ 17,460 ነፍሰጡርና አጥቢ እናቶችን በፕሮቲን የበለፀገ በቆሎ አልምተው እንዲጠቀሙ ታቅዶ 15,292 (88%) እናቶች ተሳታፊ ማድረግ ተችሏል፡፡ ለዚህም 546 ኩንታል ዘር ለማቅረብ ታቅዶ 582 (100%) ኩንታል በማቅረብ ማሰራጨት ተችሏል፡፡

በምርት ዘመኑ 14,950 ነፍሰጡርና አጥቢ እናቶችን በብረትና በዚንክ የበለፀገ ቦሎቄ አልምተው እንዲጠቀሙ ታቅዶ 15,442 (100%) እናቶች ተሳታፊ ማድረግ ተችሏል፡፡ ለዚህም 1,495 ኩንታል ዘር ለማቅረብ ታቅዶ 1607 (100%) ኩንታል ዘር ቀርቦ ተሰራጭቷል፡፡ በምርት ዘመኑ 2,572 ነፍሰጡርና አጥቢ እናቶች የእርግብ አተር እንዲያለሙ ታቅዶ 1600 (62%) እናቶች ተሳታፊ ማድረግ ተችሏል፡፡ ለዚህም 23 ኩንታል ዘር ለማቅረብ ታቅዶ 29 (100% በላይ) ኩንታል ቀርቦ ተሰራጭቷል፡፡ እንዲሁም በምርት ዘመኑ 828 ነፍሰጡርና አጥቢ እናቶች ደገራ እንዲያለሙ ታቅዶ 997 (100% በላይ) እናቶች ተሳታፊ ማድረግ ተችሏል፡፡ ለዚህም 31 ኩንታል ዘር ለማቅረብ ታቅዶ 36 (100%) ኩንታል ቀርቦ ተሰራጭቷል፡፡

በሌላ በኩል በምርት ዘመኑ 1,100 ነፍሰጡርና አጥቢ እናቶች እንቁ ዳጉሳ እንዲያለሙ ታቅዶ 1172 (100%) እናቶች ተሳታፊ ማድረግ ተችሏል፡፡ ለዚህም 28 ኩንታል ዘር ለማቅረብ ታቅዶ 32 (100% በላይ) ኩንታል ዘር ቀርቦ ተሰራጭቷል፡፡ በበጀት ዓመቱ 14,226 የተሰባጠረ አመራረት ሰርቶ ማሳያና የገበሬ በዓል ለማካሄድ ታቅደ 10,516 (74%) የሚሆነውን ለማከናወን ተችሏል፡፡ እንዲሁም 7,360 የምግብ አዘገጃጀትና አመጋገብ ሰርቶ ማሳያና የገበሬ በዓል በማካሄድ 147,200 እናቶችን ለማሳተፍ ታቅዶ 4,376 (59%) ሰርቶ ማሳያ በማከሄድ 88,613 (60%) እናቶችን ማሳተፍ ተችሏል፡፡ በንጥረ ምግብ ይዘታቸው የበለፀጉ ሰብሎች ላይ የድህረ ምርት ብክነት ለመቀነስ የሚያስችል 176,015 አየር የማያስገባ ጆንያ ለማቅረብ ታቅዶ 198,066 (100%) ኩንታል ምርት ተሰብስቧል፡፡

በበጀት ዓመቱ በምግብና ስርዓተ ምግብ ዙሪያ ለ10,171 በየደረጃው ለሚገኙ ባለሙያዎች (የክልል 40፣ የዞን 180፣ የወረዳ 2,591፣ የቀበሌ 7,360) ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ ለ50 የክልል፣ ለ176 የዞን፣ ለ3331 የወረዳና ለ8,687 የቀበሌ በድምሩ 12,235 (100%) ባለሙያዎች ስልጠናው ተስጥቷል፡፡ በተጨማሪም ለ404,800 ነፍሰጡርና አጥቢ እናቶች ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ 397,787 (98%) ለነፍሰጡርና አጥቢ እናቶች ስልጠና ተሰጥቷል፡፡ እንዲሁም ሞዴል የስርዓተ ምግብ መንደር በአዲስ ማቋቋም 99 እና ነባሮችን ለማጠናከር 70

ታቅዶ በአዲስ 124 (100%) ማቋቋምና በነባር 70 (100%) ማጠናከር ተችሏል፡፡ በበጀት ዓመቱ የምግብ ሰርቶ ማሳያ ማዕከላትን ለመገንባት 5 ታቅዶ 5 (100%) ማእከላት መገንባት ተችሏል፡፡

## የእንሰሳት ሀብት ልማት

ክልሉ ከፍተኛ ቁጥር ያለው የእንሰሳት ሀብት ባለቤት ነው፡፡በክልላችን ከእንሰሳት ሀብቱና ተዋጽኦዎች የሚገኘው እሴት ጭማሪ ከሰብል ምርት እሴት ጭማሪ ቀጥሎ ከፍተኛ ድርሻ ይዞ ይገኛል፡፡ከክልሉ ኢኮኖሚ በየዓመቱ በአማካይ ከ41.1 ቢሊየን ብር በላይ የሚሆነው እሴት ጭማሪ ከእንሰሳት ሀብቱ የሚገኝ ሲሆን በአማካይ ከ14% በላይ የሚሆነው እሴት ጭማሪ በዚህ ዘርፍ ተሸፍኖ እናገኘዋለን፡፡ ስለሆነም በበጀት ዓመቱ ወተት ምርት 1,841,733 ቶን ለማምረት ታቅዶ 1,903,058 ቶን ወይም የዕቅዱን (100%) ማከናወን ተችሏል፡፡እንዲሁም የሥጋ ምርት 551,455.3 ቶን ለማድረስ ታቅዶ 448,816 ቶን ወይም የዕቅዱን (81.3%) ማከናወን ተችሏል፡፡በበጀት አመቱ የእንቁላል ምርት 764 ሚሊዮን ለማምረት ታቅዶ 851 ሚሊዮን በማከናወን የዕቅዱን (100% በላይ) ማድረስ ተችሏል፣ የማር ምርት 30,133 ቶን ለማድረስ ታቅዶ 22,292 በማድረስ የዕቅዱን (74%) ተከናውኗል፣ የአሳ ምርት 37,554 ቶን ለማድረስ ታቅዶ 29,332 ቶን የዕቅዱን (78%) ተከናውኗል፣ ቆዳና ሌጦ 9.1 ሚሊዮን ለገቢያ ለማቅረብ ታቅዶ 6.4 ሚሊዮን (70%) መቅረብ ተችሏል፡፡

## የእንስሳት ጤና ምርመራና ጥናት

በበጀት አመቱ የእንስሳት ጤና ምርመራና ጥናትን በሚመለከት ድንበር ዘለል የእንስሳት በሽታዎችና መደበኛ የበሽታ ወረርሽኝን ለመከላከልና ለመቆጣጠር በተሰራው ስራ ለ6.4 ሚሊዮን እንስሳት የክትባት አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ 36.28 ሚሊዮን (60%) እንስሳት የክትባት አገልግሎት እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡እንዲሁም 27.2 ሚሊዮን እንስሳት የቅድመ-መከላከል የሕክምና አገልግሎት እንዲያገኙ ለማድረግ ታቅዶ 18.04 ሚሊዮን (66%) እንስሳት የቅድመ-መከላከል ሕክምና ተሰጥቷቸዋል፡፡ ለ11.2 ሚሊዮን የእንስሳት ፈውስ ሕክምና አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ 8.52 ሚሊዮን (76%) ተሰጥቷል፡፡

## የአርሶ አደር በዓል ማካሄድ

በ2016 ዓ.ም በአርሶ አደር ማሰልጠኛ ማዕከላትና በአርሶ አደር ማሳ የተካሄዱ ሠርቶ ማሳያዎችን በመጠቀም የአርሶ አደር በዓል በማዘጋጀት አዳዲስ አሰራሮችንና ቴክኖሎጅዎችን በማየት ወደ ራሳቸው ማሳ ወስደው ከልማዳዊ አሰራር ወደ ዘመናዊ የግብርና አሰራር እንዲሸጋገሩ እና ምርትና ምረታማነትን ማሳደግ እንዲችሉ የማድረግ ስራ ተሰርቷል፡፡በመሆኑም በበጀት ዓመቱ 251,679 የገበሬ በዓል ለማካሄድ ታቅዶ 177,830 (71%) የተከናወነ ሲሆን በዚህም 17,361,540 አርሶ አደሮችን ለማሳተፉ ታቅዶ ወንድ 4,739,416 ሴት 6,344,974 በድምሩ11,084,390 (64%) አርሶ አደር ለማሳተፍ ተችሏል፡፡

## የአርሶ አደር ማሰልጠኛ ማዕከላት

የአርሶ አደር ማሰልጠኛ ተቋማትን በማጠናከርና በማዘመን የሚጠበቅባቸውን ተልኮ እንዲወጡ በማድረግ የአርሶ አደሩን የእውቀትና ክህሎት ማሳደግ ያስፈልጋል፡፡በዚህም መሰረት በበጀት ዓመቱ 383 የአርሶ አደር ማሰልጠኛ ተቋማትን ለማጠናከር ታቅዶ 288 (75%) ማከናወን ተችሏል፡፡ በተጨማሪም 450 ነባር የልማት ጣቢያ ባለሙያ መኖሪያ ቤት ለመጠገን ታቅዶ በበጀት አመቱ መጨረሻ 142 (32%) መጠገን ተችሏል፡፡ የአርሶ አደር ማሰልጠኛ ተቋማት ነባሩ ጥገና ክንውኑ ካለፈው ዓመት ጋር ሲነፃፀር በቁጥር 91 መቀነስ ያሳየ ሲሆን በተጨማሪም የቀበሌ ባለሙያዎች መኖሪያ ቤት ጥገና በአንዳንድ ዞኖችና ወረዳዎች የሰላም ችግር በመኖሩ 117 መቀነስ አሳይቷል፡፡የአርሶ አደር ማሰልጠኛ ተቋማትን ደረጃ ማሳደግን በተመለከተ ከቅድመ መሰረታዊ ወደ መሰረታዊ 339 ለማሳደግ ታቅዶ 179 (53%) ከመሰረታዊ ወደ መካከለኛ 166 ለማሳደግ ታቅዶ 206 (124%) እንዲሁም ከመካከለኛ ወደ ከፍተኛ 60 ታቅዶ 30 (50%) ማሳደግ ተችሏል፡፡

## የመኽር እርሻ ሥራ እንቅስቃሴ

በ2016/17 ምርት ዘመን በመኽር 5,185,468 ሄክታር መሬት ለማልማት ታቅዶ ወደ ተግባር የተገባ ሲሆን በዚህም በበጀት አመቱ መጨረሻ 4,540,822 (88%) ሄክታር መሬት ማረስ ተችሏል፡፡በባለፈው ዓመት በተመሳሳይ ወቅት ከታረሰው 4,434,242 ሄክታር መሬት ጋር ሲነጻጸር በ106,580 ሄክታር ብልጫ አለው፡፡

### ማሳን በትራክተር ማረስ

በምርት ዘመኑ 897,809 ሄክታር መሬት በትራክተር ለማረስ ታቅዶ በበጀት አመቱ መጨረሻ በ1,622 ትራክተር በመጠቀም 571,242 (64%) ሄክታር መሬት ማረስ ተችሏል፡፡ይህም ከባለፈው ምርት ዘመን ተመሳሳይ ወቅት በትራክተር ከታረሰው 391,062 ሄክታር መሬት ጋር ሲነጻጸር በ180,180 ሄክታር ብልጫ ያለው ሲሆን እንዲሁም ከነበረው 1,524 የትራክተር ቁጥር ጋር ሲነጻጸር በ98 ትራክተር ብልጫ አለው፡፡ የትራክተር እርሻ ጭማሪ ያሳየው በየአመቱ የአርሶ አደሩ የትራክተር የመጠቀም ፍላጎት እየጨመረ መምጣት፣ 20/80 የብድር አቅርቦት በፋይናንስ ተቋማት በማመቻቸትና መንግስት ለዘርፉ የሰጠው ትኩረት ከፍተኛ በመሆኑ ነው፡፡

### ሰብል በመስመር መዝራት

በምርት ዘመኑ ይለማል ተብሎ በእቅድ ከተያዘው መሬት ውስጥ 2,462,427 ሄክታር በመስመር ለመዝራት ታቅዶ በበጀት አመቱ መጨረሻ 942,212.5 ሄክታር (38%) መሬት በመስመር ተዘርቷል፡፡ይህ አፈጻጸም ከአለፈው አመት በተመሳሳይ ወቅት በመስመር ከተዘራው 870,669 ሄክታር ጋር ሲነጻጸር በ71,543.5 ሄክታር ብልጫ አለው፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት በምርት ዘመኑ የአገዳ ሰብሎች የዘር ሽፋን በመጨመሩና የአርሶአደሮች በመስመር የመዝራት ልምድ እያደገ በመምጣቱ ነው፡፡

### የኮሞዲቲ ሰብሎች አፈጻጸም

በ2016 ዓ.ም በተመረጡ 10 የኮሞዲቲ ሰብሎች (በቆሎ፣ ቢራ ገብስ፣ ስንዴ፣ ጤፍ፣ ማሽላ፣ ሰሊጥ፣ ማሾ፣ ቦሎቄ፣ ሩዝ እና አኩሪ አተር) ጠቅላላ ከሚለማው መሬት 48.3% ድርሻ እንዲኖረው በማድረግ 2,502,782 ሄክታር ማሳ በ226 ወረዳ 8,662 ቀበሌ በመለየትና 36,542 ክላስተር በማልማት 99,800,215 ኩንታል ምርት ለማምረት ታቅዶ 2,166,912 ሄክታር (87%) ማሳ በዘር መሸፈን ተችሏል፡፡ይህም በአለፈው ዓመት በተመሳሳይ ወቅት በኩታ-ገጠም ከተዘራው 594,751 ሄክታር መሬት ጋር ሲነጻጸር በ1,572,161 ሄክታር ብልጫ አለው፡፡ አፈጻጸሙ የተሻለ የሆነው ለኮሞዲቲ ሰብሎች ልማት ልዩ ትኩረት የተሰጠ በመሆኑና ዝናብ ቀድሞ በመግባቱና ስርጭቱም የተስተካከለ በመሆኑ ነው፡፡ይህን ለማልማትም 810,026 ኩንታል የአፈር ማዳበሪያ፣ 99,096 ኩንታል ምርጥ ዘርና 34,791 ኩንታል ዘር ጥቅም ላይ

ውሏል፡፡ በዚህም ወንድ 3,345,502፣ ሴት 538,657 ድምር 3,884,159 አርሶ አደሮችን ለማሳተፍ ታቅዶ በበጀት አመቱ መጨረሻ ወንድ 1,623,573፣ ሴት 220,724 በድምሩ 1,844,297 አርሶአደሮችን ማሳተፍ ተችሏል፡፡

### የበልግ ሰብል ልማት እንቅስቃሴ

በበጀት አመቱ በበልግ 239,509 ሄክታር ማሳ በማልማት 4,260,370 ኩንታል ምርት ለማምረት ታቅዶ 247,463.6 ሄክታር (103%) ማሳ ማልማት ተችሏል፡፡ ከባለፈው ተመሳሳይ ወቅት በዘር ከተሸፈነው 230,312 ሄክታር መሬት ጋር ሲነጻጸር በ7.5% ጭማሪ ያሳያል፡፡ በዚህ ዓመት ብልጫ ያሳየበት ዋናው ምክንያት የበልግ ዝናብ አጀማመርና ስርጭት በሁሉም በልግ አብቃይ አካባቢዎች ምቹ ሁኔታ የፈጠረ በመሆኑ ነው፡፡ለዚህም 15,070.5 ኩንታል የአፈር ማዳበሪያና 1,756 ኩንታል ምርጥ ዘር መጠቀም ተችሏል፡፡

### መደበኛ ኮምፖስት ዝግጅት

የተቀናጀ የአፈር ለምነት ስራን ለማሳለጥና በዘላቂነት የመሬት ለምነትን ለማሻሻል ያስችል ዘንድ 102,031,197 ሜትር ኩብ መደበኛ ኮምፖስት ለማዘጋጀት ታቅዶ 59,503,665 ሜትር ኩብ (58%) ኮምፖስት ተዘጋጅቷል፡፡በዚህም 2,258,862 አርሶ አደሮችን ማሳተፍ የተቻለ ሲሆን 59,503,665 ሜትር ኩብ ኮምፖስት ከአፈር ጋር በማዋሃድ 1,630,313 ሄክታር ማሳ ማልማት ተችሏል፡፡

### የቨርሚ ኮምፖስት ዝግጅት

በበጀት ዓመቱ 2,265,195 ኩንታል ቨርሚ ኮምፖስት ለማዘጋጀት ታቅዶ 369,518 (16%) ኩንታል ተዘጋጅቷል፡፡በዚህም 29,914 አርሶ አደሮች ተሳታፊ ሲሆኑ 369,518 ኩንታል ቨርሚ ኮምፖስት ከአፈር ጋር በማዋሃድ 12,317 ሄክታር ማሳ ማልማት ተችሏል፡፡ምንም እንኳ አፈፃፀሙ ከአምናው ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነፃፀር በ152,731 ኩንታል ብልጫ ያለው ቢሆንም ከእቅድ አንጻር ግን በጣም ዝቅተኛ ነው፡፡ ይህ የሆነበት ዋናው ምክንያት ወረዳዎች ተስቦ ቀልዝ ከባህርዳር ለመውሰድ በተከሰተው የፀጥታ ችግር ምክንያት ስላልቻሉ ነው፡፡

### የባዮሳለሪ ኮምፖስት ዝግጅት

በበጀት አመቱ 292,152 ሜትር ኩብ ባዮስለሪ ኮምፖስት ለማዘጋጀት ታቅዶ 147,275 ሜትር ኩብ (50%) የተዘጋጀ ሲሆን በዚህም 5,620 አርሶ አደሮችን ማሳተፍ ተችሏል፡፡ በመሆኑም 147,275 ሜትር ኩብ ባዮሳለሪ ኮምፖስት ከአፈር ጋር በማዋሃድ 18,409 ሄክታር ማሳ ማልማት ተችሏል፡፡ ምንም እንኳን አፈፃፀሙ ከባለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻጸር በ21,045 ሜትር ኩብ ብልጫ ያለው ቢሆንም ከእቅድ አንጻር ሲታይ ግን በጣም ዝቅተኛ ነው፡፡ አፈፃፀሙ ዝቅተኛ የሆነበት ዋናው ምክንያት በየደረጃው ያሉ ባለሙያዎች በተከሰተው የፀጥታ ችግር ምክንያት ከቦታ ቦታ ተንቀሳቅሰው ድጋፍና ክትትል ለማድግ ስላልቻሉ ነው፡፡

### የኮትቻ አፈር ልማት

በበጀት አመቱ 677,913 ሄክታር ማሳ በዘመናዊና በባህላዊ መንገድ ለማጠንፈፍ ታቅዶ በበጀት አመቱ መጨረሻ 567,814 ሄክታር (84%) በመለየት በ5,271 ክላስተር በማደረጀት በቢቢኤም 17,698 ሄክታር እና በባህላዊ ደግሞ 173,050 ሄክታር በድምሩ 190,748 ሄክታር (28%) በማንጣፈፍ ለማልማት ተችሏል፡፡ከባለፈው ተመሳሳይ ወቅት በክላስተር ከተደራጀው 5,637 ሄክታር ጋር ሲነጻጸር በ366 በማነስ ያሳያል፡፡እንዲሁም ማጠንፈፍ ከተቻለው 192,077 ሄክታር ጋር ሲነጻጸር በ1,329 ሄክታር በማነስ ያሳያል፡፡

### በመስኖ የለማ መሬት

በነባር 280,067 ሄክታር እና በአዲስ 53,349 ሄክታር በድምሩ 333,416 ሄክታር በመስኖ ለማልማት ታቅዶ በነባር 276,896 ሄክታር (98.8%) እና በአዲስ 24,573 ሄክታር (46%) በድምሩ 301,469 ሄክታር (90%) መሬት ታርሶ በነባር 275,024 (98.2%) ሄክታር እና በአዲስ 24,740 (46.4%) ሄክታር በድምሩ 299,764 (90%) ሄክታር በዘር ለመሸፈን የተቻለ ሲሆን በዚህም 25,723,636 ኩንታል ምርት ለማምረት ታቅዶ 29,933,648 (116%) ኩንታል የመስኖ ምርት ተሰብስቧል፡፡ በነባርና በአዲስ መስኖ ልማት ወንድ 1,034,378 ሴት 105,649 በድምሩ 1,140,027 አርሶ አደሮችን ማሳተፍ ተችሏል፡፡

## ስንዴ ልማት

በበጀት አመቱ በስንዴ ልማት 250,000 ሄክታር መሬት ለማልማት ታቅዶ 151,276 ሄክታር (60.5%) በዘር መሸፈን ተችሏል። በዚህም 459,650 አርሶ አደሮችን ለማሳተፍ ተችሏል።ለመስኖ ስንዴ ስራውም 255,028 ኩንታል የአፈር ማዳበሪያ እና 198,577 ኩንታል ምርጥ ዘር ጥቅም ላይ ውሏል። በመሆኑም በመስኖ ስንዴ ከለማው መሬት ውስጥ ከ149,206 ሄክታር መሬት ላይ 5,054,186.6 ኩንታል ምርት ተሰብስቧል።



የስንዴ ሰብል -ሲያደብር ወዩ ወረዳ

## ቅመማ ቅመም ሰብሎች

በመኸር 78,902 ሄክታር በማልማት 1,232,542 ኩንታል ምርት ለማምረት ታቅዶ በበጀት አመቱ መጨረሻ 1,410 (2%) ሄክታር በዘር ተሸፍኗል።በአጠቃላይ በአትክልት፣ ስራስርና ቅመማቅመም ሰብሎች 278,553 ሄክታር መሬት በማልማት 32,747,121 ኩንታል ምርት ለማምረት ታቅዶ 127,227 (46%) ሄክታር ማሳ በዘር ተሸፍኗል። ለዚህም 598,336 ኩንታል ማዳበሪያ፣ 5,411,767 ኩንታል የተለያዩ የአትክልት እና ስራስር ቅመማቅመም ዘር እና 213,269,403 ቁርጥራጭ ለመጠቀም ታቅዶ በበጀት አመቱ መጨረሻ 182,613 (30.5%) ኩንታል ማዳበሪያ፣ 2,649,299 ኩንታል (በዋናነት ድንች) (50%) ዘር እና 3,456,912 (2%) የተለያዩ ቁርጥራጭ (የስኳር ድንች) ጥቅም ላይ ውሏል። እንዲሁም 1,695,265 ኩንታል ኮምፖስት ጥቅም ላይ ማዋል ተችሏል። በዚህም 1,300,269 አርሶ አደሮች ለማሳተፍ ታቅዶ 471,976 (61,652 ሴት) አርሶ አደሮች ተሳታፊ ሆነዋል።

### የቆላ ፍራፍሬ ልማት

በበጀት አመቱ 7,725,179 የቆላ ፍራፍሬ ችግኝ በማዘጋጀት 19,973 ሄክታር መሬት ላይ 7,725,179 ችግኝ ተከላ በማካሄድ 154,846 (46,454 ሴቶች) አርሶ አደሮችን ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ በበጀት አመቱ መጨረሻ 7,033,975 (91%) ችግኝ ተዘጋጅቷል፡፡በዚህም ከቆላ ፍራፍሬ ችግኞች ውስጥ 2,236,445 (90%) የአቮካዶ ችግኝና 1,948,403 (93%) የማንጎ ችግኝ የተዘጋጀ ሲሆን 451,738 አቦካዶ፣ 498,103 የማንጎ እና 119,680 የብርቱካን ችግኝ ተከትቦ ለተከላ ተዘጋጅቷል፡፡ በመሆኑም በበጀት አመቱ መጨረሻ 11,350 የቆላ ፍራፍሬ ችግኝ በ8 ሄክታር ማሳ ላይ የተተከለ ሲሆን በዚህም 126 አርሶ አደሮች ተሳታፊ ሁነዋል፡፡

### የደጋ ፍራፍሬ ልማት

በ2016 ዓ.ም 682,146 ችግኝ በማዘጋጀት በ474 ሄክታር መሬት ላይ ተከላ በማካሄድ 10,528 (3,158 ሴቶች) አርሶ አደሮችን ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ 571,935 (83%) ችግኝ የተዘጋጀ ሲሆን ከዚህም 407,007 የአፕል ችግኝ በመክተብ ለተከላ የተዘጋጀ ሲሆን እስከዚህ ሩብ ዓመት 1,005 ችግኝ በ1 ሄክታር መሬት ላይ ለመትከል ተችሏል፡፡

### እርሻ ሜካናይዜሽን

በክልሉ መንግስት 20በ80 የመካናይዜሽን መሳሪያዎች የመግዣ ስርዓት መሰረት አበዳሪ ባንኮችን በማፈላለግና መነሻ በጀት በመመደብ አርሶ አደሮች፣በግብርናው ዘርፍ የተሰማሩ ባለሀብቶች፣ድርጅቶች እና ተቋማት ትራክተር እንዲወስዱ የማድረግ ስራ ተሰርቷል፡፡ ከ2015/16 ምርት ዘመን በክልሉ መንግስት 30 ሚሊዮን ዶላር በማስፈቀድ ከቀረቡት 412 ትራክተሮች ውስጥ ሳይሰራጩ የከረሙትን ለአርሶአደሩ ተደራሽ ለማድረግ ሰፊ ስራ ተሰርቷል፡፡ በ2016 ዓ.ም 144 ትራክተሮችን ለአርሶ አደሩ ለማሰራጨት ታቅዶ በበጀት አመቱ መጨረሻ 169 ትራክተሮችን (ከ100% በላይ) ማቅረብና ማሰራጨት የተቻለ ሲሆን በዚህም የክልሉን የትራክተር ቁጥር ወደ 1,950 ማድረስ ተችሏል፡

እንዲሁም በክልላችን ከሚታረሰው መሬት ውስጥ 60% የሚሆነው ለመካናይዜሽን ምቹ በመሆኑ 46 የሰብል መውቂያ ኮምባይነር ለማቅረብ ታቅዶ 13 ኮምባይነር በማቅረብ ለማሰራጨት ተቻለ ሲሆን በዚህም የክልሉን የኮምባይነር ቁጥር 54 ማድረስ ተችሏል፡፡ በመሆኑም በክልሉ ያለውን የኮምባይነር ቁጥር 54 ለማድረስ ተችሏል፡፡ በተጨማሪም 23

ከፍተኛ መውቂያ መሳሪያዎችን ለማቅረብ ታቅዶ 13 ኮምባይነሮችን በማቅረብ የክልሉን የኮምባይነር ቁጥር 54 ማድረስ ተችሏል፡፡ በተመሳሳይ 186 ትሬሽር እና 902 ሸለሮችን ለማቅረብ እና ለማሰራጨት ታቅዶ 102 ትሬሸር እና 885 ሸለሮችን ማሰራጨት ተችሏል፡፡



ስንዴ በኮምባይነር ሲሰበሰብ- ሰሜን ሜጫ ወረዳ

## መንገድ ልማት

የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የመንገድ ቢሮ የሚያስተዳድራቸው ነባር መንገዶችን በመጠገን እና አዲስ መንገዶችን በመገንባት ያልተቋረጠ አገልግሎት እንዲሰጡ በማድረግ፣ የግብርና ልማትን ከማስፋፋት አንጻር በተቀመጠው አቅጣጫ መሰረት መንገዶችን በመጠገን እና በመገንባት ዞንን ከወረዳ፤ወረዳንና ቀበሌዎችን ከወረዳዎችና ከዋና መንገዶች ጋር የሚያገናኙ መንገዶችን በመጠገን እና በመገንባት ክረምት ከበጋ ያልተቋረጠ የትራፊክ አገልግሎት እንዲያገኙ ማድረግና የግብርና ምርት እና ግብዓት በወቅቱ ወደ ገበያ እንዲደርስ የሚያስችል ሁኔታ በመፍጠር ጥራቱን የጠበቀ ጥገናና ግንባታ በማከናወን ለክልሉ ልማት መፋጠን ምቹ ሁኔታ መፍጠር ነው፡፡

### በተሰሩ የጠጠር መንገዶች የስትራክቸር ግንባታ

ያደሩና በአዲስ የተጀመሩ የተለያየ መጠንና አይነት ያላቸው የቱቦ ቀበራዎችንና ስትራክቸሮችን ጨምሮ በቁጥር 308 በግንባታ ላይ ሲሆኑ 63 ስትራክቸሮች በ20 ፕሮጀክቶች አነስተኛ፣ መካከለኛ፣ ከፍተኛ መጠን ያላቸው ስትራክቸሮች በግንባታ ላይ ናቸው፡፡ከዚህ ውስጥ በአፈጻጸም ደረጃ ሲታይ 34ቱ 100% የተጠናቀቁ፣አስሩ በአማካኝ ከ80-97% አፈጻጸም የደረሱ፣ 12ቱ ከ40-69% በላይ አፈጻጸም ያላቸው ሲሆን አስሩ ደግሞ ከ10% እስከ 40% አፈጻጸም ላይ ይገኛሉ፡፡

## የኮንክሬት ድልድዮች የዲዛይን እና ግንባታ ስራ

የዲዛይን ስራቸው 100% ተጠናቆ የግንባታ ስራው ደግሞ ከ89% በላይ የተፈጸመ ሲሆን አስራ አራቱ ሙሉ በሙሉ የተጠናቀቁ፣ አራቱ ከ80% በላይ፣ አንዱ 31% አፈጻጸም ላይ የሚገኙ ሲሆን ለማሳያ ያህል ወደ ግንባታ ከገቡት ውስጥ የተከዜ ወንዝ የብረት ድልድይ መልሶ ግንባታ የሲቪል ስራው 100%፣ ማዕከላዊ ጎንደር ዞን ጥርሀሆ ወንዝ ኮንክሪት ድልድይ 100%፣ ሰሜን ጎንደር ዞን ጭራ ወንዝ ኮንክሪት ድልድይ፣ አዊ ብሄረሰብ ዞን ፈጣን ቁጥር አንድ ድልድይ፣ ኦሮሞ ብሄረሰብ ዞን ወርቄ ወንዝ ድልድይ፣ ምስራቅ ጎጃም ዞን አዧሪ ድልድይ፣ሰሜን ወሎ ዞን ጥራሬ ወንዝ ድልድይ፣ሰሜን ሸዋ ዞን ሳላ ሜዳ ቁጥር ሁለት፣ ዋግህምራ ብሄረሰብ ዞን ሚሽር ድልድይ ፣ደቡብ ጎንደር ወርቅ ውሃ እና ደቡብ ወሎ ዞን ቦርከና ወንዝ ድልድይ 100% አፈጻጸም በሚባል ደረጃ የደረሱ ሲሆን፣ ወልቃይት መከዞ ድልድይ፣ ምዕራብ ጎንደር ቋራ መሃዲድና ምዕራብ ጎጃም ዞን ለዛ ድልድይ 75% የደረሱ ናቸው።

## ተንጠልጣይ የእግረኛ ድልድዮች ዲዛይንና ግንባታ

የዲዛይን ስራቸው 100% ተጠናቆ ወደ ግንባታ ስራ የገቡ ሲሆን ከገቡት ውስጥ አርባ አራቱ 100% የተጠናቀቁ፣አንዱ 32% አፈጻጸም ላይ ይገኛል። ጠለምት ወረዳ ደበልጋይ፣ ዚገም ወረዳ ማጠን፣አየሁ ጓጉሳ ወረዳ ፈጣን፣ ዳባት ወረዳ በራ፤ ሰቆጣ ወረዳ ጥራሬ፣ ጋዝጊብላ ወረዳ ቂታ፣ላስታ ወረዳ ተከዜ፣ አልብኮ ወረዳ ሳልመኒ፣ አርማጭሆ ማህና፣ ባቲ ወረዳ ሰላጤ፣ ወንበርማ ወረዳ ዚግኒ፣ ቋራ ወረዳ ሻሆ፣ መተማ ወረዳ ገንዳውሀ፣ መቅደላ ወረዳ ሳጋ፣ ጠገዴ ወረዳ ዳውጭና፤ደጀን ወረዳ ጨየ፣ ስማዳ ወረዳ ሙጌ፣ ባህር ዳር ዙሪያ አባይ፣ ታች ጋይንት ፈጣን፣ ዳውንት ወረዳ ባርቀጋ፤አሳግርት ወረዳ ብትቻ፣ ሃገረማርያም ዛላ፣አርጡማ ፉርሲ ቦርከና፣ ደጀን ወረዳ ሙጌ ተንጠልጣይ ድልድዮች የተጠናቀቁ ናቸው።




ተንጠልጣይ ድልድይ -ማከላዊ ጎንደር ዞን አርማጭሆ ወረዳ

## የድልድይ ፕሮጀክቶች ግንባታ

በበጀት ዓመቱ የተለያዩ መጠንና አይነት ያላቸው ስትራክቸሮች ማለትም 68 የኮንክሪት፣ 24 ተንጠልጣይ የእግረኛ ድልድዮች በጥቅሉ 92 ድልድዮች ወደ ግንባታ እንዲገቡ ተደርጓል፡፡ ከዚህ ውስጥ 73 የሚሆኑት ድልድዮች ከ70-100% አማካኝ አፈፃፀም ያላቸው ሲሆን 63ቱ 100% አፈጻጸም ላይ የደረሱና በመጠናቀቅ ደረጃ ላይ ናቸው፡፡ ሌሎች ቀሪ 19 ድልዮች በ2017 በጀት ዓመት የሚጠናቀቁ ናቸው፡፡

## የገጠር ቀበሌ ማዕከላትን በመንገድ ተደራሽ ማድረግ

በመሪ ልማት ዕቅዱ ከተያዙት 3428 የገጠር ቀበሌዎች ውስጥ 2621 ቀበሌዎች በመንገድ ተደራሽነት የተገናኙ ሲሆኑ 807 ቀበሌዎች ገና በመንገድ ተደራሽ ያልሆኑ ናቸው፡፡ ስለሆነም በበጀት ዓመቱ 363 ኪሎ ሜትር መንገድ ግንባታ ታቅዶ 354.37 ኪሎ ሜትር (97.4%) በመገንባት 129 ቀበሌዎች ተገናኝተዋል፡፡ ሌላው በመንገድ ፈንድ መልሶ ግንባታ 70 ኪሎ ሜትር የሚሸፍን መንገድ (ኮሸሽላ መርገጭ፣ ዳባ አያታ፣ መንታደብር እነግዴ፣ ቁስቋም ሮቢት) ግንባታ ተጠናቆ የደረጃ ማሻሻል ስራ ተሰርቷል፡፡

## የገጠር መንገድ ጥገና

ቀደም ሲል በከፍተኛ የካፒታል ወጭ የተሰሩ መንገዶችን ዘላቂ አገልግሎት እንዲሰጡ ለማድረግ በ14 ዞኖች በ141 ፕሮጀክቶች በወረዳ ምክር ቤት በጀትና በህብረተሰብ ተሳትፎ በዓመቱ 7679 ኪሎ ሜትር (በማሽን 2028 ኪሎ ሜትር፣ በሰው ሀይል 5651 ኪሎ ሜትር)

መንገድ ለመጠገን ታቅዶ በ140 ፕሮጀክቶች 7005.59 ኪሎ ሜትር (91.23%) መንገድ መጠገን ተችሏል፡፡ በአጠቃላይ በወረዳ አስተዳደር በጀት ድጋፍና ህብረተሰብ ተሳትፎ 7005.59 ኪሎ ሜትር መንገድ የተጠገነ ሲሆን በማሽን 1908.7 ኪሎ ሜትር፣ በሰው ሃይል 5096.8 ኪሎ ሜትር ነው፡፡ በዚህ ስራ የተሳተፈ ህዝብ ወንድ 441,216 ሴት 166,469 ድምር 607,685 (95%) ሲሆን ከጥሬ ገንዘብ በተጨማሪ ህዝቡ በጉልበቱ ያበረከተው በገንዘብ ሲተመን ብር 122,323,200 (88.9%) ነው፡፡




የጠጠር መንገድ ጥገና (ከመካነ ብርሃን ከተማ _ አሠንጋ_ በለገዝ )

### በፌደራል መንገድ ፈንድ ድጋፍ የተጠገነ መንገድ

በበጀት ዓመቱ ከተጠገነው 4,560.63 ኪሎ ሜትር የጥገና ሥራ መካከል 136.8 ኪሎ ሜትር የሚሆነው ለአራት የመንግስት የልማት ድርጅቶች ኮንትራት በመስጠት የተከናወነ ሲሆን በድምሩ የተጠናቀቁ የጥገና መስመሮች ብዛት 204 ሲሆኑ ጎጃም ክላስተር በ52 መስመር 921.922 ኪሎ ሜትር፣ ወሎ በ34 መስመር 716 ኪሎ ሜትር፣ ጎንደር በ24 መስመር 697.90 ኪሎ ሜትር፣ ወልዲያ በ22 መስመር 818.70 ኪሎ ሜትር፣ሸዋ በ34 መስመር 647.74 ኪሎ ሜትር፣ ደብረታቦር በ38 መስመር 758.37 ኪሎ ሜትር መፈጸም ተችሏል፡፡ የመንገድ ፈንድ ሃብት አጠቃቀምን በተመለከተ ብር 812,955,051 ተመድቦ ሙሉ በሙሉ ስራ ላይ ውሏል፡፡

### የህብረተሰብ ተሳትፎና ሃብት ማሰባሰብ

በበጀት ዓመቱ ከህብረተሰብ ተሳትፎ ብር 793,859,769 ለማሰባሰብ ታቅዶ ብር 676,167,019 (85%) በጥሬ ገንዘብ በመሰብሰብ 265 ኪሎ ሜትር (97.4%) መንገድ መገንባት እና 7005.59 ኪሎ ሜትር (91.23%) መንገድ መጠገን ተችሏል፡፡ ከጥሬ ገንዘብ በተጨማሪ ህብረተሰቡ

በጉልበት ያደረገው ተሳትፎ በገንዘብ ሲተመን ብር 122,323,200 (88.9%) ነው፡፡ ሲጠቃለል ህብረተሰቡ በጥሬ ገንዘብና በጉልበት ብር 798,490,219 (85.7%) መሆኑን ያመላክታል፡፡




በደቡብ ወሎ ዞን በህዝብ ተሳትፎ የተሰራ አዲስ መንገድ (ኩታበር ባርቃና)

### የዜጎችን ተጠቃሚነት ለማሳደግ የወጣቶች የስራ እድል ፈጠራ

በበጀት ዓመቱ 36,336 ለዜጎች ስራ ዕድል ለመፍጠር ታቅዶ ለ 35,105 ለሚሆኑ ዜጎች የዕቅዱን 96.6% የስራ ዕድል መፍጠር የተቻለ ሲሆን ከዚህ ውስጥ 2036 ቋሚ የስራ ዕድል የተፈጠረላቸው ናቸው፡፡

### የፌደራል አስፓልት መንገዶች ክትትልና ድጋፍ

በክልላችን በኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር በዕቅድ የተያዙ 61 የመንገድ ግንባታ ፕሮጀክቶች ሲሆኑ (አዳዲስ ፕሮጀክቶች 2፣ ነባር በግንባታ ላይ ያሉ 22፣ በወቅታዊ የፀጥታ ችግር የቆሙ 23፣ በተለያዩ ምክንያቶች የተቋረጡ 14) ርዝመታቸው 3,658.68 ኪሎ ሜትር በዕቅድ ተይዞ ለስራው ማስፈጸሚያ ብር 96,802,383,353.67 የተመደበ በግዥና ምህንድስና ሂደት ላይ ያሉ ፕሮጀክቶች 5፣ በዲዛይን ላይ ያሉ 22 ፕሮጀክቶችን ጨምሮ በጥቅሉ 122 ፕሮጀክቶች ይገኛሉ፡፡

የአስፓልት መንገድ ፕሮጀክቶች አፈፃፀም በተመለከተ ደግሞ በኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር (ERA) ደረጃ ተይዘው ከነበሩ 61 ፕሮጀክቶች በክልላችን የሚገነቡ የአስፋልት መንገዶች በ2016 በጀት ዓመት ለ52 ፕሮጀክቶች በጀት የተያዘላቸው ሲሆን በዓመቱ የሚጠበቅ የግንባታ ዕቅዱ 415.38 ኪሎ ሜትር ሲሆን አንጻራዊ ሰላም ባለባቸው አካባቢዎች በ32 ፕሮጀክቶች በከፊል /መጠነኛ እንቅስቀሴ/ ወደ ስራ በመግባት 107.78 ኪሎ ሜትር (30%) የአስፓልት መንገድ ተገንብቷል፡፡

በአመቱ መጀመሪያ ከ10 ያልበለጡ ፕሮጀክቶች ነበሩ ሲሆን የበጀት ዓመቱ ሲጠናቀቅ ግን ወደ 32 የአስፓልት ፕሮጀክቶች በመጠነኛ የስራ እንቅስቃሴ ላይ ይገኛሉ፡፡ ለዚህ ለውጥ የክልሉ አስተባባሪ ኮሚቴ ክትትል የተሻለ ነው፣ በተለይ የክቡር ርዕሰ መስተዳደር ያልተቋረጠ ድጋፍ፣ ግምገማ፣ ችግር ፈች የሶስትዮሽ ግንኙነቶችና አቅጣጫ ድርሻው የጎላ ነው፡፡ የርዕሰ መስተዳደሩ የመሰረተ ልማት አማካሪ ተከታታይነት ያለው ክትትልና እገዛ ውጤት ነው፡፡

በክልላችን ቀደም ሲል በተገነቡ የፌደራል አስፓልት መንገድ የመንገድ ጥገና ፕሮጀክቶች ብዛት 39 (ከባድ ጥገና 15፣ መደበኛ ጥገና 15፣ ወቅታዊ ጥገና 9) ሲሆኑ ርዝመታቸውም 3,664.94 ኪሎ ሜትር ሲሆን ለስራው ማስፈጸሚያ ብር 2,166,529,638.71 ተመድቦ ወደ ስራ ተገብቷል፡፡

የአስፓልት መንገዶች ጥገና በ34 የጥገና ፕሮጀክቶች በ2016 በጀት ዓመት 3,664.94 ኪሎ ሜትር፣ ታቅዶ 2,557.81 ኪሎ ሜትር (70%) መንገድ በ27 የመንገድ ጥገና ፕሮጀክቶች ተጠግኗል፡፡ለጥገና ዘርፉ የተመደበውን ሃብት ለመጠቀም አሁን የመጣውን ውጤት ትኩረት ሰጥቶ ቀጣይ ከሌሎች አካላት ጋር በትብብር መስራት ይጠበቃል፡፡

### የክላስተሮች አፈፃፀም

| .ቁ | የክላስተሩ ስም | የዓመቱ ዕቅድ | የፊዚካል ስራዎች አፈጻጸም | | | | | | | | ከአመቱ አፈጻጸም በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | የቅየሳ ስራ | የምን ጣሮና ጠረጋ ስራ | የቱቦ ቀበራ ስራ | | የአፈር ድልዳሎ ስራ | ምርጥ ጠጠር የማልበስ ስራ | | የአመቱ ዕቅድ | |
| ጠቅላላ ድምር | | ኪ.ሜ | ኪ.ሜ | ኪ.ሜ | ኪ.ሜ | ቁጥር | ኪ.ሜ | ኪ.ሜ | | ኪ.ሜ | |
| | | 93.88 | 92.2 | 83.34 | 102.26 | 156 | 81.58 | 85.21 | | 93.88 | 95.09 % |
| I | የጎጃም ክላስተር ፕሮጀክቶች | 13.76 | | | 22.78 | 29 | | | | 13.76 | 49.68 % |

| .ቁ | የክላስተሩ ስም | የዓመቱ ዕቅድ | የፊዚካል ስራዎች አፈጻጸም | | | | | | | | ከአመቱ አፈጻጸም በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | የቅየሳ ስራ | የምንጣሮና ጠረጋ ስራ | የቱቦ ቀበራ ስራ | | የአፈር ድልዳሎ ስራ | ምርጥ ጠጠር የማልበስ ስራ | | የአመቱ ዕቅድ | |
| ጠቅላላ ድምር | | ኪ.ሜ | ኪ.ሜ | ኪ.ሜ | ኪ.ሜ | ቁጥር | ኪ.ሜ | ኪ.ሜ | | ኪ.ሜ | |
| II | የጎንደር ክላስተር ፕሮጀክቶች | 33.26 | 52.50 | 49.39 | 35.14 | 65 | 46.33 | 29.75 | | 33.25 | 112.5 % |
| III | የወሎ ክላስተር ፕሮጀክቶች | 38.37 | 23 | 23.10 | 44.34 | 62 | 24.85 | 55.46 | | 38.37 | 107.61 % |
| IV | የሰሜን ሸዋ ክላስተር ፕሮጀክቶች | 8.50 | 16.70 | 10.85 | | | 10.40 | | | 8.5 | 43.89 % |

## ከተማና መሰረተ-ልማት

### የከተሞች መልካም አስተዳደር አቅም ግንባታ ስራ

የከተሞች መልካም አስተዳደር አቅም ግንባታ ስራዎችን ለመስራት በተደረገው ጥረት በከተሞች የሚሰጡ የማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎቶችን ቀልጣፋና ውጤታማ ለማድረግ እንዲቻል 7 የተለያዩ የማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎት ስታንዳርዶች ተዘጋጅተው የወረዱ ሲሆን በ77 ከተማ አስተዳደሮች እና በ12 መሪ ማዘጋጃ ቤት ከተሞች የማዘጋጃቤታዊ አገልግሎት አሰጣጥ ስታንዳርዶች እንዲተገበሩ እና የአገልግሎት አሰጣጡ እንዲሻሻል ለማድረግ ታቅዶ ከ12 መሪ ማዘጋጃ ቤት ከተሞች ውስጥ 5 ከተሞች (41.7%) ወደ ሙከራ ትግበራ ገብተዋል፡፡

### ከተሞችን የተገልጋይ ዕርካታ ማሳደግ

የማዘጋጃቤታዊ አገልግሎት ስታንዳርድ በሚተገበርባቸው 77 ከተማ አስተዳደሮች እና በ12 መሪ ማዘጋጃ ቤት ከተሞች የተገልጋዩ ዕርካታ 60 በመቶ መድረሱ በጥናት ለማረጋገጥ ታቅዶ

በ18 ከተሞች የተከናወነ ሲሆን በመሬት ልማት በ13 ከተሞች የተጠናው አማካይ ውጤት 54.9 ሲሆን በግንባታ ፈቃድ በ5 ከተሞች የተጠናው አማካይ ውጤት 59.3 በመቶ ነው፡፡ የሁለቱ አማካይ ውጤት ደግሞ 57.10 በመቶ ነው፡፡

## የአገልግሎት አቅርቦት ስራ

የቄራ ግንባታ ባለባቸው 45 ከተማ አስተዳደሮች ደረጃውን የጠበቀ የቄራ አገልግሎት እንዲሰጥ ለማድረግ ታቅዶ 8,984 የቀንድ ከብት እና 2,733 የበግና ፍየል የቄራ እርድ አገልግሎት የተሰጠ ሲሆን የእሳት አደጋን ከመከላከልና ከመቆጣጠር አኳያ 171 የእሳት አደጋዎች ተከስተው በመከላከል ሊደርስ ይችል የነበረውን አደጋ መቀነስ ተችሏል፡፡

## 9ኛው የኢትዮጵያ የከተሞች ፎረም

በዘጠነኛው የኢትዮጵያ የከተሞች ፎረም ዝግጅት ላይ እንደ ክልል 50 ከተሞች ተሳትፎ እንዲያደርጉ እቅድ ተይዞ 14 (28%) ከተሞች ተሳትፈዋል፡፡ፎረሙ የዘመኑ ከተሞች ለኢትዮጵያ ብልጽግና በሚል መሪ ቃል ከየካቲት 9 - 15/2016 ዓ.ም በወላይታ ሶዶ ከተማ የተካሄደ ሲሆን በክልላችን ተሳትፎ ያደረጉ ከተሞች ዝርዝር ባህርዳር፣ ጎንደር፣ ደሴ፣ ደብረብርሃን፣ ኮምቦልቻ፣ ወልድያ፣ አላማጣ፣ ቡልጋ፣ አረርቲ፣ ደልጊ፣ ጎርጎራ፣ ሐይቅ፣ ከሚሴ እና ሰቲት ሁመራ ከተሞች ሲሆኑ የከሚሴና ደሴ ከተሞች በየፈርጃው 1ኛ እና 3ኛ ደረጃ በመያዝ የዋንጫ ተሸላሚ ሆነዋል፡፡

## የህብረተሰብ ተሳትፎ

በ2016 ዓ.ም በ683 ከተሞች በህብረተሰቡና በመንግስት በጋራ በሚከናወኑ የአካባቢ ልማት ስራዎችና ፕሮጀክቶች (የመንገድ ጠረጋና ግንባታ፣ የህዝብ መፀዳጃ ቤት ግንባታ፣ የተፋሰስና የዲች ግንባታ፣ የመብራትና የውሃ መስመር ዝርጋታ፣ የአካባቢ ማስዋብና አረንጓዴ ልማት እንዲሁም የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ስራዎች ወዘተ) ላይ ህብረተሰቡ 15% በገንዘብ፣ 15% በቁሳቁስ፣ 20% በጉልበት በድምሩ 50% እንዲያዋጣ በማድረግ 2,611,860,000 ብር የሚገመት የህብረተሰብ ተሳትፎ ለማድረግ ታቅዶ በጥሬ ገንዘብ 452,816,927.25 ብር፣ በጉልበት 483,488,302.71 ብር፣ በቁሳቁስ 316,927,984.17 ብር በድምሩ 1,253,233,214.13 ብር አስተዋጽኦ ተደርጓል፡፡ በመንግስት በኩልም 1,120,442,257.33 ብር ለአካባቢ ልማት ስራዎች ወጪ ተደርጓል፡፡ በጠቅላላው ለአካባቢ ልማት ስራዎች 2,373,675,471.46 ብር

ወጪ የተደረገ ሲሆን የህዝብ ተሣትፎ አፈፃፀም 52.8% ነው፡፡በነዚህ የልማት ስራዎች ላይ ወንድ 1,782,932 ሴት 1,632,018 በድምሩ 3,414,950 የህብረተሰብ ክፍል የተሳተፈ ሲሆን በዚህም የሴቶች ተሳትፎ ድርሻ በአማካይ 47.79 ነው፡፡

## የከተማ አገልግሎት ገቢ አሰባሰብ

በከተማ አገልግሎት ገቢ ለመሰብሰብ በተሰራው ስራ በ683 ከተሞች የገቢ ሀብታቸውን ውጤት በሚያመጣ መንገድ አሟጠው በመጠቀም የመሰረተ ልማት ወጫቸውን 70% ከራሳቸው ማዘጋጃቤታዊ አገልግሎት ገቢ እንዲሸፍኑ ለማድረግ ግብ የተያዘ ሲሆን በ606 መሪ፣ንዑስና ታዳጊ ከተሞች 7,000,128,000.00 ብር ለመሰብሰብ ታቅዶ 642,318,464.23 ብር (9.18%) መሰብሰብ ተችሏል፡፡ በገቢዎች ቢሮ በኩል ከ77 ከተማ አስተዳደሮች 15,500,000,000.00 ብር የአገልግሎት ገቢ ለመሰብሰብ ታቅዶ 3,845,021,033.56 ብር (24.81%) መሰብሰብ ተችሏል፡፡ በጠቅላላው በ683 ከተሞች 22,500,128,000.00 ብር የአገልግሎት ገቢ ለመሰብሰብ ታቅዶ 4,487,339,497.79 ብር የአገልግሎት ገቢ በመሰብሰብ የእቅዱን 19.94% መፈፀም ተችሏል፡፡ ከተሞች መሰብሰብ ካለባቸው 57 የገቢ አርእስቶች ውስጥ በአማካይ በ42 የገቢ አርዕስቶች የአገልግሎት ገቢ መሰብሰብ ተችሏል፡፡

## የከተሞችን ፋይናንስ አጠቃቀም ማሻሻል

የከተሞችን ፋይናንስ አጠቃቀም ውጤታማነት ለማሳደግና ብክነትን ለመከላከል 182 የማዘጋጃ ቤት ከተሞች ኦዲት ለማስደረግ ግብ ተይዞ 66 (36.26%) ከተሞች ኦዲት አስደርገው 3,180,373 ብር ጉድለት የተገኘ ሲሆን ከተገኘው ጉድለት 2,518,703 ብር ተመላሽ ሆኗል፡፡ ከባለፋት ዓመታት በኦዲት የተገኘው 9,101,680 ብር የገንዘብ ጉድለት 100% ተመላሽ ለማድረግ ታቅዶ 2,536,438 ብር ተመላሽ ተደርጓል፡፡

## የከተማ ፕላን ዝግጅትና አፈጻጸም

ከሀገራዊው የከተማ ልማት ስፓሻል ፕላን ጋር የተጣጣመ ክልላዊ የከተማ ልማት ስፓሻል ፕላን እና የከተሞች ክላስተር ልማት ፕላን ለማዘጋጀት ታቅዶ የክልላዊ ከተማ ልማት ስፓሻል ፕላን ዝግጅት አንድ አካል የሆነው የነባራዊ ሁኔታ ትንተና ሪፖርት የተጠናቀቀ ቢሆንም ዋናው ክልላዊ የከተማ ልማት ስፓሻል ፕላን ዝግጅት በተለያዩ ምክንያቶች ተፈፃሚ አልሆነም፡፡በበጀት ዓመቱ አሳታፊ፣ ጥራት ያለውና ወጭ ቆጣቢ የሆነ የከተማ ፕላን ዝግጅት

እንዲኖር በማድረግ ለ105 ከተሞች መሰረታዊ ካርታ፣ ለ90 መሰረታዊ የከተማ ፕላን፣ ለ15 ከተሞች መዋቅራዊ ፕላን እንዲሁም 30 የሰፈር ልማት ፕላን ለማዘጋጀት ታቅዶ የ92 (87.62%) ከተሞች መሠረታዊ ካርታ፣ ለ71 (78.89%) ከተሞች መሰረታዊ የከተማ ፕላን፣ ለ10 (66.67%) ከተሞች መዋቅራዊ ፕላን እንዲሁም 26 (86.67%) የሠፈር ልማት ፕላን ተዘጋጅቷል፡፡በተመሳሳይ የ80 ከተሞችን መሠረታዊ መረጃዎች በማሰባሰብና በማደራጀት ለተጠቃሚዎች ዝግጁ እንዲሆን ለማድረግ ታቅዶ የ71 (88.75%) ከተሞች መሠረታዊ መረጃዎች በማሰባሰብና በማደራጀት ለተጠቃሚዎች ዝግጁ እንዲሆን ማድረግ ተችሏል፡፡ከዞኖችና ከከተሞች ለሚቀርቡ የፕላን ማስተካከያ ጥያቄዎችና የፕላን ምደባ ለውጥ ጥያቄዎች 100% ምላሽ ለመስጠት ታቅዶ ከ28 ከተሞች ለቀረቡ የፕላን ማስተካከያ እና 57 የፕላን ምደባ ለውጥ ጥያቄዎች ተገቢውን ምላሽ መስጠት ተችሏል፡፡

### በከተሞች በሚፈጠሩ የፕላን ጥሰቶች ላይ እርምጃ መውሰድ

በከተሞች በሚፈጠሩ የፕላን ጥሰቶች ላይ እርምጃ በመውሰድ 100% እንዲስተካከሉ ለማድረግ ታቅዶ በ8 ከተሞች 72 የፕላን ጥሰቶች ተፈፅመው 36ቱ የተስተካከሉ ሲሆን አፈፃፀሙም 50% ነው፡፡በክልሉ የሚገኙ 683 ከተሞች በተዘጋጀላቸው የማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና አካባቢያዊ ልማትና አገልግሎቶች ቅንጅትና ትግበራ ፕላን እንዲመሩ ለማድረግ ታቅዶ በፕላን የሚመሩ ከተሞች ቁጥር 676 ማድረስ የተቻለ ሲሆን የቀሩት 7 ከተሞች በቀጣይ ፕላን ተዘጋጅቶላቸው ወደ ፕላን ትግበራ እንዲገቡ ይደረጋል፡፡

### የከተማ መሬት ልማትና ማኔጅመንት

በክልሉ ውስጥ የሚገኙ እና የከተማነት እውቅና የተሰጣቸው ከተሞች በግልጽ የሚታወቅ የፕላን ወሰን እንዲኖራቸው በማድረግ የመሬት ሃብታቸውን በሚገባ ቆጥረውና መዝግበው ማስተዳደር እንዲችሉ ከፕላንና ልማት ቢሮ ጋር በመተባበር የ215 ከተሞችን (77 ከተማ አስተዳደሮችና 138 መሪ ማዘጋጃ ቤቶች) የፕላን ወሰን እንደገና እንዲካለል በማድረግ የተሟላ መረጃ ተደራጅቶ እንዲያዝ ለማድረግ ታቅዶ በ557 (ከ100% በላይ) ከተሞች ተግባራዊ ማድረግ ተችሏል፡፡በ311 ከተሞች (77 ከተማ አስተዳደሮች፣ 138 መሪ ማዘጋጃ ቤቶች እና 96 ንዑስ ማዘጋጃ ቤት ከተሞች) የተተከሉ የቅየሳ መቆጣጠሪያ ነጥቦችን በመለየት መረጃቸው ተደራጅቶ እንዲያዝና ደህንነታቸው እንዲጠበቅ ለማድረግ ታቅዶ በ242 (35.69%) ከተሞች በመሬት ላይ የሚገኙ የቅየሳ መቆጣጠሪያ ነጥቦች መረጃ ተደራጅቶ እንዲያዝና ተገቢው ጥበቃ

እንዲደረግላቸው ተደርጓል። እንዲሁም 600 የቅየሳ መቆጣጠሪያ ነጥቦችን ለመተካት እቅድ ተይዞ 1,273 የቅየሳ መቆጣጠሪያ ነጥቦችን ለመተካት የተቻለ ሲሆን አፈጻጸሙ ከ100% በላይ ነው።

## የመሬት ሀብት ቆጠራና ምዝገባ

የመሬት ሀብት ቆጠራና ምዝገባ ስራ ለመስራት በተደረገው ጥረት በ32 ከተሞች የመሬት ሀብት ቆጠራና ምዝገባ ሥርዓት በመዘርጋት በከተሞች ውስጥ የሚገኝ 250.000 ሄክታር ቁራሽ መሬት በመቁጠር ለመመዝገብ ታቅዶ በ70 ከተሞች 49,855.37 ሄክታር (19.94%) መሬት መቁጠርና መመዝገብ ተችሏል።

## ሰነድ አልባ ይዞታዎችን የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ መስጠት

የሰነድ አልባ ይዞታዎች የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ እንዲኖራቸው በተሰራው ስራ በ468 ንዑስ ማዘጋጃ ቤቶችና ታዳጊ ከተሞች 72,800 ከፊል ሰነድ አልባ ይዞታዎች የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ለመስጠት ታቅዶ 8,139 (11.18%) የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ መስጠት የተቻለ ሲሆን በክልሉ በነበረው ወቅታዊ የፀጥታ ችግር ምክንያት ያጋጠመው የከተማ መሬት ዝርፊያና ማጭበርበር ለማስቀም ሲባል ስራው ታግዶ እንዲቆይ በመደረጉ ምክንያት አፈፃፀሙ ዝቅተኛ ሁኗል።

## ህገ ወጥ ግንባታን ማስቀረት

ህገ ወጥ ግንባታን ለማስቀረት በተሰራው ስራ በ311 ከተሞች 75,211 ህገ-ወጥ ይዞታዎች መረጃቸውን አደራጅቶ በመያዝ እና በማፍረስ 86 ሄክታር ቦታ ወደ መሬት ባንክ እንዲገባ ለማድረግ ታቅዶ በ224 ከተሞች 34,363.8 (45.69%) ህገወጥ ይዞታዎች ተደራጅተው የተያዙ ሲሆን ከነዚህም ውስጥ 15,321 (20.37%) ህገ ወጥ ግንባታ እንዲፈርሱ በማድረግ 64.59 (75.10%) ሄክታር መሬት ወደ መሬት ባንክ እንዲገባ ተደርጓል።

## የመሬት ይዞታ ፋይል አደረጃጀት

በከተማ መሬት ልማትና ማኔጅመንት ሥራዎች ዙሪያ ለሚታየው የኪራይ ሰብሳቢነትና አገልግሎት አሰጣጥ ችግር አንዱ መንስኤ የመሬትና መሬት ነክ ፋይል መረጃ አደረጃጀትና አያያዝ ሥርዓት ችግር መሆኑ ይታወቃል።በመሆኑም በ77 ከተሞች 450,000 ፋይሎችን

በሃርድ ኮፒ እና በሶፍት ኮፒ ለማደራጀት ታቅዶ በ130 ከተሞች 361,647 (80.37%) ፋይሎችን በሃርድ ኮፒ አደራጅቶ መያዝ የተቻለ ሲሆን በ112 ከተሞች 375,647 (83.48%) ፋይሎችን በሶፍት ኮፒ አደራጅቶ መያዝ ተችሏል፡፡

## የመሬት ዝግጅት እና ማስተላለፍ

በ77 ከተሞች የመሬት ዝግጅት እና ማስተላለፍ አሰራራቸው በመሬት ባንክ የአሰራር ሥርዓት እንዲመራ በማድረግ 4,000 ሄክታር መሬት ወደ መሬት ባንክ እንዲገባ ለማድረግ ታቅዶ 1,731.434 ሄክታር (43.29%) መሬት ወደ መሬት ባንክ እንዲገባ ተደርጓል፡፡ከመሬት ዝግጅት አኳያ ለተለያዩ አገልግሎቶች የሚውል 500 ሄክታር መሬት ለጨረታ ለማዘጋጀት ታቅዶ 285.6515 ሄክታር (57.13%) መሬት ማዘጋጀት ተችሏል፡፡ 5,000 ሄክታር መሬት ለምደባ ለማዘጋጀት ታቅዶ 1,632.71 ሄክታር (32.65%) መሬት ማዘጋጀት ተችሏል፡፡ በጠቅላላው ለጨረታና ለምደባ 5,500 ሄክታር መሬት ለማዘጋጀት ታቅዶ 1,918.37 ሄክታር መሬት (34.88%) ማዘጋጀት ተችሏል፡፡ከተዘጋጀው መሬት መካከል ለተለያየ አገልግሎት የሚውል 200 ሄክታር ቦታ በጨረታ ለማስተላለፍ ታቅዶ 64.77 ሄክታር (32.39%) መሬት ለተጠቃሚዎች ተላልፏል፡፡ ከማህበራት ውጪ በምደባ 2,000 ሄክታር መሬት ለማስተላለፍ ታቅዶ 856.1013 ሄክታር (42.81%) መሬት ለተጠቃሚዎች ተላልፏል፡፡ ለ1,800 መኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበራት 1,800 ሄክታር ቦታ ለማስተላፍ ታቅዶ ለ1,253 የቤትስራ ማህበር ለተደራጁ ወንድ 15,659 ሴት 7,780 በድምሩ ለ23,439 ተጠቃሚዎች 1,051.633 ሄክታር (58.42%) መሬት ማስተላለፍ ተችሏል፡፡በጠቅላላው 4,000 ሄክታር መሬት ለተጠቃሚ ለማስተላለፍ ታቅዶ 1,907.7343 ሄክታር (47.69%) መሬት ለተጠቃሚ ማስተላለፍ ተችሏል፡፡ እንዲሁም በወልቃይት ጠገዴ ሰቲት ሁመራ ዞን ወደ ቀያቸው ለተመለሱ ተፈናቃዮች በቤትሙሉ ከተማ ለ960 አባውራና እማውራ ለእያንዳቸው 250 ካሬ ቦታ ርክክብ ተደርጓል፡፡

## የቀጠና ዋጋና የቦታ ደረጃ

በበጀት አመቱ 110 ከተሞች በፕላን ወሰን ክልል ውስጥ የሚገኝ ቦታቸውን የቦታ ደረጃ እና የቀጠና ዋጋ እንዲያሻሽሉ እና ሌሎች 110 ከተሞች የቀጠና ዋጋና የቦታ ደረጃ በአዲስ አዘጋጅተው ወደ ተግባር እንዲገቡ ለማድረግ ታቅዶ 90 (81.82%) ከተሞች የቀጠና ዋጋ እና የቦታ ደረጃቸውን ያሻሻሉ ሲሆን 44 (40%) ከተሞች የቀጠና ዋጋ እና የቦታ ደረጃ በአዲስ አዘጋጅተው አጸድቀው ወደ ተግባር እንዲገቡ ተደርጓል፡፡

### የልማት ክትትል

በ252 ከተሞች በጨረታና በምደባ ቦታ ለተለያዩ አገልግሎት ተወስደው በውላቸው መሰረት ጥቅም ላይ ያልዋሉ (ወደ ልማት ያልገቡ) ቦታዎችን ክትትል በማድረግ ወደ ልማት ያልገቡ 400 ቦታዎችን በመንጠቅ 25 ሄክታር መሬት ወደ መሬት ባንክ ለማስገባት ታቅዶ በ75 (29.76%) ከተሞች ክትትል በማድረግ ወደ ልማት መግባት ያልቻሉ 82 (20.50%) ቦታ የተነጠቁ ሲሆን 22.54 (90.16%) ሄክታር መሬት ወደ መሬት ባንክ ገቢ ተደርጓል፡፡ በ21 ከተሞች የሊዝ አፈፃፀም ኦዲት ለማድረግ ታቅዶ 4 (19.05%) ከተሞች ኦዲት የተደረጉ ሲሆን 60 ከተሞች ወደ ሊዝ ስርዓት እንዲገቡ ተደርጓል፡፡

### የሊዝ እና የቦታ ኪራይ ክፍያ አሰባሰብ

በ311 ከተሞች (77 ከተማ አስተዳደሮች፣138 መሪ ማዘጋጃ ቤቶች እና 96 ንዑስ ማዘጋጃ ቤት ከተሞች) በሊዝና በኪራይ ለተጠቃሚዎች የተላለፉ ይዞታዎች በውላቸው መሰረት ተገቢውን የሊዝና የቦታ ኪራይ ክፍያ በወቅቱ እንዲፈፅሙ በማድረግ ከሊዝ ይዞታዎች 1.5 ቢሊዮን ከኪራይ ይዞታዎች 0.2 ቢሊዮን በድምሩ 1.7 ቢሊዮን ብር ለመሰብሰብ ታቅዶ በ276 ከተሞች ከሊዝ ይዞታዎች 1.327 (88.47%) ቢሊዮን ብር የተሰበሰበ ሲሆን ከኪራይ ይዞታዎች 0.168 (84.00%) ቢሊዮን ብር በድምሩ 1.495 (87.94%) ቢሊዮን ብር መሰብሰብ ተችሏል፡፡

### የተጎሳቆሉ የከተማ አካባቢዎችን በመለየት መልሶ ማልማት

በ8ቱ ሪጅዮፖሊታን ከተሞችና በየዞን መቀመጫ ከተሞች የፀደቁና የተጎሳቆሉ የከተማ አካባቢዎችን በመለየት 5 ሄክታር መሬት በመልሶ ማልማትና 25 ሄክታር መሬት በከተማ ማደስ እንዲለማ ለማድረግ ታቅዶ ምስራቅ ጎጃም ዞን ደጀን ከተማ 0.4202 ሄክታር እና ደቡብ ወሎ ዞን ሀርቡ 0.07 ሄክታር፤ ኩታበር 0.08 ሄክታር፤ ሱሉላ 0.4 ሄክታር በድምሩ 0.53 ሄክታር መሬት በከተማ ማደስ እንዲሁም 0.9502 ሄክታር በመልሶ ማልማት በጠቅላለው 1.48 ሄክታር መሬት ማልማት ተችሏል፡፡

### የስመ-ንብረት ዝውውር

በበጀት አመቱ ለሚቀርቡ 30,000 የስመ-ንብረት ዝውውር አገልግሎት ፈላጊዎች በስታንዳርዱ መሰረት አገልግሎት እንዲያገኙ በማድረግ 5 ቢሊዮን ብር የአገልግሎት ገቢ ለመሰብሰብ ታቅዶ

በዞኖችና በከተሞች ለ22,008 ተገልጋዮች የስመ ንብረት ዝውውር አገልግሎት በመስጠት 944,991,129 ብር ገቢ መሰብሰብ ተችሏል፡፡

## ለልማት ተነሽዎች ካሳ መክፈል

በልማት ምክንያት ከይዞታቸው ለሚነሱ 5,100 ግለሰቦች ማህበራዊ እንቅስቃሴያቸውን በማያዛባ ሁኔታ 300 ሄክታር ትክ ቦታ እና 2.96 ቢሊዮን ብር ካሳ ለመስጠት ታቅዶ ለ3,048 (59.76%) የልማት ተነሽዎች 76.46 (25.49%) ሄክታር ትክ ቦታ የተሰጠ ሲሆን 2.017 ቢሊዮን ብር ካሳ መክፈል ተችሏል፡፡በአጠቃላይ በመሬት ዘርፍ ረቂቅ የህግ ማዕቀፎች የማዘጋጀት ሂደቱ እና የአሰራር ስርዓቱን ለማሻሻል ጥረት መደረጉ፣ ልዩ ፋይዳ ላላቸው አዳዲስ ፕሮጀክቶች በቦርድ ውሳኔ መሰጠቱ፣ ለአገልግሎት ዘርፍ የማስፋፊያ ቦታ ውሳኔ በመሰጠቱ፣ ከስመ ንብረት ዝውውር እና ከመሬት የሚሰበሰብ ገቢ እያደገ መምጣቱ በጥንካሬ የሚጠቀሱ ቢሆንም በክልላችን ከተሞች የተፈጠረው የፀጥታ ችግር በአገልግሎት አሰጣጡ፣ በህገ ወጥ መሬት ወረራ፣ በመሬት ሀብት ቆጠራ እና በልማት ክትትል ተግባራት አፈፃፀም ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ አሳድሯል፡፡

## የቤቶች ልማትና አስተዳደር ስራ

በከተሞች እድገትና በተለያዩ ገፊ ምክያቶች ከገጠር ወደ ከተሞች የሚደረግ ፍልሰትን ተከትሎ የመኖሪያ ቤት አቅርቦት ልዩ ትኩረት ማግኘት ያለበት ተግባር ነው፡፡ በበጀት ዓመቱ ይህን ችግር ለማቃለል በተለያዩ የመኖሪያ ቤት ልማት አማራጮች 42,154 መኖሪያ ቤቶች ተገንብተው አገልግሎት እንዲሰጡ ለማድረግ ታቅዶ በተለያዩ የቤት ልማት ስትራቴጂዎች 27,312 (64.79%) ቤቶች (በሪልስቴት 353 ቤቶች፣ በመኖሪያ ቤት ህብረት ሥራ ማኀበራት 11,904 ቤቶች፣ በግለሰቦች 13,783 ቤቶች፣ ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው ነዋሪዎች 1,272 ቤቶች) ተገንብተዋል፡፡

## የቤት ልማት ፕሮግራም

ከደረጃ በታች የሆኑ ቤቶች የማሻሻያ ልማት (ጥገና) ለማካሄድ የሚያስችል 10 ሚሊየን ብር በከተሞች እንዲበጀት በማድረግ 2,000 ቤቶች ደረጃቸው እንዲሻሻል ለማድረግ ታቅዶ 4,377,852 ብር በመበጀት ለ1,720 (86%) ቤቶች እድሳት እና ጥገና ማድረግ ተችሏል፡፡ በተለያዩ የቤት ልማት ፕሮግራሞች ተጠቃሚ ለመሆን የተመዘገቡ ቤት ፈላጊዎች 10 ቢሊዮን

ብር እንዲቆጥቡ ለማድረግ ታቅዶ በህብረት ስራ ማህበር የቤት ልማት ፕሮግራም ተጠቃሚ ለመሆን የተመዘገቡ ቤት ፈላጊዎች 1.255 ቢሊዮን ብር መቆጠብ ችሏል፡፡

## የዝቅተኛ ነዋሪዎች ቤት ግንባታ ማከናወን

የዝቅተኛ ነዋሪዎች ቤት ግንባታ ለማከናወን የሚያስችል 117,250,000 ብር ከዚህ ውስጥ 40% (46,900,000 ብር) በህብረተሰብ ተሳትፎ፣ 30% (35,175,000 ብር) ከተማው የሚመድበው በጀት እና 30% (35,175,000 ብር) መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችንና ባለሀብቶችን በማሳተፍ ለማሰባሰብ ታቅዶ ከህብረተሰብ ተሳትፎ 69,682,965 ብር፣ ከተሞች ከራሳቸው በጀት 26,512,567 ብር እንዲሁም መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችንና ባለሀብቶችን በማሳተፍ 12,285,000 ብር በድምሩ 108,480,532 ብር (92.52%) መሰብሰብ ተችሏል፡፡

## የአቅመ ደካማ ቤቶች ግንባታና ጥገና ስራ

በሀምሌና ነሀሴ ወር የ2015 ዓ.ም የክረምት ተግባራት ዕቅድ በማዘጋጀትና በጎ ፈቃደኞችን በማስተባበር 500 የአቅመ ደካሞች የመኖሪያ ቤቶችን ለመገንባትና ለመጠገን ታቅዶ ብቸና ከተማ ላይ በጉልበት 110,000 ብር፣ በቁሳቁስ 61,200 ብር፣ በእውቀት 5,000 ብር በድምሩ 176,750 ብር በመሰብሰብና 550 የሰው ኃይል በማሳተፍ 5 የአቅመ ደካማ ቤቶችን በአዲስ መገንባት ተችሏል፡፡እንዲሁም በጥሬ ገንዘብ 25,000 ብር፣ በጉልበት 968,900 ብር፣ በቁሳቁስ 26,900 ብር፣ በእውቀት 20,000 ብር በድምሩ 178,479 ብር በመሰብሰብና 9,689 የሰው ኃይል በማሳተፍ 217 (ሰሜን ሸዋ 35፣ ደቡብ ወሎ 41፣ ምስራቅ ጎጃም 86፣ ደቡብ ጎንደር 34፣ ማዕከላዊ ጎንደር 21) የአቅመ ደካማ ቤቶችን ጥገና ማድረግ ተችሏል፡፡

## የመንግስት ቤት አስተዳደር

የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ያልወጣላቸውን 18,740 የመንግስት ቤቶች በመለየት የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ እንዲኖራቸው ለማድረግ ታቅዶ 5,322 (28.4%) ቤቶች ካርታ ተሰርቶላቸዋል፡፡በመንግስት ባለቤትነት የሚከራዩ 36,000 ቤቶችን የኪራይ ዋጋ ለማሻሻል እንዲቻል ለ23,203 ቤቶች ፍረጃ ለማድረግ ታቅዶ የ3,443 (9.56%) ቤቶች የኪራይ ዋጋ ተሻሽለ ሲሆን የ3,418 (14.73%) ቤቶች ፍረጃ ማከናወን ተችሏል፡፡

### ያለአግባብ የተያዙ የመንግስት ቤቶችን ማስመለስ

ያለአግባብ የመንግስት ቤት የያዙ 500 ተጠቃሚዎች ላይ ርምጃ በመውሰድ በህጉ መሰረት ለሌሎች አዲስ ተከራዮች እንዲተላለፍ ለማድረግ ታቅዶ 374 (74.8%) ያለአግባብ የተያዙ ቤቶችን በማስለቀቅ ለተጠቃሚዎች ማስተላለፍ ተችሏል፡፡በመንግስት ቤቶች ላይ ህገወጥ ተግባር የሚፈጽሙ 700 ተከራዮችን በመለየት የማስተካከያ ርምጃ ለመውሰድ ታቀዶ ህገወጥ ተግባር የተፈፀመባቸውን ቤቶች በመለየት 253 (36.14%) ቤቶች ላይ እርምጃ መውሰድ ተችሏል፡፡እንዲሁም በመንግስት ባለቤትነት የሚከራዩ 49,164 ቤቶች የውል እድሳት ለማድረግ ታቅዶ 20,849 (42.41%) ቤቶች የውል እድሳት ማድረግ ተችሏል፡፡

### መኖሪያ ቤቶችን መረጃ በመረጃ ቋት (ሶፍትዌር) እንዲገቡ ማድረግ

የ18,740 መኖሪያ ቤቶችን መረጃ ለሶፍትዌሩ ግብዓት በሚሆን መንገድ ለማደራጀት እና 30,000 ቤቶችን ወደ ዘመናዊ የመረጃ ቋት (ሶፍትዌር) እንዲገቡ ለማድረግ ታቅዶ የ9,274 (49.49%) ቤቶችን መረጃ በማደራጀት ከነዚህም መካከል 7,810 (26.03%) ቤቶችን ወደ ዘመናዊ የመረጃ ቋት (ሶፍትዌር) ማስገባት ተችሏል፡፡ይሁን እንጅ ከክልሉ ወቅታዊ የፀጥታ ችግር ጋር በተያያዘ በከተሞች ኢንተርኔት በመቋረጡ ምክንያት የምዝገባ ስራው አፈፃፀም ዝቅተኛ ነው፡፡

### የከተሞች ተቋማዊና መሠረተ ልማት ማስፋፊያ ፕሮግራም

የከተማ መሰረተ- ልማት ስራዎች የከተሞች ተቋማዊና መሠረተ ልማት ማስፋፊያ ፕሮግራም (UIIDP) አፈፃፀምን በሚመለከት የ1ኛው ምዕራፍ የከተሞች ተቋማዊና መሠረተ ልማት ማስፋፊያ ፕሮግራም (UIIDP-I) በ2015 በጀት ዓመት የተጠናቀቀ ሲሆን 2ኛው ምዕራፍ የሰነድና የሌሎች ቅድመ ዝግጅት ስራዎች ባለመጠናቀቃቸው ምክንያት እንደ ሀገር በ2016 በጀት ዓመት አለመጀመሩ ይታወቃል፡፡ይሁን እንጅ በፕሮግራሙ መቋረጥ በከተሞች የነበረው ለውጥና መነቃቃት ወደ ኋላ እንዳይመለስ በክልሉ መንግስት ለ2016 በጀት ዓመት የሽግግር ወቅት ባለፈው ዓመት የአለም ባንክ የመደበውን በጀት 70% ያህሉን ለፕሮግራሙ ተጠቃሚ ከተሞች መመደብ ተችሏል፡፡በዚህ መሠረት የፕሮግራሙ ተጠቃሚ ከተሞች የተመደበላቸውን በጀት እና ከ2015 በጀት ዓመት የዞረ የፕሮግራሙን በጀት መነሻ በማድረግ የ2016- 2018 ዓ.ም ተንከባላይ የ3 ዓመት መዋለንዋይ እቅድ በማዘጋጀትና በማስጸደቅ እንዲፈጽሙ

ይጠበቃል፡፡ በዚህም መሠረት አብዛኛው ከተሞች ዘግይተውም ቢሆን እቅዳቸውን በክልል ደረጃ አጸድቀዋል፡፡

## የተንከባለሉ ፕሮጀክቶች አፈጻጸም

በ20 ከተሞች በፕሮጀክት ባህሪያቸውና በአፈጻጸም አቅም ማነስ ምክንያት ከ2015 ዓ.ም የተንከባለሉ 89 ፕሮጀክቶች (49 ፕሮጀክቶች ጎንደር ከተማ) የሚገኙ ሲሆን ከነዚህም ውስጥ 46 ኘሮጀክቶች የተጠናቀቁ 20 ፕሮጀክቶች በስራ ላይ ያሉ 4 ፕሮጀክቶች ወደ ሥራ ያልገቡ እና 20 ፕሮጀክቶች (ጎንደር 18፣ ቡሬ 1፣ ወረታ 1) ውላቸው የተቋረጠ ፕሮጀክቶች ናቸው፡፡

## በአዲስ የታቀዱ ፕሮጀክቶች

በአዲስ የታቀዱ ፕሮጀክቶችን በተመለከተ 435 ፕሮጀክቶች የአካባቢና ማህበራዊ ተጽእኖ ግምገማ ጥናትና ልየታ የተሰራላቸው ሲሆን ከነዚህም ውስጥ 396 (91%) ፕሮጀክቶች የአካባቢና ማህበራዊ ተጽእኖ የይሁንታ ፈቃድ አግኝተዋል፡፡ በ29 ከተሞች ከታቀዱ 441 አዲስ ፕሮጀክቶች ውስጥ 217 ፕሮጀክቶች (49%) የተጠናቀቁ ሲሆን 26 ፕሮጀክቶች (5.9%) አፈጻጸማቸው ከ80% በላይ ሆነዋል፡፡ 22 ፕሮጀክቶች (4.99%) አፈጻጸማቸው ከ50 - 80% ያሉ ናቸው፡፡ስድስት ፕሮጀክቶች አፈጻጸማቸው ከ50% በታች ሲሆኑ ቀሪዎቹ 210 ፕሮጀክቶች ምንም ስራ ያልጀመሩ ናቸው፡፡

## የጥገና ፕሮጀክቶች

የጥገና ፕሮጀክቶችን በተመለከተ በ28 ከተሞች 224 የጥገና ፕሮጀክቶች የታቀዱ ሲሆን 64 (28.57%) ፕሮጀክቶች የተጠናቀቁ ሲሆን 2 ፕሮጀክቶች (0.9%) አፈጻጸማቸው ከ80% በላይ ያሉ ናቸው፡፡ 4 ፕሮጀክቶች (1.8%) አፈጻጸማቸው ከ50 - 80% ያሉ ሲሆን 14 ፕሮጀክቶች (6.25%) አፈጻጸማቸው ከ50% በታች የሆኑ ናቸው፡፡ቀሪዎቹ 170 ፕሮጀክቶች (75.9%) ምንም ስራ ያልጀመሩ ናቸው፡፡

## የፕሮጀክት በጀት አጠቃቀም

የፕሮጀክት በጀት አጠቃቀምን በተመለከተ በፕሮግራሙ ከታቀፉት 32 ከተሞች መካከል 22 ከተሞች የዞረ የUIIDP በጀት ያላቸው ሲሆን 19 ከተሞች የዞረ በጀታቸውን ሙሉ በሙሉ ተጠቅመዋል፡፡አጠቃላይ የከተሞች ተቋማዊና መሰረተ-ልማት ፕሮግራም (UIIDP) በጀት

አጠቃቀም ሲታይ የዞረ ጠቅላላ ብር 310,729,445.92 ሲሆን ከዚህ ውስጥ ብር 223,466,866.12 (71.9%) ጥቅም ላይ ውሏል፡፡እንዲሁም በፕሮግራሙ ከታቀፉት 32 ከተሞች መካከል 26 ከተሞች ዕቅዳቸው በክልል የጸደቀና በጀታቸው የሚታወቅ ሲሆን በነዚህ 26 ከተሞች ብር 6,808,704,020.52 የከተሞች ተቋማዊና መሰረተ-ልማት ፕሮግራም ያልሆነ (Non-UIIDP) በጀት ታቅዶ በበጀት አመቱ መጨረሻ ብር 3,618,269,550.68 (53.14%) ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ በአጠቃላይ በ28 ከተሞች ብር 7,119,433,466.44 ተቋማዊና መሰረተ-ልማት ፕሮግራም ያልሆነ እና የሆነ (UIIDP+non-UIIDP) በበጀት ዓመቱ የታቀደ ሲሆን እስካሁን ብር 3,841,736,416.80 (53.96%) ጥቅም ላይ ውሏል፡፡

## የከተሞች ተቋማዊና መሰረተ ልማት ፕሮግራም

የከተሞች ተቋማዊና መሰረተ ልማት ፕሮግራም (UIIDP) ባልታቀፉ ከተሞች የመሰረተ ልማት ፕሮጀክት አፈፃፀም ሲታይ የከተሞች ተቋማዊና መሰረተ ልማት ፕሮግራም (UIIDP) ባልታቀፉ ከተሞች በ2015 በጀት ዓመት 850 ፕሮጀክቶች የነበሩ ሲሆን ከነዚህም ውስጥ 797 ፕሮጀክቶች የተጠናቀቁ ሲሆን ቀሪዎቹ 53 ፕሮጀክቶች ወደ 2016 በጀት ዓመት የዞሩ ናቸው፡፡ከነዚህ 53 የተንከባለሉ ፕሮጀክቶች ውስጥ 38 ፕሮጀክቶች የተጠናቀቁ ሲሆን 12 ፕሮጀክቶች ከ50% - 80% የአፈፃፀም ደረጃ ያላቸው ናቸው፡፡ ሶስት ፕሮጀክቶች ደግሞ የግንባታ ደረጃቸው ከ50% በታች ላይ ይገኛል፡፡ባለው ወቅታዊ ክልላዊ የፀጥታ ሁኔታ ምክንያት ምስራቅ ጎጃምና አዊ በከፊል እንዲሁም ምዕራብ ጎጃም ሙሉ ለሙሉ በ2016 የታቀዱ የመሰረተ ልማት ግንባታ ፕሮጀክቶችን ያላሳወቁ ቢሆንም የከተሞች ተቋማዊና መሰረተ ልማት ፕሮግራም (UIIDP) ባልታቀፉ ከተሞች በ2016 በጀት ዓመት 497 የግንባታ ፕሮጀክቶች የታቀዱ ሲሆን ከነዚህም መካከል 485 ፕሮጀክቶች የአካባቢና ማህበራዊ ተጽእኖ ግምገማ ጥናት ሰነድ ተዘጋጅቶላቸው 452 ፕሮጀክቶች የአካባቢና ማህበራዊ ተጽእኖ የይሁንታ ፈቃድ አግኝተው ወደ ግንባታ እንዲገቡ ተደርጓል፡፡ ከነዚህም ውስጥ 307 ፕሮጀክቶች የተጠናቀቁ ሲሆን 45 ፕሮጀክቶች አፈጻጸማቸው ከ50 - 80% ያሉ ናቸው፡፡ እንዲሁም 45 ፕሮጀክቶች አፈጻጸማቸው ከ50% በታች ያሉ ሲሆን 55 ፕሮጀክቶች ደግሞ በጨረታ ሂደት ላይ ያሉ ናቸው፡፡ ቀሪዎቹ 45 ፕሮጀክቶች ምንም ስራ ያልጀመሩ ናቸው፡፡በዚህ በጀት ዓመት ለ138 መሪ ማዘጋጃ ከተሞች ለመሰረተ ልማት ማስፋፊያና የስራ ዕድል ፈጠራ በክልሉ መንግስት ለእያንዳንዳቸው የ1 ሚሊዮን ብር በጀት የተመደበላቸው ሲሆን ቅድመ ሁኔታውን

አሟልተው ለተገኙ 66 መሪ ማዘጋጃ ከተሞች የክልሉ ድጎማ በጀት እንዲለቀቅላቸው ተደርጓል፡፡

## የከተሞች ጽዳት፣ አረንጓዴ ልማትና ውበት ሥራ

የከተሞች ጽዳት፣ አረንጓዴ ልማትና ውበት ሥራዎች ሲታይ በ300 ከተሞች የሚገኙ 8,000 ተቋማትና ግለሰቦች ከ20 - 50 ሜትር ርቀት ግቢያቸውንና አካባቢያቸውን (የውሃ ማፋሰሻ ቦዮችን) እንዲያፀዱ ለማድረግ ታቅዶ በ310 (103.33%) ከተሞችና ክፍለ ከተሞች የሚገኙ 22,656 (ከ100% በላይ) ተቋማት እና በ347 ከተሞች የሚገኙ ነዋሪዎች የፅዳት ቀን ወስነው ግቢያቸውንና አካባቢያቸውን ማጽዳት ችለዋል፡፡



የከተማ ውበትና አረንጓዴ ልማት

## የደረቅ ቆሻሻ አወጋገድ

በ138 ከተሞች በደረቅ ቆሻሻ ማስወገድ የተደራጁ 302 ነባር ማህበራትን በማጠናከር በከተሞች ከሚያመነጩት ቆሻሻ 1,100,000 ሜትር ኩብ ቆሻሻ በተገቢው ቦታ ለማስወገድ ታቅዶ በ101 ከተሞች  የሚገኙ 224 ነባር ማህበራትን በማጠናከር 1,097,460.60 (99.77%) ሜትር ኩብ ቆሻሻ በተገቢው ቦታ እንዲወገድ ተደርጓል፡፡ እንዲሁም በ68 ከተሞች 132 አዲስ ማህበራትን ለማደራጀት ታቅዶ በ19 ከተሞች 37 ማህበራትን በማደራጀት ለ722 ወንድ እና ለ722 ሴት በድምሩ ለ1,444 ዜጎች ቋሚ የስራ እድል መፍጠር ተችሏል፡፡በ16 ከተሞች እንደ የከተሞች የእድገት ደረጃ የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ በመስፈርቱ መሰረት ከ3ኛ ወገን ነጻ እንዲሆን

ለማድረግ ግብ ተይዞ በ16 ከተሞች በስታንዳርዱ መሰረት የቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ ከ3ኛ ወገን ነፃ ለማድረግ ታቅዶ በ4 ከተማ ተከናውኗል። በ12 ከተሞች የደረቅ ቆሻሻ ጊዜዊ ማቆያ ወይም የቅብብሎሽ ጣቢያ ለማዘጋጀት ታቅዶ በ10 ከተሞች ማከናወን ተችሏል። እንዲሁም በ200 ከተሞች ቁጥጥር የሚደረግበት ጊዜያዊ የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ እንዲያዘጋጁ እቅድ ተይዞ በ120 ከተሞች ማዘጋጀት ተችሏል።



የደረቅ ቆሻሻ አሰባሰብና አወጋገድ

## የአረንጓዴ አሻራ ችግኝ ተከላ

የክረምት ጊዜን በዘፈቀደ ላለማሳለፍ ከሐምሌ 1/2015 ጀምሮ የአረንጓዴ አሻራ ችግኝ ተከላ እቅድ እና ቼክሊስት በማዘጋጀት በእቅዱ እና በቼክሊስቱ ላይ ከፈጻሚ አካላት ጋር የጋራ መግባባት ፈጥሮ ወደ ስራ ለመግባት ጥረት የተደረገ ሲሆን በዚህም በ683 ከተሞች 880,000 የህብረተሰብ ክፍል በማሳተፍ በፓርኮች፣ በመንገድ አካፋዮችና በወንዞች ዳርቻ 22 ሚሊዮን ችግኞችን በመትከል 1,510 ሄክታር አዲስ አረንጓዴ ቦታዎችን ለማልማት ታቅዶ በ383 (56.08%) ከተሞች ወንድ 489,525 ሴት 432,204 በድምሩ 921,729 (104.74%) የህብረተሰብ ክፍሎችን በችግኝ ተከላ እና እንክብካቤ ዙሪያ ግንዛቤ በመፍጠርና በቀጥታ

በማሳተፍ 19,568,605 (88.95%) ችግኞችን መትከል ተችሏል፡፡ በዚህ ችግኝ ተከላ መርሃ ግብርም 1,850.98 ሄክታር (122.58%) አረንጓዴ ቦታ ማልማት ተችሏል፡፡



አረንጓዴ ልማት (ችግኝ ተከላ)

## የመዝናኛ ፓርኮችን ማልማት

በ32 ከተማ አስተዳደሮች 32 አዲስ አገልግሎት የሚሰጡ የመዝናኛ ፓርኮች በስታንዳርድ ዲዛይን እንዲለሙ እና ለ200 ነባር የመዝናኛ ፓርኮች እንክብካቤ ለማድረግ ታቅዶ በ12 ከተሞች 12 (46.15%) አዲስ የመዝናኛ ፓርኮች የለሙ ሲሆን በ71 ከተሞች ለሚገኙ 186 (93%) ነባር የመዝናኛ ፓርኮች እንክብካቤ ተደርጓል፡፡ እንዲሁም ለ6,446 ሄክታር ነባር አረንጓዴ ቦታዎች እንክብካቤ ለማድረግ ታቅዶ 3,549.92 ሄክታር (55.07%) አረንጓዴ ቦታዎች እንክብካቤ ማድረግ ተችሏል፡፡

## በከተሞች ችግኝ ጣቢያ ማቋቋም

በ41 ከተሞች (የራሳቸው ችግኝ ጣቢያ የሌላቸው ከተሞችን በመለየት) 41 አዲስ ችግኝ ጣቢያዎች እንዲለሙ እና ለ184 ነባር ችግኝ ጣቢያዎች እንክብካቤ ለማድረግ ታቅዶ 12

(29.27%) አዲስ ችግኝ ጣቢያ የተቋቋመ ሲሆን ለ115 (62.5%) ነባር ችግኝ ጣቢያዎች እንክብካቤ ተደርጓል፡፡ በ215 ከተሞች (77 ከተማ አስተዳደሮችና እና 138 መሪ ማዘጋጃቤቶች) በኘላን የተመላከቱ 1500 አረንጓዴ ቦታዎችን በመለየት የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ እንዲሰራላቸው ለማድረግ ታቅዶ በ110 ከተሞች የሚገኙ 1,445 (96.3%) አረንጓዴ ቦታዎች የተለዩ ሲሆን ከነዚህም ውስጥ ለ1,027 (71.07%) አረንጓዴ ቦታዎች የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ተሰርቶላቸዋል፡፡

## የከተማ ሴፍቲ ኔትና ምግብ ዋስትና ፕሮግራም

በክልላችን የከተማ ሴፍቲ ኔትና ምግብ ዋስትና በፕሮግራም በታቀፉ 18 ከተሞች ለምግብ ዋስትና ተጋላጭ የሆኑ 96,680 ዜጎችን በአካባቢ ልማት ስራዎች ላይ በማሳተፍ የምግብ ዋስትናቸውን ለማረጋገጥ ታቅዶ በመጀመሪያው ዙር 14,333 ወንድ እና 20,652 ሴት በድምሩ 34,985 ዜጎች፣ በሁለተኛና ሦስተኛ ዙር 22,556 ወንድ እና 31,594 ሴት በድምሩ 54,150 ዜጎች፣ በተጨማሪ የገንዘብ ድጋፍ 2,675 ወንድ እና 4,870 ሴት በድምሩ 7,545 ዜጎች በአጠቃላይ 96,680 ዜጎችን (ወንድ 39,564 ሴት 57,116) በፕሮግራሙ ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል።በ18 ከተሞች ለሚገኙ 94,508 (61,430 ሴቶች) መስራት ለሚችሉ ዜጎች በአካባቢ ልማት ስራዎች ላይ ተሳታፊ በማድረግ 617,806,800 ብር ለማስተላለፍ ታቅዶ ዳባትን ጨምሮ በ18ቱ ከተሞች ወንድ 8,407 ሴት 21,656 በድምሩ 30,063 ሰሪ ኃይሎችን የከተሞችን ገጽታ ሊቀይሩ በሚችሉ በ5ቱ የማህበረሰብ አቀፍ ሥራዎች በማሳተፍ ወንድ 39,108 ሴት 56,814 በድምሩ 95,922 (ከ100% በላይ) የቤተሰብ አባላትን ተጠቃሚ ማድረግ የተቻለ ሲሆን በዚህም ብር 603,762,576 (97.73%) ለማስተላለፍ ተችሏል፡፡ በመሆኑም የሴቶች ተሳትፎና በተጠቃሚ 92.49% ማድረስ ተችሏል፡፡



የከተማ ሴፍቲኔትና ምግብ ዋስትና ዙሪያ ውይይት ሲደረግ- ደብረማርቆስ

## የዘላቂ ኑሮ ማሻሻያ ሥራ

ከድህነት ወለል በታች የሚኖሩና በአካባቢ ልማት ስራዎች ላይ ተሳታፊ የሆኑ 29,219 የቤተሰብ ሃላፊዎች በዘላቂ ኑሮ ማሻሻያ ፕሮግራም እንዲታቀፉ በማድረግ በዘላቂነት ኑሯቸውን እንዲያሻሽሉ ለማድረግ ታቅዶ ለ7,130 የአካባቢ ልማት ተጠቃሚ ቤተሰቦች የማሕበራዊ አገልግሎት ተጠቃሚነት ትስስር ለመፍጠር ታቅዶ 9,105 ተጠቃሚዎች የጤና መድን ሽፋን፣ 1,270 ተጠቃሚዎች የትምህርት ቤት ምገባ፣ 4,137 ተጠቃሚዎች የትምህርት ቤት ቁሳቁስ

(ደብተር እስክርቢቶ ዩኒፎርም)፣1,186 ተጠቃሚዎች የጎልማሶች ትምህርት፣ 742 ተጠቃሚዎች በቴክኒክና ሙያ ትምህርት ቤት፤ኮሌጅ፤ የሙያ ትምህርት፣ 1,150 ተጠቃሚዎች የቀበሌ ቤት እንዲያገኙ ድጋፍ የተደረገላቸው ሲሆን 403 ተጠቃሚዎች የመኖሪያ ቤት ዕድሳት የተደረገላቸው ሲሆን 54 ተጠቃሚዎች ነጻ የትራንስፖርት አገልግሎት አግኝተዋል፡፡በበጀት አመቱ 25,102 የኑሮ ማሻሻያ ድጋፍ ተጠቃሚዎች በከተማ ግብርና እና ከግብርና ውጪ ባሉ ተጨማሪ የገቢ ማስገኛ ስራዎች ላይ እንዲሰማሩ በማድረግ 99,285,076 ብር ገቢ እንዲያገኙ እና ከሚያገኙት ገቢ 56,799,000 ብር እንዲቆጥቡ ለማድረግ ታቅዶ ወንድ 2,941 ሴት 18,671 በድምሩ 24,935 (99.3% በላይ) የኑሮ ማሻሻያ ድጋፍ ተጠቃሚዎች (74.87% ሴቶች) በከተማ ግብርና እና ከግብርና ውጪ ባሉ ተጨማሪ የገቢ ማስገኛ ስራዎች ላይ እንዲሰማሩ በማድረግ 143,117,646 ብር ገቢ የተገኘ ሲሆን ከተገኘው ገቢ ውስጥም 46,867,948 ብር ተቆጥቧል፡፡

የገንዘብ ድጋፍ ለማግኘት የሚያስችሉ የቅደም ተከተል የኑሮ ማሻሻያ ድጋፎችን ላጠናቀቁ 10,864 የመጀመሪያው ዙር ልማታዊ ሴፍቲኔት ተጠቃሚዎች ብር 360,667,439 የገንዘብ ድጋፍ እንዲያገኙ ለማድረግ ታቅዶ ወንድ 2,941 ሴት 7,827 ድምር 10,768 (99.17%) ተጠቃሚዎች (72.76% ሴቶች) 359,622,893.70 ብር ግራንት ፈንድ የተላለፈላቸው ሲሆን በግል ስራ እንዲጀምሩ ተደርጓል፡፡

### የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ሬጉላቶሪና አቅም ግንባታ ተግባር

የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ብቃት ማረጋገጫና ምዝገባ ስርዓቱን በማጠናከር በክልሉ ለሚንቀሳቀሱ የዘርፉ ተዋናዮች በግብዓት፣ በአደረጃጀት እና በክህሎት ብቃት በማረጋገጥ ምዝገባ ለማድረግ ታቅዶ የክልሉን ተቋራጮችና አማካሪዎች ቁጥር ከማሳደግ እና ተወዳዳሪ ስራ ተቋራጮችን እና አማካሪዎችን ከመፍጠር አንፃር 4,186 ሥራ ተቋራጮችን (አዲስ 2,000፣ እድሳት 2,013፣ እድገት 173) ብቃት በማረጋገጥ ለመመዝገብ ታቅዶ ለ3,642 (87%) ሥራ ተቋራጮች (አዲስ 1635፣ እድሳት 1849፣ እድገት 158) ምዝገባ ተደርጓል፡፡ ለ426 አማካሪዎች (አዲስ 100፣ እድሳት 300፣ እድገት 26) ብቃት በማረጋገጥ ምዝገባ ለማድረግ ታቅዶ 310 (72.77%) አማካሪዎች (አዲስ 95፣ እድሳት 200፣ እድገት 15) ምዝገባ ተደርጓል፡፡ለ3,500 ኮንስትራክሽን ባለሙያዎች የሙያ ፍቃድ ምዝገባ ለማድረግ ታቅዶ ለ3,602 (102.91%) ባለሙያዎች ምዝገባ ተደርጓል፡፡ በክልሉ የሚገነቡ 325 የመንግስት ግንባታ ፕሮጀክቶች ምዝገባ ተደርጓል፡፡

### ግንባታዎች በህንፃ አዋጁ ኮድና ስታንዳርዶች መሰረት እንዲከናወኑ ማድረግ

በክልሉ የሚከናወኑ ሁሉም ግንባታዎች ከቅድመ ግንባታ እስከ ድህረ ግንባታ ድረስ በህንፃ አዋጁ ኮድና ስታንዳርዶች መሰረት እንዲገነቡ ለማድረግ የታቀደ ሲሆን የህንጻ አዋጅ አደረጃጀት የተፈጠረባቸው 206 ከተሞች፣ ክፍለ ከተሞች እና መሪ ማዘጋጃ ቤቶች ለ55,000 ፕሮጀክቶች የፕላን ስምምነት፣ ለ55,000 ፕሮጀክቶች የግንባታ ፈቃድ በመስጠት፣ ለ41,580 ፕሮጀክቶች በግንባታ ወቅት ቁጥጥር ለማድረግ ታቅዶ ለ43,461 (79.02%) የፕላን ስምምነት እና ለ42,093 (76.53%) ፕሮጀክቶች የግንባታ ፈቃድ የተሰጠ ሲሆን ለ31,972 (76.89%) ግንባታዎች ቁጥጥር ማድረግ ተችሏል። በእነዚህ ከተሞች ተገንብተው ለተጠናቀቁ 225 ግንባታዎች የመጠቀሚያ ፈቃድ ለመስጠት ታቅዶ ለ70 (31.11%) ግንባታዎች የመጠቀሚያ ፈቃድ መስጠት ተችሏል።

## ህዳሴ ግድብ

ኢትዮጵያውያን እየገነቡት ያለው ታላቁ የኢትዮጵያ የህዳሴ ግድብ ነገን የሚያሳይ እና ዘመን ተሻጋሪ አገራዊ ፕሮጀክት ነው።የታላቁ ሕዳሴ ግድብ ፕሮጀክት ግንባታ ለአገራችን ዜጎች ብሔራዊ መግባባት በማምጣት የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነትንና የትብብር መድረክ የፈጠረ በመሆኑ ግድቡ መሠረት ከተጣለበት ጊዜ ጀምሮ የተወሰኑ መሰናክሎች ቢኖሩም በህዝቡ ልብ ውስጥ በመሆን እየተገነባ አሁን ለፍሬ በቅቷል።



የኢትዮጵያ ታላቁ የህዳሴ ግድብ ከፊል ገፅታ

## ማህበራዊ ሚዲያን በመጠቀም መረጃ ማስተላለፍ

የግድቡን የሥራ ደረጃና ወቅታዊ ሁኔታዎች ላይ ያተኮሩ መረጃዎችን ከተለያዩ የሀገር ውስጥ ሚዲያዎች በሕትመትና በኤሌክትሮኒክስ የተላለፉትን ዘገባዎች በጽ/ቤቱ የፌስ ቡክ አድራሻ በመልቀቅ ለሕዝብ መረጃ የማቅረብና የፌስ ቡክ ተከታዮችን ቁጥር የማሳደግ ሥራ ተሠርቷል፡፡በዚህ መሠረት በተለያዩ ሚዲያዎች በተለይም ከፋና፣ ከዋልታ፣ ከኢቲቪ፣ አሚኮ እና ከሌሎች ሚዲያዎች የተገኙ እንዲሁም በጽ/ቤቱ የተዘጋጁ 127 የጽሑፍና የምስል ዜናዎች፣ 26 የተንቀሳቃሽ ምስል (ቪዲዮ) 15 የጽሑፍ ብቻ፣112 በምስል መረጃዎች እንዲሁም 46 አጫጭር መልዕክቶች በማዘጋጀት በጽ/ቤቱ ፌስ ቡክ መልቀቅ ተችሏል፡፡ እንዲሁም ከፌደራል ህዳሴ ግድብ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት ፌስ ቡክ ገጽ ላይ የተገኙ ዜናዎችን በጽ/ቤቱ ፌስ ቡክ ገጽ አማካይነት ለተጠቃሚ ማድረስ ተችሏል፡፡

## መደበኛ ሚዲያን በመጠቀም መረጃ ማስተላለፍ

የአማራ ሚዲያ ኮርፖሬሽንን በመጠቀም በሁሉም ሚዲየሞች እና በክልሉ በሚገኙ FM ጣቢያዎች በወቅታዊ የህዳሴ ግድብ ዙሪያ ስለአለው እንቅስቃሴ የተለያዩ አካላትን በማነጋገር የተለያዩ ዘገባዎችን ዘግቦ ከማስተላለፉ በላይ ለቀጣይ በምን መልኩ ድጋፍ መቀጠል እንዳለበት አስተያየቶቻቸውን በመሰብሰብ ሰፊ የሚዲያ ሽፋን እንዲያገኝ ተደርጓል፡፡ከዚህ በተጨማሪም ፋና ጎንደር፣ የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት፣ዲደብሊው አማረኛ ፕሮግራም የታላቁ ህዳሴ ግድብ 13ኛ ዓመት ክብረ በዓልን አስመልክተው በክልላችን በህዳሴ ግድብ ዙሪያ የተሰሩ መረጃዎችን በመዘገብ መረጃው ለህዝብ ተደራሽ ሆኗል፡፡

## የሚዲያና የሕዝብ ንቅናቄ

የክልላችን ሕዝብ ለታላቁ የህዳሴ ግድብ ግንባታ እያደረገ ያለውን የጉልበት ድጋፍ፣ የገንዘብና የዕውቀት ድጋፍ መረጃ በመስጠት የሕዝብ ንቅናቄ እና ተሳትፎ ሥራ ተሰርቷል፡፡ይህንንም በአማራ ሚዲያ ኮርፖሬሽን፣በኢቲቪ፣ በፋና ብሮድ ካስት፣ በዋልታ ሽፋን ያገኘ ሲሆን በተለይም በክልላችን በተካሄደው የአረንጓዴ አሻራ ዘመቻ ላይ በችግኝ ተከላ ወቅት፣ ይህንን ተግባር ከታላቁ ህዳሴ ግድብ ጋር በማያያዝ ግንዛቤ በመስጠት የሕዝብ ንቅናቄ መፍጠር ችሏል፡፡

## የተፋሰስ ልማት ሥራ

የህዳሴ ግድቡን መሠረት ባደረገ መልኩ የተፈጥሮ ሀብት ልማት ጥበቃ ሥራዎችና በሥነ-ሕይወታዊ ዘዴ የተፋሰስ ልማት ስራ ተሰርቷል፡፡ በዚህም መሠረት የታላቁ ህዳሴ ግድብ ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶ እስከ አሁን ድረስ በተፋሰስ ልማት ሥራዎቻችን በተከታታይ ለ13 ዓመታት በአጠቃላይ የጉልበት አስተዋፅኦው በገንዘብ ሲተመን በድምሩ ብር 35,796,382,422.00 መሰብሰብ ተችሏል፡፡

## የታላቁ ህዳሴ ግድብ ግንባታ 13ኛ ዓመት በዓል አከባበር

የታላቁ ህዳሴ ግድብ የመሠረት ድንጋይ የተቀመጠበትን 13ኛ ዓመት በዓል አከባበር በተመለከተ በመነሻነት ከፌደራል የታላቁ ህዳሴ ግድብ ግንባታ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት በመጣው የመነሻ ዕቅድ መሰረት ዕቅድ በማዘጋጀት ለሁሉም መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት ለዞን እና ከተማ አስተዳደሮች እንዲሁም ለክልሉ የህዝብ ግንኙነት ኃላፊዎች በድምሩ ለ112 ተቋማት በደብዳቤ ማሳወቅ ተችሏል፡፡ በዚህ መሰረት የተለያዩ የክልል ተቋማት የተወያዩ ሲሆን ገንዘብ ቢሮ ጽ/ቤታችንን በጠየቀው መሰረት የጽ/ቤታን የህዝብ ግንኙነት ማወያያ ሰነድ አዘጋጅቶ አቅርቧል፡፡ እንዲሁም የአብክመ የመንግስት ኮሙኒኬሽን ቢሮ ኃላፊዎች፣ ዳይሬክቶሬቶች፣የዞንና የከተማ ኮሙኒኬሽን መምሪያ ኃላፊዎችና የአሚኮ ከፍተኛ አመራሮች በተገኙበት መጋቢት 6 ቀን 2016 ዓ.ም በባህር ዳር ከተማ ስለ 13ኛው የታላቁ ህዳሴ ግድብ ግንባታ ዓመት በዓል አከባበር የአንድ ቀን ውይይት ተካሂዷል፡፡

## መረጃዎችን ወደ ሕዝብ ማድረስ

በልዩ ልዩ የሚዲያ ተቋማት ወቅታዊ የህዳሴ ግድብ ግንባታ ዋና ዋና ጉዳዮች ላይ በተለይም 95 በመቶ በላይ የሚሆነው የግድቡ ሥራ ተጠናቅቆ የውሃ ሙሌት እና የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጨት በጀመረበት ወቅት ላይ በመሆናችን የመረጃ ፈላጊዎች ቁጥር ጨምሯል፡፡ በዚህም መሰረት ጽ/ቤቱ ለአገር ውስጥ ሚዲያዎች የክልሉ ህዝብ ለታላቁ ህዳሴ ግድብ ያበረከተውን አስተዋፆኦ በተመለከተ መረጃ ሰጥቷል፡፡በህብረት ችለናል በሚል መሪ ቃል በራሪ ወረቀት ተዘጋጅቶ በክልሉ ለሚገኙ ሁሉም ተቋማትና ድርጅቶች ተሰራጭቷል፡፡ ልዩ ልዩ ባነሮች ተዘጋጅተው በተለያዩ ቦታዎች ላይ እንዲለጠፉ ተደርጓል፡፡እንዲሁም የክልሉ ኮሙኒኬሽን ቢሮ በዓሉን አስመልክቶ የፎቶ አውደርእይ አዘጋጅቶ መረጃዎችን ተደራሽ አድርጓል፡፡

## የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ ሥራ

በበጀት ዓመቱ እስከ አሁን ድረስ የህዳሴ ግድቡን ዓላማ መሠረት ባደረገ መልኩ በተለያዩ ቦታዎች በችግኝ ተከላ የተሸፈነ መሬት 381,360 ሔክታር ሲሆን በዚህ መሬት ላይ 1.522 ቢሊዮን ችግኝ ተተክሏል፡፡በዚህም መሰረት በተፈጥሮ ሃብት ልማት ስራ የተሳተፉ አርሶ አደሮች ብዛት በድግግሞሽ  54,639,347 ሰዎች ናቸው፡፡የህዝቡ ተሳትፎ የጉልበት አስተዋጽኦ በገንዘብ ሲተመን ብር 1,994,516,328.00 ነው፡፡

## ለህዳሴ ግድቡ የተሰበሰበ ገንዘብ

የህዳሴ ግድቡ ግንባታ በቦንድ ግዥ እና በልገሳ የገንዘብ አስተዋፅኦው በየኅብረተሰብ ክፍሉ ሲተነተን እንደሚከተለው ድርሻ አለው፡-

ከመንግሥት ሠራተኞች = ------------------------------------------- ብር 512,064,351.05

ከባለሀብቱና ከንግዱ ህብረተሰብ = ---------------------------------- ብር 101,473,801.19

ከአርሶ አደሩ = -------------------------------------------------------- ብር 236,649,255.08

ከድርጅቶችና ተቋማት እንዲሁም ከልዩ ልዩ የህብረተሰብክፍሎች --- ብር 362,234,606.15

በልገሳ ከተለያዩ የኅብረተስብ ክፍሎች     ------------------------------ ብር 9,290,065.69

ድምር ------------------------------  ብር 1,221,712,079.16 ተሰብስቧል፡፡

ከልዩልዩ የገቢ ማስገኛ ፕሮጀክቶችና ፕሮግራሞችብር 31,388,850.00 ሲሆን ጠቅላላ ድምር ብር 1,253,100,929.16 መሰብሰብ ተችሏል፡፡

በአጠቃላይ የህዳሴ ግድቡ ከተጀመረበት ጊዜ አንሥቶ እስከ አሁን ድረስ ከቦንድ ግዥ፣ ከልገሳ፣ ከልዩ ልዩ ፕሮጀክቶችና ፕሮግራሞች፣ከተፋሰስ ልማት ሥራዎች በድምሩ ብር 37,049,483,351.16 ተሰብስቧል፡፡



ለታላቁ ህዳሴ ግድብ ማስገንቢያ ገንዘብ የለገሱ

### የችግኝ ተከላን በተመለከተ

የህዳሴ ግድቡ በደለል እንዳይሞላ በክልላችን በተለያየ ቦታ ላይ ከፍተኛ የሆነ የችግኝ ተከላ ፕሮግራም ተካሂዷል፡፡ በዚህም መሠረት ሐምሌ 10 ቀን 2015 ዓ.ም በነበረ የችግኝ ተከላ ፕሮግራም ላይ ኅብረተሰቡ መሳተፍ ችሏል፡፡ በመሆኑም ህብረተሰቡ በተደጋጋሚ በተለያየ ጊዜና ቦታ በነቂስ ወጥቶ ለአረንጓዴው ልማት እርብርብ ማድረግ በመቻሉ በየደረጃው ከፍተኛ የሆነ ውጤት መገኘቱ ተዘግቧል፡፡

## ኅብረት ስራ ማህበራት ማስፋፊያ

### መሰረታዊ ኅብረት ሥራ ማኅበራትን ማቋቋም

በበጀት ዓመቱ 2,600 መሰረታዊ ኅብረት ሥራ ማኅበራትን ለማቋቋም ታቅዶ 2,478 መሰረታዊ ኅብረት ሥራ ማኅበራት የተቋቋሙ ሲሆን አፈፃፀሙ ከ95% ሆኗል፡፡ የተቁቋሙት ኅብረት ስራ ማህበራትም 426 የተፋሰስ ተጠቃሚዎች ኅብረት ስራ ማኅበራት፣ 39 የገንዘብ ቁጠባ እና ብድር ኅብረት ስራ ማኅበራት፣ 1,951 የመኖሪያ ቤት እና አካባቢ ልማት ኅብረት ስራ ማኅበራት እንዲሁም 24 የሸማቾች ኅብረት ስራ ማኅበራት ሲሆኑ ከተቋቋሙት ሸማች መሠረታዊ ኅብረት ስራ ማኅበራት መካከል 5 በክልል የመንግስት ተቋማት ፣13 በዞን ፣ በከተማ እና በወረዳ አስተዳደር ደረጃ በሚገኙ የመንግስት ሰራተኞች እና ቀሪዎቹ በ6 በከተማ ነዋሪዎች የተደራጁ ሲሆን እየተከሰተ ያለውን የኑሮ ውድነት በተደራጀ አግባብ ለመፍታት ጥረት ተደርጓል፡፡ በሌላ መልኩ በእነዚህ አዲስ በተቋቋሙ መሰረታዊ ኅብረት ስራ ማህበራት 140,451 (ሴት 43,297) አባላትን በማሳተፍ፣ ብር 856,407,495 መነሻ ካፒታል በማሰባሰብ እንዲሁም በገንዘብ ቁጠባ እና ብድር ኅብረት ስራ ማህበራት ብር 9,339,630 መደበኛ ቁጠባ በማሰባሰብ ማቋቋም ተችሏል፡፡



የፋና ሁለገብ የገበሬዎች ህብረት ስራ ማህበር ጠቅላላ ጉባኤ- ደበብ ወሎ (ተሁለዴሬ)

## ዩኒየን ማደራጀት

የኅብረት ሥራ ማኅበራትን ዩኒየን ከማደራጀት አኳያ በምስራቅ ጎጃም ዞን እና በደቡብ ወሎ ዞን ሁለት የዘር ብዜትና ግብይት ዩኒየኖችን ማደራጀት የተቻለ ሲሆን 26 መስራች አባላትን እና ብር 3,140,000 መነሻ ካፒታል ይዞ የተቋቋመ ሲሆን ከመመዝገቢያ ብር 260,000 እና ከወረት ዕጣ 2,880,000 ብር በመያዝ ማደራጀት ተችሏል፡፡



የፀሀይ ሁለገብ የገበሬዎች ህብረት ሥራ ማህበራት ዩኒየን ጠቅላላጉባ-ማዕከላዊ ጎንደር

## አዲስ አባላትን ማፍራት

በነባር መሰረታዊ ኀብረት ሥራ ማህበራት 192,985 (ሴት 55,963) አባላትን ለማስገባት ዕቅድ ተይዞ 147,805 (ሴት 52,778) አባላት የተለያዩ መሠረታዊ ኀብረት ሥራ ማህበራት አባል ማድረግ ተችሏል፡፡አፈፃፀሙ ከ100% በላይ ሆኗል፡፡ አዲስ ከገቡ አባላት መካከል የሴቶች ድርሻ 35.7% ነው፡፡በተመሳሳይ 225 መሰረታዊ የኅብረት ሥራ ማኅበራትን የዩኒየን አባል ለማድረግ ታቅዶ 369 መሰረታዊ ህብረት ሥራ ማህበራትን አባል በማድረግ የተከናወነ ሲሆን አፈፃፀሙ ከ100% በላይ ሆኗል፡፡

## የውስጥ የካፒታል አቅም ማሣደግ

የኅብረት ሥራ ማኅበራት የሚያጋጥማቸውን የገንዘብ እጥረት ለመፍታት የካፒታል ምንጭ ከውስጥና ከውጭ ከሚገኝ ፋይናንስ መጠቀም ይገባቸዋል፡፡በመሆኑም ከውስጥ ከሚገኝ የካፒታል ምንጭ ኅብረት ሥራ ማኅበራት በራሳቸው ጥረትና በአደራጅ ተቋሙ ድጋፍ አዲስ አባላት ወደ ማኅበራቸው እንዲቀላቀሉ በማድረግና ለነባር አባላት ተጨማሪ ዕጣዎችን በመሸጥ የሚገኝ ካፒታል ሲሆን ሌላኛው ደግሞ ኅብረት ሥራ ማኅበራቱ ከሚያካሂዱት የምርትና አገልግሎት ግብይትና የንግድ እንቅስቃሴ ከሚገኝ ትርፍ ነው፡፡በበጀት ዓመቱ በነባር ኅብረት ስራ ማኅበራት ካፒታላቸውን በብር 816,808,908 ለማሳደግ እቅድ ተይዞ በብር 761,732,144 ማሳደግ የተቻለ ሲሆን አፈፃፀሙም ከ100% በላይ ማከናወን ተችሏል፡፡

## የገንዘብ ቁጠባ አገልግሎትን ማሳደግ

በበጀት ዓመቱ ብር 1,576,972,191 በነባር የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ስራ ማኅበራት መደበኛ ቁጠባ ለማሰባሰብ ታቅዶ፤ ብር 1,502,971,280 መደበኛ ቁጠባ በማሰባሰበ ማከናወን የተቻለ ሲሆን የእቅዱን ከ100% በላይ መፈፀም ተችሏል፡፡

## የብድር ስርጭት አግልግሎትን ማሳደግ

በ2016 ዓ.ም ብር 5,126,055,269 በነባር የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ስራ ማኅበራት ለአባሎቻቸው ብድር ለማሰራጨት አቅደው ብር 6,088,503,896 ብድር በማሰራጨት ከ100% በላይ ማከናወን የተቻለ ሲሆን በዚህም 85,408 (ሴት 29,903) ተጠቃሚ ሆነዋል፡፡

## የአነስተኛ መድን አገልግሎት መስጠት

በአነስተኛ መድን ብር 2,101,751,753 ብድር አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ ብር 1,368,836,293 የተሰጠ ሲሆን አፈፃፀሙ 65% ማድረስ የተቻለ ሲሆን በዚህም ወንድ 67,069፣ ሴት 15,916 በድምሩ 82,985 አባላት ተጠቃሚ ሆነዋል፡፡ በበጀት ዓመቱ ብር 36,395,133 አርቦን ለመሰብሰብ ታቅዶ ብር 21,056,925 በመሰብሰብ 58% መፈጸም የተቻለ ሲሆን በዓመቱ ጉዳት የደረሰባቸው ግለሰቦች 191 /ሴት 60/ ሲሆን ለዚህ የተከፈለ ጠቅላላ ካሳ ብር 5,392,4758 /ለሴቶች ብር 1,446,901 ነው፡፡

## የእንስሳት መኖ ማምረት

በበጀት ዓመቱ 71,400 ኩንታል የእንስሳት መኖ በ7 የመኖ ማቀነባበሪያ ፋብሪካ ዩኒየኖች ለማምረት ታቅዶ 17,032 ኩንታል የእንስሳት መኖ ማምረት የተቻለ ሲሆን አፈፃፀሙ 23.8% የእቅዱን መፈፀም ሲሆን በዚህም ከተመረተው 14,639 ኩንታል የተለያዩ አማራጮችን በመጠቀም መሸጥ ተችሏል፡፡



የእንስሳት መኖ ማምረቻ-

## ምግብ ዘይት ማምረት

በ2016 ዓ.ም 300,000 ሊትር የምግብ ዘይት በ3 የምግብ ዘይት አምራች ኀብረት ስራ ማህበራት ለማምረት ታቅዶ 100,260 ሊትር የምግብ ዘይት በማምረት ገበያ በማረጋጋት በኩል ወሳኝ ሚናቸውን እየተወጡ ሲሆን አፈፃፀሙ 33.4% ማድረስ የተቻለ ሲሆን 93,316 ሊትር የምግብ ዘይት በመሸጥ ህብረተሰቡ ተጠቃሚ እንዲሆን ተደርጓል፡፡

## የፒፒ ቦርሳ እና ምንጣፍ ማምረት

በበጀት ዓመቱ 2,031,855 ከረጢቶችን በአድማስ ዩኒየን ለማምረት ታቅዶ 550,000 የከረጢት ምርቶችን በማምረት ለተጠቃሚ ማቅረብ የተቻለ ሲሆን አፈፃፀሙ 27% ሆኗል፡፡ ከከረጢት ሽያጭ ገቢ ለመሰብሰብ በተሰራው ስራ የተለያዩ የሽያጭ አማራጮች በመጠቀም 457,500 ከረጢቶች መሸጥ ተችሏል፡፡



## የፒፒ ባግና ምንጣፍ ማምረት አድማስ ዩኒዬን-

## የማዳበሪያ ግዥና ስርጭትንን በተመለከተ

| ተ.ቁ | ማዳበሪያ አይነት | የተገዛ | ከማዕከላዊ መጋዘን ወደ ዩኒየንየገባ | ወደመሰረታዊ ማህበር የተጓጓዘ | ለአርሶአደር የተሰራጨ | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | ለመኸር | ለመስኖ | ድምር |
| 1 | ዩሪያ | 3,754,980 | 2,235,557 | 2,032,419 | 1,879,400 | 94,215 | 1,973,615 |
| 2 | ኤን ፒ ኤስ | 72,080 | 147,660 | 138,068 | 79,072 | 436 | 79,508 |
| 3 | ኤን ፒ ኤስ + ቢ | 4,230,840 | 2,898,281 | 2,612,204 | 2,314,178 | 68,282.50 | 2,382,460 |
| ድምር | | 8,057,900 | 5,281,498 | 4,782,691 | 4,272,650 | 162,933.50 | 4,435,583 |

## የኦዲት አገልግሎት መስጠት

በበጀት ዓመቱ ለ3,313 መሠረታዊ የኅብረት ሥራ ማህበራት የኦዲት አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ 2,357 በማከናወን አፈፃፀሙ 71% ሆኗል፡፡ የኦዲት አገልግሎት ካገኙት ኅብረት ስራ ማህበር መካከል 2,275 በመሠረታዊ ኅብረት ስራ ማህበር ሲሆን ከእነዚህም መካከል 1,197 ያህሉ ብር 310,764,266 እና 35 ኅብረት ስራ ማህበራት እና ዩኒየን 656,037,067 ብር ትርፍ ማግኘት የቻሉ ሲሆን በተቃራኒው በመሠረታዊ ኅብረት ስራ ማህበራት እና በዩኒየኖች ብር 12,545,982 ኪሳራ ታይቶባቸዋል፡፡ ከኪሳራ ለማውጣት በተሰራው ስራ በድርድር ብር 19,107,667እና በፍርድ ቤት ውሳኔ ብር 10,709,930 በድምሩ ብር 29,817,597 ማስመለስ ተችሏል፡፡

## የኢንስፔክሽን አገልግሎት መስጠት

በበጀት ዓመቱ መሠረታዊ ኅብረት ስራ ማኅበራትን አቅም ከመገንባት በተጨማሪ ለ1,700 መሠረታዊ ኅብረት ስራ ማኅበራት የኢንስፔክሽን አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ ለ2,640 የኢንስፔክሽን አገልግሎት የተሰጠ ሲሆን ከ100% በላይ መፈፀም ተችሏል፡፡

## የሕግ አገልግሎት

የኅብረት ሥራ ማኅበራትን ወክሎ በአደራጅ መስሪያ ቤቱ የህግ ባለሙያ እና በአቃቢ ህግ መስሪያ ቤት አቃብያነ ህግ ክስ የመመስረት ስራ የተከናወነ ሲሆን ለ252 ኅብረት ሥራ ማኅበራት በ287 ጉዳዮች ብር 40,461,966 ክስ የተመሰረተ ሲሆን በ167 ጉዳዮች ብር 11,226,297 ለኅብረት ሥራ ማኅበራት ተወሰኗል፡፡

## ለህብረት ስራ ማህበራት የተደረገ ድጋፍ

በዘርፉ ለተደራጁ 70 የኅብረት ሥራ ማኅበራት ለእያንዳንዳቸው 1.5 ሚሊየን ብር የሚያወጡ የቁሳቁስ ድጋፍ የተደረገላቸው ሲሆን ከተደረገላቸው ድጋፎች መካከል 104 የወተት መሰብሰቢያ አልሙኒየም ካን፣ 27 ክሬም መለያ፣ 26 ወተት መናጫ ቸርነር ፣ 28 ዲፕ ፍሪጂ ፣ 6 ጀኔነተር ፣ 19 ባለሶስት እግር ተሽከሪካሪዎች እና መሰል ለስራው አስፈላጊ የሆኑ ማቴሪያሎች ተገዝተው ስራ ላይ እንዲውሉ የተደረገ ሲሆን በተመሳሳይ የመሰረተ ልማት የግብዓትና የአቅም ግንባታ ስራዎች በፕሮጀክቱ ተከናውነዋል፡፡

## አቅም ግንባታ

ከግብርና ትራንስፎርሜሽን ኢንስቲቲዩት ጋር በመተባበር ለ166 /ሴት 39 / ሠልጣኞች በገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት ምዘና፣ በመልካም አስተዳደር፣ በአደጋ ስጋት አመራር እና ትርፍ ክፍፍል ለዞንና ከተማ አስተዳደር ኃላፊዎች ፣ ለባለሙያዎች ፣ ለዩኒዩን ስራ አመራር ቦርድ እና ቅጥር ሰራተኞች የአቅም ግንባታ ስልጠና መስጠት ተችሏል፡፡



የአቅም ግንባታ ስልጠና

# ንግድና ገበያ ልማት

## በቴክኖሎጅ የተደገፈ አገልግሎት መስጠት

የንግድ፣ሆቴልና ሬስቶራንት ንዑስ ዘርፍ ከአገልግሎት ሴክተር ከፍተኛውን ድርሻ የሚይዝ ንዑስ ዘርፍ ሲሆን በአማካይ 33.8% የሚሆነውን የአገልግሎት ዘርፍ እሴት በመጨመር እንዲሁም በአማካይ ከ10.3% በላይ የሚሆነውን የክልሉን ኢኮኖሚ በየዓመቱ ይሸፍናል፡፡ስለሆነም በተሰራው ስራ በቴክኖሎጅ የተደገፈ አገልግሎት በማሳደግ የንግድ ምዝገባ፣ፈቃድ መስጠትና እድሳት አገልግሎቶችን 100% በኦንላይን በማካሄድ የንግድ ፈቃድ ቁጥሩን ወደ 544,903 ለማሳደግ በ97,295 የንግድ ምዝገባ አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ 25,473 (26%) የተከናወነ ቢሆንም ክንውኑ በማነስ ያሳያል፡፡

## የንግድ ፈቃድ አገልግሎት መስጠት

በበጀት ዓመቱ 116,535 የንግድ ፈቃድ አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ ለ40,622 (34%) መፈጸም ተችሏል፡፡ በሌላ መልኩ ደግሞ ለ428,763 የንግድ ፈቃድ እድሳት አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ 218,774 (51%) የንግድ ስራ ፈቃድ ማደስ ቢቻልም አፈጻጸሙ በማነስ ያሳያል፡፡ በአጠቃላይ በበጀት አመቱ የንግድና ምዝገባ አገልግሎት በኦንላይን መስጠት የተቻለ ሲሆን የ2016 በጀት ዓመት የንግድ ፈቃድ እድሳት ሰኔ 30 የሚጠናቀቅ ቢሆንም የኢፌዲሪ ንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር ክልሉ ያጋጠመውን ችግር ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት የንግድ ፈቃድ ያላደሱ ነጋዴዎች ተግባራቸውን እያከናወኑ ጎን ለጎን እስከ 2017 ዓ.ም ድረስ ማደስ

እንደሚችሉ አቅጣጫ የተቀመጠ በመሆኑ ተቋሙ ይህንን ተግባር በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ማጠናቀቅ ይኖርበታል።

## የንግድ ድርጅቶች የበር ከበር ክትትልና ቁጥጥር

በውጭ ኢንስፔክሽን 1,340,221 ንግድ ድርጅቶች የበር ከበር ክትትልና ቁጥጥር ለማድረግ ታቅዶ 797,422(59%) ማከናወን ቢቻልም አፈፃፀሙ ዝቅተኛ የሆነበት ምክንያት ክልላችን ባጋጠመው የፀጥታ ችግር በአንዳንድ የክልላችን አካባቢዎች በተለያየ ጊዜ የንግድ ድርጅቶች በመዘጋታቸው እና በተፈለገው መጠን ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ ባለመቻሉ ነው።በሌላ በኩል በተደረገው ክትትልና ቁጥጥር ስራ ከተገኘው 64,656 ህገ ወጥ ተግባራት ውስጥ ከተወሰደው አስተዳደራዊ እርምጃ ውስጥ 45,579 የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ፣15,054 እሽጋ፣3,662 እገዳ፣6 ስረዛ እንዲሁም በተወሰደው ህጋዊ እርምጃ በፍርድ ቤት ክስ የተመሰረተባቸው 72 በድምሩ 64,373 (99.6%) ሲሆን በአጠቃላይ በተወሰደው እርምጃ የተገኘ ውጤት 58,679 (91%) ነው።ከዚህም አኳያ የመጠቀሚያ ጊዜ (የአገልግሎት ጊዜ) ያለፈባቸውን የኢንዱስትሪ ምርቶች በመገኘታቸው ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት በጠጣር 12,554 ኪሎ ግራም እና በፈሳሽ 96,089 ሊትር የማሰባሰብና የማስወገድ ርምጃ የተወሰደ ሲሆን በገንዘብ ሲተመንም 3,088,573 ብር ነው።

ሌላዉ ጉዳይ ህጋዊ ስርዓቱ እንዲያድግ የንግድ ድርጅቶችን የበር ከበር ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ በመጋዘኖች ያለአግባብ የተከዘነ ምርት 47,498 ኩንታል ሰብልና 9,322 ኩንታል የኢንዱስትሪ ምርት እና 61,000 ሊትር ዘይት ሊያዝ ተችሏል፣በብር ሲገመት ጠቅላላ ቅጣት ብር 57,241,359 ከዚህ ውስጥ በሞዴል 85 ወይም በአደራ የተቀመጠ ብር 12,943,035 እንዲሁም ገቢ የተደረገ ብር 44,298,324 ነው።

## የአስተያየት መስጫ መዝገብ በንግድ ድርጅት ማስቀመጥ

በበጀት አመቱ 335,056 የአስተያየት መስጫ መዝገብ በንግድ ድርጅት ለማስቀመጥ ታቅዶ 194,285 (58%) ማከናወን የተቻለ ሲሆን የክልሉን ህጋዊ የንግድ ሽፋን ለመለየት ነጋዴዎችን በደረጃ ለመፈርጅ በበጀት ዓመቱ 1,340,221 ታቅዶ 728,197 (58%) የተከናወነ ሲሆን በዚህም፡- A= 394,901 B= 218,664 C= 114,632 በደረጃ መፈረጅ ተችሏል። በአመቱ ህጋዊ የንግድ ሽፋኑን 54.2% ማድረስ ተችሏል።

## የመለኪያ መሳሪያዎችን ቬሪፋይ (ምርመራ) ማድረግ

ተጠቃሚነትን ከማሳደግ አንጻር ሸማቹ የህብረተሰብ ክፍል ከሚጐዳበት ተግባር አንዱ የሆነው ባልተስተካከለና ሆን ተብሎ በሚጭበረበር የመለኪያ መሳሪያዎች የሚሰጠው አገልግሎት በመሆኑ ይህንን ተግባር ለመቀነስ የሚያስችል የቬሪፊኬሽን ስራ የተሰራ ሲሆን 545,372 የመለኪያ መሳሪያዎችን ቬሪፋይ (ምርመራ) ለማድረግ ታቅዶ 315,917 (58%) ለሚሆኑ የመለኪያ መሳሪያዎች ምርመራ ተደርጓል፡፡

## የንግድ ድርጅቶች ህጋዊ ደረሰኝ እንዲያሳትሙ ማድረግ

የሸማቹን ማህበረሰብ መብት ለማስከበር የንግድ ድርጅቶች ህጋዊ ደረሰኝ እንዲያሳትሙና ለተጠቃሚው እንዲሰጡ ማድረግ ሲሆን አዲስና ነባር ደረሰኝ ማሳተምና ለተጠቃሚዎች እንዲሰጡ መከታተል 137,882 ታቅዶ 62,258 (45%) የተከናወነ ሲሆን በዝርዝር ሲታይ አዲስ 30,012 ታቅዶ 10,177 (34%) እንዲሁም ነባር 107,870 ታቅዶ 52,081 (48%) የንግድ ድርጅቶች ደረሰኝ በማሳተምና ለተጠቃሚዎች እንዲሰጡ ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ ተችሏል፡፡

## የገበያ ትስስር መፍጠር

ከሰብል ገበያ ትስስር ጋር በተገናኘ በሀገር ውስጥ ገበያ የሰብል ምርት ትስስር ለመፍጠር በድህረ እና በቅድመ የሰብል ምርት ትስስር በዓመቱ 4,349,303 ኩንታል ለማስተሳሰር ታቅዶ 3,162,932 (73%) ማስተሳሰር ተችሏል፡፡ከባለፈው ተመሳሳይ ወቅት 4,417,055 ጋር ሲነጻጸር 1,254,123 ኩንታል በማነስ ያሳያል፡፡የኢንዱስትሪ ምርት ትስስርን ስንመለከት ዘይት 5,000,000 ሊትር ታቅዶ 5,582,950 (ከ100%በላይ)፣ፓስታና መኮሮኒ 50,000 ኩንታል ታቅዶ 35,526 (71%)፣የስንዴ ዱቄት 20,000 ኩንታል ታቅዶ 85,384 (ከ100%በላይ) እንዲሁም ፈሳሽ ሳሙና 50,000 ሊትር ታቅዶ 81,284 ሊትር (>100% ) ማስተሳሰር ተችሏል፡፡ በተጨማሪም የሸማቾች ህብረት ስራ ማህበራትና ዩኔኖች ከራሳቸው አቅም 420 ሚሊዮን በተጨማሪ ያለባቸውን የካፒታል ችግር ለመፍታት ከ18 ዞኖች፣ ከተሞችና ወረዳዎች የተዘዋዋሪ ብድር ብር 689,001,899 ሚሊዮን በድምሩ 1.1 ቢሊየን ብር ተዘዋዋሪ ብድር በመመደብ በድግግሞሽ ለምርት ግዥ ጥቅም ላይ ለማዋል ታስቦ 556,894 (93%) ኩንታል የግብርና ምርት እንዲሁም የኢንዱስትሪ ምርት በፈሳሽ 5.58 ሚሊዮን ሊትር ፣ በጠጣር 157,000 ኩንታል፣ 81,284 ሊትር ሳሙና፣ 345.17 ሚሊየን ሊትር ነዳጅ ፣ 21.3 ሚሊየን

እንቁላል፣ 2.5 ሚሊየን ዶሮ እና 119 ሚሊዮን ሊትር ወተት ለመንግስት ሰራተኞችና ለከተማ ነዋሪዎች በተመጣጣኝ ዋጋ በማቅረብ የኑሮ ውድነቱን ለማረጋጋት ጥረት ተደርጓል።



የእንስሳት ተዋፅኦ ምርቶችን በትስስር ሲቀርብ ደቡብ ወሎ ዞን ኮምቦልቻ ከተማ

## የተለያዩ ምርቶችን ወደ ውጭ ሀገር ወይም ወደ ሀገር ውስጥ መላክ

ወደ ውጭ የሚላኩ አስገዳጅ ምርቶች የጥራጥሬና የቅባት እህሎችን (ሰሊጥ፣ ቦሎቄ፣ ማሾ፣ አኩሪ አተር እና ቡና) ከፍ በማድረግ የውጭ ምንዛሬ ለማግኘት በመጀመሪያ ደረጃ የገበያ ማዕከል ግዥ ተፈጽሞ ወደ ኢትዮጵያ ምርት ገበያ እና ማዘጋጃ መጋዘን 5,864,841 ኩንታል በመሸኛ ለመላክ ታቅዶ 3,941,544 ኩንታል (67%) ምርት ማቅረብ የተቻለ ሲሆን ከባለፈው ተመሳሳይ ወቅት 3,765,193 ጋር ሲነጻጸር 176,351 (4.6%) በመብለጥ ያሳያል። አስገዳጅ የግብርና ምርቶች ሰሊጥ 2,000,000 ኩንታል ለመላክ ታቅዶ 1,666,227 ኩንታል (83%) ምርት የተላከ ሲሆን ከጥራጥሬ ሰብሎች ነጭ ቦሎቄ 541,216 ኩንታል ታቅዶ 164,587 (30%)፣ቀይ ቦሎቄ 186,136 ኩንታል ታቅዶ 48,134 (26%)፣ቡላ ቦሎቄ 105,750 ኩንታል ታቅዶ 158,636 (>00%)፣ ጥቁር ቦሎቄ 3,450 ኩንታል ታቅዶ 817 ኩንታል (24%)፣ ማሾ 519,395 ኩንታል ታቅዶ 599,364(>100%) እንዲሁም አኩሪ አተር 2,500,000 ኩንታል ታቅዶ 1,303,779 (52%) በመሸኛ መላክ ተችሏል። ጠቅላላ ከተላከው የአስገዳጅ የሰብል ምርት በዓመቱ 515 ሚሊዮን ዶላር ይገኛል ተብሎ ታቅዶ ከሰሊጥ 290.45 ሚሊዮን ዶላር፣ ከጥራጥሬ ሰብሎች 187 ሚሊዮን ዶላር በድምሩ 478 (92.8%) ሚሊዮን ዶላር የውጭ ምንዛሬ ማግኘት ተችሏል።በሌላ በኩል ለሀገር ውስጥ የዘይት ፋብሪካዎች በመሸኛ የተላከ አኩሪ አተር 445,104 ኩንታል ነው። በውል እርሻ ለውጭ ገበያ ወደ መዳረሻ የተሸኘ አስገዳጅ ጥራጥሬ ምርቶች 1,293,827 ኩንታል ሲሆን በዝርዝር ሲታይ ነጭ ቦሎቄ 37,529፣ ቀይ ቦለቄ

40,182፣ ቡላ ቦለቄ 157,417፣ ጥቁር ቦለቄ 635፣ ማሾ 348,113 እና አኩሪ አተር 709,951 ነው፡፡ በኢንቨስትመንት እርሻ ለውጭ ገበያ ወደ መዳረሻ የተሸኘ አስገዳጅ ጥራጥሬ ምርቶች 70,885 ኩንታል ሲሆን በዝርዝር ሲታይ ማሾ 11,437 እና አኩሪ አተር 59,448 ነው፡፡

## የኢንዱስትሪ ምርቶችን ወደ ውጭ ገበያ መላክ

የኢንዱስትሪ ምርቶችን ወደ ዉጪ ገበያ በመላክ የውጭ ምንዛሬ ግኝትን ለማሳደግ አግሮፕሮሰሲንግ (ፕሮቲን ፓውደር፣ ሽቶ፣ ጣሂናን) በዓመቱ 25,38 ቶን ለውጭ ገበያ ለማቅረብ ታቅዶ 25,384 (>100%) ቶን ማቅረብ ተችሏል፡፡ በተጨማሪም የኬሚካል ውጤቶች (ጠርሙስ) በዓመቱ በቁጥር 7,000,000 ለውጭ ገበያ ለማቅረብ ታቅዶ 4,200,000 (60%) ፣ ጨርቃጨርቅና አልባሳት በዓመቱ 5,000,000 ለውጭ ገበያ ለማቅረብ ታቅዶ 3,718,828 (74%) ፣ ቆዳና የቆዳ ውጤቶች በዓመቱ 550,000 ስኩየር ፊት ለውጭ ገበያ ለማቅረብ ታቅዶ 256,622 (47%) እንዲሁም የእንጨት ውጤቶችን በዓመቱ በቁጥር 1,000 ለውጭ ገበያ ለማቅረብ ታቅዶ 6,000 (ከ100% በላይ) ማቅረብ ተችሏል፡፡የኢንዱስትሪ ምርቶችን ወደ ውጭ በመላክ በበጀት ዓመቱ 38 ሚሊዮን ዶላር ለማግኘት ታቅዶ 31,956,824 ሚሊዮን ዶላር (84%) ማግኘት ተችሏል፡፡

## የእንሰሳት እና እንስሳት ተዋፅኦ ምርት ትስስር

የእንሰሳት እና እንስሳት ተዋፅኦ ምርት ትስስር ለማድረግ በተሰራው ስራ 1,639,586 የቁም እንስሳት ወደ ቀጣዩ መዳረሻቸው በመሸኛ እንዲጓጓዙ ለማድረግ ታቅዶ 896,391 (55%) የተከናወነ ሲሆን ከባለፈው ተመሳሳይ ወቅት 1,400,041 ጋር ሲነጻጸር 503,650 (35.97%) በማነስ ያሳያል፡፡ በሌላ በኩል የቆዳና ሌጦ ምርት ከፋብሪካዎች ጋር ለማስተሳሰር በዓመቱ 4,147,501 ታቅዶ 2,839,913 (68.5%) ማስተሳሰር ተችሏል፡፡በተጨማሪም የዓሳ ምርት 2,963 ቶን ለማስተሳሰር ታቅዶ 1,926.00 (65%) ቶን ማስተሳሰር ተችሏል፡፡ከባለፈው ተመሳሳይ ወቅት 3,546,523 ጋር ሲነጻጸር ቆዳና ሌጦ 706,610 (19.24%) እንዲሁም አሳ በ542 (21.9%) ቶን በማነስ ያሳያል፡፡ የወተት ምርት ግብይት በዓመቱ 181,499,000 ሊትር ታቅዶ 130,380,000 ሊትር (72%)፣ የስጋ ግብይትን 586 ቶን ሥጋ ለማስተሳሰር ታቅዶ 771(132%) ለማስተሳሰር ተችሏል፡፡በሌላ በኩል በሃገር ውስጥ ገበያ የእንሰሳት እና እንሰሳት ተዋጽኦ ትስስር ለመፍጠር የማር ምርት 18,590 ክንውን 12,944 (70%) ፣ የእንቁላል ምርት ታቅዶ 29,710,245 ክንውን 26,058,452 (88%)፣የዶሮ ምርት ትስስርን 3,006,048

ታቅዶ ክንውን 2,657,859 (88%) ፣ የተቀነባበረ የእንስሳት መኖ 1,624 ቶን ታቅዶ ክንውን 1,527 ቶን (94.03%) ማስተሳሰር ተችሏል፡፡

## የቁም እንሰሳትና አሳ ኤክስፖርት ማድረግ

ከቁም እንሰሳት ኤክስፖርት አንፃር ዳልጋ ከብት በቁጥር 1,215 ኤክስፖርት ለማድረግ ታቅዶ 93 (7.6%) የተላከና ከዚህም የሚጠበቅ የውጭ ምንዛሬ 729,304 ዶላር ለማግኘት ታቅዶ 55,800 ዶላር (7.6%) እንዲሁም በግና ፍየል በቁጥር 22,528 ለመላክ ታቅዶ 25,990 (115%) የተላከና ከዚህም 1,576,960 ዶላር ለማግኘት ታቅዶ 1,819,300 (115%) ዶላር ማግኘት ተችሏል፡፡ዓሳ ምርትን ኤክስፖርት ለማድረግ 25 ቶን ታቅዶ 31.36 ቶን (125%) በመፈፀም ተችሏል፡፡ከዚህ ውስጥ ከደረቅ ዓሣ የተገኘ የውጭ ምንዛሬ በዶላር 8,412 ዶላር ለማግኘት ታቅዶ 6,272 (75%) ዶላር ማግኘት ተችሏል፡፡በአጠቃላይ ከቁም እንስሳትና ዓሳ ኤክስፖርት የሚጠበቅ የውጭ ምንዛሬ 2,314,676 በዶላር ታቅዶ 1,881,372 (81%) ዶላር በማግኘት ተችሏል፡፡



ኤክስፖርት የተደረጉ በጎች ኦሮሞ ብሄረሰብ ዞን ባቲ ከተማ

## የገበያ ማዕከላትን ማቋቋም

የገበያ ማዕከል ማለት በጥቃቅን እና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝና በሌሎች አምራችና አገልግሎት ሰጭዎች ምርቶቻቸውንና አገልግሎታቸው በብዛት ለሸያጭ የሚያቀርቡበት የመገበያ ህንፃ ሲሆን በበጀት አመቱ የገበያ ማዕከላትን ከ1,456 ወደ 1,610 በማሳደግ የተረጋጋ የመገበያያ ቦታ መፍጠርና ግብይቱን ለማሳለጥ አዲስ የገበያ ማዕከላት ማቋቋም 245 ታቅዶ 60 (25%) የተለያዩ የገበያ ማዕከላትን በማቋቋም የግብይት ስርዓቱን በማሳለጥ የግብይት ተዋናኞችን

ተጠቃሚ ለማድረግ ጥረት ተደርጓል፡፡ ነባር ገበያዎችን በማጠናከር የግብይት ማዕከላትን ለግብይት ተዋናኞች ምቹ በማድረግ የግብይት ስርዓቱን ለማሳለጥ 1,350 ታቅዶ 938 (69%) የገበያ ማዕከላትን የማሻሻል ስራ ተሠርቷል፡፡



የደብረማርቆስ ሁለተኛ ደረጃ የቁም እንስሳት ገበያ ማዕከል

# ውሃ እና ኢነርጂ

## ንፁህ መጠጥ ውሀ አቅርቦት

ልዩ ልዩ 1,200 አነስተኛ ውሃ ተቋማት ለመገንባት ታቅዶ 485 ውሃ ተቋማት በመገንባት የዕቅዱን (53%) ማከናወን ተችሏል፡፡የክልሉን የንጹህ መጠጥ ውሃ ሽፋን የ2% የሽፋን እድገት በመጨመር ከ73.64% ወደ 75.64% ለማድረስ ታቅዶ 1.9% በማሳደግ 75.54% ማድረስ ተችሏል፡፡ በተጨማሪም 462,016 ህዝብ ንፁህ መጠጥ ውሀ ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ 430,972 (93.28%) ህዝብ ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡በተጨማሪም የገጠር ንጹህ መጠጥ ውሃ አቅርቦት ሽፋን የ2% እድገት በመጨመር 73.85 ወደ 75.85% ለማሳደግ ታቅዶ 1.2% በማከናወን ሽፋኑን (75.05%) ማድረስ የተቻለ ሲሆን 259,801 ህዝብ ማስጠቀም ተችሏል፡፡በተመሳሳይ በከተማ በ2015 ዓ.ም መጨረሻ ከተደረሰበት 72.17% የንጹህ መጠጥ ውሃ ሽፋን በመነሳት የ2% ሽፋን እድገት በመጨመር የከተማን ንጹህ መጠጥ ውሃ ሽፋን ወደ 74.17 % ለማሳደግ ታቅዶ 3.1% የሽፋን እድገት በመጨመር 75..27% ማድረስ የተቻለ ሲሆን 171,171 (የዕቅዱ ከ100% በላይ) ህዝብ ተጠቃሚ እንዲሆን አስችሏል፡፡





*መጠጥ ውሃ ፕሮጀክት-ባህርዳር ዙሪያ (አቡነ ሀራ)*

## የውሀ ተቋማት ጥገና

በበጀት አመቱ 10,000 ቀላል፣ መካከለኛና ከባድ የተለያዩ የውሀ ተቋማት ጥገና ለማከናወን ታቅዶ 14,542 የተለያዩ ተቋማት የተጠገኑ ሲሆን ቀላል ጥገና 7,329 (135.7%)፣መካከለኛ 5,012 (156.6%) እንዲሁም ከባድ ጥገና 2,201 (157.2%) ተከናውኗል፡፡በከተማ ያለውን የውሀ ብክነት አሁን ካለበት 22.05% ወደ 21.53% በመቀነስ ንጽህናውን የጠበቀ የመጠጥ ውሀ ለህብረተሰቡ ለማድረስ ታቅዶ ወደ 22% ማድረስ ተችሏል፡፡ የገጠር የውሀ ተቋማት የብልሽት ምጣኔ ከ11.45% ወደ 11.35% ለመቀነስ ታቅዶ የብልሽት ምጣኔውን በ0.12 በመቶ በመቀነስ ወደ 11.23% ዝቅ ማድረግ ተችሏል፡፡

## የሀይል አቅርቦትን ማሳደግ

የሃይል አቅርቦ 2015 ዓ.ም ከደረሰበት 6.6 ሜጋ ዋት ላይ 0.79 ሜጋ ዋት በመጨመር ወደ 7.39 ሜጋ ዋት ለማሳደግ ታቅዶ 0.51% በመጨመር 7.11 (64.6) ሜጋ ዋት ማድረስ ተችሏል፡፡ በበጀት ዓመቱ 92,000 የተሻሻሉ ማገዶ ቆጣቢ ቴክኖሎጂዎችን በሰለጠኑ አምራቾች

ለማስመረትና ለማሰራጨት ታቅዶ 103,483(112.5%) የተሻሻሉ ማገዶ ቆጣቢ ቴክኖሎጂዎችን በሰለጠኑ አምራቾች ማስመረትና ማሰራጨት ተችሏል።

## የውሀ ምርትና ስርጭት

የውሃ አገልግሎቶች የውሃ ምርትና ስርጭት በውሀ አገልግሎቶች 70,260,870 ሜትር ኩብ ውሃ ለማምረት ታቅዶ 59,046,959 ሜትር ኩብ ውሀ (84.03%) ማምረት የተቻለ ሲሆን ከተመረተው መካከል 46,050,722 ሜትር ኩብ (78%) ውሀ ማሰራጨት ተችሏል።

## የውሀ ፕሮጀክቶችን ማጠናቀቅ

በ2016 ዓ.ም 12 ከፍተኛ የመጠጥ ውሃ ፕሮጀክቶችን ለማጠናቀቅ ታቅዶ 14 ከፍተኛ ንጹህ መጠጥ ውሃ ተቋማትን ለማጠናቀቅ ተችሏል።በተመሳሳይ በገጠር በወረዳ ካፒታል በጀት 1200 አነስተኛ የውሃ ተቋማትን ለመገንባት ታቅዶ 648 አነስተኛ የውሃ ተቋማት ማጠናቀቅ ተችሏል።ይህም አፈጻጸም 53.33% ነው።



*ንፁህ የመጠጥ ውሃ ፕሮጀክት--በሰሜን ሸዋ ዞን (አረርቲ)*

## የውኃ ኮሚቴዎችን ማቋቋምና ማጠናከር

በ2016 ዓ.ም የውኃ ኮሚቴዎችን ለማቋቋምና ለማጠናከር በተሰራው ስራ 780 አዲስ የውኃ ኮሚቴ ማቋቋም ተችሏል።አፈጻጸሙም ከበጀት ዓመቱ 65% ነው።እንዲሁም ነባር የውሀ ኮሚቴዎችን ለማጠናከር በተሰራው ስራ አፈጻጸሙ 98.91% ማድረስ ተችሏል።

## የገጠር ንፁህ መጠጥ ውኃ ተጠቃሚዎችን ማህበር ማደራጀት

በ2016 ዓ.ም 20 የገጠር ንፁህ መጠጥ ውኃ ተጠቃሚዎችን ማህበር ለማደራጀት ታቅዶ 23 የገጠር ንፁህ መጠጥ ውኃ ተጠቃሚዎች ማህበራትን በማደራጀት ከ100% በላይ መፈጸም ተችሏል፡፡ እንዲሁም 23 የገጠር መጠጥ ውኃ አገልግሎት ለማደራጀት ታቅዶ 10 የገጠር መጠጥ ውኃ አገልግሎት የማደራጀት ተግባራት ተከናውኖ አፈጻጸሙም 62.5% ሲሆን በእነዚህ በተደራጁ ማህበራትና አገልግሎት ጽ/ቤቶች 145 የስራ እድል በመፍጠር 93.5% መፈጸም ተችሏል፡፡



*የገጠር ንፁህ መጠጥ ውኃ ተቋማት ማህበር*

## ውኃ ኃብትና ተፋሰስ አስተዳደር

የገፀ ምድርና ከርሰ ምደር መረጃ መሰብሰብ፤መተንተንና ማደራጀት እንዲሁም ጥናትና ምርምር ማካሄድ፣የጎርፍ አደጋ ተጋላጭ የሆኑ ቦታዎችን መለየትና የወንዝ መግራት ስራዎችን መስራትና የተሰሩትንም መቆጣጠር፣ በውኃ የመጠቀም ፈቃድ የሚያወጡ ግለሰቦች /ድርጅቶችን/ የጥናት ሰነዶችን መገምገምና ማፅደቅ፣የክልሉን የንፁህ መጠጥ ውኃ የተለያዩ የውኃ ማከሚያ ኬሚካሎችን በመጠቀምና ተያያዥ ስራዎችን በመስራት የመጠጥ ውኃን የጥራት ደረጃ ማሻሻል፣ የውኃ ጥራት መቆጣጠሪያ መመሪያ ማዘጋጀት፣በክልሉ በየጊዜው የሚከሰቱ ውኃ ወለድ በሽታዎችን መከላከልና መቆጣጠር፣ እንዲሁም በውኃው ዘርፍ ለሚሰሩ ድርጅቶችና ግለሰቦች ለአዲስ እና ነባር የሙያ እና የተቋራጮች ፈቃድ መስጠት ተችሏል፡፡

## የኤሌክትሪክ ኢነርጂ ምንጮችና ቴክኖሎጂ ልማት

ከፀሀይ ኃይል ኤሌክትሪክ የሚያመነጩ ሲስተሞችን ተጠቃሚ አባወራና እማወራ ቁጥር ቀደም ሲል ከተደረሰበት የተጠቃሚ ቁጥር 1,223,758 አባወራ/እማወራ ላይ 115,020 በመጨመር

ወደ 1,338,778 ተጠቃሚ ማድረስ ተችሏል፡፡የተቋማት ቁጥርን 110 ወደ 145 ማሳደግ ተችሏል፡፡ ከየኃይል አቅርቦት አንጻር 7390 ኪሎ ዋት (0.739MW) በመጨመር በፊት ከተደረሰበት 6.6 ሜጋ ዋት ወደ 7.39 ሜጋ ዋት ለማሳደግ ታቅዶ በበጀት አመቱ መጨረሻ 0.51 ሜጋ ዋት በመጨመር አጠቃላይ የሀይል አቅርቦቱን 7.11 ሜጋ ዋት በማድረስ የእቅዱን 69.% ማከናወን ተችሏል፡፡ እንዲሁም 10 የተቋም ሶላር ኦፍግሪድና አንድ የማህበረሰብ ጥናትና ዲዛይን ስራ 100% ማጠናቀቅ ተችሏል፡፡በበጀት አመቱ 30,000 አባወራ/ እማወራዎችን ተጠቃሚ የሚያደርግ የኤሌክትሪክ ምድጃና ምጣድ ምርቶችን ለማሰራጨት ታቅዶ ለ22,251 አባወራ/እማወራ ተጠቃሚ ሁነዋል አፈጻጸሙም 74.17% ሆኗል፡፡

## ማገዶ ቆጣቢ ቴክኖሎጂዎችን በማምረት ማሰራጨት

በ2016 ዓ.ም 92,000 የተሻሻሉ ማገዶ ቆጣቢ ቴክኖሎጂዎችን በሰለጠኑ አምራቾች ለማስመረትና ለማሰራጨት ታቅዶ 103,483 የተሻሻሉ ማገዶ ቆጣቢ ቴክኖሎጂዎችን /ምርጥ፤ጎንዜ፤ፈጠነች፤ላቀች፣አውራአምባ እና ሮኬት ማስመረትና ማስራጨት ተችሏል፡፡የእቅድ አፈፃፀሙም 112.48% መሆኑን ያሣያል፡፡በመሆኑም የተሻሻሉ ማገዶ ቆጣቢ ቴክኖሎጂዎች ስርጭት ሽፋን በ2.02% በመጨመር በ2015 ዓ.ም መጨረሻ ከተደረሰበት 67.07% ወደ 69.09% ለማሳደግ ተችሏል፡፡በዚህም 310,449 ህዝብ ቀጥተኛ ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡

## የቤተሰብ ባዮ-ጋዝ ቴክኖሎጂ ማስገንባት

በበጀት ዓመቱ 1,000 የቤተሰብብ ባዮ-ጋዝ ቴክኖሎጂ ለማስገንባት ዕቅድ ተይዞ 1,893 ማስገንባት ተችሏል፡፡የዕቅድ አፈጻጸሙም 189.3% መሆኑን ያሣያል፡፡በ2015 መጨረሻ ከደረሰበት ከ17,435 ወደ 19,328 ላማሳደግ ተችሏል፡፡በዚህም ከ 9,465 ህዝብ በላይ ቀጥተኛ ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡

## የሳኒቴሽን መሰረተ ልማት ጥናት፤ድዛይንና ግንባታ ክትትል

ከሳኒቴሽን መሰረተ ልማት ጥናት፤ድዛይንና ግንባታ ክትትል ዘርፍ በሚመለከት በአለም ባንክ የበጀት ድጋፍ የ4ቱ ከተሞች ባህርዳር፣ ደሴ፣ ጎንደርና ደብረ ብርሃን የቢዝነስ ፕላንና የውኃ ብክነት ቅነሳ የጥናትና ዲዛይን ስራ፣ አነስተኛ ገቢ ባላቸው አካባቢዎች የውኃ ማስፋፊያ ጥናት፣ በ3ቱ ከተሞች (ደሴ፣ ጎንደርና ደብረ ብርሃን) የፍሳሽ ቆሻሻ አስተዳደር የመካከለኛና የረጅም ጊዜ ዝርዝር ጥናትና ዲዛይን ስራ፣ በውኃ ልማት ፈንድ የበጀት ድጋፍ በ2ቱም ከተሞች

(እንጅባራና አረረቲ) የቆሻሻ ፍሳሽ አስተዳደር የአዋጪነት ጥናት ድራፍት ጥናት ቀርቦ የግምገማ ስራ ተከናውኗል።

### የህዝብ መጸዳጃ ቤቶች እና የፍሳሽ ቆሻሻ ማጣሪያ ግንባታ

በበጀት አመቱ በአለም ባንክ የበጀት ድጋፍ የህዝብ መጸዳጃ ቤቶች ግንባታ በባህር ዳር፣በጎንደር፣በደሴ እና በደብረብርሃ ከተሞች በተለያየ የአፈጻጸም ሁኔታ ላይ ይገኛሉ።በአለም ባንክ የበጀት ድጋፍ የሚከናወነው የፍሳሽ ቆሻሻ ማጣሪያ ግንባታ በ3ቱም ከተሞች (ደሴ፣ ጎንደርና ደብረብርሃን) የፍሳሽ ቆሻሻ ማጣሪያ ግንባታና ክትትል ስራ በማስጀመር በአማካይ 60% ለማድረስ ሲሰራ ቆይቶ በሶስቱም ከተሞች ግምባታው ተጀምሯል።



*በባህር ዳር ከተማ የተገነቡ የህዝብ መጸዳጃ ቤቶች*

## እንስሳትና ዓሳ ሀብት ልማት

### ወተት ሀብት ልማት

በጀት ዓመቱ የወተት ምርታማነትን በተመለከተ ከአንድ ላም በቀን በአማካኝ የሚታለብ የወተት ምርት ከአካባቢ ላም ወደ 1.9 ሊትር እና ከተሻሻሉ ዝርያዎች ወደ 12 ሊትር ለማድረስ ታቅዶ ከአካባቢ ላም 1.75(92%) ሊትር እና ከተሻሻሉ ዝርያዎች 10.7(89%) ሊትር ማድረስ የተቻለ ሲሆን በአመቱ 1,841,733 ቶን የወተት ምርት ለማምረት ታቅዶ 1,903,068 ቶን የተመረተ ሲሆን አፈጻጸሙም ከ100% በላይ ማምረት ተችሏል፡፡



በደብር ብርሃን ከተማ በባለሃብት ደረጃ እየተሰራ ያለ የወተት ሃብት ልማት ስራ

## የስጋ ምርትና ምርታማነት

በ2016 በጀት ዓመት የአንድ እንስሳት አማካኝ የሥጋ ምርታማነት ከዳልጋ ከብት ከ133 ኪሎ ግራም ስጋ ለማግኘት ታቅዶ 133 (100%) ኪሎ ግራም ስጋ፣ ከበግ 15 ኪሎ ግራም ለማግኘት ታቅዶ 13.4 (89%) ኪሎ ግራም ስጋ፣ ከፍየል 14 ኪሎ ግራም ለማግኘት ታቅዶ 13 (92%) ኪሎ ግራም ስጋ ፤ ከተሻሻለ ዶሮ 2 ኪሎ ግራም ስጋ ለማሳደግ ታቅዶ እስካሁን 1.8 (90%) ኪሎ ግራም ስጋ ማድረስ የተቻለ ሲሆን ከጠቅላላ የስጋ 551,455 ቶን ሥጋ ለማምረት ታቅዶ 448,816 ቶን ስጋ ማምረት የተቻለ ሲሆን አፈጻጸሙን 100% ማድረስ ተችሏል፡፡ ከዳልጋ ከብት 382,433 ቶን ስጋ፣ ከበግ 106,399 ቶን ስጋ፣ ከፍየል 62,399 ቶን ስጋ እና ከዶሮ 1,6754 ቶን ስጋ ለማግኘት ታቅዶ ከዳልጋ ከብት 280,603 (73%) ቶን ስጋ፤ ከበግ 89,934 (84%) ቶን ስጋ፣ ከፍየል 52,485 (84%) ቶን ስጋ እና ከዶሮ 13,572 (81%) ቶን ስጋ ማግኘት ተችሏል፡፡

## የእንቁላል ምርትና ምርታማነት

በበጀት ዓመቱ የእንቁላል ምርታማነት ከአካባቢ ዶሮ 65፣ ከተሻሻለ የቤተሰብ ዶሮ 146 ለማድረስ ታቅዶ ከአካባቢ ዶሮ 65 (100%)፣ ከተሻሻሉ ዶሮ 145 (99%) እንቁላል ለማድረስ የተቻለ ሲሆን በአጠቃላይ በበጀት ዓመቱ 764 ሚሊዮን እንቁላል ለማምረት ታቅዶ 851 ሚሊዮን እንቁላል የተመረተ ሲሆን አፈጻጸሙም 100% ማምረት ተችሏል፡፡



በደብረ ብርሃን ከተማ ደብረ ሆላን የዶሮ እርባታ ማዕከል

## የማርና ሰም ምርታማነት ማሳደግ

በበጀት ዓመቱ የማር ምርታማነትን ለማሳደግ በአንድ ቀረጣ ከባህላዊ ቀፎ 11 ኪሎ ግራም፣ ከሽግግር ቀፎ 28 ኪሎ ግራም እና ከዘመናዊ ቀፎ 44 ኪሎ ግራም ማር ለማድረስ ታቅዶ በዓመቱ ከባህላዊ ቀፎ 7.5 ኪሎ ግራም (68%) ኪሎ ግራም፣ ከሽግግር ቀፎ 22 ኪሎ ግራም (79%) እና ከዘመናዊ ቀፎ 28 ኪሎ ግራም (64%) ማር ማድረስ ተችሏል፡፡ከሁሉም የቀፎ አይነቶች 30,133 ቶን ማር ለማምረት ታቅዶ እስካሁን 22,292 ቶን ማር የተመረተ ሲሆን አፈጻጸሙም 74% ማምረት ተችሏል፡፡ይህም ከዘመናዊ ቀፎ 7,086 ቶን፤ ከሽግግር ቀፎ 3,499 ቶን እና ከባህላዊ ቀፎ 19,547 ቶን ማር ለማምረት ታቅዶ ከዘመናዊ ቀፎ 4,960 (70%) ቶን፣ ከሽግግር ቀፎ 4,242 (100%) ቶን እና ከባህላዊ ቀፎ 13,090 (67%) ቶን ማር ማምረት ተችሏል፡፡ የሰም ምርትን 1, 656 ቶን ለማምረት ታቅዶ 856 ቶን (52%) ሰም ማምረት ተችሏል፡፡

## የቆዳና ሌጦ ምርት በጥራት ማቅረብ

የቆዳና ሌጦ ምርት 9.1 ሚሊዮን ለማምረት ታቅዶ 6.40 ሚሊዮን ቆዳና ሌጦ ማምረት የተቻለ ሲሆን አፈጻጸሙም 70% ማምረት ተችሏል፡፡ በዚህም 1,788,329 የዳልጋ ከብት፣

4,819,427 የበግ እና 2,501,254 የፍየል ሌጦ ለማምረት ታቅዶ የዳልጋ ከብት 1,818,407 (100%) የበግ 3,678,600 (76%) እና የፍየል ሌጦ 3,232,674 (100%) ቆዳና ሌጦ ማምረት ተችሏል፡፡

## ዓሳ ሀብት ልማት

በበጀት አመቱ የዓሳ ግብርናን ከማስፋፋት አንጻር 1,328 የዓሳ ኩሬ ለማዘጋጀት እና 502,700 የዓሣ ጫጩት ለመጨመር ታቅዶ 208 (16%) ኩሬዎች በማዘጋጀት 308,926 (61%) ዓሳ ጫጩት በተዘጋጁ ኩሬዎችና ውሃማ አካላት መጨመር ተችሏል፡፡

## የእንስሳት መኖ አቅርቦት እና እንስሳት ማድለብ

በበጀት ዓመቱ 49 ሚሊዮን ቶን ድርቆ መኖ ለማምረት ታቅዶ እስከ አሁን 56 ሚሊየን ቶን (100%) ድርቆ መኖ ማምረት ተችሏል። የእንስሳትን ምርታማነትን ለመጨመር 59,472 ቶን የተመጣጠነ መኖ ለማቅረብና ጥቅም ላይ እንዲውል ታቅዶ 70,053 ቶን ምጥን መኖ ማቅረብ ሲቻል አፈጻጸሙም 100% ማቅረብና ጥቅም ላይ ማዋል ተችሏል።የመኖ ዘር ብዜት ለማካሄድ ታቅዶ በበጀት ዓመቱ 2,503 ሄክታር (40%) ማከናወን የተቻለ ሲሆን 15,594 ኩንታል የመኖ ዘር ለማምረት ታቅዶ 5,626 ኩንታል (36%) ማምረት ተችሏል።በመሆኑም የቀረቡ የተለያዩ መኖዎችን በመጠቀም እንስሳትን ማድለብ ተችሏል።



እንስሳት ማድለብ- ደብረ ብርሀን ከተማ

## የእንስሳት ዝርያን ማሻሻል

የዳልጋ ከብት ዝርያን ለማሻሻል በተፈጥሮ ድራት 222,000፣ በተሻሻለ ኮርማ 200,000 እና በሲንክሮኒይዜሽን 62,000 በድምሩ 422,000 ለማዳቀል ታቅዶ በተፈጥሮ ድራት 93,595 (42%)፣ በተሻሻለ ኮርማ 123,100 (62%) እና በሲንክሮኒይዜሽን 3,763 (6%) በድምሩ 220,458(46%) ማዳቀል ተችሏል፤በሶስቱም መንገድ 204,668 ጥጆችን ለማስወለድ ታቅዶ 129,336 (63%) ጥጆችን ማስወለድ ተችሏል፡፡



በጎንደር ከተማ በሴክስድ ሴመን የተወለዱ ጥጆች

## የእንስሳት ጤና አገልግሎት ማሻሻል

በበጀት ዓመቱ ለ60.4 ሚሊዮን እንስሳት የክትባት አገልግሎት፣ ለ27.2 ሚሊዮን ቅድመ መከላከል ህክምና፣ ለ11.2 ሚሊዮን እንስሳት የፈውስ ህክምና ለመስጠት ታቅዶ ለ36.28 ሚሊዮን (60%) የክትባት አገልግሎት፣ ለ18.04 ሚሊዮን (66%) የቅድመ መከላከል ህክምና፣ 8.52 ሚሊዮን (76%) ለታመሙ እንስሳት ህክምና መስጠት ተችሏል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ለ1.1 ሚሊዮን እንስሳት ላብራቶሪ ምርመራ ለማካሄድ ታቅዶ ለ194,809 (17%) እንስሳት የላብራቶሪ ምርመራ ማካሄድ ተችሏል፡፡

የእንስሳት ጤና አገልግሎትን ተደራሽ ለማድረግ 110 ክሊኒኮችን ለመገንባት ታቅዶ 8 ክሊኒኮችን ብቻ ማከናወን ተችሏል፡፡በሚሰጠው የህክምና አገልግሎት 20 ሚሊዮን ብር የአገልግሎት ክፍያን ለመሰብሰብ ታቅዶ 8.11 ሚሊዮን ብር (41%) የአገልግሎት ክፍያ መሰብሰብ መቻሉ፣ ለመድሀኒት ግዥ የሚውል 2.14 ሚሊዮን ብር ተዘዋዋሪ በጀት ለማስመደብ ታቅዶ 11.57 (100%) ማስመደብ ተችሏል፡፡ የእንስሳት ህክምና አገልግሎት የሚሰጡ 1,735 ክሊኒኮችን ኦዲት ለማስደረግ ታቅዶ 704 (41%) ማከናወን ተችሏል፡፡

# ፕላንና ልማት

## የመረጃ አሰራር ስርዓትን በቴክኖሎጂ በማዘመን

በበጀት ዓመቱ የክልሉን እምቅ ሃብት የሚያሳይ 1 ሰነድ ለማደራጀት ታቅዶ የሀብት ምንጭ ዘርፎችን በመሬት ሃብት፣ በውሃ ሃብት፣ በቁሳዊ ሃብት እና በቱሪዝም ሃብት በመለየት በዓመቱ 1 ሰነድ በማዘጋጀት የእቅዱን 100% መፈጸም ተችሏል፡፡በየወረዳው የተሰሩ አገልግሎት ሰጭ ተቋማት ስርጭታቸውን ከስታንዳርዱ አንፃር ለመገምገም 1 ሰነድ ለማዘጋጀት በእቅድ የተያዘ ሲሆን በዓመቱ ከታቀዱ 9 ወረዳዎች ውስጥ በዓመቱ የ9 ወረዳዎችን በማከናዎን የዕቅዱን 100% መፈጸም ተችሏል፡፡አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማት ስርጭት ፍትሃዊ እንዲሆን አለም አቀፍ መስፈርቶችን በመጠቀም የ9 ወረዳዎችን መረጃ በ1 ሰነድ ለማዘጋጀት እቅድ ተይዞ 1 በማከናወን 100% መፈጸም ተችሏል፡፡

የክልሉን አጠቃላይ የልማት አመልካች /Development Indicator/ ለመስራት የ10 ዓመቱን ዕቅድ መሰረት ያደረገ የ15 ተቋማት የመረጃ መሰብሰቢያ ፎርማቶችን ለማዘጋጀት ዕቅድ የተያዘ ሲሆን በዕቅዱ መሰረት የ15 ተቋማት የመረጃ መሰብሰቢያ ፎርማት ተዘጋጅቷል፡፡ በዚህም መሰረት የእቅዱን 100% ማከናወን ተችሏል፡፡ በተዘጋጀው ፎርማት መሰረትም በዓመቱ የ14 ተቋማት መረጃ ለመሰብሰብ ዕቅድ ተይዞ የ14 ተቋማት መረጃ መሰብሰብ ተችሏል፤ አፈፃፀሙም 100% ማከናወን ተችሏል፡፡

በተመረጡ ከተሞች የሶሺዮ-ኢኮኖሚ ጥናት ለማካሄድ የሚያስችል በዓመቱ 2 መረጃ ማሰባሰቢያ ፎርማትና መጠይቆች ለማዘጋጀት ዕቅድ ተይዞ በባህር ዳር ከተማ በሚገኙ ተቋማት መረጃው የተሰበሰበ ሲሆን አፈፃፀሙም 100% ማከናወን ተችሏል፡፡

በክልል ደረጃ ለሚዘጋጀው የ2017 በጀት ዓመት እቅድ በግብዓትነት እንዲያገለግል ለማድረግ የ2017 ዓ.ም የክልሉን ህዝብ ብዛት በነጠላ እድሜ እና በ5 ዓመት የእድሜ ክፍፍል በመተንበይ ለክልል ሴክተር መስሪያቤቶች እና ለሁሉም ዞኖች መረጃው በቴሌግራም እንዲደርስ ተደርጓል፡፡

ለበጀት ቀመር የሚውል የህዝብ ብዛት መረጃ (ከ2015-2017 ዓ.ም) እና ለትምህርት የደረሱ ህጻናት በዕድሜ ክፍፍል የ2017 ዓ.ም መረጃ ለገንዘብ ቢሮ፤ ለከተሞች የደረጃ ሽግግር ውድድር የሚያገለግል የ284 ከተሞችን የ2016 ዓ.ም የህዝብ ብዛት መረጃ ለከተማና መሰረተ ልማት ቢሮ በማደራጀት ተልኳል፡፡

በክልል ደረጃ የህዝብ ብዛት መረጃ ለማሰባሰብና ለማደራጀት የሚያስችል 1 የድርጊት መርሃ-ግብር ለማዘጋጀት ታቅዶ በክልሉ የሚገኙ ከተሞችን ወሰንና የህዝብ ብዛት መረጃ ወቅታዊ ለማድረግ የሚያስችል ፕሮጀክት ፕሮፖዛል በማዘጋጀት 100% መፈጸም ተችሏል፡፡

## ችግር ፈቺ የፖሊሲ ትንታኔዎች፣ የጥናት እና ምርምር ስራዎች

በበጀት አመቱ በስራ ላይ የዋሉ የማክሮ ኢኮኖሚ ፖሊሲዎች በተለይም የፊዚካል ፖሊሲ አፈጻጸም 24 መረጃዎችን ለማደራጀት ታቅዶ 17 የተከናወነ ሲሆን አፈጻጸሙም 73.9% ነው፡፡በጥናትና ምርምር ስራ የተለዩ የጥናት መስኮችና የተዘጋጀ ዝርዝር የድርጊት መርሃ ግብር የሚያሳይ በዓመቱ 1 ሰነድ ለማዘጋጀት የታቀደ ሲሆን 1 ሰነድ በማዘጋጀት አፈጻጸሙን 100% ማድረግ ተችሏል፡፡

የአገሪቱን የ10 አመት እቅድ መሰረት አድርጎ ከፖሊሲ፣ ከስትራቴጅ፣ ከአዋጅ፣ ከአገሪቱ አገር በቀል የኢኮኖሚ ሪፎርም አጀንዳ እንዲሁም ከICT የትኩረት መስኮች አንፃር መታቀዱን በመገምገም ለውሳኔ ሀሳብ የሚረዳ እና ለእቅዱ ግብአት የሚሆን ፖሊሲዎችን መሰረት ያደረገ ጽሁፍ ተደራጅቶ ቀርቧል፡፡

## አስተዳደራዊ ወሰን ማካለል እና መረጃዎችን ማደራጀት

በወረዳዎች እና በከተማ አስተዳደሮች ያሉ ቀበሌዎች ብዛት እንዲሁም ከዞንና ከወረዳ ዋና ከተማ ያላቸውን ርቀት በኪሎ ሜትር መረጃ ለመሰብሰብ፣ ለማደራጀትና ለተጠቃሚዎች ለማሰራጨት 238 ወረዳዎች በእቅድ ተይዘው የነበረ ሲሆን በክልሉ የነበረውን ስድስት ዓይነት ካርታዎችን ወደ አንድ በማምጣት በዞን ደረጃ የሚገኙ ወሰኖችን አጣርቶ የመከለስ ስራ ተከናውኗል፡፡

የ20 ከተሞችን አስተዳደራዊ ወሰን ለውጥ መሰረት በማድረግ ታቅዶ የ2 ከተሞችን (አርጡማ ፉርሲ ወረዳ - የጨፋ ሮቢት ከተማ እና ጃናሞራ ወረዳ - የመካነ ብርሃን ከተማ) የህዝብ ብዛት መረጃ ወቅታዊ ማድረግ በመቻሉ በወቅታዊ ችግር ምክንያት 10% ብቻ ማከናወን ተችሏል፡፡

## የፕላን ትግበራና ክትትል ዘርፍ

የ2016 በጀት ዓመት ክልላዊ የልማትና መልካም አስተዳደር ዕቅድን ማጠናቀቅና ማስጸደቅ በዕቅድ 1 ሰነድ የተያዘ ተግባር ሲሆን ክንውን 1 የዕቅድ ሰነድ በማዘጋጀት ማስጸደቅ ተችሏል አፈጻጸሙም 100% ነው፡፡

## እቅድ ማስተዋወቅ

በበጀት አመቱ 400 ለሚደርሱ በየደረጃው ላሉ የዞንና የወረዳ አካላት የ10 ዓመት መሪ የልማት ዕቅድና የ2016 በጀት ዓመት ክልላዊ የልማትና መልካም አስተዳደር ዕቅድ ለማስተዋወቅ ታቅዶ 100 ለሚሆኑ የክልል ተሳታፊዎች በማስተዋዎቅ የዕቅዱን 25% መፈጸም ተችሏል፡፡ አፈጻጸሙ ዝቅተኛ የሆነበት ምክንያት በወቅታዊው የጸጥታ ችግር ምክንያት ወደ ዞንና ወረዳዎች መድረስ ባለመቻሉ ነው፡፡

## የልማት ኘሮጀክት እቅድ ዝግጅት፣ ክትትልና ግምገማ፤

ለአዲስ ፕሮጀክቶች የመጀመሪያ ደረጃ የፕሮጀክት ጽንሰ ሃሳብ መለያ 1 መስፈርት ለማዘጋጀት በዕቅድ ተይዞ በዓመቱ 1 መስፈርት በማዘጋጀት አፈጻፀሙ ከዕቅዱ ጋር ሲነጻፀር 100% ነው፡፡

በዓመቱ ለአዲስ ፕሮጀክቶች የአዋጭነት ጥናት ማድረጊያ 1 መስፈርት ለማዘጋጀት ታቅዶ 1 በመፈጸሙ የዕቅዱን 100% ማከናወን ተችሏል፡፡

የልማት ፕሮጀክቶችን የፕላን መረጃዎች ምቹ በሆነ መንገድ ለማደራጀት በዓመቱ 1 ጊዜ ለማከናወን በዕቅድ የተያዘ ሲሆን 1 ጊዜ በጥራት መያዝ የተቻለ በመሆኑ አፈጻፀሙ 100% ሆኗል፡፡

አዋጭ የልማት ፕሮጀክቶች በበጀት እንዲደገፉ ለማድረግ የሚያስችል መረጃ በመመዘኛ መስፈርቱ መሰረት በማደራጀት ለክልሉ ርዕሰ መስተዳድር ጽ/ቤት፣ ለገንዘብ ቢሮና ጉዳዩ ለሚመለከታቸው አካላት መላክ ተችሏል፡፡

የ2016 በጀት ዓመት ለአዲስና ነባር ኘሮጀክቶች ካፒታል በጀት እቅድ በዓመት 1 ጊዜ ለ17 ተቋማት ማዘጋጀትና ማደራጀት በዕቅድ ተይዞ ለ17 ተቋማት 1 ጊዜ ማዘጋጀትና ማደራጀት የተቻለ ሲሆን 100% መፈጸምተ ችሏል፡፡

በበጀት ዓመቱ የካፒታል በጀት የጸደቀላቸውን መስሪቤቶች (ለ35 ተቋማት) ፕሮጀክቶች መረጃ ለመያዝ ታቅዶ ለ35 ተቋማት በመስራት የእቅዱን 100% መፈጸም ተችሏል፡፡

በፌደራል በጀት የሚሰሩ ኘሮጀክቶችን መረጃ በመለየት የውሀና የመብራት ፕሮጀክቶችን ክትትልና ድጋፍ ለማድረግ ታቅዶ 2 ፕሮጀክቶችን በማከናወን የእቅዱን 100% መፈጸም ተችሏል፡፡

ከገንዘብ፣ከፍትህ እና ከፕላን የተውጣጡ ባለሙያዎች በተመረጡ የልማት ፕሮጀክቶች አፈጻጸም ላይ በዓመት 2 ጊዜ የሰነድ ምርመራ ለማድረግ ታቅዶ ምርመራውን 1 ጊዜ ማድረግ በመቻሉ የእቅዱን 50% ማከናወን ተችሏል፡፡

# አካባቢና ደን ጥበቃ ልማት

## የአሰራር ሥርአቶችን ማውጣት

በበጀት አመቱ የአካባቢ ህግ ተከባሪነትን በማረጋገጥ ረገድ በክልሉ ውስጥ በአካባቢ ላይ የሚደርሰውን ብክለትና ብክነት እንዲሁም የደን ሀብቶችን ዝውውር የመቆጣጣር ኃላፊነት ለባለስልጣኑ የተሰጠው ሲሆን ይህንንም እውን ለማድረግ የአሰራር ሥርአቶችን በማውጣት በመተግበር ላይ ይገኛል፡፡ በመሆኑም ሁለት መመሪያዎችን እንደገና ለማሻሻል የሚያስችል መረጃ የማሰባሰብና ረቂቁን የማዘጋጀ ስራ ተሰርቷል፡፡

### የአካባቢ ተፅዕኖ ሰነድ በመገምገም ይሁንታ ፈቃድ መስጠት

በ2016 ዓ.ም የልማት ፕሮጀክቶች የሚያቀርቡትን የአካባቢ ተፅዕኖ ሰነድ በመገምገም 4,500 ለሚሆኑ የልማት ፕሮጀክቶች ይሁንታ ፈቃድ ለመስጠት ታቅዶ መስፈርቱን አሟልተው ለተገኙ 4,239 (›100%) ፕሮጀክቶች ሰርተፊኬት የተሰጠ ሲሆን እንዲሁም ለ2,500 ፕሮጀክቶች የይሁንታ ፈቃድ ዕድሳት አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ ለ3,086 (›100%) ፕሮጀክቶች ማደስ ተችሏል፡፡ከይሁንታ ፈቃድ፣ ዕድሳትና ቅጣት በድምሩ 1,720,000 ብር ለመሰብሰብ ታቅዶ ብር 1,062,010 (62%) መሰብሰብ ተችሏል፡፡በአካባቢ አማካሪነት ለመሰማራት ለሚጠይቁ 8 ድርጅቶችና 40 ሙያተኞች ፈቃድ ለመስጠት ታቅዶ መስፈርቱን አሟልተው ለተገኙ 8 (100%) ድርጅቶችና 48 (>100%) ሙያተኞች ፈቃድ ተሰጥቷል፡፡ ለ10 አማካሪ ድርጅቶች እና 60 ባለሙያዎች የፈቃድ ዕድሳት ለማድረግ ታቅዶ ለ8 (80%) ድርጅቶችና 59 (98%) ባለሙያዎች ፈቃድ ተሰጥቷል፡፡የይሁንታ ፈቃድ ለተሰጣቸው ፕሮጀክቶች የአካባቢ ክዋኔ ኦዲት በማድረግ የማስተካከያ እርምጃ መውሰድን በሚመለከት በ3,000 ፕሮጀክቶች ላይ ክዋኔ ኦዲት ለማካሄድ ታቅዶ በ2,693 ፕሮጀክቶች ላይ የኦዲት ሥራ በማድረግ ግብረ መልስ የተሰጠ ሲሆን አፈጻጸሙ 90% ነው፡፡በክዋኔ ኦዲት ወቅትም የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናት ሰነዱን አለመተግበር፣ የአካባቢ አሃድ አቋቋሞ የሰለጠኑ ባለሙያዎችን አለመቅጠር እና በተሰጣቸው ቅድመ ሁኔታ አለመስራት በጉድለት ታይቷል፡፡

## ፕሮጀክቶችን ክትትል ማድረግ

የማምረቻና አገልግሎት መስጫ ተቋማት የአካባቢ ህግ አክብረው መሥራታቸውን በክትትልና ቁጥጥር ማረጋገጥን በተመለከተ 3,500 ፕሮጀክቶች በገቡት ውለታ መሰረት መተግበራቸውን በክትትል ለማረጋገጥ ታቅዶ 3,042 (87%) በሚሆኑት ላይ ክትትል የተደረገ ሲሆን ከፍተኛ ብክለትና ብክነት ባደረሱ እና የህግ ጥሰት በፈጸሙ 129 ፕሮጀክቶች ላይ አስተዳደራዊና ህጋዊ እርምጃ ተወስዷል። በክትትልና ቁጥጥር ወቅት የተወሰኑ ፕሮጀክቶች ግቢያቸውን በአጥር አለመለየት፣ደረቅ ቆሻሻን ለይቶ በአግባቡ አለማስወገድ፣ ፍሳሽ ቆሻሻን ወደ አካባቢ መልቀቅ፤ የሥራ ላይ ደህንነት መጠበቂያ ቁሳቁስ አቅርቦት አለመኖር፣ የአቧራ መቀነሻ እና መከላከያ ስልቶችን አለመጠቀም ችግሮች በክትትሉ እንደታዩ ለማየት ተችሏል።



የአካባቢ ጥበቃና ኦዲት ባለሙያዎች የመስክ ቁጥጥር-ኮምቦልቻ ከተማ

## ብክለትን የማስወገድ ስራ መስራት

የአካባቢ ብክለት ይወገድልኝ አቤቱታና ጥቆማ በመቀበል ማጣራትና ምላሽ በመስጠት ረገድ ከህብረተሰቡ ለሚቀርቡ 2,500 የብክለት ይወገድልኝ ጥያቄዎችና ጥቆማዎችን በመቀበል መፍትሄ እንዲሰጥ ለማድረግ ታቅዶ 2,007 (›100%) ጥቆማዎችን በመቀበል ምላሽ እንዲያገኙ ተደርጓል።ጥቆማዎቹ በድምጽ ብክለት፣ በህገ ወጥ ደንጋይና አሸዋ ማምረት፣ በህገ ወጥ እርድ፣በግንባታ ተረፈ ምርት አለመነሳት፣በደረቅና ፍሳሽ ቆሻሻ አወጋገድ፣ በውሃ አዘል መሬቶች ብክነት፣ በኬሚካልና ድምፅ ብክለት፣ በተፈጥሮ ሃብት ጉዳቶች (በደን መጨፍጨፍ፣ በመሬት መንሸራተት እና የኳሪ ሳይት ቁፋሮ) ላይ ያተኮሩ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ተችሏል።



ብክለት ይብቃ ውበት ይንቃ በሚል መሪ ቃል የተካሄደ ውይይት

## በከተሞች የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ክትትል እና ቁጥጥር ስራ ማከናወን

በከተሞች የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ክትትል እና ቁጥጥር ስራ ለማከናወን በተሰራው ስራ በ8 ከተሞች እና 77 ከተሞች የደረቅ ቆሻሻና ፈሳሽ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ዙሪያ ክትትልና ቁጥጥር ለማድረግ ታቅዶ በ97 ከተሞች እና በ11 ሪጅኦፖሊታን ከተማ አስተዳደሮች ክትትል በማድረግ አፈጻጸሙ 100% ሲሆን ክትትል በተደረገባቸው ከተሞች የቋሚና ጊዜያዊ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ አለመኖር፣ በባለድርሻ አካላት መካከል ተቀናጅቶ አለመስራት፣ የደረቅ ቆሻሻ አስወጋጅ ማህበራት አለመጠናከር እንዲሁም የአመራሩ ትኩረት ማነስ ችግሮች እንዳሉ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

## ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ መገንባት

ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ ግንባታ ስልትን ለህብረተሰቡ በማስገንዘብ፣የልቀት ቅነሳ ተግባር መስሪያቤቶችን በማስተባበር እና በመከታተል ረገድ የCRGE ተግባሪ መስሪያቤቶች ተጠሪ ባለሙያ/ፎካል እንዲመደቡ እና የአየር ንብረት ለውጥ ሥራዎችን በትኩረት እንዲሰሩ የሚያስችል ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ግብረ-መልስ መስጠት ተችሏል፡፡ ክልላዊ የሙቀት አማቂ ጋዝ የልቀት መጠን የ10 ዓመት (2012-2022) መነሻ ዕቅድ በባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ አማካኝነት የተጠና ሲሆን ውጤቱ እንደሚያሳየውም በ4ቱ ዋና ዋና ሴክተሮች የልቀት መጠኑ 79,829,885 mmt co2e ነው፡፡የአየር ንብረት ለውጥ ተፅዕኖን ለመቋቋምና ለመቀነስ የሚረዱ 12 የአረንጓዴ ቴክኖሎጅዎች በተቋማት እንዲተገበሩ ክትትል የተደረገ ሲሆን የተሻሻሉ ሃይል ቆጣቢ ሶላር፣ ሶላር ፓፐ ቴክ፣ የበግ፣ ዶሮና ንብ እርባታ፣ የተሻሻሉ ማገዶ ቆጣቢ ምድጃዎች፣ እንስሳት ማድለብ፣ ቨርሚ ኮምፖስት ዝግጀት፣ የተራቆተ አካባቢ

ማልማት፣ የውበትና ገፀ ምድር ልማት፣ ባዮ ጋዝ የማስተዋወቅ፣ ተደራሽ የማድረግና የመከታተል ስራ የተከናወነ ሲሆን 136,278 ቴክኖሎጂዎች ተደራሽ ሆነዋል፡፡

## የቀይ ቀበሮን የመኖሪያ ስፍራ መለየት

በበጀት አመቱ የቀይ ቀበሮ መኖሪያ ስፍራ በመለየት በታሳቢ ጥብቅ ስፍራነት እንዲጠናና እንዲከለል በማድረግ በኩል በጉባላፍቶና አንጎት ወረዳዎች በሚገኙ 8 ቀበሌዎች 1,269 ሄክታር መሬት በታሳቢ ጥብቅ ስፍራነት እንዲጠናና እንዲከለል ተደርጓል፡፡



የቀይ ቀበሮ ዝርያዎች እና መኖሪያዎቻቸው

## በአረንጓዴ አሻራ የተሰሩ ተግባራት

በጎንደር ከተማ የአረንጓዴ አሻራን ለማከናወን የሚያስችል የንቅናቄ ዕቅድ ተዘጋጅቶ ወደ ትግበራ የተገባ ሲሆን በዚህም 412,345 የውበት፣ የደንና ፍራፍሬ ችግኞች እንዲተከሉ ማስተባበር ተችሏል፡፡ ሌላው በወራሪና ተስፋፊ አረም ዝርያዎች ስፋትና ስርጭት አራት (4)፣ በውሃ አዘል መሬቶች አያያዝና አጠቃቀም አንድ (1) እንዲሁም በአደገኛ ንጥረ ነገሮች መረጃ ማሰባሰብና ጥናት አስር (10) ሰነዶች በዞኖችና ከተማ አስተዳደሮች ተጠንተዋል፡፡



የአረንጓዴ አሻራ ችግኝ ተከላ ንቅናቄ ፕሮግራም

## የደን ልማትና ጥበቃ ስራዎችን ማሻሻል

በመንግስት ደኖች ውስጥ 3,500 ሄክታር መሬት ላይ 875,000 ችግኞችን በማበልጸጊያነት ለመትከል ታቅዶ 4,899.7 ሄክታር መሬት ላይ 2,517,131 ችግኞችን መትከል የተቻለ ሲሆን አፈጻጸሙ በሄክታር 100% እና በችግኝ ከ100% በላይ ሆኗል፡፡ይህ አፈጻጸም ከባለፈው ተመሳሳይ በጀት አፈጻጸም ጋር ሲነጻጸር በመብለጥ የሚያሳይ ሲሆን ይህን አፈጻጸም የበለጠ ለማሻሻል ከፍተኛ ጥረት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡



የዲከረንስ ደንን በማልማት-ጓጉሳ ሽኩዳድ ወረዳ

## በደን ልማት ላይ የተሰማሩ ፕሮጀክቶች አፈፃፀም

በደን ልማት ላይ በተሰማሩ ፕሮጀክቶች አማካኝነት በ500 ሄክታር መሬት ላይ 1.5 ሚሊዮን ችግኞችን ለመትከል ታቅዶ በ1476.7 ሄክታር መሬት ላይ 2,434,373 ችግኞችን መትከል የተቻለ ሲሆን አፈጻጸሙ በሄክታር እና በችግኝ ከ100% በላይ ነው፡፡1,166,158.6 ሄክታር ለሚሆኑ የተፈጥሮ ደኖች የተጠናከረ ጥበቃ በማካሄድ ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ ለመገንባት ለሚደረገው ጥረት አስተዋጽኦ ለማበርከት ታቅዶ ለ1,091,400.61 ሄክታር (94%) የተፈጥሮ ደኖች ጥበቃ ተደርጓል፡፡

## ለደን የተጠናከረ ጥበቃ ማድረግ

በ4,500 ኃይማኖት ተቋማት ለሚገኙ ደኖች ጥበቃ ለማድረግ ታቅዶ ለ3,290 የኃይማኖት ደኖች ጥበቃ የተደረገ ሲሆን አፈጻጸሙ 54% ነው፡፡ ለ42,500 ሄክታርር የቀርቀሃ መሬት የተጠናከረ ጥበቃ ለማካሄድ ታቅዶ በአዊ፣ ደቡብ ወሎ፣ ማዕከላዊ ጎንደርና ምዕራብ ጎንደር ዞኖች 22,804 ሄክታር

የቀርቀሃ ደን የተጠበቀ ሲሆን አፈጻጸሙ 54% ነው፡፡ 100,000 ሄክታር የተራቆተ ተራራማ መሬት ከንክኪ ነጻ ሆኖ እንዲያገግም ለመከለልና ለማልማት ታቅዶ 83,327 ሄክታር የተራቆተ መሬት እንዲያገግም በማድረግ 83% መፈጸም የተቻለ ሲሆን አፈጻጸሙ ከባለፈው ተመሳሳይ በጀት ዓመት አፈጻጸም ጋር ሲነጻጸር 95 በመቶ በማነስ ያሳያል፡፡

## አሣታፊ የደን አያያዝ ሥርዓት ተግባራዊ ማድረግ

በበጀት አመቱ 150,000 ሄክታር ደን በአሳታፊ የደን አያያዝና አስተዳደር ስርዓት እንዲጠበቅ ለማድረግ ታቅዶ 122,804.61 ሄክታር (82%) መሬት እንዲጠበቅ የተደረገ ሲሆን ከባለፈው ተመሳሳይ በጀት ዓመት አፈጻጸም ጋር ሲነጻጸር 20 በመቶ በማነስ ያሳያል፡፡

## የደን ንግድ ፈቃድ መስጠት

ለ415 ሰዎች የደን ምርት ውጤቶች የጅምላና ችርቻሮ ንግድ ፈቃድ ብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ለመስጠት ታቅዶ ለ30 ሰዎች የብቃት ማረጋገጫ በመስጠት 7% መፈጸም እንዲሁም ለ60 ነጋዴዎች የደን ምርት ውጤቶች የማምረት ፈቃድ እድሳት ለማድረግ ታቅዶ ለ229 (›100%) ነጋዴዎች እድሳት ተደርጓል፡፡በዕጣንና ሙጫ ማምረት ለመሰማራት ፈቃድ ለመውሰድ ጥያቄ ላቀረቡና መስፈርቱን አሟልተው ለተገኙ 21 ባለሀብቶችና 39 የተደራጁ ወጣቶች በድምሩ 60 ሰዎች ፈቃድ ተሰጥቷል፡፡

## የደን ውጤቶችን ወደ ገበያ ማቅረብ

በበጀት አመቱ 6,550 ኩንታል ዕጣን (ነጭ 4,913 እና ጥቁር 1,637) እንዲመረትና ወደ ገበያ እንዲቀርብ ለማድረግ ታቅዶ 6,908 ኩንታል ዕጣን (ነጭ 6,038 እና ጥቁር 770) ተመርቶ ለገበያ የቀረበ ሲሆን አፈጻጸሙ ›100% ነው፡፡ በተጨማሪም 6.5 ሚሊዮን ኩንታል ከሰል ከባህር ዛፍና ዲከረንስ ግራር በህጋዊ መንገድ ተመርቶ ወደ ገበያ እንዲቀርብ ለማድረግ በታቀደው መሠረት 2,700,792 ኩንታል (42%) ከሰል እንዲሁም 2,000 ኩንታል ሙጫ ለማምረት በዕቅድ ተይዞ 1,327 ኩንታል ሙጫ ተመርቶ በህጋዊ መንገድ ተንቀሳቅሷል፡፡አፈጻጸሙ 66% ነው፡፡



የዲከረንስ ደንን በማልማት የከሰል ምርት ማምረት-ጓጉሳ ሽኩዳድ ወረዳ)

## ከደን ሀብት ገቢ መሰብሰብ

ከተለያዩ የደን ምርት ውጤቶች የልማትና ሮያሊቲ ክፍያ ብር 250 ሚሊዮን ገቢ ለመሰብሰብ ታቅዶ ብር 97.4 ሚሊዮን ብር ገቢ እንዲሰበሰብ ተደርጓል፡፡አፈጻጸሙ 39% ሲሆን ከባለፈው ተመሳሳይ በጀት ዓመት አፈጻጸም ጋር ሲነጻጸር 57 በመቶ እንደቀነሰ ያሳያል፡፡ በህገ ወጥ መንገድ ተከማችቶና ሲዘዋወር የተገኘ የደን ምርት ውጤት ክትትልና ቁጥጥር በማድረግና በመውረስ 2.8 ሚሊዮን ብር ገቢ ለመሰባሰብ ታቅዶ 0.93 ሚሊዮን ብር ለመንግስት ገቢ የተደረገ ሲሆን አፈጻጸሙ 33% ነው፡፡ ለ140 ደኖች (120 የማህበረሰብ፣ 19 የማህበራት እና 1 የመንግስት) የደን ማኔጅመንት ፕላን በማዘጋጀት የደን አያያዝ ስርዓቱን ለማሻሻል ታቅዶ 15 የማህበረሰብ ደኖች እና 1 የማህበራት ደን በድምሩ ለ15 ደኖች የማኔጅመንት ፕላን በማዘጋጀት 11% መፈጸም ተችሏል፡፡

## በደን ዘርፍ ቋሚ የስራ ዕድል መፍጠር

በደን ዘርፍ ለ25,000 (ሴ- 10,000) ቋሚ የስራ እድል እንዲሁም ጊዜያዊ የሥራ ዕድል ለ225,000 (ሴ- 90,000) በድምሩ ለ250,000 (ሴ- 100,000) ሰዎች የሥራ ዕድል ለመፍጠር ታቅዶ በቋሚ ለ11,785 (ሴ- 2,122) እና በጊዜያዊ ለ71,143 (ሴ- 14,644) በድምሩ ለ82,928 (ሴ- 12,449) ሰዎች የሥራ ዕድል መፍጠር ተችሏል፡፡ አፈጻጸሙ 33% ሲሆን የሥራ ዕድል ከተፈጠረላቸው መካከል የወጣቶች ድርሻ 46,397 (ሴ 11,524) ነው፡፡ከደንና የደን ውጤቶች ጋር በተያያዘ በክልሉ የሚገኙ 795,000 (እማወራ 319,000) የህብረተሰብ ክፍሎችን የቤተሰብ ገቢ በአማካይ ከ5-10% ያህል ከደንና የደን ውጤቶች እንዲያገኙ ድጋፍ ለማድረግ ታቅዶ 170,150 (እማወራ 46,966) ሰዎች ገቢያቸው አድጓል፡፡ ክንውን 21% ሲሆን ከዚህ ውስጥ የወጣቶች ድርሻ 51,364 (ሴ- 17,186) ሆኗል፡፡

## የዱር እንስሳት ጥብቅ ስፍራችን ማልማት

የዱር እንስሳት ጥብቅ ስፍራዎችን ማልማትና የህብረተሰቡን ተጠቃሚነት ከማረጋገጥ አኳያ በጥብቅ ስፍራዎች የሚገኘው 2,000 ሄክታር የተራቆተና የተጎዳ መሬት እንዲያገግምና እንዲለማ ለማድረግ ታቅዶ 2,007 ሄክታር መሬት እንዲያገግም ተደርጓል፡፡ ይህም በአቡነዮሴፍ፣ አባይ ሚሊኒየም እና ጉና ጥብቅ ስፍራዎች የተከናወነ ሲሆን አፈጻጸሙ 100% ነው፡፡ በጥብቅ ስፍራዎች በየወሩ የዱር እንስሳት በሽታ ቅኝትና ክትትል 96 ጊዜ ለማከናወን ታቅዶ በመንዝ፣ አቡነዮሴፍ እና ቦረና ሣይንት 72 ጊዜ የተከናወነ ሲሆን አፈጻጸሙ 75% ነው፡፡ በዱር እንስሳት ጥብቅ ስፍራዎች አካባቢ የሚኖሩ 4,000 (ሴ- 1,750) ሰዎች በተለያዩ የልማት ሥራዎች ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ ታቅዶ 6,872 (ሴ

2,073) (›100%) ሰዎች በፍራፍሬ ልማት፣ በንብ ማነብ፣ በሣር ሽያጭ፣ በግንባታና በመሳሰሉት ተጠቃሚ የሆኑ ሲሆን የወጣቶች ድርሻ 2,473 (ሴ- 869) ነው፡፡



የዱር እንስሳት ጥበቃና ልማት

## በጥብቅ ስፍራዎች የጎብኝዎችን ቁጥር ማሳደግ

በጥብቅ ስፍራዎች የጎብኝዎችን ቁጥር 40,000 (ሴ- 15,000) ለማድረስ ታቅዶ 439 (ሴ- 156) የአገር ውስጥና የውጭ ቱሪስቶች በጮቄ፣ ጎደቤ፣ አቡነዮሴፍ ጥብቅ ስፍራዎች ተገኝተው ጎብኝተዋል፡፡አፈጻጸሙ ዝቅተኛ (1%) ሲሆን የወጣቶች ድርሻ 102 (ሴ- 24) ነው፡፡አፈጻጸሙ ከባለፈው ተመሳሳይ በጀት ዓመት አፈጻጸም ጋር ሲነጻጸር በ84 በመቶ እንደቀነሰ የሚያሳይ ሲሆን ለአፈጻጸሙ መቀነስ በጸጥታው ችግር የጎብኝዎች ቁጥር በመቀነሱ እንደሆነ በምክንያትነት ተቀምጧል፡፡ በጥብቅ ስፍራዎች ከኢኮ ቱሪዝም፣ ከፊልምና ሌሎች አገልግሎቶች 1.2 ሚሊዮን ብር ገቢ ለመሰብሰብ በታቀደው መሠረት ብር 2,836,775 መሰብሰብ ተችሏል፡፡ አፈጻጸሙ ከ100% በላይ ነው፡፡ በሁሉም የዱር እንስሳት ጥብቃ ስፍራዎች 750,000 ሰው/ስዓት አሰሳና ቅኝት ሥራ ለማከናወን ታቅዶ 390,050 ሰው/ስዓት የአሰሳና ቅኝት ሥራ ተከናውኗል፡፡ አፈጻጸሙ 52% ነው፡፡



የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገር ጎብኝዎች የጮቄ ተራራን ሲጎበኙ-ምስራቅ ጎጃም

### በአካባቢና ብዝሃ ህይወት ሀብት ላይ ሊከሰት የሚችለውን ጉዳት መቀነስ

በአካባቢና ብዝሃ ህይወት ሀብት ላይ ሊከሰት የሚችለውን ጉዳት ለመቀነስ 180,000 ሄክታር መጤ ወራሪ ዝርያዎችን ለማስወገድ ታቅዶ 75,305.26 ሄክታር መጤና ወራሪ አረም ዝርያዎችን በማስወገድ 42% መፈጸም የተቻለ ሲሆን አረም በማስወገድ 750,000 (ሴ- 375,000) ሰዎች በዘመቻ እንዲሳተፉ ለማድረግ ታቅዶ 686,904 (ሴ- 254,348) የህብረተሰብ ክፍሎች ተሣትፈዋል፡፡ ክንውኑ ከ92% ሲሆን ከተሳታፊዎች መካከል 461,527 (ሴ- 155,322) ወጣቶች ናቸው፡፡በሌላ በኩል የውሃማ አካልና ዉሃ አዘል መሬት ስርዓተ ምህዳሮችን ደህንነት መጠበቅ በሚመለከት በጣና ቁርቆስ ገዳም አካባቢ የሚገኘውን የእንቦጭ አረም ህብረተሰቡን በማሳተፍ ለ22 የስራ ቀናት አንድ የማስወገጃ ማሽን በመጠቀም 9,900 ሜትር ኩብ አረም ማስወገድ ተችሏል፡፡ በአጠቃላይ በደቡብ ጎንደር፣ ማዕከላዊ ጎንደርና ባህር ዳር ከተማ 413.46 ሄክታር የእምቦጭ አረም ማስወገድ የተቻለ ሲሆን በስራውም 15,118 (ሴ- 3,405) ሰዎች በዘመቻ ተሳትፈዋል፡፡

## የኢንዱስትሪእና ኢንቨስትመንት ልማት

### *በክልሉ ኢኮኖሚ የኢንዱስትሪው ድርሻ*

የክልላችንን ኢንዱስትሪ ለክልሉ ኢኮኖሚ በአማካይ የ44.92 ቢሊየን ብር እሴት ጭማሪ ወይም ደግሞ የ15% ድርሻ አለው፡፡ በክልላችን አምራች ኢንዱስትሪው ከኮንስትራክሽን ዘርፉ ቀጥሎ ለኢንዱስትሪው እሴት ጭማሪ ማድረግ አስተዋፅኦ እያደረገ የሚገኝ ዘርፍ ነው፡፡ዘርፉ በአማካይ ከ18.92 ቢሊየን ብር በላይ እሴት ጭማሪ ለኢንዱስትሪው በማበርከት ላይ ይገኛል፡፡ከአጠቃላይ ኢኮኖሚው በአማካይ የ6.2 በመቶ ድርሻ ያለው ይህ ዘርፍ ከኢንዱስትሪው እሴት ጭማሪ መካከል የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪው በአማካይ የ42 በመቶ ድርሻ ያለው መሆኑን አመታዊ የጥቅል ምርት ግመታ መረጃ ያመለክታል፡፡



አባይ የምግብ ፋብሪካ ሲጎበኝ

## በክልሉ ኢንቨስትመንት ፍሰቱን ማሳደግ

የክልሉን ፀጋዎች በማስተዋወቅ የኢንቨስትመንት ፍሰቱን ለማሳደግ በተሰራው ስራ በራሳቸው ተነሳሽነት የሚመጡትን ባለሃብቶችን ጨምሮ በተለያዩ ስልቶች ፕሮሞት በማድረግ 4,200 ባለሀብቶችን አዲስ የኢንቨስትመንት ፈቃድ እንዲያወጡ ለማድረግ ታቅዶ 437 ቢሊየን ብር ካፒታል ያስመዘገቡ እና ወደ ስራ ሲገቡ ለ532,411 ዜጎች የስራ እድል ሊፈጥሩ የሚችሉ 2,650 ባለሃብቶች የኢንቨስትመንት ፈቃድ እንዲያወጡ የተደረገ ሲሆን አፈፃፀሙ 63% ሆኗል፡፡በተመሳሳይ የኢንቨስትመንት ፈቃድ ዕድሳት በበጀት ዓመቱ ማሳደስ ያለባቸውን ፕሮጀክቶች መረጃ በመለየትና በማደራጀት በተለያዩ መንገዶች በመቀስቀስ 4,414 ባለሀብቶች ፈቃዳቸውን እንዲያሳድሱ ለማድረግ ታቅዶ 3,215 (72.8%) ፕሮጀክቶች ፈቃዳቸው ታድሷል፡፡ እንዲሁም ካሁን በፊት ፈቃድ ለወሰዱ ባለሃብቶች 66 ትክ እና 58 ለውጥ የኢንቨስትመንት ፈቃድ አገልግሎት መስጠት ተችሏል፡፡

በ2016 ዓ.ም በተመረጡና አዋጭ በሆኑ የኢንቨስትመንት ዘርፎች ኢንቨስት የሚያደርጉ አቅምና ፍላጎት ያላቸውን ባለሀብቶች በመለየት ከመመልመል አንጻር 730 ነባር፣ 5,223 አዳዲስ፣ 285 ዲያስፖራ ባለሃብቶችንና 297 ሞዴል አርሶ አደሮችን በአጠቃላይ 6,535 አቅም ያላቸውን ባለሃብቶች ለመለየትና ለመመልመል ታቅዶ 747 ነባር፣4,297 አዳዲስ፣176 ዲያስፖራ ባለሃብቶችንና 158 ሞዴል አርሶ አደሮችን በአጠቃላይ 3,164 (51.7%) አቅም ያላቸውን ባለሃብቶች ለመለየትና ለመመልመል ተችሏል፡፡

## ለኢንዱስትሪ ቀጠናዎች ለተለያዩ ፕሮጀክቶች የሚውል መለየት

በሁሉም ኢንዱስትሪ ቀጠናዎች ለተለያዩ ፕሮጀክቶች አገልግሎት የሚውል በሳይት ፕላን የተመላከተ መሬት ከ3ኛ ወገን ነጻ ማድረግ 1,400 ሄክታር መሬት ነጻ ለማድረግ ታቅዶ ክንውን 556.41(39.6%) መፈፀም የተቻለ ሲሆን ከአምራች ኢንዱስትሪው ውጭ ለሆኑ ሌሎች የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች መሬት በማዘጋጀት ከ3ኛ ወገን እንዲፀዳ በማድረግ በአጠቃላይ በግብርና፤በሆርቲካልቸርና በአገልግሎት ዘርፍ 8,473.841 ሄክታር መሬት በሳይት ፕላን በማመላከትና 7,747.141 ሄክታር መሬት ከሦስተኛ ወገን ለማፅዳት ታቅዶ 16,569.09 ሄክታር መሬት በሳይት ፕላን በማመላከት 14,758.705 (100%) ሄክታር መሬት ከሶስተኛ ወገን በማጽዳትና በካሳ ክፍያ ለባለሃብቶች ለማመቻቸት ተችሏል፡፡ በተመሳሳይ ተገምግመው ላለፉ

ፕሮጀክቶች መሬት ማስተላለፍን በተመለከተ በበጀት ዓመቱ ለ724 ፕሮጀክቶች መስሪያ ቦታ ለማስተላለፍ ታቅዶ ለ309 ፕሮጀክቶች 337.44 ሄክታር መሬት ማስተላለፍ ተችሏል፡፡

## የአምራች ኢንዱስትሪ ፕሮጀክቶችን ወደ ስራ ማስገባት

የአምራች ኢንዱስትሪ ፕሮጀክቶችን ወደ ስራ ለማስገባት በተደረገው ጥረት ወደ ግንባታ ማስገባት ዕቅድ 534፣ክንውን 212 (39.7%)፣ግንባታ ማጠናቀቅ ዕቅድ 300፣ክንውን 140 (46.6%) እንዲሁም ወደ ማምረት የገቡ ፕሮጀክቶች ዕቅድ 218፣ክንውን 122 (55.9%) ማከናወን ተችሏል፡፡በሌላ በኩል ክፍት በሆኑ የመስሪያና መሸጫ ወለሎች ኢንተርፕራይዞችን ማስገባትን በተመለከተ ኢንተርፕራይዞች ከአሁን በፊት ተገንብተው ክፍት በሆኑት እና በተለቀቁት ላይ 100% ለማስተላለፍ ታቅዶ ክፍት በነበሩ 23 ሸዶች ኢንተርፕራይዞችን ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡

## ለረጅም ጊዜ ቦታ አጥረው የተቀመጡ ፕሮጀክቶችን ወደ ስራ ማስገባት

በአምራች ኢንዱስትሪው እና በሌሎች የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶችን ለረጅም ጊዜ ቦታ አጥረው የተቀመጡ ፕሮጀክቶችን በጥናት በመለየት ወደ ስራ እንዲገቡ ከመደገፍ ጋር በተገናኘ በአምራች ኢንዱስትሪው ዘርፍ ተሰማርተው የተለያዩ ድጋፍ ተደርጎላቸው ወደ አፈጻጸም ባልገቡት 70 ፕሮጀክቶች ላይ የማስጠንቀቂያና መሬት የመንጠቅ እርምጃ የተወሰደባቸው ሲሆን መሬት የተነጠቁት 49 ፕሮጀክቶች 152.2585 ሄክታር መሬት የተነጠቀ ሲሆን ከአምራች ኢንዱስትሪው ዘርፍ ውጭ የሆኑ ለረጅም ጊዜ መሬት አጥረው የተቀመጡ እና ከታለመለት ዓላማ ውጭ ያዋሉ 35 የግብርና፣31 ሆልቲካልቸር እና 91 የአገልግሎት ሰጭ ፕሮጀክቶች በድምሩ በ157 የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች እርምጃ ለመውሰድ ታቅዶ ከ4 ፕሮጀክቶች 652.2455 ሄክታር መሬት በመንጠቅ ወደ መሬት ባንክ ገቢ ማድረግ ተችሏል ፡፡

## ለአምራች ኢንዱስትሪዎችን የመሰረተልማት ችግር መፍታት

በምርት ላይ ያሉ አምራች ኢንዱስትሪዎችን የመሰረተልማት ችግር ለመፍታት በተመለከተ የአምራች ኢንዱስትሪዎችን ምርታማነት በመጨመር የማምረት አቅማቸውን ለማሳደግ ያለባቸውን የመሰረተ ልማት ችግር በሚፈልጉት መጠንና ጥራት ማሟላት የሚያስፈልግ ሲሆን አነስተኛ 327፣መካከለኛ 170 እና ከፍተኛ 90 በድምሩ የ587 ምርት ላይ ያሉ አምራች ኢንዱስትሪዎችን የመሰረተ ልማት

ችግር ለመፍታት ታቅዶ አነስተኛ 137፣መካከለኛ 104፣ከፍተኛ 58 በድምሩ 299 (50.9%) ለሚሆኑ አምራች ኢንዱስትሪዎች የመሰረተ ልማት ችግር መፍታት ተችሏል፡፡

በተጨማሪም ከአምራች ኢንዱስትሪው ውጭ ላሉ ለሌሎች የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች የመሰረተልማት ችግር መፍታትን በሚመለከት በዞን፣በከተማ አስተዳደሮች እና በባለሃብቶች ቅንጅት ምርት/ አገልግሎት ለጀመሩ 524 የግብርና፣87 ሆርቲካልቸር እና 1,083 ለአገልግሎት ሰጭ ፕሮጀክቶች በድምሩ 1,672 ፕሮጀክቶች የመንገድ፤የመብራት (3 ፌዝ ቆጣሪ፣ፖል፣ትራንስፎርመርና የሃይል አቅርቦት)፤የውሀ እና የቴሌ መሰረተ ልማት ችግሮችን በመለየት ለመፍታት ታቅዶ ለ344 (20.5%)ፕሮጀክቶች የመሰረተልማት ችግር መፍታት ተችሏል፡፡በሌላ በኩል የአምራች ኢንዱስትሪዎች እና ሌሎች የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶችን የፋይናንስ አገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለመደገፍ በተሰራው ስራ150 በፕሮጀክት ላይ ያሉ የአምራች ኢንዱስትሪ ፕሮጀክቶችን የሊዝ ፋይናንስ ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ 80 (53.3%) ፕሮጀክቶችን ተጠቃሚ ማድረግ የተቻለ ሲሆን የተጠቀሙት የብድር መጠን ብር 2.498 ቢሊየን ነው፡፡በተመሳሳይ 230 ፕሮጀክቶች የፕሮጀክት ፋይናንስ ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ 99 (40%) ፕሮጀክቶች ተጠቃሚ ሲሆኑ የተጠቀሙት የብድር መጠን እቅድ 15.55 ቢሊየን ክንውን (92.6%) ቢሊየን ብር ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡በተመሳሳይ ምርት ላይ ላሉ አምራች ኢንዱስትሪዎች የሊዝ ፋይናንስ ችግር በመለየት የብድር ተጠቃሚ እንዲሆኑ መደገፍ ተችሏል፡፡

በበጀት ዓመቱ 226 አነስተኛና 89 መካከለኛ በድምር 315 አምራች ኢንዱስትሪዎችን የሊዝ ፋይናንስ ችግር ለመፍታት ታቅዶ 270 አነስተኛ፣መካከለኛ 129 በድምሩ ለ399 (100%) አምራች ኢንዱስትሪዎች የሊዝ ፋይናንስ ችግር የተፈታ ሲሆን ተጠቃሚነት በብር 599.76 ሚሊየን ብር ለማስጠቀም ታቅዶ 1.259 (100%) ቢሊየን ብር የሊዝ ፋይናንስ ብድር ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡

ሌሎች የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶችን የፋይናንስ አገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆኑ መደገፍ በሊዝ ፋይናንስ ተጠቃሚ የሆኑ ፕሮጀክቶች በሚመለከት በበጀት ዓመቱ በግብርናና ሆርቲካልቸር ፕሮጀክት ተጠቃሚ የሆኑ 65 ፕሮጀክቶች ሲሆኑ 2.0599 ቢሊዮን ብር ተጠቃሚ ሲሆኑ የስራ ማስኬጃ ብድር ለ2 የግብርና ፕሮጀክት 0.004 ቢሊዮን ብር እና ለ24 የአገልግሎት ፕሮጀክቶች የ 0.41175 ቢሊዮን ብር በድምሩ 26 ፕሮጀክት 0.41575 ቢሊዮን ብር ተጠቃሚ እንዲሆኑ ተደርጓል፡፡ በተጨማሪም የአምራች ኢንዱስትሪዎችን አማካይ የማምረት አቅም

ከ56.04 ወደ 73% ለማሳደግ ግብ ተይዞ በበጀት ዓመቱ የአምራች ኢንዱስትሪዎችን የማምረት አቅማቸውን ለማወቅ ካሉት አምራች ኢንዱስትሪዎች ውስጥ በሁሉም ዘርፍ 50 ፐርሰንቱን የማምረት አቅም በመለካት የደረሱበትን የማምረት አቅም 2015 በጀት አመት ከነበረው ከ56.04 ወደ 73% ለማድረስ እየተሰራ ይገኛል፡፡ በዚህ መሠረት በጀት ዓመቱ የ1,219 አነስተኛ፣ የ427 መካከለኛና የ186 ከፍተኛ በድምሩ 1,832 ኢንዱስትሪዎችን ለመለካት ታቅዶ የ584 አነስተኛ፣የ179 መካከለኛና የ78 ከፍተኛ በድምሩ 841 ኢንዱስትሪዎችን የማምረት አቅም የተለካ ሲሆን አፈጻጸሙ 45.9% በመሆኑም የኢንዱስትሪዎችን የማምረት አቅም ማወቅ አለመቻሉን ያሳያል፡፡

መካከለኛና ከፍተኛ ኢንዱስትሪዎችን ከዩኒቨርሲቲዎች ጋር አነስተኛ ኢንዱስትሪዎችን ከቴክኒክ ሙያ ኮሌጆች ጋር ትስስር እንዲፈጥሩ በማድረግ የክህሎት ችግሮቻቸውን በመፍታት የማምረት አቅማቸውን ከፍ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ስለሆነም የአምራች ኢንዱስትሪዎችን የማምረት አቅማቸውን ለማሳደግ የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት የድጋፍ ማዕቀፎች መስጠት ወሳኝ ጉዳይ በመሆኑ በበጀት ዓመቱ ለ1,153 አነስተኛ፣ ለ427 መካከለኛና ለ165 ከፍተኛ በድምሩ ለ1,745 ኢንዱስትሪዎች ኤክስቴንሽን አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ ለ838 አነስተኛ፣ ለ288 መካከለኛ እና ለ76 ከፍተኛ በድምር ለ1,202 (68.3%) ኢንዱስትሪዎች የኤክስቴንሽን አገልግሎት መስጠት ተችሏል፡፡

## ኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች የግብዓት አቅርቦት ችግር መፍታት

በአምራች ኢንዱስትሪዎች መካከል እርስ በእርስ በተፈጠረ ትስስር ተጠቃሚ ለማድረግ በተሰራ ስራ ለ128 አነስተኛ፣ ለ79 መካከለኛ፣ለ37 ከፍተኛ በድምሩ ለ244 አምራች ኢንዱስትሪዎች የ295.79 ሚሊየን ብር፤55,137 ቶን ግብዓት በማቅረብ የአምራች ኢንዱስትሪዎችን የግብዓት ችግር ለመፍታት ታቅዶ የ30.386 ቢሊየን ብር 29,028.28 ቶን በማቅረብ ለ79 አነስተኛ፣ ለ35 መካከለኛ እና ለ24 ከፍተኛ በድምሩ ለ138 አምራች ኢንዱስትሪዎች የግብዓት ችግርን ለመፍታት የተቻለ ሲሆን አፈጻጸሙ በኢንዱስትሪ ቁጥር 56.6% በግብዓት መጠን 52.6% ማከናወን ተችሏል፡፡ በተጨማሪም ከትስስር ውጭ ማለትም ከግብዓት አቅራቢዎች፣ ከነጋዴዎች እና ከአምራቾች በሚገኝ ግብዓት በበጀት ዓመቱ ለ296 አነስተኛ፣ ለ185 መካከለኛ እና ለ91 ከፍተኛ በድምሩ ለ572 አምራች ኢንዱስትሪዎች የ3.3 ሚሊየን ብር ፤149,004 ቶን ግብዓት በማቅረብ የአምራች ኢንዱስትሪዎችን የግብዓት ችግር ለመፍታት ታቅዶ የ13.447 ቢሊየን ብር፤ 349,534.21 ቶን በማቅረብ ለ164 አነስተኛ፣ ለ79 መካከለኛ እና ለ48 ከፍተኛ

በድምሩ ለ294 አምራች ኢንዱስትሪዎች የግብዓት ችግርን ለመፍታት የተቻለ ሲሆን አፈጻጸሙም በኢንዱስትሪ ቁጥር 51.4% በግብዓት መጠን 100% መፈጸም ተችሏል፡፡

## የአምራች ኢንዱስትሪዎች የደረጃ ሽግግር መስራት

ከአነስተኛ ወደ መካከለኛ ደረጃ 51፣ ከመካከለኛ ወደ ከፍተኛ 33 በድምሩ 84 ኢንዱስትሪዎች ሽግግር ለመስራት ታቅዶ ከአነስተኛ ወደ መካከለኛ ደረጃ 21፣ ከመካከለኛ ወደ ከፍተኛ ደግሞ 1 በድምሩ 22 (26.2%) አምራች ኢንዱስትሪዎች ተሸጋግረዋል፡፡

በአምራች ኢንዱስትሪዎች እና በሌሎች የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ከሚገኑ ምርቶች የሚገኝ የኤክስፖርት ገቢን ለማሳደግ ለነባርና በአዲስ ምርታቸውን ወደ ውጭ የሚልኩ አምራች ኢንዱስትሪዎችን ሁለንተናዊ ድጋፍ በማድረግ እና ተጨማሪ አቅም በመፍጠር ምርታቸውን ወደ ውጭ እንዲልኩ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ የኤክስፖርት ገቢን የማሳደግ ስራ እየተሰራ ይገኛል፡፡ በዚህም በነባር አነስተኛ 1 ፣መካከለኛ 7፣ከፍተኛ 32 በድምሩ ከ40 ነባር አምራች ኢንዱስትሪዎች 73,713 ቶን በመላክ 117.71 ሚሊዮን ዶላር የውጭ ምንዛሬ ለማግኘት ታቅዶ አነስተኛ 1፣መካከለኛ 10፣ከፍተኛ 27 በድምሩ 38 አምራች ኢንዱስትሪዎች 137,741.4021 ቶን በመላክ 134.658 ሚሊዮን ዶላር የውጭ ምንዛሬ ማግኘት የተቻለ ሲሆን በነባር ሆርቲካልቸር (የአበባ፣አትክልት፤ፍራፍሬ) ወደ ውጭ ምርታቸውን የሚልኩ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ብዛት ዕቅድ 8 ሲሆን ክንውን 9 ሆኗል፡፡ 3,000 ቶን ምርት ለመላክ ታቅዶ 2,787.046 ቶን ምርት በመላክ 15.182 ሚሊየን ዶላር የተገኘ ሲሆን በአጠቃላይ 140,528.4481 ቶን በመላክ 149.84 (100%) ሚሊየን ዶላር ገቢ ማግኘት ተችሏል፡፡

## የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶችን የሀገር ውስጥ የገበያ ድርሻ ማሳደግ

በ2016 ዓ.ም 501 ተኪ ምርት የሚያመርቱ አምራች ኢንዱስትሪዎችን በመለየትና በመደገፍ 68 አይነት ተኪ ምርቶች በማምረት በ204,806 ቶን ምርት 279.88 ሚሊዮን ዶላር የውጭ ምንዛሬን ለማስቀረት/መተካት/ ታቅዶ 355 አምራች ኢንዱስትሪዎችን በመለየትና በመደገፍ 77 አይነት ምርቶች እንዲመረቱ በማድረግ 564,132.24 ቶን ምርት ላይ 1.19664 ቢሊየን ዶላር የውጭ ምንዛሬን መተካት/ማስቀረት/ ተችሏል፡፡አፈጻጸሙ በተኪ ምርት እና በገቢ መጠን 100% ነው፡፡



በኪ. የመኪና መገጣጠሚያ ፋብሪካ -ደብረ ብርሃን

# ግብርና ምርምር

## የምርምር ሙከራዎችን ማከናወን

በግብርና ምርምር ዘርፍ 628 ሙከራዎችን ለመስራት ታቅዶ 526 (84%) የተከናወነ ሲሆን በሰብል 257፤ በእንስሳት 141፤ በአፈርና ውሃ ምርምር 61፤ በደን 44፤ በምግብ ሳይንስ 10 ፣ በዘር 7 እና በማህበራዊ ምጣኔ ሀብት ምርምር 17 የምርምር ሙከራዎች ማከናወን ተችሏል፡፡በሌላ በኩል በሰብል ምርምር ዘርፍ በመኸር 288 እና በመስኖ 42 በድምሩ 330 የምርምር ስራዎች ለማከናወን ታቅዶ በመኸር 223፣ በመስኖ 30 በድምሩ 253 (77.8%) ማከናወን ተችሏል፡፡ በክልሉ በተፈጠረው የፀጥታ ችግር ምክንያት በደብረ ብርሃን ግብርና ምርምር ማዕከል 17 ሙከራዎች፣ ጎንደር ግብርና ምርምር ማዕከል 7 ሙከራዎች፣ በአዴት ግብርና ምርምር ማዕከል 39 ሙከራዎች እና 3 በስሪንቃ ግብርና ምርምር ማዕከል ሙከራዎች ባለመከናወናቸው አፈጻጸሙን ዝቅ እንዲል አድርጎታል፡፡ በበጀት ዓመቱ መጨረሻ 37 ቴክኖሎጂዎች/ ምክረሃሳቦች ለማውጣት ታቅዶ ከዚህ በታች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

## በ2016 ዓ.ም የተሻሻሉ ዝርያዎች ያስለቀቁ ተመራማሪዎች

| የሰብል አይነት እና የዝርያው ስም | የዝርያው ዝርዝር መግለጫ | ያስለቀቀው ተመራማሪ ስም |
|---|---|---|
| ማሽላ-ፀሐይ | ይህ ፀሐይ (ETSC15350-2-2 — white reddish seed color) የተሰኘው የማሽላ ዝርያ- በጎንደር ግብርና ምርምር ማዕከል የተለቀቀ በሽታንና ተባይን (stem borer) መቋቋም የሚችል፣ በመካከለኛ ደረጃ የሚደረስ (medium maturity)፣ የቅጠሉን አረንጓዴነት ጠበቆ የሚቆይ (stay green leaf)፣ የ1000 የዘር ክብደቱ የተሸለ (32.43 ግራም)፣ በአርሶ አደሮች ተመራጭ የሆነና የተሻለ ምርት መስጠት የሚችል የማሽላ ዝርያ በ2016 ተለቋል፡፡ በሄክታር 41.48 ኩንታል ምርት የሚሰጥና ከተሻሻለው ማወዳደሪያ ዝርያ (Melkam, 32.86 ኩንታል /ሄክታር፣ የ1000 የዘር ክብደት 26.56 ግራም) በ26% የምርት ብልጫ ያለዉ በመሆኑ በመተማ፣ ጠገዴ እና ተመሳሳይ ቦታወች መመረት የሚችል መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ | አቶብርሃኑ ፈንታሁን |

| | | |
|---|---|---|
| ማሽላ- በለጠው II | በለጠው II [(ETSC 300552 (Teshale X E36-1) (BC3F3)] የተሰኘው የማሽላ ዝርያ- በደብረ ብርሃን ግ/ም/ማዕከል በሽታን መቋቋሞ የሚችል (leaf diseases)፣ ፈጥኖ በመድረስ ድርቅን መቋቋም የሚችል፣ ትልቅ የዘለላ ርዝማኔ (larger panicle length)፣ ነጭ የዘር ቀለም ያለው፣ የቅጠሉን አረንጓዴነት ጠበቆ የሚቆይ (stay green leaf) እና በአርሶ አደሮች ተመራጭ የሆነና የተሻለ ምርት መስጠት የሚችል የማሽላ ዝርያ በ2016 ተለቋል፡፡ በሄክታር 52.1 ኩንታል ምርት የሚሰጥና ከተሻሻለው ማወዳደሪያ ዝርያ (Beletew, 40.6 ኩንታል/ሄክታር) በ28% የምርት ብልጫ ያለው በመሆኑ በቆቦ፣ ሸዋሮቢት፣ ጃማ እና ተመሳሳይ ቦታወች መመረት የሚችል መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ዝርያው አሲዳማነትን ተቋቁሞ የተሻለ ምርት የሚሰጥ በመሆኑ በክልሉ በአሲዳማነት የተጠቃውን ከ1.6 ሚሊዮን በላይ ማሳ ወደ ምርት ለመመለስ ትልቅ ተስፋ ተጥሎበታል፡፡ |  አልታዬ ጥሩነህ  አዕምሮ ዋለ(ዶ/ር)  ሹመት ጫቅሌ |

| | | |
|---|---|---|
| በቆሎ- ውቅር | ውቅር((DT STR-Y SYN — OPV) የተሰኘ የበቆሎ ዝርያ የሰቆጣ ግ/ም/ማዕከል ከ BETin ጋር በመተባበር ድርቅን እና የአቀንጭራን ጉዳት ተቋቁሞ የተሻለ ምርት መስጠት የሚችል የበቆሎ ዝርያ በ2016 ተመዝግቧል፡፡ በሄክታር 45.42 ኩንታል ምርት የሚሰጥና vitamin A content (1.29 mgkg-1) ከተሻሻለው ማወዳደሪያ ዝርያ (Melkasa 6Q, 42.02 ኩንታል/ሄክታር፣ vitamin A content = <1 mgkg-1) በ8% የምርት ብልጫና ቢያንስ በ29%vitamin A content ብልጫ ያለው በዋግምራ፣ ላሲበላ፣ ስሪንቃ፣ ቆቦ፣ በለሳ፣ እብናት እና ተመሳሳይ ቦታወች መመረት የሚችል መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ |  ክንዳለም ያረጋል  ፕሮፌሰር ካሳሁን ተስፋዬ  ዶ/ር አሎ አማን |
| በቆሎ- ሮሃ | ሮሃ(PVA SYN 13 - Biofortified — OPV) - የሰቆጣ ግ/ም/ማዕከል ከ BETin ጋር በመተባበር ድርቅን መቋቋም የሚችልና በንጥረ ነገር ይዘቱ (Biofortified, vitamin A) የተሻለ፣ ተባይና በሽታን መቋቋም የሚችል የበቆሎ ዝርያ በ2016 ተመዝግቧል፡፡ በሄክታር 42.74 ኩንታል ምርት የሚሰጥና vitamin A content (1.46 mgkg-1) ከተሻሻለው ማወዳደሪያ ዝርያ (Melkasa 6Q, 42.02 ኩንታል/ሄክታር,vitamin A content = <1 mgkg-1) ጋር ሲነጻጸር በ vitamin A content ቢያንስ የ46% ብልጫ ያለዉ ሲሆን፣ ቀይ የዘር ቀለም ያለዉ፣ በእሸቱ እና ተቀቅሎ |  ክንዳለም ያረጋል  ፕሮፌሰር ካሳሁን ተስፋዬ  ዶ/ር አሎ አማን |

| | | |
|---|---|---|
| | ለመብላት ተመራጭ የሆነ ዝርያ በዋገምራ፣ ሳሊበሳ፣ ስሪንቃ፣ ቆቦ፣ በለሳ፣ እብናት እና ተመሳሳይ ቦታወች መመረት የሚችል መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ | |
| በቆሎ-አበበ | አበበ(EARLY WHITE — OPV) - የሰቆጣ ግ/ም/ማዕከል ከ BETin ጋር በመተባበር ድርቅን መቋቋሞ የሚችልና የተሻለ ምርት መስጠት የሚችል የበቆሎ ዝርያ በ2016 ተመዝግቧል፡፡ በሄክታር 48.88 ኩንታል ምርት የሚሰጥና ከተሻሻለው ማወዳደሪያ ዝርያ (Melkasa 6Q, 42.02 ኩንታል/ሄክታር) በ16% የምርት ብልጫ ያሳየ፣ ነጭ የዘር ቀለም ያለውና ለእንጀራ ጥቅም እንዲውል በአርሶ አደሮች የተመረጠ በመሆኑ በዋገምራ፣ ሳሊበሳ፣ ስሪንቃ፣ ቆቦ፣ በለሳ፣ እብናት እና ተመሳሳይ ቦታወች መመረት የሚችል መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ |  ክንዳለም ያረጋል  ፕሮፌሰር ካሳሁን ተስፋዬ  ዶ/ር አሎ አማን |
| አኩሪ አተር-ጠረፍወርቅ | ጠረፍወርቅ(TGX-1990-47f) የተሰኘ በጎንደር ግ/ም/ማዕከል በሽታን መቋቋም የሚችል (rust, leaf blotch & leaf spot)፣ ትልልቅ የዘር መጠን (large seeded) ያለው፣ የተሻለ | ጎበዜ ጨቅሌ |

| | | |
|---|---|---|
| | ምርት መስጠት የሚችል እና የፕሮቲን ንጥረ ነገር ይዘቱ የተሸለ የአኩሪ አተር ዝርያ በ2016 ዓ.ም ተለቋል፡፡ በሄክታርር 26.75 ኩንታል ምርት የሚሰጥና የፕሮቲን ይዘቱ (41.9%) ከተሻሻለው ማወዳደሪያ ዝርያ (SCS-1, 17.41 ኩንታል/ሄክታር ምርት፣ 39.9% የፕሮቲን ይዘት) በ54% የምርት ብልጫ ያለው በመሆኑ በመተማ፣ ምዕራብ አረማጭሆ፣ ጃዊ እና ተመሳሳይ ቦታወች መመረት የሚችል መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ | |
| ሽንብራ-ጣና | ጣና(DZ-2012-CK-0291 — kabuli type) - በጎንደር ግ/ም/ማዕከል በሽታን መቋቋም የሚችል (wilt & root rot)፣ ነጭ የዘር ቀለም ያለው፣ በአርሶ አደሮች ተመራጭ የሆነና የተሻለ ምርት መስጠት የሚችል የሽምብራ ዝርያ በ2016 ተለቋል፡፡ በሄክታር 21.72 ኩንታል ምርት የሚሰጥ ከተሻሻለው ማወዳደሪያ ዝርያ (Asnakew, 15.43 ኩንታል/ሄክታር) በ41% የምርት ብልጫ ያለው በመሆኑ በከፍተኛና መካከለኛ ቦታዎች (ዳባት፣ ወገራ፣ ጎንደር ዙሪያ፣ ድንቢያ፣ ጣቁሳ) እና ተመሳሳይ ቦታዎች መመረት የሚችል መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ | አንተነህ አደባባይ  |
| ጥቁር አዝሙድ-ጤና | ጤና-(Moyale-230777) - በጎንደር ግ/ም/ማዕከል በአርሶ አደሮች ተመራጭ የሆነና የተሻለ ምርት መስጠት የሚችልና ጥራቱ የተሻለ የጥቁር አዝሙድ ዝርያ በ2016 ተለቋል፡፡ በሄክታር 9.05 ኩንታል ምርት የሚሰጥ፣ Oleoresin content 48.7% እና ከተሻሻለው ማወዳደሪያ ዝርያ (Aden, 6.28 | አቶ አዘዘ ውቤ  |

| | | |
|---|---|---|
| | ኩንታል/ሄክታር፣ Oleoresin content 36%) በ44% የምርት እና Oleoresin content 35% ብልጫ ያለዉ በመሆኑ አዝሙድ አብቃይ መካከለኛ ከፊታ ባላቸዉ አካባቢዎች (ጣቁሳ፣ ደነቢያ) እና ተመሳሳይ ቦታወች መመረት የሚችል መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ | |
| ድንች-ተስፋ | ተስፋ(CIP-313020.31) - በአዴት ግ/ም/ማዕከል በሽታን መቋቋም የሚችል፣ በአርሶ አደሮች ተመራጭ የሆነና የተሻለ ምርት መስጠት የሚችል የድንች ዝርያ በ2016 ተለቋል፡፡ በሄክታር 424.65 ኩንታል ምርት የሚሰጥና ከተሻሻለው ማወዳደሪያ ዝርያ (Worku, 310.10 ኩንታል/ሄክታር) በ37% የምርት ብልጫ ያለው በመሆኑ ድንች አብቃይ በሆኑ ሰሜን ምዕራብ ኢትዮጵያ፣ መካከለኛዉ ኢትዮጵያ፣ አርሲ እና ተመሳሳይ ቦታዎች መመረት የሚችል መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ | አቶ አንሙት ታሪክ  |

## ዝርያ መልቀቅ እና ማላመድ

በአገር አቀፍ የዝርያዎች ገምጋሚ ቡድን የተገመገሙ ምርታማነትን፣ ጥራትን፣ ድርቅና በሽታ መቋቋምን መሰረት በማድረግ 9 ዝርያዎች (2 የማሽላ፣ 3 የበቆሎ፣ 1 የአኩሪ አተር፣ 1 የሽምብራ፣ 1 የድንች፣ 1 የጥቁር አዝሙድ) ተለቀዋል፡፡ ዝርያን ከማላመድ አንጻር በብርዕና አገዳ ሰብሎች (በጤፍ፣ ማሽላ፣ ዳጉሳ፣ ዳቦ ስንዴ)፣ በጥራጥሬ ቅባትና ጭረት ሰብሎች (ሽምብራ፣ ላም አተር፣ አተር፣ አኩሪ አተር፣ ምስር፣ ቦሎቄ) እና አትክልትና ፍራፍሬ ሰብሎች (ቲማቲም፣ የፈረንጅ ቀይ ሽንኩርት፣ ነጭ ሽንኩርትና ማንጎ)

ሊካሄዱ በታቀዱ ተሳትፏዊ የዝርያ መረጣ ጥናቶች በተለያዩ ስነ-ምህዳሮች የአርሶ አደሩን ፍላጎት የሚያሟሉ በአጠቃላይ 14 ዝርያዎችን ለመምረጥ ታቅዶ እየተሰራ ነው፡፡

## የሰብል በሽታዎችንና ተባዮችን መቆጣጠር የሚያስችል ቴክኖሎጅ ማውጣት

የሰብል በሽታዎችንና ተባዮችን መቆጣጠር የሚያስችሉ የተቀናጀ እና የተናጠል ቁጥጥር ዘዴዎችን በመጠቀም 6 ቴክኖሎጂዎች ለማውጣት ታቅዶ 6 ማውጣት ተችሏል፡፡ ከቴክኖሎጂዎቹ ውስጥ የሰሊጥ ሌፍ ስፖት በሽታን መቆጣጠር የሚያስችሉ ጸረ ፈንገስ ኬሚካሎችን መለየት፣የሰሊጥ ዌብ ወርም ተባይን መቆጣጠር የሚያስችሉ ጸረ ተባይ ኬሚካሎችን መለየት እና የቦሎቄ አጠውልግ በሽታን ለመቆጣጠር የሚያስችሉ ኬሚካሎችን መለየት የመሳሰሉት ናቸው፡፡

## ዘር ምርምር እና ቴክኖሎጂ/ምክረ-ሃሳብ/ ማውጣት

በዘር ጥራት ከታቀዱ 7 የምርምር ሥራዎች መካከል 4 (57%) የተከናወኑ ሲሆን ከ7ቱ ሙከራዎች 3ቱ በጸጥታ ችግር ምክንያት ተቋርጠዋል፡፡ በበጀት ዓመቱ 1 ቴክኖሎጂ/ምክረ-ሃሳብ/ ይወጣል ተብሎ ይጠበቃል፡፡ ከነዚህም ሥራዎች መካከል በምዕራብ አማራ የተለያየ የዘር ደረጃ የዘር መጠንና የአዘራር ዘዴ በጤፍ የዘር ጥራት፣ ምርትና የመባዛት ችሎታ ላይ ያለውን ተጽዕኖ መገምገም፤ በማሾ የዘር ማሸጊያ እና የማቆያ ጊዜ በዘር ጥራትና ቆይታ ላይ ያለውን ሁኔታ መገምገም ጥናት፤ በአኩሪ አተር የዘር ማሸጊያ እና የማቆያ ጊዜ በዘር ጥራትና ቆይታ ላይ ያለውን ሁኔታ መገምገም በዋናነት ይጠቀሳሉ፡፡

## እንስሳት ምርምር

የእንስሳት ምርምር በዋናነት በእንስሳት ዝርያ ማሻሻል፣ በመኖ ልማት፣ በእንስሳት ጤና፣ ስነ-አመጋገብን ማሻሻል እና የእንስሳት አያያዝ ላይ የሚያተኩሩ ናቸው፡፡ እነዚህም የምርምር ስራዎች የሚከናወኑት በዳልጋ ከብት፣ በበግና ፍየል፣ በዶሮ፣ በንብ እና በዓሳ ላይ ነው፡፡ በበጀት ዓመቱ 153 ሙከራዎችን ለማከናወን ታቅዶ 141 (90.78%) ሙከራዎች ተከናውነዋል፡፡ በተጨማሪም 23 ቴክኖሎጂዎችን/ምክረ-ሃሳቦችን/ ለማውጣት ታቅዶ በመስራት

ላይ ሲሆን ከተከናወኑት 40 ሙከራዎች ተጠናቀው ለዓመታዊ ግምገማ ፎረም የሚቀርቡ ይሆናሉ፡፡

## የግብርና ጥራት ደህንነት

በበጀት አመቱ የግብርና ጥራት ደህንነትን በሚመለከት የግብርናን ምርትና ምርታማነት ለማሣደግ የግብርና ግብዓቶችን የጥራትና የቁጥጥር ስራ በማካሄድ ጥራቱና ጤንነቱ የተጠበቀ ግብዓት ለተጠቃሚው እንዲደርስና በተባይ የሚባክነው ምርት እንዲቀንስ የበኩሉን እስተዋፅኦ እያበረከተ ይገኛል፡፡

## የመስክ ሰብሎች ዘር ጥራት ቁጥጥር

የመስክ ሰብሎች ዘር ጥራት ቁጥጥርን ስንወስድ በመኸር ሰብሎች የመስክ የዘር ጥራት ቁጥጥር በማካሄድ በ2016 ዓ.ም በመስክ ሰብሎች በመኸር 12,866 ሄክታር መሬትና 291,124 ኩንታል የሚገመት ምርት ላይ በመስክ የዘር ጥራት ቁጥጥር ለማድረግ ታቅዶ በ12,605 ሄክታር (98%) የዘር ማሳ እና 280,635 ኩንታል (96%) የሚገመት ዘር ላይ የጥራት ቁጥጥር ተደርጓል፡፡ የመስክ ዘር ጥራት ቁጥጥር ስራ ካለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነፃፀር በጥራት ቁጥጥር በ1,388.4 ሄክታር (10%) ማሳ ቅናሽ ያሳየ ሲሆን የመስክ የዘር ጥራት ቁጥጥር ከተደረገበት ውስጥ 12,249 ሄክታር (97.2%) የዘር ማሳና 275,287 ኩንታል (98.1%) የዘር ምርት የጥራት ደረጃ መስፈርቱን አሟልቶ የተገኘ ሲሆን 356 ሄክታር (2.8%) የዘር ማሳና 5,348 ኩንል ምርት ከጥራት ደረጃ በታች በመሆኑ ከዘርነት እንዲወጣ ተደርጓል፡፡ የመስክ ዘር ጥራት ቁጥጥር ስራው በድቃይና ድቃይ ባልሆኑ ሰብሎች ላይ የተከናወነ ሲሆን ስራው በ14 ዞኖች ስር በሚገኙ 61 ወረዳዎችና 124 ቀበሌዎች በ16,081 ወንድ በ1,531 ሴት በድምሩ በ17,612 አርሶ አደሮች ማሳ ላይ ተከናውኗል፡፡ የዚህ አመት የመስክ ዘር ጥራት ቁጥጥር ስራ ካለፈው አመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነፃፀር በ1,388.4 ሄክታር (10%) ማሳ ቅናሽ አሳይቷል፡፡በክልሉ የተፈጠረው ያለመረጋጋትና የሰላም ችግር ለመቀነሱ ዋናው ምክንያት ነበር፡፡ በዚህ ዓመት የዘር ምርት ግመታ በአብዛኛው በዘር አምራች ድርጅት ባለሙያዎች፣ በወረዳና በቀበሌ የግብርና ባለሙያዎች የተከናወነ ሲሆን በጥራት ቁጥጥር ካለፈ የዘር ማሳ 280,635 ኩንታል የዘር ግምት ተሰርቶ 189,543 ኩንታል (67.54%) ዘር ማሰባሰብ ተችሏል፡፡

## አዲስ የተለቀቁ የሰብል ዝርያዎች

በበጀት አመቱ አዲስ የተለቀቁ የሰብል ዝርያዎች በተመለከተ ምርታማነትን፣ ጥራትን፣ ድርቅና በሽታ መቋቋምን መሰረት በማድረግ በአገር አቀፍ የዝርያዎች ገምጋሚ ቡድን የተገመገሙ 9 ዝርያዎች (2 የማሽላ፣ 3 የበቆሎ፣ 1 የአኩሪ አተር፣1 የሽምብራ፣ 1 የድንች፣ 1 የጥቁር አዝሙድ) ተለቀዋል::

## የመነሻ ቴክኖሎጂ ብዜት

የመነሻ ቴክኖሎጂ ብዜት በመኸር ወቅት በ21 የብርዕና አገዳ፣ ጥራጥሬና ቅባት ሰብሎች በበጀት አመቱ መጨረሻ በ230.34 ሄክታር ማሳ 3,164.73 ኩንታል ዘር መሰብሰብ ተችሏል፡፡ይህም ከታቀደው 3,846.5 ኩንታል 82.27% ይሸፍናል፡፡ በአጠቃላይ በመነሻ ዘር ብዜት የክልሉን ፍላጎት ለማሟላት በማሽላ፣ በጤፍ፣ በስንዴ፣ በሰሊጥ፣ በአኩሪ አተር የተሻለ አፈጻጸም ታይቷል፡፡

## አትክልትና ፍራፍሬ ብዜት

በአትክልትና ፍራፍሬ በተለይ በድንችና በአምስት ፍራፍሬ ሰብሎች በግሪን ሃውስ 550,000 የድንች ሚኒ ቲዩበር ለማባዛት ታቅዶ 323,850 የተከናወነ ሲሆን አፈጻጸሙ 58.88% ነው፡፡ በማኅበረሰብ የድንች ዘር ብዜት ከታቀደው 1,662 ኩንታል መካከል 642 ኩንታል ተሰብስቦ ለአርሶ አደር ተሰራጭቷል፡፡ ከ316,330 በላይ ብርቱካናማ የስኳር ድንች ዝርያዎች ቁርጥራጭ የተባዛ ሲሆን 235,668 ቁርጥራጭ ተሰራጭቷል፡፡ በመነሻ ፍራፍሬ ብዜት 22,500 ችግኞች ለማባዛት ታቅዶ 21,161 ችግኞች ተባዝቷል፡፡ 15,380 ችግኞች ተሰራጭቷል፡፡ በአትክልት ዘር ብዜት 460,000 የሽንኩርት ኮረት በማዘጋጀት 450,000 ተሰራጭቷል፡፡ በተጨማሪም በቁጥር 6,000 የበርበሬ ችግኝ በማዘጋጀት 5,600 ተሰራጭቷል፡፡በመኖ ዘር ብዜት 126.3 ኩንታል የመኖ ዘር ለመሰብሰብ ታቅዶ 58.65 ኩንታል ተመርቷል፡፡ ይህም ከዕቅዱ 46.44% ነው፡፡

## ሰብል ምርምር

በኢንስቲትዩት ከታቀዱት 330 (288 በመኸር፣ 42 በመስኖ) የምርምር ስራዎች 253 (223 በመኸር፣ 30 በመስኖ) ሙከራዎች በታሰበላቸው ደረጃ የተከናወኑ በመሆኑ አፈፃፀሙ 77.85% ነው፡፡ በክልሉ በተፈጠረው የፀጥታ ችግር ምክንያት በአዴት ግብርና ምርምር ማዕከል 39 ሙከራዎች፣ በደብረ ብርሃን ግብርና ምርምር ማዕከል 17 ሙከራዎች፣ ጎንደር ግብርና

ምርምር ማዕከል 7 ሙከራዎች እንዲሁም ስሪንቃ ግብርና ምርምር ማዕከል 3 ሙከራዎች ክትትል ያልተደረገባቸው በመሆኑ የሙከራዎች አፈጻጸም ዝቅ እንዲል አድርጎታል፡፡በአጠቃላይ 37 ቴክኖሎጂዎች ለማውጣት ታቅዶ 30 ተከናውኗል፡፡ አፈፃፀሙም 81%

## መስኖ እና ቆላማ አካባቢዎች ልማት

### የጥናትና ዲዛይን

ከመስኖና ቆላማ ስራዎች አንጻር ሲሰሩ ከነበሩ የበጀት አመቱ ተግባራት መካከል የጥናትና ዲዛይን ሥራዎች ናቸው፡፡በመሆኑም የጥናትና ዲዛይን ሥራዎች አፈጻጸም በ2014 በጀት ዓመትና በፊት የጥናትና ዲዛይን ሥራቸው በአማካሪዎች ተጀምሮ ያደሩ 15,060 ሄክታር መሬት ማልማት የሚችሉ እና ወ- 18,863 ሴ- 3,978 ድ- 22,841 የህብረተሰብ ክፍሎችን ተጠቃሚ የሚያደርጉ 21 መካከለኛና ከፍተኛ መስኖ ፕሮጀክቶችን በ2015 በጀት ዓመት ከደረሱበት አማካይ 64.1% አፈፃፀም በመነሳት 35.9% በመፈጸም 98.6% ለማድረስ እና 13 ፕሮጀክቶችን ለማጠናቀቅ ታቅዶ 26.38% በማከናወን 73.48% በመፈጸም አጠቃላይ 90.48% ማድረስ የተቻለ ሲሆን 11,760 ሄክታር ማልማት የሚችሉ 18 ፕሮጀክቶችን ለማጠናቀቅ ታቅዶ 1,050 ሄክታር ማልማት የሚችሉና ወ- 310 ሴ- 149 ድ-459 ማህበረሰብ ተጠቃሚ የሚያደርጉ 2 ፕሮጀክቶች ማጠናቀቅ ተችሏል፡፡

### ተጀምረው ያደሩ ፕሮጀክቶች

በመንግስት አማካሪ ድርጅቶች በ2015 በጀት ዓመት ተጀምረው ያደሩና በተለያየ አፈጻጸም ላይ የሚገኙ የማልማት አቅማቸው 71,550.40 ሄክታር የሆነና 239,5867 ህዝብ የመስኖ ልማቱ ተጠቃሚ የሚያደርጉ 49 መካከለኛ ፕሮጀክቶችን ከደረሱበት አማካኝ አፈፃጸም 30.4% በመነሳት 44.61% በመፈጸም አማካኝ አፈጻጸማቸውን 75% ለማድረስ ታቅዶ 31.8% በማከናወን 71.3% በመፈጸም አጠቃላይ የፕሮጀክቱን አፈጻጸም 62.2% ማድረስ የተቻለ ሲሆን ከእነዚህ ፕሮጀክቶች ውስጥ 5,662 ሄክታር ማልማት የሚችሉ 11 ፕሮጀክቶችን ለማጠናቀቅ ታቅዶ 6,412 ሄክታር ማልማት የሚችሉና 17,278 ማህበረሰብ ተጠቃሚ የሚያድርጉ 13 ፕሮጀክቶችን ማጠናቀቅ ተችሏል፡፡

### የነባር ፕሮጀክቶች አፈፃፀም

በ2015 ዓ.ም ተጀምረው ያደሩና በተለያዩ አፈጻጸም ላይ የሚገኙ የማልማት አቅማቸው 672 ሄክታር የሆነና 1,938 ህዝብ የመስኖ ልማቱ ተጠቃሚ የሚያደርጉ 8 ነባር ፕሮጀክቶችን

በ2015 በጀት ዓመት ከደረሱበት 15% አማካኝ አፈጻጸም በመነሳት 60% በመፈጸም 75% ለማድረስ ታቅዶ 34.38% በማከናወን 57.3% መፈጸም የተቻለ ሲሆን አጠቃላይ የፕሮጀክቱን አፈጻጸም 49.38% ማድረስ ተችሏል፡፡ ከእነዚህ ፕሮጀክቶች ውስጥ 350 ሄክታር የሚያለሙ 3 ፕሮጀክቶችን ለማጠናቀቅ ታቅዶ 250 ሄክታር የሚያለሙና 721 የህብረተሰብ ክፍሎችን ተጠቃሚ የሚያደርጉ 2 ፕሮጀክቶችን ማጠናቀቅ ተችሏል፡፡

## አዲስ አነስተኛ ፕሮጀክቶች ጥናትና ዲዛይን ስራ

በዞንና ወረዳዎች ደረጃ የማልማት አቅማቸው 732.10 ሄክታር የሆነና 1,894 የህብረተሰብ ክፍሎችን ተጠቃሚ የሚያደርጉ የ15 አዲስ አነስተኛ ፕሮጀክቶች ጥናትና ዲዛይን ስራ 100% ለማጠናቀቅ ታቅዶ 80% መፈጸም የተቻለ ሲሆን 512 ሄክታር ማልማት የሚችሉና 1,325 የህብረተሰብ ክፍሎች የመስኖ ልማቱ ተጠቃሚ የሚያደርጉ 12 ፕሮጀክቶች ጥናትና ዲዛይን ሥራ ማጠናቀቅ የተቻለ ሲሆን በምዕራብ ጎንደር የሚገኙ 3 ፕሮጀክቶች ምንም ስራ እንዳልጀመሩ ያሳያል፡፡

## የአካባቢና ማህበራዊ ተጽዕኖ ግምገማ ማካሄድ

የአካባቢና ማህበራዊ ተጽዕኖ ግምገማ ማካሄድን በሚመለከት በ2016 ዓ.ም አዲስ ለሚገነቡ የመስኖ ፕሮጀክቶች ከአማካሪ ድርጅቶች ጋር ውል በመያዝ እና ቢሮው በራሱ የአካባቢና ማህበራዊ ተጽዕኖ ግምገማ ጥናትና ዲዛይን ሰነድ በማዘጋጀት 43 ፕሮጀክቶችን የአካባቢና ማህበራዊ ተጽዕኖ ግምገማ የይሁንታ ማረጋገጫ ሰርቲፊኬት እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡

## የፕሮጀክቶች ግንባታና ክትትል

በዘላቂ የልማት ግብ ፕሮጀክቶች 8,156.5 ሄክታር ማልማት የሚችሉና 12,851 የህብረተሰብ ክፍሎችን ተጠቃሚ የሚያደርጉ ነባር 23 ፕሮጀክቶች ግንባታ በ2015 ዓ.ም ከደረሱበት 58.2% አማካኝ አፈፃፀም በመነሳት 82.8% ለማድረስ ታቅዶ 9.8% በማከናወን 39.8 መፈጸም የተቻለ ሲሆን አጠቃላይ የፕሮጀክቱን አፈጻጸም 68% ማድረስ ተችሏል፡፡ በበጀት ዓመቱ 7 ፕሮጀክቶች ወደ ግንባታ የገቡ ሲሆን ከዚህ መካከል 843 ሄክታር ማልማት የሚችልና 2,170 የህብረተሰብ ክፍል ተጠቃሚ የሚያደርግ 6 ፕሮጀክት (ቃሊና፣ ላህ ፍኖተ ስላም፣ ታችኛው ኳሽኒ፤ሚሊ ኮትቻ ማስፋፊያ 2፤ሰባት ወደል እና አንት ዉኃ ስማዳ) ማጠናቀቅ ተችሏል፡፡



## በለስ የተቀናጀ ስኳር ልማት ፕሮጀክት የአናት እና ዋናቦይ

## በ2016 ዓ.ም በፊት የተጀመሩ ፕሮጀክቶች

በ2013 ዓ.ም እና ከዚያ በፊት የተጀመሩ 1,496 ሄክታር ማልማት የሚችሉና 3,039 የህብረተሰብ ክፍሎችን ተጠቃሚ የሚያደርጉ 30 አነስተኛ ፕሮጀክቶች በ2015 ዓ.ም ከደረሱበት 59.5% አማካኝ አፈፃፀም በመነሳት 86.55% ለማድረስ ታቅዶ 13.98% በማከናወን 51.68% መፈፀም የተቻለ ሲሆን አጠቃላይ የፕሮጀክቱን አፈጻጸም 73.48% ማድረስ ተችሏል፡፡ ከዚህም ውስጥ 826.2 ሄክታር የሚያለሙ 20 ፕሮጀክቶች ለማጠናቀቅ ታቅዶ 626.29 ሄክታር ማልማት የሚችሉና 1,156 የህብረተሰብ ክፍሎችን ተጠቃሚ የሚያደርጉ 9 ፕሮጀክቶች (እማሙዝ፣ ግባዛ፣ በበሳር፣ ጎሊና፣ አረባ፤ ቱሉ ባቡኛ ጫውሪና፣ ድቁሳ እና ብልቅ) ማጠናቀቅ ተችሏል፡፡

በበጀት አመቱ 1,923.40 ሄክታር ማልማት የሚችሉ በ2014 የተጀመሩ 27 ነባር አነስተኛ ፕሮጀክቶች ግንባታ በማስጀመር በ2015 ከደረሱበት 52.69 በመቶ አማካኝ አፈፃፀም በመነሳት 27.4% በመፈጸም 80.1% ለማድረስ ታቅዶ 9.29% በማከናወን 33.9% በመፈጸም አጠቃላይ የፕሮጀክቱን አፈጻጸም 61.98% ማድረስ ተችሏል፡፡ ከእነዚህ ፕሮጀክቶች ውስጥ 527.4 ሄክታር ማልማት የሚችሉ 17 ፕሮጀክቶችን ለማጠናቀቅ ታቅዶ 112.9 ሄክታር ማልማት የሚችልና 272 አባዋራ ተጠቃሚ የሚያደርጉ 3 ፕሮጀክት (ምንጭ ግድብ፤ ጭ/ጫ/ንጩት እና ሆሲ) ማጠናቀቅ ተችሏል፡፡

2015 ዓ.ም የተጀመሩ 2,364.37 ሄክታር ማልማት የሚችሉና 4,230 ህብረተሰብ ተጠቃሚ የሚያደርጉ 38 አነስተኛ ፕሮጀክቶች ግንባታ በ2015 ዓ.ም ከደረሱበት 31.75% አማካኝ

አፈፃፀም በመነሳት 38.59% በማከናወን 70.34% ለማድረስ ታቅዶ 31.7% በማከናወን 82% በመፈጸም አጠቃላይ አፈጻጸሙን 63.45% ማድረስ ተችሏል፡፡ከነዚህ መካከል 758.37 ሄክታር ማልማት የሚችሉ 15 ፕሮጀክቶችን ለማጠናቀቅ ታቅዶ 758.37 ሄክታር ማልማት የሚችሉና 1,720 አባዋራ ተጠቃሚ የሚያደርጉ 14 ፕሮጀክት (ቆሬ፣ መዝገቦ ምድር፣ ቁሴች፣ ህዝብ አምባ፣ ማሪቱ፣ ሸማ ማጠያ፣ ገበያ ወንዝ፣ እንደራስ፣ ቀሳውስት፣ ጨቂ/ልቅሜ ምንጭ፣ ሎኮ፣ በለስ2፣ ሸማ፣ ሙቀጫ ድንጋይ፣እና ጉቻት) ማጠናቀቅ ተችሏል፡፡

በ2015 ዓ.ም የተጀመሩ 7,843 ሄክታር ማልማት የሚችሉ እና 8,557 ህብረተሰብ ተጠቃሚ የሚያደርጉ 26 መካከለኛ ፕሮጀክቶች ግንባታ በ2015 ዓ.ም ከደረሱበት 5.26% አማካኝ አፈፃፀም በመነሳት 17.61% በማከናወን 31% ለማድረስ ታቅዶ 11 ፕሮጀክቶችን ወደ ግንባታ በማስገባት 4.36% ብቻ በማከናወን 9.62% ማድረስ ተችሏል፡፡

## በግብርና እድገት ፕሮግራም (ኤጀፒ) ፕሮጀክቶች

በግብርና እድገት ፕሮግራም (ኤጀፒ)ፕሮጀክቶ 2,230.5 ሄክታር ማልማት የሚችሉ 3,491 የህብረተሰብ ክፍሎች ተጠቃሚ የሚያደርጉ 8 ነባር ፕሮጀክቶች ግንባታ በ2015 ዓ.ም ከደረሱበት 73.12% በመነሳት 100% ለማድረስ ታቅዶ 8 ፕሮጀክቶችን ግንባታቸውን እንዲያጠናቀቁ በማድረግ ለልማት ዝግጁ ተደርጓል፡፡

## ተሳትፏዊ ፕሮግራም (በኢፋድ) ፕሮጀክቶች

የኢፋድ-2 የተሳትፏዊ አነስተኛ መስኖ ልማት ፕሮግራም-2 አጠቃላይ በፕሮግራሙ ወደ ግንባታ የገቡት 35 ሲሆኑ ከነዚህ መካከል 32 ፕሮጀክቶች ሙሉ በሙሉ ተጠናቀው የመጨረሻ ርክክብ ተደርጎባቸዋል፡፡ በተቋረጡት ሦስት ፕሮጀክቶች (አጠባ-1 እና አጠባ-2) ምትክ 171 ሶላር ፓምፖችን ለሰሜን ጎንደር (50 ለዳባት እና 121 ለጠለምት) ማድረስ ተችሏል፡፡ በአሁኑ ሰዓት የተጠናቀቁት የመስኖ ተቋማት 6,245 ሄክታር መሬት በማልማት ሴ- 2,053 ወ- 8,515 ድ- 10,568 የህብረተሰብ ክፍሎችን ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡

### በአፍሪካ ልማት ባንክ የገንዘብ ድጋፍ የሚገነቡ መስኖ ልማት ፕሮጀክቶች

በአፍሪካ ልማት ባንክ የገንዘብ ድጋፍ በሰቆጣ ቃል ኪዳን ፕሮግራም 629.43 ሄክታር መሬት የማልማት አቅም ያላቸውና ወ- 2,274 ሴ- 916 ድ- 3,190 የማህበረሰብ ክፍሎችን ተጠቃሚ የሚያደርጉ 23 የመስኖ ፕሮጀክቶች በ2015 ከነበሩበት 16.8% በመነሳት 90.39% ለማድረስ ታቅዶ 64.2% በመፈጸም አጠቃላይ የፕሮጀክቱን አፈጻጸም 81% ማድረስ ተችሏል፡፡ ከነዚህ ፕሮጀክቶች ውስጥ በበጀት ዓመቱ 199.93 ሄክታር የማልማት አቅም ያላቸውና 1,137

አባዋራዎችን ተጠቃሚ የሚያደርጉ 12 (ሰጎሬ፣ ዛሮታ፣ ሙዙ፣ ጀርስን፣ ቦሹ፣ ዱሪና፣ በጁ፣ ግድቡት፣ ቂጤማ ወንዝ፣ ዋሻዉ፣ ዶቅማዉ፣ ዚባ) ፕሮጀክቶች ግንባታ በማጠናቀቅ ወደ ልማት እንዲገቡ ተደርጓል።

## በጦርንት የተጎዱ አካባቢዎችን መልሶ ማቋቋም ፕሮጀክቶች

በጦርነቱ ከፍተኛ ውድመት በደረሰበት በሰሜን ወሎ ዞን ራያ ቆቦ ወረዳ እና ቆቦ ከተማ የሚገኙ የከርሰ ምድር መስኖ ልማት ፕሮጀክቶች ወደ ስራ ለማስገባት በተያዘው እቅድ መሰረት የማልማት አቅማቸው 440.8 ሄክታር የሆኑና 6,590 የማህበረሰብ ክፍሎችን ተጠቃሚ የሚያደርጉ 10 የግፊት እና ከፊል ግፊት መስኖ ልማት ፕሮጀክቶችን በመለየት ባለፈው በጀት ዓመት ከጢስ እሳት ውሃ ስራዎች ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ጋር ውል ተወስዶ ወደ ሥራ የተገባ ሲሆን  ፓምፕ፣ የፓምፕ ኬብል፣ መገጣጠሚያዎችና ቧንቧዎች ግዥ ተፈጽሞ እቃዎችን የማቅረብ ስራ ተሰርቷል።

## የባለአነስተኛ ይዞታ መስኖ ልማት ፕሮግራም ፕሮጀክቶች

የባለአነስተኛ ይዞታ መስኖ ልማት ፕሮግራም ፕሮጀክቶች ሲታዩ በተለያዩ ዞን እና ወረዳዎች የሚገኙ አጠቃላይ 981.76 ሄክታር የማልማት አቅም ያላቸውና 2,339  የህብረተሰብ ክፍሎችን ተጠቃሚ የሚያደርጉ 20 አነስተኛ መስኖ ፕሮጀክቶች በ2015 መጨረሻ ድረስ ከደረሱበት 62.61% አማካኝ አፈጻጸም በመነሳት 100% ለማድረስ ታቅዶ አጠቃላይ አፈጻጸሙን 77.86% ማድረስ ተችሏል። ወደ ግንባታ ከገቡ ፕሮጀክቶች 524.26 ሄክታር ማልማት የሚችሉና 1,133 አባዎራዎችን ተጠቃሚ የሚያደረጉ 8 ፕሮጀክቶች (ጉሎሜዳ፣ ላይኛው ሚሌ፣ ትግዛ፣ ግድቡት፣ ዥጣ፣ቀጭኒት፣ ጌደራ እና ቡርቃ) ግንባታ ማጠናቀቅ የተቻለ ሲሆን ወደ ግንባታ የገቡት ፕሮጀክቶች ቁጥር አናሳ ቢሆንም አማካይ አፈጻጸማቸው ግን ጥሩ የሚባል ሁኔታ ላይ ይገኛል።



አጓት ውሃ የመስኖ ፕሮጀክት

## በልዩ ልዩ መያድ የሚሰሩ የመስኖ ልማት ፕሮጀክቶች

በልዩ ልዩ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የሚሰሩ የመስኖ ልማት ፕሮጀክቶች አፈፃፀም ሲታይ በክልሉ ውስጥ ቀጥታ ግንኙነታቸው ከወረዳ ጋር የሆኑ በልዩ ልዩ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የሚሰሩ የመስኖ ልማት ፕሮጀክቶች የበጀት ድጋፍ እየተገነቡ ያሉ ሲሆን በ2016 በጀት አመቱ 715 ሄክታር ማልማት የሚችሉና 2334 የማህበረሰብሰብ ክፍሎችን ተጠቃሚ የሚያደርጉ 17 ፕሮጀክቶች ግንባታ በማከናወን በ2015 ከነበሩበት 56.21% በመነሳት 100% ለማድረስ ታቅዶ 42.5% በማከናወን አጠቃላይ የፕሮጀክቱን አፈጻጸም 98.71% ማድረስ ተችሏል፡፡ ሁሉንም ፕሮጀክቶች ግንባታ ለማስጀመር ቢታቀድም 680 ሄክታር ማልማት የሚችሉና 2217 የህብረተሰብ ክፍሎችን ተጠቃሚ የሚያደርጉ 16 መስኖ ፕሮጀክቶችን ግንባታ ማጠናቀቅ ተችሏል፡፡

## ከፍተኛ የመስኖ ፕሮጀክቶች አፈጻጸም

ከፍተኛ የመስኖ ፕሮጀክቶች አፈጻጸም ሲታይ በክልላችን በፌደራልም ይሁን በሌሎች አካላት የሚከናወኑ ማንኛውንም የመስኖ ስራዎች ለክልሉ ልማት የሚኖራቸውን ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ ግምት ውስጥ በማስገባት እና በአዋጅ የተሰጠውን ተግባርና ሃላፊነት ለመወጣት በባለቤትነት መንፈስ አስፈላጊውን ክትትልና ድጋፍ ማድረግ ስላለበት በፌደራል መስኖና ቆላማ አካባቢ ልማት ሚኒስቴር አማካኝነት በጥናትና ዲዛይን፣ በግንባታ ላይ የሚገኙ እና ግንባታቸው የተጠናቀቁ ከፍተኛ የመስኖ ልማት ፕሮጀክቶችን አፈፃፀማቸውን ለማሻሻል ከማህበራዊ እና ከባቢያዊ ጉዳዮች ጋር በተያያዘ ሊያጋጥሙ የሚችሉ ተግዳሮቶችን ለመፍታት ክትትል እና ድገፍ ለማድረግ እና በትብብር ስራዎችን እየሰራ ይገኛል፡፡ አጠቃላይ በተደረገው ክትትል መሠረት የሜጋ ፕሮጀክቶች አፈጻጸም ሲታይ ከፍተኛ የመስኖ ልማት ፕሮጀክቶች አጠቃላይ ያላቸው አፈጻጸም ዝቅተኛ እንደሆነ እና አብዛኛዎች ፕሮጀክቶች መጠናቀቅ ከሚገባቸው ጊዜ በላይ ለብዙ ዓመታት ያህል ተጓተው ይገኛሉ፡፡ እነዚህ ፕሮጀክቶች ለመጓተት ከሚጠቀሱ ምክንያቶች ውስጥ አንዱ የካሳ ክፍያ አለመከፈል ሲሆን በላይኛው ርብ፣ ታችኛው ርብ፣ መገጭ እና አጅማ ጫጫ ከፍተኛ የመስኖ ፕሮጀክቶች ለ1,138 አርሶ አደሮች 1,160 ሚሊዮን ብር የካሳ ክፍያ እንዳልተከፈለ የሚያሳይ ሲሆን ይህ ችግር ከሚመለከታቸው አካላት ጋር

በመወያየት አፋጣኝ መፍትሄ በመስጠት ወደ ግንባታ የሚገቡበት ሁኔታ ሊመቻች ይገባል፡፡



መይሳ የመስኖ ፕሮጀክት- ደቡብ ወሎ

## በኢፌዴሪ መስኖና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር የጥናት እና ዲዛይን ስራ

በኢፌዴሪ መስኖና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር የጥናት እና ዲዛይን ስራ ለመስራት እቅድ ከተያዙት ነባር ፕሮጀክቶች መካከል ሽንፋ 86,000 ሄክታር፣ አይማ ግድብ 25,000 ሄክታር፣ መቻላ ግድብ 15,000 ሄክታር፣ ተላ ግድብ 7,000 ሄክታር እና አንገረብ 50,000 ሄክታር በድምሩ 183,000 ሄክታር የሚያለሙ 5 ከፍተኛ መስኖ ፕሮጀክቶች በ 334.7 ሚሊዮን ብር ውል በመውሰድ ሰራዎች እየተከናወኑ ይገኛሉ፡፡ የእነዚህ ፕሮጀክቶች የጥናትና ዲዛይን ስራ በተመለከተ ሽንፋ 37%፣ አንገረብ 30%፣ አይማ 17.5%፣ መቻላ 10% እንዲሁም ተላ 10% ማድረስ የተቻለ ሲሆን መቻላ እና ተላ ፕሮጀክቶች የጥናትና ዲዛይን ስራ በዚህ በጀት ዓመት እንዳልተሰራ ያሳያል፡፡

## የተቋማት አስተዳደርና ጥገና ሥራ

የተቋማት አስተዳደርና ጥገና ሥራዎች አፈፃፀም ሲታይ 1,460 ሄክታር የሚያለሙና 1,432 የህብረተሰብ ክፍል ተጠቃሚ የሚያደርጉ 22 የመስኖ አውታሮችን ለመጠገን ታቅዶ 885 ሄክታር የሚያለሙና 2,058 የህብረተሰብ ክፍል ተጠቃሚ የሚያደርጉ 13 መስኖ አውታሮች ተጠግነዋል፡፡ በሰቆጣ ቃልኪዳን በጀት በፌደራል እና በክልል መንግስት በተመደብ በጀት 495.5 ሄክታር ማልማት የሚችሉ 14 ፕሮጀክቶችን የጥገና ስራ ማከናወን ተችሏል፡፡ 231 የመስኖ ውኃ ተጠቃሚዎች ማህበራትን ለማቋቋም ታቅዶ 206 ማህበራትን የማቋቋም እንዲሁም 367 ማህበራትን ለማጠናከር ታቅዶ 472 ማህበራትን የማጠናከር ስራ ተሰርቷል፡፡ በበጀት አመቱ 11,471 ኪሎ ሜትር ዘመናዊና ባህላዊ የመስኖ ቦይ ጠረጋ ስራና 144 የመስኖ ፕሮጀክቶችን

የአናት ስራ ጠረጋ ለማከናወን ታቅዶ 1,712.8 ኪሎ ሜትር ዘመናዊ የመስኖ ተቋማት እና 6,948 ኪሎ ሜትር የባህላዊ ቦይ ጠረጋ ማከናወን ተችሏል፡፡በተመሳሳይ በተዘዋዋሪ ብድር 3,100 የውሀ መሳቢያ ሞተር ፓምፕ ግዥ በመፈጸምና ፍትሀዊነትን መሰረት ያደረጉ መስፈርቶችን በማዘጋጀት 3,061 የውሃ መሳቢያ ፓምፖች ለአርሶ አደሮች ማሰራጨት ተችሏል፡፡

# መሬት ልማት

## የማሳ ካርታ ማዘጋጀት

በ2016 ዓ.ም ለ380,944 ባለይዞታዎች 1,422,081 የማሳ ካርታ በማዘጋጀት የ2ኛ ደረጃ የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ለመስጠት ታቅዶ ለ388,528 (አባወራና እማወራ 169,474፣ አባወራ 64,408፣ እማወራ 92,793፣ የጋራ ይዞታ ከባልና ሚስት ውጭ 9,092፣ የወል 7,889፣ ለመንግስት ተቋማት ለ1,924፣ መንግስታዊ ላልሆኑ ተቋማት 1,953) ባለይዞታዎች 1,476,269(104%) የማሳ ካርታ ተዘጋጅቶ የተሰጠ ሲሆን አፈፃፀሙ ከባለይዞታ 102% ነው፡፡ ለ17,133፣ ተጋላጭ ህበረተሰብ ክፍሎች የ2ኛ ደረጃ የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ለመስጠት ታቅዶ በዓመቱ ለ1,145 (ወንድ -668፣ ሴት-1,326) (ወላጆቻቸውን በሞት ያጡ ህፃናት 682 (ወንድ -416፤ ሴ-251)፣ አካል ጉዳተኞች 437(ወንድ 212፣ ሴት 225)፣ አረጋውያን 485 (ወንድ 424፣ ሴት 258) የ2ኛ ደረጃ የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት የተሰጠ ሲሆን አፈፃፀሙ 7% ነው፡፡

## የቤተሰብ ጥሪት ማጎልበቻ ስርአት መገንባት

የቤተሰብ ጥሪት ማጎልበቻ ስርአት ለመገንባትን በተሰራው ስራ 47513 ባለይዞታዎች የ2ኛ ደረጃ የይዞታ ማረጋገጫ ደብተራቸውን የብድር ዋስትና አስይዘው ብር 712,695,000 የብድር ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ ታቅዶ 3,256 (ወንድ 2,135 ሴት 1,121 (7%) ባለይዞታዎች ደብተራቸውን በማስያዝ ብር 161,090,433.096 (23%) እንዲበደሩ ተደርጓል፡፡197,199 ባለይዞታዎችን 672,653 ማሳ ወደ ኮምፒውተር በማስገባት መሬት መረጃ ደህንነትና አሰራር ቅልጥፍና ስርዓት ለማሻሻል እንዲያስችል በእቅድ ተይዞ አፈፃፀሙ ከአመቱ እቅድ ከባለይዞታ 122,974 (62%) እና ከማሳ ብዛት 770,974 (115%) ማከናወን ተችሏል፡፡

### የመሬት መረጃን አጣርቶ መመዝገብ

በበጀት አመቱ 24,882 ሁሉም የመሬት ይዞታ ለውጦች (ስጦታ፣ ውርስ፣ ልውውጥና ኪራይ) መረጃ አጣርቶ ለመመዝገብ ታቅዶ በአመቱ ውስጥ 13,478 በማንዋል ግብይት ተካሂዷል፡፡ይህም የመሬት ግብይት ከአመቱ 54% መፈፀም ተችሏል፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ ከሚሰጡ የመሬት ግብይት ውል ምዝገባ አገልግሎቶች 3,732,300 ለመሰብሰብ ታቅዶ ብር 5,275,503(141%) ተሰብስቧል፡፡

## የባለይዞታዎችን የግብይት መረጃ መመዝገብ

በ2016 ዓ.ም 262,893 ባለይዞታዎችን ግብይት መረጃ በNRLAIS ለመመዝገብ ታቅዶ የ78,741 ባለይዞታዎችን ግብይት የተከናወነ ሲሆን አፈፃፀሙ ከአመቱ እቅድ 30% ሆኗል፡፡ በሲስተሙም በዋና ዋና ግብይት አይነቶች ማለትም ልውውጥ፤ ስጦታ፤ ውርስ፤ ኪራይና ሌሎች በድምር 83479 (ወንድ 52501 ሴት 30978) በሲስተም ግብይት ተካሂዷል፡፡ ነገር ግን ሲስተሙ 2016 ዓ.ም አጋማሽ በፊት ሪፖርት በባለይዞታ ብቻ ይወጣ ስለነበር የተሟላ መረጃ ማግኘት አስቸጋሪ አድርጎት ቆይቷል፡፡ በባለይዞታ አይነትና ስብጥር ሪፖርት አለማውጣቱም ተጨማሪ ችግር ሁኖ ቆይቷል፡፡፤ የወቅቱ የፀጥታ ችግር፤ ሲስተሙን የመጠቀም አቅም በወረዳ ደረጃ አነስተኛ መሆን፤የመገልገያ ኮምፒተሮች፤ ስካነሮችና ሌሎች ግብአቶች በአያያዝ ምክንያት ተገቢ ግልጋሎት ሳይሰጡ መበላሸት፤ የሰርቨሮች አቅም ማነስ፤ የኔትወርክ ችግር፤የቢሮ ጥበትና ለአገልግሎት ምቹ የሆነ ቦታ አለመኖር የተፈለገውን ያህል ርቀት እንዳንሄድ ግብይቱን ክትትል ለማድረግ አንድ ችግር ሁኖ ተስተውሏል፡፡ በተመሳሳይ ወረዳዎች ቁጥር መብዛትና ፀጥታው ችግር እንዲሁም የወረዳዎች ጆኦግራፊያዊ ስብጥር መስፋት ለክትትልና ድጋፍ ለክልሉ ስታፍ አለመመቸትም የበለጠ እንዳንፈጥን አድርጓል፡፡ የክላስተር አደረጃጀቱ በተፈለገው መጠን ውጤታማ አለመሆኑና ዞኖችና ወረዳዎች ትኩረት ማነስም አንዱ ችግር ሁኖ ተስተውሏል፡፡

በመሆኑም ስራውን ለማጠናከር የሚያስችል ክትትልና ድጋፍ ተጠናክሮ ሊቀጥል የሚችልበትን የስራ ክፍላችን ስምሪት በመስጠት ለማጠናከር እየተሞከረ ሲሆን፤ የዞኖችን አቅም ማጠናከርም እንደ ዋነኛ ስትራቴጂያዊ አቅጣጫ ተቀምጦ በመከናወን ላይ ይገኛል፡፡ በበጀት አመቱም 17 ወረዳዎችን በናርሌስ በማቀፍ ለማስመረቅ ታቅዶ 13 ወረዳዎችን በናርሌስ አቅፈን ለቫሪፊኬሽን

በማዘጋጀት ላይ ሲሆን ክልላዊ ሽፋኑም በዲጂታል መረጃ አስተዳደር ስርአት ግንባታ ወደ 126 ወረዳ በማድረስ (86.2%) መፈፀም ተችሏል፡፡

## የከተማ መሬት ይዞታ መብት ምዝገባ ስራ

የከተማ መሬት ይዞታ መብት ምዝገባ ስራዎች ለመስራት በተደረገው ጥረት 77,400፣ ይዞታዎችን በሰነድ ለማጣራትና ለማረጋገጥ፤የተረጋገጡ ይዞታዎችን የይዞታ ማረጋገጥ ውጤት ለህዝብ ይፋ ለማድረግ፤ ይዞታቸው የተረጋገጠላቸው መሆኑን የሚገልጽ ማስረጃ ለመስጠት እና የይዞታ መብት የተረጋገጥላቸው ይዞታዎችን ማስረጃ ለመብት ምዝገባ ርክክብ ለማድረግ ታቅዶ 12,483 (16%) ይዞታዎችን ማጣራትና ማረጋገጥ ተችሏል፤ 9,923 (11%) ይዞታዎችን ለህዝብ ይፋ ተደርገዋል፣ 13,060 (17%) ይዞታዎችን ለባለይዞታዎች ጊዜአዊ ማስረጃ ተሰጧል ለ14,283 (18%) ማስረጃዎችን ርክክብ መፈፀም ተችሏል፡፡



በከተማ መሬት ይዞታ መዝገባና መረጃ ስርዓት ግንባታ የተሰጠ ስልጠና-ኮምቦልቻ

## ባለይዞታዎችን የመብት ምዝገባ ማከናወን

በ2016 ዓ.ም በ14ቱ ከተሞች በይዞታ ቁጥር 77,400 ባለይዞታዎችን የመብት ምዝገባ በማከናወን ለባለይዞታዎች የመብት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ለመስጠት ታቅዶ 14974 (19%) የተመዘገበ ሲሆን ከዚህ ውስጥ በCRPRS ሲስተም የተመዘገበ 1747 ሲሆን ለ13,945 ባለይዞታዎች የመብት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት በመስጠት ከአመቱ 18% መፈፀም ተችሏል፡፡

## የመሬት አጠቃቀምና አያያዝ ስራ

የመሬት አጠቃቀምና አያያዝ ስራዎች አኳያ በበጀት ዓመቱ ለ177,374፣ የመሬት ተጠቃሚ ባለይዞታዎች አሳታፊ የመሬት አጠቃቀም ዕቅድ በማቀድ የተዘጋጀውን እቅድ ለማስረከብ

ታቅዶ ለ65,282 (37%) ለመሬት ተጠቃሚ ባለይዞታዎች የመሬት አጠቃቀም እቅድ ተዘጋጅቶ ለ46,366 (26%) ባለይዞታዎች ርክክብ የተፈጸመ ሲሆን የመሬት አጠቃቀም እቅድ የተዘጋጀላቸውን ባለይዞታወች መረጃ ወደ ኮፒውተር ለማስገባት 432,560 ባለይዞታ ተግባራዊ ለማድረግ ታቅዶ 271,704(72%) ባለይዞታ ወደ ኮምፒውተር የማስገባት ስራ ተከናውኗል፡፡

## የቀበሌ ማእከላት ግንባታ ስራ

የገጠር ቀበሌ ማእከላት የእድገት ማእከል ሆነው የአርሶ አደሩን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ አገልግሎቶች ተደራሽነትና ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ ያላቸው ሚና የጎላ ነው፡፡ ይህን እውን ለማድረግ በበጀት ዓመቱ 200፣ በአዲስ የቀበሌ ማእከል ፓኬጅ ፕላን ለማዘጋጀት ታቅዶ 80 (40%) ፓኬጅ ፕላን ተዘጋጅቷል፡፡የተዘጋጀውን የቀበሌ ማዕከል ፕላን ወደ መሬት በማውረድ 170 ቀበሌወች ብሎክ እንዲከፈትላቸው ለማድረግ ታቅዶ 77(45%) ቀበሌወች ብሎክ እንዲከፈትላቸው የተደረገ ሲሆን በ152 ቀበሌዎች 17,490 ቦታዎችን የፕላን ሽንሽና ለማካሄድ ታቅዶ በ177 ቀበሌዎች 6,376 ቦታዎች ተሸንሽነዋል፡፡12,966፣ የተሸነሸኑ የግንባታ ቦታዎችን ለተጠቃሚዎች ለማስረከብ ታቅዶ 6,551(51%) ቦታዎችን ማስረከብ ተችሏል፡፡15,522፣ተጠቃሚዎችን ግንባታ ለማስጀመር ታቅዶ 6,458 ተጠቃሚዎች ግንባታ ሲጀምሩ 10,463፣ተጠቃሚዎች ግንባታ እንዲያጠናቅቁ ለማድረግ ታቅዶ 5,778 (55%) ግንባታቸውን አጠናቀዋል፡፡

## ሳይት ፕላን መስጠትና ስመንብረት ዝውውር

በ2016 ዓ.ም 14,209፣ ሳይት ፕላን ለመስጠት ታቅዶ 8,001 (56%) ሳይት ፕላን የተሰጠ ሲሆን 10,070፤ ግንባታ ላጠናቁ ተጠቃሚዎች ቋሚ ካርታ ለመስጠት ታቅዶ ለ4,878 (48%) ገንቢዎች ቋሚ ካርታ ተሰጥቷል፡፡ የ883፣ ግለሰቦችን ስመንብረት ለማዛወር ታቅዶ 881 ተጠቃሚዎች ስመ ንብረት ዝውውር ፈፅመዋል እንዲሁም ከቀበሌ ማእከላት የአገልግሎቶች ክፍያዎች በበጀት ዓመቱ ብር 15,000,000፣ ለመሰብሰብ ታቅዶ ብር 10,698,145 (70%) ገቢ መሰብሰብ ተችሏል፡፡

## የካሳ ምትክና ዘላቂ መልሶ ማቋቋም ስራ

የካሳ ምትክና ዘላቂ መልሶ ማቋቋም ስራዎችን ስናይ በልማት ምክንያት ከይዞታቸው ለሚነሱ 50,502 ባለይዞታዎች 12,626 ሄክታር መሬት ብር 22.69 ቢሊዮን ለመገመት ታቅዶ የ19,756 የልማት ተነሽዎች ለ3,121 ሄክታር(25%) መሬት ብር 9.084 (40%) ቢሊዮን የተገመተ ሲሆን በልማት ምክንያት ከይዞታቸው ለሚነሱ 50,502 ባለይዞታዎች ብር 22.69 ቢሊዮን እንዲከፈል ለማድረግ ታቅዶ የ13,424 (እማወራና አባወራ 7,916፣ እማወራ 2,750፣ አባወራ 2,758) የልማት ተነሽዎች ብር 5.63 ቢሊዮን ብር የካሳ ክፍያ ተከናውኗል፡፡ አፈፃፀሙ ከባላይዞታ 27% ሲሆን ባለፈው አመት ለባለይዞታዎች ብር 9,461,060,000 ካሳ ተገምቶ ሳይከፈል ቀርቶ በዚህ አመት የተከፈለ መጠን 1,012,595,545(11%) ነው፡፡

## በልማት ምክንያት ተነሺ ባለይዞታዎችን መልሶ ለማቋቋም

በልማት ምክንያት ተነሺ ባለይዞታዎችን መልሶ ለማቋቋም በዓመቱ ለ5,050 ባለይዞታዎች የመኖሪያ ቤት መስሪያ ቦታ እንዲያገኙ ለማድረግ በዕቅድ ተይዞ 3,405 (67.4%) (አባውራ 672፣ እማውራ 856፣ አባወራና እማወራና 1,873) ባለይዞታዎች የመኖሪያ ቤት መስሪያ ቦታ እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡ እንዲሁም ዕድሜያቸው 18 ዓመትና ከዚያ በላይ የሆናቸው የልማት ተነሺ ቤተሰብ አባላት የመኖሪያ ቤት መስሪያ ቦታ እንዲያገኙ ለማድረግ በአመቱ ለ10,100፣ በዕቅድ ተይዞ ለ4,145 (41%) (ወንድ 2,569፣ ሴት 1,576) የሚሆኑ ልጆች የመኖሪያ መስሪያ ቦታ እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡ ተነሺ ባለይዞታዎችን ለማቋቋም ከሚሰራው ስራ አንዱ የመስሪያ ቦታ ማመቻቸት ነው፡፡ በዚህም በአመቱ ለ2,525፣ ባለይዞታዎች የመስሪያ ቦታ እንዲያገኙ ለማድረግ በዕቅድ ተይዞ 1,534 60.8%) (ወንድ 1,000፣ ሴት 534) ባለይዞታዎች የመስሪያ ቦታ እንዲያገኙ የተደረገ ሲሆን ለ1,386፣ ተነሽ ባለይዞታዎች ትክ የእርሻ መሬት ለመስጠት በእቅድ ተይዞ ለ937 (67.5%) (አባውራ 174፣ እማውራ 202፣ ባለትዳር 561) ባለይዞታዎች ትክ የእርሻ መሬት ሲሰጥ በአመቱ ለ25,251 ባለይዞታዎች ባላቸው የካፒታል አቅም መሰረት በተለያዩ የስራ ዘርፎች እንዲሰማሩ ለማድረግ በዕቅድ ተይዞ ለ8,987 (ወንድ 6,369፣ ሴት 2,554) ባለይዞታዎች ተደራጅተው ወደ ስራ እንዲገቡ ተደርጓል፡፡ አፈፃፀሙ 35.6% ነው፡፡

## ለልማት ተነሽዎች የብድር አገልግሎት መስጠት

በልማት ምክንያት ለሚነሱ ባለይዞታዎች በዘላቂነት እንዲቋቋሙ ለማስቻል አንዱ የብድር አገልግሎት እንዲያገኙ ማስቻል ነው፡፡ በዚህም የአመቱ ዕቅድ 3,030፣ የብድር አገልግሎት

እንዲያገኙ ዕቅድ ተይዞ 949 (31.3%) (ወንድ 686፣ ሴት 263) ተጠቃሚዎች 73.91 ሚሊዮን ብር የብድር አገልግሎት እንዲያገኙ ሲደረግ 16,464፣ ተነሺ ባለይዞታዎች ያላቸውን ካፒታል መሰረት በማድረግ በተሰማሩበት የኑሮ አማራጭ የገቢያ ትስስር እንዲፈጠርላቸው በዕቅድ ተይዞ 3,711( ወንድ 2,476 ሴት 1,235) ባለይዞታዎች የገቢያ ትስስር እንዲፈጠርላቸው ተደርጓል፡፡ አፈፃፀሙ 22.5% ነው፡፡

## ነፃ መሬት መለየትና ለባለሀብቶች ማስተላለፍ

ነፃ መሬት መለየትና ለባለሀብቶች ለማስተላለፍ በተሰራው ስራ ዕቅድ 10,650 ለግብርና ኢንቨስትመንት የሚውል እና ለባለሃብቶች የሚተላለፍ መሬት ለመለየት ታቅዶ 8,597 ሄክታር ነፃ መሬት (በምዕራብ ጎንደር፤ ሰ/ጎንደር፣ ደ/ጎንደር፣ ማዕ/ጎንደር፣ ሰ/ወሎ እና ደቡብ ወሎ ዞኖች) በመለየት የእቅዱን 81% ሲፈጸም 162 ሄክታር ለኢንዱስትሪ ፕሮጀክቶች የሚውል ነጻ መሬት ለመለየት ታቅዶ በዞንና ወረዳ ደረጃ የሚተላለፍ 286 ሄክታር በመለየት የአመቱን እቅድ 176% መፈጸም ተችሏል፡፡60 ሄክታር ለአገልግሎት ዘርፍ የሚውል ነጻ መሬት ለመለየት ታቅዶ 42 (70%) ሄክታር በዞንና ወረዳ ደረጃ የሚተላለፍ መሬት መለየት ተችሏል፡፡ በድምሩ በሶስቱም ዘርፎች (በግብርና ፣ በኢንዲስትሪና በአገልግሎት) የተለየ ነፃ መሬት በዓመት እቅድ 10,872፣ ክንውን 8,925 ሄክታር (82%) መሬት የመለየት ስራ ተሰርቷል፡፡ በዚህም ነጻ መሬት በተለየባቸው ዞኖች ነጻ መሬቶችን ለማስተላለፍ በዞን ደረጃ በግብርና ኢንቨስትመንት ዘርፍ 79 ባለሃቶች፣ በኢንዱስትሪ ኢንቨስትመንት ዘርፍ 158 ባለሃብቶች፣ በአገልግሎት ዘርፍ 42 ባለሃብቶች በድምሩ 279 ባለሀብቶችን የመለየት ስራ ተሰርቷል፡፡ አፈፃፀሙ 80% ነው፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ በበጀት ዓመቱ 5,283,480 የአገልግሎት ገቢ ብር ከሁሉም ዘርፎች ለመሰብሰብ ታቅዶ በጠቅላው በሁሉም ዘርፎች ብር 35,107,437 መሰብሰብ ተችሏል፡፡ አፈፃፀሙ 66% ነው፡፡

## የገጠር ካዳስተር ካርታ ዝግጅት ስራ

የገጠር ካዳስተር ካርታ ዝግጅት ስራ ለመስራት በተደረገው ጥረት የ250 ቀበሌዎችን የመስክ ካርታ ለማዘጋጀት ታቅዶ የ87 ቀበሌዎች (96,135 በካርታ ቁጥር) የመስክ ካርታ በማዘጋጀት 35% ማከናወን የተቻለ ሲሆን የ300 ቀበሌዎችን የህዝብ ማስተቻ ካርታና ተያያዥ መረጃ ለማዘጋጀት ታቅዶ የ119 ቀበሌዎች ካርታ በማዘጋጀት 40% ማከናወን ተችሏል፡፡ እንዲሁም በበጀት ዓመቱ የ275 ቀበሌዎችን የማሳ ካርታና ተያያዥ መረጃዎችን ለማዘጋጀት ታቅዶ የ198 ቀበሌዎች 1,131,730 ማሳ ካርታ በማዘጋጀት የእቅዱን 72% ማከናወን ተችሏል፡፡

## የኢንቨስትመንት መሬት ስራ

የገጠር ኢንቨስትመንት መሬት በአዲስ የተለዩ 50 የኢንቨስትመንት መሬት መረጃን ለማሰባሰብ፣ ለማደረጃትና ለመስጠት በእቅድ ተይዞ 50 (100%) ተከናውኗል፣አዲስ ውል ለሚወስዱ ለ200፣ ባለሃብቶች የማሳ ካርታ ለማዘጋጀትና ለመስጠት ታቅዶ ለ47 ባለሀብቶች ተዘጋጅቶ እንዲወስዱ በማድረግ ከዓመቱ 24% የተፈጸመ ሲሆን ነባር ውል ለሚያድሱ ለ40 ባለሃብቶች የማሳ ካርታ ለማዘጋጀትና ለመስጠት ታቅዶ ለ6 ባለሀብቶች ተዘጋጅቶ እንዲወስዱ በማድረግ 15% መፈፀም ተችሏል፡፡

## የከተማ ካዳስተር ካርታ ዝግጅት

የከተማ ካዳስተር ካርታ ስራዎች ለመስራት በተደረገው ጥረት በከተሞች፣ ክፍለ ከተማ/ ቀበሌ፣ሰፈር፣ብሎክና ፓርስልን ያካተተ 14 ጠቋሚ (ኢንዴክስ) ካርታ እንዲዘጋጅ ታቅዶ 10 ካርታ ማዘጋጀት የተቻለ ሲሆን ኦርቶፎቶውን በመጠቀም 77 የቀጠና ጠቋሚ ካርታ ለማካለል ታቅዶ 52 ካርታ 190 የሰፈር ጠቋሚ ካርታ ተካሏል፡፡ለ77,400 ባለ ይዞታወች የይዞታ መረጃ በመስብሰብ ለእያንዳንዱ በተዘጋጀው ጠቋሚ ካርታ መሰረት መለያ ኮድ ለመስጠትና ይዞታን፣የይዞታ ባለቤቶችን በገላጭ መረጃን ከስእላዊ መረጃ ጋር በልዩ ኮድ ለማስተሳሰር የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ማዘጋጀትና በመስክ የተሰጠውን መለያ ኮድ /UPIN/ ወደ ጅኦ ዳታ ቤዝ እንዲገባ ለማድረግ ታቅዶ 22,013 ኮድ መስጠት የተቻለ ሲሆን 21,418 በልዩ ኮድ ተሳስሯል እንዲሁም 22,013 ወደ ጅኦ ዳታ ቤዝ እንዲገባ ሲደረግ 14,210 የይዞታ ጠቋሚ ካርታዎች ተዘጋጅቷል፡፡



ለከተማ መሬት እና ፕላን ዘርፍ ባለሙያዎችየብቃት ተኮር ስልጠና ሲሰጥ

## የካዳሰተራል ቅየሳ ስራ

የካዳስተራል ቅየሳ ስራዎች አንጻር በበጀት ዓመቱ በከተሞች ለ77,400፤ የይዞታ ወሰን ማካለል እና ቅየሳ ስራ ለመስራት ታቅዶ 22,693 (29%) የይዞታ ወሰን የማካለል ስራ 22,693 (29%) የይዞታ ወሰን ቅየሳ ስራ የተሰራ ሲሆን 1,600 የ2ኛ ደረጃ እና የ3ኛ ደረጃ የቅየሳ መቆጣጠሪያ ሞኑመንት በስታንዳርድ መሰረት በማምረት ለመትከል ታቅዶ 455 ሞኑመንት በማምረት የተተከለ ሲሆን ከዓመቱ 28% መፈፀም ተችሏል፡፡

## የመልካም አስተዳደር ስራ

የመልካም አስተዳደር ስራዎችን ለመስራት በተደረገው ጥረት አላግባብ ይዞታቸውን ያጡ ተጋላጭ የህብረተሰብ ክፍሎችን መረጃ በማጥራት ይዞታቸው እንዲመለስላቸው ለማድረግ የ7,440 (ወንድ 4,442፣ ሴት 2,998) ባለመብቶች ወላጆቻቸውን ያጡ ህፃናት፣ አረጋውያን፣ አካል ጉዳተኞችና ሌሎችም) መሬት እንዲመለስላቸው ታቅዶ ለ1921 (26%) ባለ ይዞታወች (ወንድ 944 ሴት 977) ማስመለስ የተቻለ ሲሆን1916 ከመሬት ይዞታ መብት ህጉ ከነፈጋቸው አካላት መሬት በአመቱ 227 ሄክታር ለማስመለስ ታቅዶ ከተለያየ ወረዳዎችና ቀበሌዎች የ891 ህግ ከነፈጋቸው አካላት 402 ሄክታር መሬት ማስመለስ ተችሏል፡፡ አፈፃፀም ከባለይዞታ 47 ሲሆን ከማሳ ስፋት 177 ፐርሰንት ነው፡፡ እንዲሁም 41,088 የተወረሩና የተገፉ ወል መሬቶች ላይ መሬት ማስከበርና ማስመለስ ስራ በመስራት በአመቱ 15,842 ሄክታር መሬት ማስመለስ ስራ ለመስራት ታቅዶ ከተለያየ ወረዳዎችና ቀበሌዎች የ28,355 ህገ-ወጦች 7,957 ሄክታር መሬት ማስመለስ ስራ ተከናውኗል አፈጻጸም ከባለይዞታ 69 ፐርሰንት ከማሳ ስፋት 50 ፐርሰንት ሆኗል፡፡በመሆኑም ሊያጋጥም የሚችልን የመልካም አስተዳደር ችግር መፍታት ተችሏል፡፡



መሬት አሰተዳደር ሰርዓት ለፋርድ ቤት አገልግሎት አሠጣት ባለው ሚና የምክክር መድረክ-ባህርዳር

## ገቢ

### ግብር ከፋዩ ማህበረሰብ ያለበት ሁኔታ

በበጀት ዓመቱ በተደረገው የቅንጀት ስራ ደረጃ “ሀ”753፣ ደረጃ “ለ”699፣ ደረጃ “ሐ”25,331 ፣ ማህበራት 3,050 በድምሩ 29,833 ግብር ከፋዮች ወደ ንግድ መረቡ የገቡ መሆኑ እና 520 ግብር ከፋዮች የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ እንዲጠቀሙ እና ተገቢውን ግብር በመክፈል የመንግስትን ለመንግስት የቁሳርን የቁሳር እንዲሉ የማድረግ ስራ የተሰራ ሲሆን በአንፃሩ ደግሞ በክልሉ የተፈጠረውን የፀጥታ ችግር እንደ ሽፋን በመጠቀም ግብራቸውን በወቅቱ አሳውቀው አለመክፈል፣ ወደ 802 የሚሆኑ ግብር ከፋዮች ብር 534,432,474.65 የያዘ በሃሰተኛ ደረሰኞች ግዥ በማቅረብ ለማጭበርበር ጥረት እያደረጉ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

በተመሳሳይ ድርጅት ላይ ፈቃድ በመቀያየር ግብር በመሰወር ደረጃ “ሀ”750 ፣ ደረጃ“ለ”148 ፣ደረጃ “ሐ” 9752 እና ማህበራት 341 በድምሩ 10,991 ግብር ከፋዮች ከንግድ መረቡ የወጡ መሆኑ፣ ለሸጡት እቃና ለሰጡት አገልግሎት ለተጠቃሚው ደረሰኝ አለመስጠትና ፣አልፎ አልፎ ደረሰኝ እንኳ ቢቆርጡም የዕቃ ቁጥር መቀነስ እና ከመሸጫ ዋጋ በታች አድርጎ ሽያጭ መፈፀም (Under invoice)፣ ከገቢ ተቋሙ ክትትል በመሰወር በጭለማና ድብቅ በሆነ መጋዝን ያለ ደረሰኝ ግብይት መፈፀም የመሳሰሉት ሁኔታዎች በገቢ ግብር ከፋዩ ማህበረሰብ ዙሪያ የታዩ አመለካከቶች በመሆናቸው መታረም አለባቸው፡፡



*ህብረተሰቡ ግብር ሲከፍል*

### የተሰበሰበ ገቢ

ክልሉ ያጋጠሙትን ሰው ሰራሽ እና ተፈጥሯዊ ተግዳሮቶች በመቋቋም የጀመረውን የልማት ጉዞ ለማስቀጠል እና ድህነትን ለመቀነስ ዘመናዊ የታክስ ስረዓት ዘርግቶ እና የህግ

ተገዥነትን አረጋግጦ አመራሮችን እና ፈጻሚዎችን ለስራ ዝግጁ በማድረግ እና አጋር አካላትን ማለትም የደረጃ "ሀ" የደረጃ "ለ" እና "ሐ" ግብር ከፋዮችን በንቅናቄ መድረኮች ፣በሞንታርቦ ፣በበራሪ ወረቀት እና በልዩ ልዩ የቅስቀሳ እና የማሳወቂያ መንገዶችን ተጠቅሞ ግብር በወቅቱ እንዲከፍሉ በማድረግ የክልሉ ኢኮኖሚ የሚያመነጨውን ገቢ በተገቢው መንገድ በማሰባሰብ የክልሉን የልማት ፋይናንስ ፍላጎት ለማሳካት ቢሮው ከፍተኛ ስራ ሰርቷል፡፡ በዚህም የመደበኛ ገቢ ብር 56.15 ቢሊዮን ለመሰብሰብ ታቅዶ የነበረ ሲሆን ክንውን ብር 37,436,730,030 ሆኗል፡፡ አፈፃፀሙም 66.67% ነው፡፡

ከከተማ አስተዳደር የአገልግሎት ገቢ ብር 15.50 ቢሊዮን ለመሰብሰብ ታቅዶ ክንውን ብር 4,679,027,219 ነው፡፡ አፈፃፀሙም 30.19% ሆኗል፡፡ ከመንግስት ተቀጣሪዎች የስራ ግብር ብር 8.4 ቢሊዮን ለመሰብሰብ ታቅዶ ክንውኑ ብር 7,848,752,106 ሲሆን አፈፃፀሙም 93.36% ነው፡፡

ከግልና ከመንግሥታዊ የልማት ድርጅቶች ተቀጣሪዎች የስራ ግብር ብር 7.56 ቢሊዮን ለመሰብሰብ የታቀደ ሲሆን ክንውን ብር 6,484,235,811 ሲሆን አፈፃፀሙ 85.72 ሆኗል፡፡በበጀት ዓመቱ 1.046 ቢሊዮን የኪራይ ገቢ ለመሰብሰብ ታቅዶ ክንውን ብር 455,863,635 ለመሰብሰብ ተችሏል፡፡አፈፃፀሙም 43.57% ነው፡፡ በ2016 ዓ.ም ከንግድ ትርፍ ግብር ብር 6.76 ቢሊዮን ለመሰብሰብ ታቅዶ ክንውን ብር 3,419,880,120 ሲሆን አፈፃፀሙም 50.61% ነው፡፡

በ2016 ዓ.ም ከተጨማሪ እሴት ታክስ ግብር ብር 13.10 ቢሊዮን ለመሰብሰብ የታቀደ ሲሆን ክንውን ብር 9,101,588,828 ነው፡፡ አፈፃፀሙ ከአመቱ 69.47% ነው፡፡በበጀት ዓመቱ ከተርን ኦቨር ታክስ ግብር ብር 5.28 ቢሊዮን ለመሰብሰብ የታቀደ ሲሆን ክንውን ብር 1,461,759,810 ነው፡፡አፈፃፀሙም 27.66% ነው፡፡ ከአርሶ አደሮች ከእርሻ ሥራ ገቢ ግብር እና ከመሬት መጠቀሚያ ብር 508.79 ሚሊዮን ለመሰብሰብ የታቀደ ሲሆን ክንውን ብር287,297,866 ለመሰበሰብ ተችሏል፡፡ አፈፃፀሙም ከአመቱ 56.47% ነው፡፡ በበጀት ዓመቱ ውዝፍ ካለባቸው ከ18,742 ግብር ከፋዮች ብር 1,288,604,156 ለመሰብሰብ የታቀደ ሲሆን እስከ ሰኔ 30 የከፈሉ 9,134 /48.74%/ ግብር ከፋዮች ብር 489,268,520/ የተሰበሰበ ሲሆን አፈጻጸሙ 37.97% ነው፡፡

በ2016 ዓ.ም ከፌዴራል መንግስቱ በቀመሩ መሰረት ለክልላችን ሊላክልን ይችላል በሚል ብር 16,126,002,043 ለመሰብሰብ ታቅዶ እስከ ሰኔ 30 2016 ዓ.ም ድረስ 12,634,700,820 (78%) መሰብስብ ተችሏል፡፡የቅድመ ግብርና የተጨማሪ እሴት ታክስ ዊዝ ሆልዲንግ ትርፍን በተመለከተ ብር 2,980,122,033 ለመሰብሰብ በእቅድ የተያዘ ሲሆን እስከ ሰኔ 30 2016 ዓ.ም ድረስ ብር 2,320,757,443 (78%) መሰብሰብ ተችሏል፡፡ ከመንግስት ዩኒቨርስቲዎች ተመርቀው የወጭ መጋራት መክፈል ከሚገባቸው ብር 44,000,0000 ለመሰብሰብ ታቅዶ እስከ ሰኔ 30 2016 ዓ.ም ብር 33,646,106.37 መሰብሰብ ተችሏል አፈጻጸሙ (76.47%) ሆኗል፡፡ በአጠቃላይ በበጀት አመቱ ከዋና ዋና የግብር ገቢ ምንጮች 71.650.000.000 ብር ገቢ ለመሰብሰብ ታቅዶ 421.167.572.49 ገቢ ለመሰብሰብ የተቻለ ሲሆን አፈጻጸሙ 68.78% ነው፡፡

## የተገልጋዮችን እርካታ ማሳደግ

የቀረቡ የታክስ በዛብኝ ቅሬታዎችን በመመርመር እና በማጣራት በየደራጃው የሚሰጡ አገልግሎቶች ቀልጣፋ፣ ተደራሽ፣ ከአድሎ የፀዳና ፍትሀዊ ለማድረግ ታቅዶ የተሰራ ሲሆን በዚህም እስከ ሰኔ 30 ዓ.ም በአገልግሎት አሰጣጥ ዙሪያ 875 ቅሬታዎች ቀርበው 828(94.63%) ምላሽ ያገኙ ሲሆን ምላሽ ያልተሰጠው ደግሞ 47/5.37%/ ናቸው፡፡

ሌላው የተገልጋዮችን ፍላጎት ከማሟላት አኳያ ለሚጠይቁት አገልግሎት ፈጣን ምላሽ መስጠት ሲሆን በዚህም የክሊራንስ ይሰጠኝ ጥያቄ ፤የሥራ ግብር ክፍያ ማስረጃ 8,742 ፣ የወጭ መጋራት 964 ፣ የባንክ ብድር 19,002 ፣ የጨረታ መሳተፊያ ማስረጃ 1,234 ፣ ለንግድ ዘርፍ መቀየሪያ 2,779 ፣ ለንግድ ፈቃድ ማደሻ 185,170 ፣ አዲስ ንግድ ፈቃድ ለሚያወጡ ደንበኞች ማስረጃ 17,448 ፣ ስመ-ንብረት ዝውውር 15,885 ፣ የተሽከርካሪ ምርመራ 18,796 ፣ የደረሰኝ የህትመት ጥያቄ 8,386 እና የድርጅት መዝጊያ ክሊራንስ 10,284 ሌሎች ልዩልዩ ጉዳዮች 2,253 በድምሩ 290,943 ግብር ከፋዮች ባቀረቡት ጥያቄ መሰረት ከላይ የተጠቀሱትን የተለያዩ አገልግሎቶች እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡

## የንግድ ግብር ከፋዮችን ቁጥር ማሳደግ

በበጀት አመቱ የደረጃ "ሀ" የደረጃ "ለ" እና የደረጃ 'ሐ" የንግድ ግብር ከፋዮችን ቁጥር 406,344 ለማሳደግ በዕቅድ የተያዘ ሲሆን ክንውኑን 394,286 በማድረስ አፈጻጸሙን ወደ

/97.03%/ ማድረስ ተችሏል፡፡በመሆኑም ለምስጉን ግብር ከፋዮ እውቅናና ሽልማት መስጠት ተችሏል፡፡




*ለምስጉን ግብር ከፋዮች እውቅናና ሽልማት ሲሰጥ*

## ማዕድን ሃብት ልማት

### የኮንስትራክሽን ማዕድናት የማምረት ስራ ፈቃድ መስጠት

በበጀት ዓመቱ ኢንቨስትመንትን በማጐልበት የማዕድን ነክ ፋብሪካዎች እንዲገነቡ 230 (79 የምርመራ እና የ151 የምርት) ፈቃዶችን ለመስጠት ዕቅድ ተይዞ 235 (158 የምርመራ፣ 77 የምርት) ፈቃዶችን ማከናወን ተችሏል፤ አፈፃፀሙም ከ100% በላይ ሆኗል፡፡

በበጀት ዓመቱ ለ1,362 በማዕድን ዘርፍ ለሚሰማሩ ኢንተርፕራይዞች በአነስተኛ ኮንስትራክሽንና ባህላዊ የማዕድን ማምረት ስራ ፈቃድ ለመስጠት ዕቅድ ተይዞ 1,203 ማከናወን በመቻሉ አፈፃፀሙ 88.32 በመቶ ሆኗል፡፡

### ከማዕድን ኢንቨስትመንት የተገኘ ገቢና የስራ እድል

በማዕድን ኢንቨስትመንት ዘርፍ የሚመዘገብ የ7 ቢሊዮን ብር የካፒታል መጠን ለማስመዝገብ ዕቅድ ተይዞ 6,289,319,898 ብር ማስመዝገብ በመቻሉ አፈጻጸሙ 89.84% ሊሆን ችሏል፡፡ ለዜጐች የስራ እድል መፍጠርን በተመለከተም በበጀት ዓመቱ በማዕድን ዘርፍ ከሚሰማሩ ባለሃብቶች፣ ኩባንያዎች እና ኢንተርፕራይዞች ለ27,087 (ወንድ 17,633፣ ሴት 9,454) ዜጐች

የስራ ዕድል ለመፍጠር ዕቅድ ተይዞ ለ25,233 ዜጎች (ወንድ 16,510 ሴት 8,723) የስራ ዕድል ተፈጥሯል፤ አፈጻፀሙም 93.15% ነው፡፡

## የውጭ ምንዛሬ ገቢ

በበጀት ዓመቱ 26,026 ኪሎ ግራም የኦፖል ማዕድናትን እና 120 ኪሎ ግራም ወርቅ ወደ ውጭ በመላክ ለማዕከላዊ ገበያ በማቅረብ 6,260,445 የአሜሪካ ዶላር ለማግኘት ዕቅድ ተይዞ 3,714,274 ዶላር የውጭ ምንዛሬ ተገኝቷል።በመሆኑም 59.32% የምንዛሬ አፈፃፀም አሳይቷል፡፡

## የውጭ ምንዛሬን ማዳን

በውጭ አገር የሚገቡትን ማዕድናት በአገር ውስጥ ማዕድናት ለመተካት ከተያዘው ግብ አኳያ በበጀት አመቱ 375,000 ቶን ምርት በመተካት 64,657,637 ዶላር ለማዳን ታቅዶ 390,380 ቶን ምርት በመተካት 67,309,462.46 ዶላር የውጭ ምንዛሬ ማዳን ተችሏል፤በዚህም ከምርትም ሆነ የውጭ ምንዛሬን ከማዳን አንጻር ከ100% በላይ መፈጸም ተችሏል፡፡

## የማዕድን ምርት መጠንን ማሳደግ

በበጀት ዓመቱ በክልላችን የሚመረተውን የኮንስትራክሽን የማዕድን ምርት መጠን 6,757,148 ኪዩቢክ ሜትር ለማድረስ ዕቅድ ተይዞ 8,950,883 ኪዩቢክ ሜትር የኮንስትራክሽን ማዕድን ምርት እንዲመረት በመደረጉ አፈፃፀሙ ከ100% በላይ መሆን ችሏል፡፡

## የማዕድን ነክ ፋብሪካዎች ድጋፍና ክትትል

በበጀት ዓመቱ 8 ከፍተኛ የማዕድን ነክ ፋብሪካዎችን የሲሚንቶ፣ የድንጋይ ከሠል፣ የግራናይት፣ የማርብልና የጅብሠም ወዘተ ድጋፍና ክትትል ለማድረግ ዕቅድ ተይዞ 8 እያመረቱ ያሉትን ምርታቸውን እንዲያሳድጉና እየተገነቡ ያሉትን ደግሞ የግንባታ ፍጥነታቸውን እንዲጨምሩ የድጋፍና ክትትል ስራ ተሰርቷል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ በመካከለኛና አነስተኛ የማእድን ነክ ኢንዱስትሪዎች ላይ በተደረገው ድጋፍና ቁጥጥር 128 ባለፈቃዶች ህጉን እንዲያከብሩና ወደ ህጋዊነት እንዲመለሱ ተደርገዋል፡፡ በሌሎች 506 የጊዜ ገደባቸው ለተጠናቀቁ እና 41 ውሉን ያላከበሩ ፈቃዶችን የመሰረዝ፣ የመዝጋትና ወደ ሌሎች ኢንተርፕራይዞች የማስተላለፍ ስራዎች ተሰርተዋል፡፡ በገቡት ውል መሠረት ወደ ስራ ባልገቡ ባለፈቃዶች ላይ በተገኙ ጉድለቶች መሰረት 534 ማስጠንቀቂያ፣ 451 የመሰረዝና

355 የመዝጋት ሥራዎች ተከናውነዋል፡፡እንዲሁም በበጀት አመቱ ለለሚ ናሽናል ሲሚንቶ ፋብሪካ ድጋፍና ክትትል በማድረግ ስራ እንዲጀምር ማድረግ ተችሏል፡፡




የለሚ ናሽናል ሲሚንቶ ፋብሪካ-ሰሜን ሸዋ ዞን እንሳሮ ወረዳ (ለሚ ከተማ)

## ሥራና ስልጠና

### የሥራ ዕድል ፈጠራና ኢንተርፐራይዝ ልማት

በበጀት ዓመቱ በከተማ 591,494፣ በገጠር 640,786 በድምሩ 1,232,280 ስራ ፈላጊዎችን ለመመዝገብ ታቅዶ፣ በከተማ ወንድ 291,290፣ ሴት 285,602 በድምሩ 576,892፤ በገጠር ወንድ 318,783፣ ሴት 188,921 በድምሩ 507,704 በጠቅላላው በከተማና በገጠር ወንድ 610,073፣ ሴት 474,523 በድምሩ 1,084,596 ስራ ፈላጊዎች ተመዝግበዋል፡፡ አፈፃፀሙም በከተማ 97.53%፣ በገጠር 79.23% ሲሆን በአጠቃላይ ስራ ፈላጊዎችን ከመመዝገብ አንጻር 88% ማከናወን ተችሏል፡፡

በከተማና በገጠር ከተመዘገቡት ስራ ፈላጊዎች ውስጥ 13,000 ከስደት ተመላሾችን ለመመዝገብ ታቅዶ 18,104 (ወንድ 6,098፣ ሴት 12,006) መመዝገብ በመቻሉ አፈጻጸሙ 139% ሆኗል፡፡ 2,160 አካል ጉዳተኞችን ለመመዝገብ ታቅዶ 3,391 (ወንድ 2,097፣ ሴት 1,294) መመዝገብ በመቻሉ አፈጻጸሙ 156% ሆኗል፡፡ 60,000 የዩኒቨርስቲ ምሩቃንን ለመመዝገብ ታቅዶ 54,008 (ወንድ 31,900፣ ሴት 22,108) መመዝገብ በመቻሉ አፈጻጸሙ 90% ሆኗል፡፡ 90,000 የቴክኒክና ሙያ ምሩቃንን ለመመዝገብ ታቅዶ 83,095 (ወንድ 36,468፣ ሴት 46,627 ) መመዝገብ በመቻሉ አፈጻጸሙ 92% ሆኗል፡፡



አዲሱ ቴዎድሮስና ጓደኞቹ የንብ ማነብ ሽርክና ማህበር /ንፋስ መውጫ/

## በከተማ የኢንተርፕራይዝ ምሥረታና ሥራ ዕድል ፈጠራ

በበጀት ዓመቱ በከተማ በሚከናወኑ በግብርና፣ በኢንዱስትሪና በአገልግሎት ዘርፎች 41,357 ኢንተርፕራይዞች በመመስረት ለ591,494 የስራ ዕድል ለመፍጠር ታቅዶ 21,129 ኢንተርፕራይዞች የተመሰረቱ ሲሆን በዚህም ቋሚ የስራ እድል የተፈጠረላቸው ወንድ 170,521፣ ሴት 201,550 በድምር 372,071 ሲሆኑ ጊዜያዊ የስራ እድል የተፈጠረላቸው ደግሞ ወንድ 107,750፣ ሴት 71,998 በድምሩ 179,748 ስራ ፈላጊዎች በአጠቃላይ ወንድ 278,271፣ ሴት 273,548 በድምሩ ለ551,819 ስራ ፈላጊ ዜጐች የሥራ ዕድል መፍጠር ተችሏል፤ አፈፃፀሙ ሲታይም በኢንተርፕራይዝ 51%፣ በስራ ዕድል ፈጠራ ደግሞ 93.32% ማከናወን ተችሏል።



ጁኒየር ጋርመንት ባህርዳር

## የኢንተርፕራይዝ ምሥረታና ሥራ ዕድል ፈጠራ

በበጀት ዓመቱ በገጠር በተከናወኑ በግብርና፣ በኢንዱስትሪና በአገልግሎት ዘርፎች 26,818 ኢንተርፕራይዞች በመመስረት ለ640,786 የስራ ዕድል ለመፍጠር ታቅዶ 7,236

ኢንተርፕራይዞች የተመሰረቱ ሲሆን በዚህም ቋሚ የስራ እድል የተፈጠረላቸው ወንድ 201,464፣ ሴት 95,275 ድምር 296,739 ሲሆኑ ጊዜያዊ የስራ እድል የተፈጠረላቸው ደግሞ ወንድ 90,749፣ ሴት 31,689 ድምር 122,438 ናቸው፡፡ በአጠቃላይ ሲታይ ወንድ 292,213፣ ሴት 126,964 በድምሩ ለ419,177 ስራ ፈላጊ ዜጐች የሥራ ዕድል መፍጠር ተችሏል፡፡ አፈፃፀሙም ሲታይ በኢንተርፕራይዝ 26.98%፣ በስራ ዕድል ደግሞ 65.41% ማከናወን ተችሏል፡፡

## የኢንተርኘራይዞችና አንቀሳቃሾች መረጃ

በክልሉ በአጠቃላይ በኢንዱስትሪ ዘርፍ 28,695 ኢንተርፕራይዞች (ወንድ 56,078፣ ሴት 24,995 ድምር 81,073 አንቀሳቃሽ)፣ በግብርና ዘርፍ 6,626 ኢንተርፕራይዞች (ወንድ 17,943፣ ሴት 8,470 ድምር 26,413 አንቀሳቃሽ)፣ በአገልግሎት ዘርፍ 106,254 ኢንተርፕራይዞች (ወንድ 100,131፣ ሴት 55,847 ድምር 155,978 አንቀሳቃሽ) በአጠቃላይ 141,575 ኢንተርፕራይዞች (ወንድ 174,152፣ ሴት 89,312 ድምር 263,464 አንቀሳቃሽ) ይገኛሉ፡፡

## በተቋቋሙ ኢንተርኘራይዞች የተፈጠረ የሥራ ዕድል

በበጀት ዓመቱ በከተማና በገጠር 68,175 ኢንተርፕራይዞችን በመመስረት 1,232,280 (ቋሚ 985,824 እና ጊዜያዊ 246,456) የሥራ ዕድል ለመፍጠር ታቅዶ 28,365 ኢንተርፕራይዞች የተቋቋሙ ሲሆን በጠቅላላው 970,996 የስራ ዕድል መፍጠር ተችሏል፤ ከእነዚህ ግለሰቦች መካከል ወንድ 1,278፣ ሴት 62,283 ድምር 63,561 የስራ እድል ተጠቃሚዎች የውጭ አገር የስራ ስምሪት ቋሚ የስራ እድል የተፈጠረላቸው ናቸው፡፡በጥቅሉ አፈፃፀሙ ሲታይ በኢንተርፕራይዝ 41.6%፣ በስራ ዕድል ፈጠራ ደግሞ 78.79% ማከናወን ተችሏል፡፡

## በተፈጠረው የስራ ዕድል የምሩቃን ተጠቃሚነት

በበጀት ዓመቱ በከተማና ገጠር ለ150,000 (በከተማ 105,314፣ በገጠር 44,686) ምሩቃን የስራ እድል ለመፍጠር ታቅዶ በከተማ በቋሚ የስራ እድል 47,657፣ በጊዜያዊ የስራ እድል 12,374 በድምሩ 60,031 (57%) እንዲሁም በገጠር በቋሚ የስራ እድል 11,033፣ በጊዜያዊ የስራ እድል 1,650 በድምሩ 12,683 (28.38%) ተመራቂዎች የስራ እድል ተፈጥሯል፡፡ በአጠቃላይ ሲታይ ወንድ 37,049፣ ሴት 35,665 በድምሩ 72,714 (48.47%) ምሩቃን የስራ እድል ተፈጥሮላቸዋል፡፡

## የአገር ውስጥ የገበያ ትስስር

በበጀት ዓመቱ በከተማና በገጠር በሀገር ውስጥ ገበያ በዕድገት ተኮር ዘርፎች ለ40,000 (በከተማ 32,000፣ በገጠር 8,000) ኢንተርፕራይዞች፣ ለ160,000 (በከተማ 128,000፣ በገጠር 32,000) አንቀሳቃሾች ብር 5,670,900,000 (በከተማ 4,536,736,000፣ በገጠር 1,134,164,000) በገበያ ለማስተሳሰር ታቅዶ ለ27,631 (በከተማ 23,427፣ በገጠር 4,204) ኢንተርፕራይዞች ለ109,608 (ወንድ 72,799፣ሴት 36,809) አንቀሳቃሾች በብር 4,642,318,409 (በከተማ 4,074,423,913፣ በገጠር 567,894,496) የገበያ ትስስር መፍጠር የተቻለ ሲሆን አፈፃፀሙ በኢንተርፕራይዝ 69.07%፣ በአንቀሳቃሽ 68.50%፣ በብር 81.86% መፈፀም ተችሏል፡፡

## የውጭ ሀገር የገበያ ትስስር

በበጀት ዓመቱ በኤክስፖርት ስታንዳርድ የማምረትና ወደ ውጭ ሀገር ኤክስፖርት ለማድረግ አቅምና ፍላጐት ያላቸውን 126 ኢንተርፕራይዞች (1,260 አንቀሳቃሾች) 1,360,002 (USD) ዶላር የውጭ ሀገር የገበያ ትስስር ለመፍጠር ታቅዶ 62 ነባርና 20 አዲስ በድምሩ 82 ኢንተርፕራይዞች ወንድ 370፣ ሴት 245 በድምሩ 615 አንቀሳቃሾች ከምርት ሽያጭ 656,900 (USD) ዶላር ገቢ ማግኘት ተችሏል፤ አፈፃጸሙ በኢንተርፕራይዝ 65.07%፣ በአንቀሳቃሽ 48.80%፣ በብር 48.30% መፈፀም ተችሏል፡፡

## ቁጠባና ብድር

የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን የፋይናንስ ችግር ለመፍታት እንዲያመችና የቁጠባ ባህል እንዲጐለብት ለማድረግ በበጀት አመቱ ብር 2,680,330,729 (በከተማ 2,144,264,583፣ በገጠር 536,066,146) እንዲቆጥቡ ለማድረግ ታቅዶ ከ106,094 (በከተማ 84,474፣ በገጠር 21,620) ቆጣቢዎች ብር 2,063,493,433 (በከተማ 1,462,645,893፣ በገጠር 600,847,540) ማሰባሰብ የተቻለ ሲሆን አፈፃፀሙም በብር 76.98% ማከናወን ተችሏል፡፡

## የሰልጣኞች ቁጠባ

በመንግስት ኮሌጆች ነባርም ሆነ አዲስ ሰልጣኞች በስልጠና ቆይታቸው ወቅት ለኢንተርፕራይዝ ምስረታ ቅድሚያ ማሟላት ከሚገባቸው መስፈርቶች አንዱ የሆነውን ብድር ለማግኘት እንዲረዳቸው የፕሮጀክታቸው 20% ቁጠባ ብር 176,618,000 መቆጠብ የሚል እቅድ ተይዞ በስልጠና ላይ ካሉት 37,335 ሰልጣኞች መካከል ወንድ 5,870፣ ሴት 8,435 ድምር 14,305

ነባርና አዲስ ሰልጣኞች ብር 7,734,674.74 (4.37%) እንዲቆጥቡ ተደርጓል፤ አፈፃፀሙም በስልጠና ላይ ካሉት ጋር ሲነጻጸር 38.31% ነው፡፡

## የብድር ስርጭት

የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን የፋይናንስ ችግር ለመፍታት በበጀት አመቱ በመደበኛ ብድር ለ23,385 ኢንተርፕራይዞች (46,770 አንቀሳቃሾች) 1,753,882,655 ብር ብድር ለመስጠት ታቅዶ፣ በመደበኛ ብድር ለ14,048 ኢንተርፕራይዞች (25,965 አንቀሳቃሾች) 1,130,209,249 ብር ተሰራጭቷል፤ አፈፃፀሙም በኢንተርፕራይዝ 60.07%፣ በአንቀሳቃሽ 55.51%ና በብር 64.44% ተከናውኗል፡፡

በበጀት ዓመቱ ተዘዋዋሪ ብድር ብር 1,596,530,756 ለ7,983 ኢንተርፕራይዞች (ለ15,965 አንቀሳቃሾች) በማሰራጨት ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ ለ4,820 ኢንተርፕራይዞች (ለ5,599 አንቀሳቃሾች) ብር 590,793,512 ብድር መስጠት ተችሏል፡፡ አፈፃፀሙም በኢንተርፕራይዝ 60.37%፣ በአንቀሳቃሽ 35.07% እና በብር 37% ማከናወን ተችሏል፡፡

## የኢንተርፕራይዞች የዕድገት ደረጃ ሽግግር

በበጀት ዓመቱ የእድገት ደረጃንና ክፍተትን መሠረት ያደረገ የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን ድጋፍ በመስጠት በትኩረት ዘርፍ የተሰማሩ በሁሉም ደረጃዎች 13,445 ኢንተርፕራይዞችን (በከተማ 12,101፣ በገጠር 1,345) ከደረጃ ደረጃ ለማሸጋገር ታቅዶ በከተማ 7,976፣ በገጠር 0 በድምሩ 7,976 ኢንተርፕራይዞችን ማሸጋገር ተችሏል፤ አፈፃፀሙ 59.32% ተከናውኗል፡፡

## የመስሪያና መሸጫ ቦታ አቅርቦት

በበጀት ዓመቱ በከተማና በገጠር ለ50,500 ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች (ለ380,000 አንቀሳቃሾች) 21,500 ሄክታር የመስሪያና የመሸጫ ቦታ በማዘጋጀትና ጥቅም ላይ በማዋል ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ ለሼድ ግንባታ 318.88 ሄክታር፣ ለግብርና 11,801.79 ሄክታር፣ ለሌሎች (አሸዋ፣ ድንጋይ፣ የወንዝ ጠጠር፣ ወዘተ...) 2,986 ሄክታር በድምሩ 15,106.67 ሄክታር መሬት (አፈጻጸሙ 70.26%) በማዘጋጀት 6,941 ኢንተርፕራይዞችን (ወንድ 51,742፣ ሴት 16,976 በድምሩ 68,718 አንቀሳቃሾችን) በተዘጋጀው መሬት ተጠቃሚ ማድረግ የተቻለ ሲሆን አፈጻጸሙም በኢንተርፕራይዝ 13.74% እና በአንቀሳቃሽ 18% ማከናወን ተችሏል፡፡

ከተዘጋጀው ቦታ ውስጥም ሥራ ላይ የዋለው ለሼድ ግንባታ 83.64 (26.23%) ሄክታር፣ ለግብርና 9,621.08 (81.52%) ሄክታር እና ለሌሎች (አሸዋ፣ ድንጋይ፣ የወንዝ ጠጠር ወዘተ) 1,055.17 (35.34%) ሄክታር በድምሩ 10,759.89 (71.23%) ሄክታር ሥራ ላይ ውሏል፡፡

## አደጋ መከላከልና ምግብ ዋስትና

### የቅድሚያ ማስጠንቀቂያና ምላሽ ተግባራት

በክልሉ ውስጥ የሚታየውን የአደጋ ስጋት ሁኔታ በመከታተል ሳምንታዊ (98%) መረጃ ተሰብስቦ ወደ ዳታ ቤዝ ገብቶ ለሚመለከታቸው አካላት በወቅቱ እንዲደርስ ተደርጓል፡፡ የክልሉን አጠቃላይ የመረጃ ልውውጥና የዝግጁነት አቅም ለማጎልበት በዓመቱ 12 ፎረሞችን ለማካሄድ ታቅዶ 12 ጊዜ /100%/ ፎረሞችን ማካሄድ ተችሏል፡፡ ትኩረት የሚሹ (Hot spot classification) በመጀመሪያ ዙር 101 ወረዳዎች፣ በ2ኛ ዙር 114 ወረዳዎች በዕቅዱ መሰረት ተለይተው ለህጻናት እና እናቶች ተጨማሪ አልሚ ምግብ ድጋፍ እንዲደረግላቸው የቅርብ ክትትል ተደርጓል፡፡ የ2015/16 የመኸር ቅድመ ምርት ግምገማ ጥናት ከወቅቱ የፀጥታ ችግር ጋር በተያያዘ በሁሉም ዞኖች ተንቀሳቅሶ ማካሄድ ባይቻልም መረጃዎችን ከሁሉም ዞኖች አሰባስቦ ጥናት እንዲካሄድ ተደርጓል፡፡በዚህም 3,995,754 ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው የህብረተሰብ ክፍሎች መረጃ ለሚመለከተው መላክ ተችሏል፡፡ የክረምቱን ዝናብ ተከትሎ የጎርፍ፤ የበረዶ፣ መሬት መንሸራተት እና ሌሎች አደጋ በተከሰተባቸው ዞኖች በተለያዩ 3 ወረዳዎች የአስቸኳይ ጊዜ አደጋ ስጋት ጥናት ማድረግ ተችሏል፡፡ በዚህም አስፈላጊ መረጃዎችን በማደራጀት ለተጎጅዎች አስፈላጊ ምግብ ነክና ምግብ ነክ ያልሆኑ ድጋፎችን ለማድረስ ምቹ ሁኔታ መፍጠር ተችሏል፡፡

በክልላችን የምግብ ዋስትና መታጣት ችግር የከፋ ይሆናል ተብለው በተለዩ ወረዳዎች ያለውን የስነ ምግብ ሁኔታ ለማወቅ ይቻል ዘንድ ፈጣን ዳሰሳዊ የስነ ምግብ ጥናት /Rapid Nutrition Assessment/ በ5 ወረዳዎች ተከናውኖ መረጃው ለሚመለከታቸው አካላት በመላኩ የጎርፍ አደጋ ስጋት፣ የመሬት መንሸራተት፣ የበረዶ፣ የተባይ፣ የግሪሳ ወፍ፣ ቢጫ ዋግ፣ እንበጣና ሌሎች የአደጋ ክስተቶች፣ ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብና ከባድ ነፋስ ያስከተለውን ጉዳት በመከታተል የደረሰውን ጉዳት የማሳወቅ ስራ በመሰራቱ በክልሉ ከዝናብ እጥረት ጋር በተያያዘ የተፈጠረው ድርቅ ተጋላጭ የሆኑ 43 ወረዳዎች ለሚገኙ 429 ቀበሌዎች ውስጥ የሚኖሩ

1,846,895 ህዝብ ድጋፍ እንዲደረግለት አስፈላጊው የድጋፍ ጥያቄ ቀርቦ የአቅርቦት ችግርን ባገናዘበ መልኩ የዕለት ምግብ ድጋፍ እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡

በበጀት ዓመቱ በጠቅላላው 541 ወንድና 656 ሴት በድምሩ 1,197 የቤተሰብ ኃላፊዎች በተለያዩ የአደጋ ስጋት ቅነሳ ተግባራት ላይ እንዲሰማሩ ለተደረጉ ተጠቃሚዎች ቀጣይነት ያለው ድጋፍ ማድረግ ተችሏል፡፡የተለያዩ ረጅ ድርጅቶች 18 የፕሮጀክት ፕሮፖዛሎችን አዘጋጅተውና ሃብት አፈላልገው ከተቋሙ ጋር በመፈራረም በተለያዩ ወረዳዎችና የተፈናቃይ ካምፖች ምግብ እና ምግብ-ነክ ያልሆኑ ድጋፎችን እንዲያደርጉ ድጋፍ ተደርጓል፡፡በዚህም በሁሉም ተፈራራሚ ሴክተሮች ለ4,837,651 ተጠቃሚዎች 1,733,630,343 ብር የሚያወጡ ልዩ ልዩ ድጋፎች እንዲሁም ለ22,857 ተጠቃሚዎች 228,801,201 ብር የገንዘብ ድጋፍ ተደርጓል፡፡ከክልሉ መጠባበቂያ ክምችት በተሰጠ ምላሽ ከክልል ሃብት በአጠቃላይ በዘጠኝ ዙር 55,069 ኩንታል እህል ተፈቅዶ 54,827.3 ኩንታል ተጓጉዞ 51,184.3 ኩንታል (93.4%) ለ51,955 ተጠቃሚዎች ተጓጉዞ ተሰራጭቷል፡፡



ሰሜን ወሎ ጃራ መጠለያ ላሉ ተፈናቃዮች እርዳታ ሲደረግ

## የምግብ ዋስትና ፕሮግራም

በአደጋ ለተጎዱና ተጋላጭ ለሆኑ 576,632 የመደበኛው ሴፍቲኔት የማህበረሰብ ልማት ተጠቃሚዎች እና ከልማታዊ ሴፍቲኔት ውጭ ለሆኑ 420,579 በጠቅላላው ለ997,211 ተጠቃሚዎች በ2 ዙር ለትራንስፈር አገልግሎት የሚውል በድምሩ በበጀት ዓመቱ ለትራንስፈር 390,778,520 ብር እንዲሁም ለስራ ማስኬጃ 1,314,753 ብር ተፈቅዶ ለተጠቃሚዎች ማድረስ ተችሏል፡፡በበጀት ዓመቱ በመደበኛ የእህል ድጋፍ 37,798 ሜትር ቶን ለተጠቃሚዎች ድጋፍ ለማቅረብ ታቅዶ 33,319 ሜትር ቶን ቀርቦ 27,717 ሜትር ቶን (86%) ለተጠቃሚዎች ማሰራጨት ተችሏል፡፡



በጃናሞራ ወረዳ በድርቅ ለተጎዱ እርዳታ ሲደረግ

## የማህበረሰብ ልማት ስራዎች

በፀጥታ ችግር ውስጥ ሆኖም 65,858 ሄክታር የእንክብካቤ ስራ፣19,285 ሄክታር የአፈር እና ውሃ ተግባራት፣2,514 ሄክታር የስነ ህወት አፈር ጥበቃ ስራዎችን መስራት ተችሏል፡፡

ካለው የፀጥታ ሁኔታ ጋር በተያያዘ ምቹ ባይሆንም 66 የንፁህ መጠጥ ውሃ ግንባታ፣ 1,852.98 ሄክታር አነስተኛ መስኖ ልማት፣ 845 ኪሎ ሜትር ርዝመት ያላቸው አነስተኛ የመንገድ ፕሮጀክቶች፣ 65 ማህበራዊ አገልግሎት ሠጭ ተቋማት ግንባታ፣ 194 ስነ ምግብ ተኮር ፕሮጀክቶችን መገንባት በመቻሉ፣ የካፒታል ፕሮጀክቶች ማስፈፀሚያ ግብዓቶች ግዥ 144,940,698 ብር ጥቅም ላይ እንዲውል ተደርጓል፡፡



የመጠጥ ውሃ ስራ ግንባታ -ደባርቅ ወረዳ

# ገንዘብና ልማት

## የበጀት ዝግጅት

መረጃ በማቀናበር ለ2017 ዓ.ም የሚሆን የሁሉንም እርከኖች የወጪ ግዴታና የክልሉ የቀጣይ ዓመት የገቢ ዕድገትን ታሳቢ ባደረገ መልኩ ጊዚያዊ የበጀት ጣሪያ ለማዘጋጀት ለክልል ቢሮዎችና ለወረዳዎች የበጀት ጥሪ ለማስተላለፍ ታቅዶ ለሁሉም ባለበጀት መስሪያቤቶች የበጀት ጥሪ በማስተላለፍ እቅዱን ሙሉ በሙሉ የመፈጸም ስራ ተሰርቷል፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ ከሁሉም ባለበጀት መስሪያቤቶች የበጀት ጥያቄ ለመቀበል ታስቦ የሁሉም መስሪያቤቶች ጥያቄ ቀርቦ ሰነዱ በመመርመር ለበጀት ስሚ ዝግጁ እንዲሆን ተደርጓል፡፡ከዚህ ተግባር ላይ በየአመቱ የሚያጋጥመው ችግር በተቀመጠው ጊዜ ገደብ ጥያቄ አለማቅረብ ሲሆን ውሃ ቢሮ፤ማረሚያ ቤቶች ኮሚሽን እጅግ ዘግይተው ያቀረቡ እንደሆነ ተገልጾ በቀጣይ መደግም እንደሌለበት ተመላክቷል፡፡

## የበጀት ምንጭ እና አጠቃቀም

የልማት ፋይናንስ ውጤታማ በሆነ መንገድ በመምራት የክልሉን ኢኮኖሚ ወደ ተሻለ ሁኔታ በማምጣት ድህነትን ለመቅረፍ ለሚያስችሉ ለኢኮኖሚና ማህበራዊ ዘርፎች ልማት ማስፈጸሚያ ከክልሉ የውስጥ ገቢ ብር 89,279,467,000፣ ከፌዴራል መንግስት ጥቅል የቀመር መደበኛ ድጋፍ ድርሻ ብር 44,519,851,979፣ ለዘላቂ ልማት ግቦች ማስፈፀሚያ ብር 3,024,000,000 እና ከውጭ አገር እርዳታ ብር 581,153,208 በድምሩ ብር 137,408,472,187 የክልሉ ልማት ማስፈፀሚያ በጀት ሆኖ እንዲጸድቅ ተደርጎ ወደ ስራ የተገባ ሲሆን አፈጻጸሙ ሲታይ ብር 61.58 ቢሊዮን መደበኛ እና 11.18 ቢሊዮን ካፒታል በድምሩ ብር 72.76 ቢሊዮን ወጭ ሁኖ ስራ ላይ ውሏል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በቻናል አንድ ብር 11.08 ቢሊዮን ከነበረው በጀት ውስጥ ብር 8.78 ቢሊዮን ወጭ በማድረግ የበጀቱን 79% መፈፀም ተችሏል፡፡በሌላ በኩል ደግሞ ከዩኤን ከተገኘው ብር 1,376,187,000 ላይ ብር 930,492,440.62 ወጭ በማድረግ ስራ ላይ የዋለ ሲሆን ቀሪው በጀት የመጠቀሚያ ጊዜው ያልደረሰ እንደሆነ ተመላክቷል፡፡

## ፍትሃዊ የግዥ ስርዓት ማስፈን

ፍትሃዊ የግዥ ስርዓት በማስፈንና በእጅ የሚገኝን ውስን ሀብት በአግባቡ ከመጠቀም አኳያ ለአፈጻጸም ያስቸገሩ ጉዳዮች ላይ የግንባታ ጥናትና ንድፍ ስራ እና የምክር አገልግሎት (የግዥ መመሪያ ቁ1/2016) የማሻሻያ የውሳኔ በማዘጋጀት ከሚመለከታቸው ተቋማት፣አጋር አካለት ጋር በመመካከር የተገኙ ሀሳቦችን በማካተትና በማጽደቅ በክልሉ ለሚገኙ የክልል ሴክተር መስሪያቤቶች፤ለዞኖች ለከተማ አሰተዳደሮችና ወረዳዎች እንዲሁም የክልል ተጠሪ ተቋማት መመሪያውን እንዲያውቁት እና ወደ ተግባር እንዲገቡ በማድረግ ያለአግባብ የሚፈጸሙ ግዥዎችን እንዲከላከሉ ብሎም  የክልሉን ሀብት ከብክነት እንዲታደጉ የማድረግ ስራ ተሰርቷል፡፡ከዚሁ ጋር በተያያዘ 34 የግዥ አፈጻጸም ቅሬታዎች ቀርበው 13 ቅሬታዎች አግባብነት ያላቸው በመሆኑ ግዥ ፈፃሚ መስሪያቤቶች የተሰጠውን ውሳኔ አስተካክለው እንዲፈጽሙ አቅጣጫ ተሰጥቷል፡፡ ቀሪዎቹ 21 ቅሬታዎች አግባብነት የሌላቸው መሆኑ ተገልጾ ለቅሬታ አቅራቢዎች መልስ ተሰጥቷል፡፡

## ፕሮጀክቶችን በውጤታመነት መጠቀም

በ2016 ዓ.ም 252 አዳዲስ ኘሮጀክቶች ስምምነት በመፈራረም 6 ቢሊየን ብር ለማግኘት ታቅዶ 174 (70 ፐርሰንት) አዳዲስ ኘሮጀክቶች ስምምነት በመፈጸም 9.5 ቢሊዮን (100 ፐርሰንት በላይ) ብር ለማግኘት ተችሏል፡፡ ከነዚህ ፕሮጀክቶች መካከል አርባ ሶስቱ በዞንና በወረዳ  131 ፕሮጀክቶች  በክልል ደረጃ ስምምነት የተወሰደባቸው ናቸው፡፡ አዲስ በሚፈረሙ ኘሮጀክቶች 10 ሚሊየን ህዝብ ተጠቃሚ ይሆናል ተብሎ የታቀደ ሲሆን  በበጀት አመቱ መጨረሻ 6.4 ሚሊየን ህዝብ በላይ ተጠቃሚ ሊሆን ችሏል፡፡ከዚህ መካከል 33 የሚሆኑት ድርጅጅቶች ደግሞ ብር 2,115,521,932 በጀት 2,654,724 የህብረተሰብ ክፍሎችን የሚሸፍን የአደጋ ጊዜ ምላሽ ፕሮጀክታቸው በህይወት አድን ተግባራት ላይ በመሰማራት ከሚያጋጥሙ የከፋ ችግሮች ለመታደግ የሚያስችሉ ፕሮጀክቶች  እንደሆኑ ተመላክቷል፡፡

## የበጀት አጠቃቀም ውጤታማነት ማሳደግ

የክልል ባለበጀት መስሪያቤቶችን በጀት አጠናቆ ለማፅደቅ ታቅዶ የክልል ቢሮዎች መደበኛና ካፒታል በጀት ቀደም ብሎ ተዘጋጅቶ ጣሪያው በክልል ምክር ቤት እንዲጸድቅ የተደረገ ሲሆን የክልል ቢሮዎች ድርሻ  በቢሮ ኃላፊዎች ተገምግሞ  ለካቢኔው ቀርቦ መደበኛ በጀቱ እንዲጸድቅ

ተድረጓል፡፡በዚህም ከመደበኛ በጀት ለደመወዝ እና ለስራ ማስኪያጃ 14,198,326,000 ብር የተመደበ ሲሆን የቢሮዎች የበጀት አመዳደብ ከባለፈው አመት ጋር ሲነጻጸር የአስተዳደርና ጠቅላላ አገልግሎት 26 በመቶ በመቀነስ፣ ኢኮኖሚ ዘርፉ 20.8 በመቶና ማህበራዊ ዘርፉ 13.05 በመቶ ጭማሪ እንዳሳዩ ተመላክቷል፡፡

ሌላው የካፒታል በጀት ሲሆን የክልሉን የካፒታል በጀት ድርሻ በማሳደግ በክልሉ የሚሰሩ መሰረተ ልማቶች እንዲሟሉ ቢሮው አቅዶ እየሰራ ይገኛል፡፡ በዚህም መሰረት የካፒታል በጀት እድገት ሲታይ 2015 ዓ.ም ከነበረው 12.13 ቢሊየን ብር በ2016 ዓ.ም ወደ 18.37 ቢሊየን እንዲያድግ የተደረገ ሲሆን ካለፈው ዓመት ጋር ሲነጻጸር በ6.2 ቢሊየን ብር አብላጫ እንዳለው ተመላክቷል፡፡ ነገር ግን በተፈጠረው የጸጥታ ችግር የገቢ አሰባሰቡ ችግር ላይ በመውደቁና ለጸጥታ ስራ የሚወጡ ወጪዎች በመጨመራቸው የካፒታል ፕሮጀክቶች አዲስ እንዳይጀመሩና ነባሮችም በአማካይ የፕሮጀክቱ 10 በመቶ ብቻ እንዲመደብ በማድረግ እስከ 4 ቢሊየን ብር በጀት እንዳይመደብና በመስሪያቤቶች ስም ተቀምጦ የገቢ አሰባሰቡ እየታየ እንዲለቀቅ ታሳቢ ተደርጎ ቀሪው በጀት ለኢኮኖሚ ዘርፍ 7,399,364,476 /51.81በመቶ/ ለማህበራዊ ዘር 5,437,524,651 /38 በመቶ/ ለአስተዳደር ዘርፍ 1,445,054,524 /10.12 በመቶ/ ድርሻ እንዲይዙ ተደርጓል፡፡

## የበጀት አስተዳደር

በክልሉ የጸደቀው በጀት በተያዘለት የጊዜ ገድብ ለተያዘለት ዓለማ በወቅቱ ስራ ላይ እንዲውል የመከታተል ፤ከተደለደለ በኂላ በስራ ሂደት የሚያጋጥሙ ችግሮችን የመፍታት የተጨማሪ የበጀት ጥያቄዎችን መርምሮ የውሳኔ አስተያየት የማቅረብ ፤በበጀት ዓመቱ ላይ የሚገኙ ተጨማሪ ገቢዎች ካሉ በተጫማሪ በጀትነት የማሳወጅ ተግባራት ማከናወን የሚሰሩ ተግባራት ናቸው፡፡በዚህም መሰረት የክልል ባለበጀት መስሪያቤቶችን የመደበኛና ካፒታል በጀት አፈጻጸም ሪፖርት በመቀበል ለማዘጋጃትና አፈጻጸሙ ተሰባስቦ የመገምገም ስራ ተሰርቷል፡፡በዚህም ስራ ላይ የማይውሉ ተራፊ በጀቶችን ለማሰባሰብና እንደገና ለመደልደል መስሪያቤቶች ተራፊ በጀት እንዲያቀርቡ በደብዳቤ የመጠየቅ ስራ ተሰርቷል፡፡

በክልሉ የተገኙ ተጨማሪ በጀቶችን ለማሳዎጅ ታቅዶ በ2015 በጀት ከእቅድ በላይ የተሰበሰቡ በልዩ ሁኔታ የተፈቀዱ ገቢዎችን፣ ከወጪ ቀሪ ሃብቶችን ፣ በማዘጋጀትና ረቂቅ አዋጅ

በማዘጋጀት ብር 1,072,746,124.00 በክልል መስሪያቤቱ ቀርቦ በተጨማሪ በጀትነት እንዲታወጅ ተደርጓል፡፡

ብድር የወሰዱ አስተዳደር እርከኖች በበጀት ዝውውር ለማስመለስ ታቅዶ በ2015 በጀት ዓመት በ2016 በጀት ዓመት ተመላሽ ታሳቢ ብድር የወሰዱ ከ58 ወረዳዎችና ከተማ አስተዳደሮች ብር 446,814,122.00 የበጀት ዝውውር በማዘጋጀት እንዲመለስ የማድረግ ተግባር ሙሉ በሙሉ ተከናውኗል፡፡

የ2016 ዓ.ም የተስተካከለ በጀት መዝጋትን በተመለከተ በተቀመጠለት የጊዜ ገደብ ለመዝጋት ታቅዶ ነገር ግን በወቅታዊ የጸጥታ ችግር ምክንያት ዞኖች ቀርበው መናበብ ባይችሉም በሌሎች አማራጮች መረጃዎችን በመቀበል በጀቱን የማጠቃለል ስራ ተሰርቷል፡፡

የሚጠየቁ የተጨማሪ በጀት ጥያቄዎችን መርምሮ ውሳኔ በማስተላለፍና በጀት በማዛወር በኩል የተለያዩ ተጨማሪ ጥያቄዎች ቀርበው ውሳኔ በመስጠት የማስተላፍ ስራ የተሰራ ሲሆን በበጀት አመቱ ከ555 የበጀት ዝውውሮችን በማዘጋጀት ብር 1,476,412,408.00 ከመጠባበቂያ፣ ካሳ፣ማችንግ ፈንድ፣ ቫትና የሰው ኃይል አገልግሎት በጥቅል ከተያዘ በጀት የማስተላለፍ ስራ ተሰርቷል፡፡

# III.ማህበራዊ ዘርፍ

## ትምህርት

### ሰብአዊ ግባት ማሟላት

የአማራ ክልል የትምህርት ዘርፍ በየዓመቱ ለኢኮኖሚው በአማካይ የ8.4 ቢሊየን ብር እሴት ጭማሪ እያበረከተ ይገኛል፡፡ ከማህበራዊ ልማት ዘርፍ ስራዎች አንዱና ምናልባትም ለክልላችን ሁሉን አቀፍና ዘላቂ ለውጥ ትልቅ ሚና የሚጫወተው ለዜጎች ተደራሽና ጥራቱ የተጠበቀ የትምህርት ስራ መስራት ነው፡፡ስለሆነም በቅድመ ዝግጅት ተግባር ግብአት ማሟላት አንዱ ሲሆን የተለያዩ የተግባር ላይ የአቅም ግንባታ ስልጠናዎችን በመስጠት ሰብአዊ ግብአትን ማሟላት ቀዳሚው ተግባር ነው፡፡በዚህም ከሚያስፈልገው 235,600 የሰው ሀይል መካከል 223,811 (ወንድ 126,331፣ሴት 97,840) ወይም 95% በስራ ላይ ናቸው፡፡



የመምህራን ስራ ላይ ስልጠና -ባህር ዳር

## ቁሳዊ ግብዓቶችን ማሟላትና መጠገን

በቅድመ-ዝግጅት ወቅት ከተከናወኑ ተግባራት መካከል ቁሳዊ ግብዓቶችን ለማሟላት በተሰራው ስራ 6,187 ክፍሎችን በአዲስ መገንባት የተቻለ ሲሆን ከእነዚህም መካከል 3,954 የመማሪያ ክፍሎችና 2,233 ለሌሎች አገልግሎቶች የሚውሉ ክፍሎች ናቸው። በተጨማሪም 8,882 ክፍሎችን መጠገን የተቻለ ሲሆን ከእነዚህም ውስጥ 5,136 የመማሪያ ክፍሎችና 3,746 ለሌሎች አገልግሎቶች የሚውሉ ክፍሎች ናቸው። በሌላ በኩል 92,298 ኮምባይንድ ዴስክ ለማቅረብ ታቅዶ 79,178(85.78%) ኮምባይንድ ዴስክ ማቅረብ ተችሏል ።

## የበጀት አመቱ ትምህርት አጀማመር

በክልሉ በሚገኙ ሁሉም ትምህርት ቤቶች በተለያዩ ምክንያቶች ቅድመ ዝግጅት ስራዎች ተጠናቀው በተመሳሳይ ቀን ትምህርት መጀመር ባይቻልም ያጋጠሙ ፈተናዎችን ተቋቁመው በቂ ዝግጅት ከአደረጉ 507 አጸደ ህፃናት መካከል 424 (83.6%)፣ 6,737 አንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል 4,990 (74.1%) እና 515 ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል 355 (98.9%) ትምህርት ቤቶች በትምህርት የመጀመሪያው ቀን ትምህርት መስጠት ጀምረው አሁንም እየሰሩ ይገኛሉ።



የበጀት አመቱ ትምህርት አጀማመር -ባህር ዳር

## የትምህርት ጥራት ማስጠበቅ

የትምህርት አግባብነትና ጥራትን ለማጎልበት የመምህራን እና ትምህርት አመራሩን አቅርቦት፣ ተነሳሽነት እና ብቃትን ማሳደግ ሌላኛው ቁልፍ ስትራቴጅካዊ አቅጣጫ ነው፡፡በዚህም ከቅድመ አንደኛ እስከ ሁለተኛ ደረጃ ድረስ የሚያስተምሩ መምህራን እና ትምህርት አመራሮች የትምህርት ደረጃ ለደረጃው የተቀመጠውን መስፈርት እንዲያሟሉ ለማድረግ እየተሰራ ይገኛል፡፡ለዚህ የሚያገለግል ረቂቅ መመሪያ ተዘጋጅቶ ለመተግበር ጥረት ተደርጓል፡፡የትምህርት አመራሩንና መምህሩን ሙያ የሚያሻሽሉ ልዩ ልዩ የአቅም ማጎልበቻ ስልጠናዎች ተሰጥተዋል፡፡

## አዲሱ ስርዓተ ትምህርት የመፅሀፍ ጥምርታ

አዲሱ ስርዓተ ትምህርት ከተጀመረ የአንደኛና መካከለኛ ደረጃ መጽሐፍት ተማሪ ጥምርታ 1:2 ለማድረስ ታቅዶ ለተማሪዎች አገልግሎት በመስጠት ላይ የሚገኘው መጽሃፍት ብዛት 8,038,353 (የአንደኛ ደረጃ መጽሃፍት 5,771,623፣ የመካከለኛ ደረጃ መጽሃፍት 2,266,730) የደረሰ ሲሆን አሁን ተመዝግበው በመማር ላይ ለሚገኙ ተማሪዎች በሁሉም የትምህርት አይነት መድረስ የሚገባው መጽሃፍ ብዛት (በትምህርት አይነት በየክፍሉ ተማሪ ብዛት ተባዝቶ) 18,835,187 በመሆኑ የተማሪ መጽሃፍት ጥምርታው ከ1:2.34 ደርሷል፡፡ይህም ከታቀደው ጋር ሲነጻጸር 85.4% ተፈጽሟል፡፡ ይሁንና ይህ አፈጻጸም በርካታ የክልሉ ህጻናት ትምህርት ስላልጀመሩ የተገኘ ሲሆን ሁሉም ተማሪዎች ወደ ትምህርት ቤት ከተመለሱ አማካይ ጥምርታው አንድ መጽሃፍ ለ3 ተማሪ እና ለ4 ተማሪ አካባቢ ሊሆን እንደሚችል ያሳያል፡፡ይሁን እንጂ በክልላችን ውስጥ በተፈጠረው የፀጥታ ችግር ምክንያት ትምህርት ባልተጀመረባቸው ዞኖችና ትምህርት ጀምረውም ከካዘና ማዕከላት ወደ ትምህርት ቤቶች ለማጓጓዝ አስቸጋሪ ወደ ሆኑ አካባቢዎች ማሰራጨት አልተጀመረም፡፡



የአዲሱን ስርዓተ ትምህርት ሞጁል ዝግጅት -ባህር ዳር

## መምህራንን በስራ ላይ ማቆየት ምጣኔንን ማሻሻል

የመምህራንን ከስራ የመልቀቅ ምጣኔ ወደ 2.0% (ወንድ 2.3%፣ ሴት 1.6%) ዝቅ ለማድረግ ታቅዶ በሁሉም ደረጃ በማስተማር ላይ ከሚገኙ 206,441 (ወንድ 111,732፣ ሴት 94,709) መምህራን መካከል የለቀቁ መምህራን 4,459 (ወንድ 2,774፣ ሴት 1,685) ወይም 2.2% (ወንድ 2.5%፣ ሴት 1.8%) ሲሆን አፈጻጸሙ ከእቅዱ ጋር ሲነጻጸር 92.6% ነው፡፡ በመሆኑም በበጀት አመቱ ዝቅተኛ የመልቀቅ ምጣኔ ተመዝግቧል፡፡

## የትምህርት ቤቶችን የኢንስፔክሽን ደረጃ ማሻሻል

የክልላችን ትምህርትቤቶች በግብአት በሂደት እና በሚያስመዘግቡት ውጤት ሲመዘኑ ደረጃቸው ያልተሻሻለ እና ለመማር ማስተማር ምቹ ያልሆኑ ናቸው፡፡ይህን ሁኔታ በመቀየር የትምህርት ቤቶችን ደረጃ በቀጣይነት በማሻሻል ለመማር ማስተማር ሂደቱ ምቹ ለማድረግ ደረጃ 3 እና ደረጃ 4 የደረሱ የቅድመ አንደኛ ደረጃ፣የአንደኛና መካከለኛ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርትቤቶችን ድርሻ ማሳደግ የሚያስችሉ ስራዎችን ለመስራት በአመታዊ እቅድ ተካቷል፡፡

የትምህርትቤቶች ኢንስፔክሽን አገልግሎት በስፋት ሲሰጥ የቆየው ለአንደኛ፣መካከለኛ እና ለሁለተኛ ደረጃ ትምህርትቤቶች ብቻ ነበር፡፡ይሁንና በአለፉት ሁለት አመታት በክልሉ የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርትቤቶች (አፀደ ህጻናት እና "ኦክፍሎች") የኢንስፔክሽን ስታንዳርድ ተዘጋጅቶ ደረጃ መስጠት የተጀመረ መሆኑ በደረጃው ያለውን የጥራት ችግር ለመረዳት እና ለማሻሻል አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡ ከዚህ በመነሳት ደረጃ 3 የደረሱ የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርትቤቶችን ብዛት እስከ አመቱ መጨረሻ ድረስ 5% ለማድረስ ታቅዶ አጠቃላይ የኢንስፔክሽን አገልግሎት ከአገኙ እና ደረጃ ከተሰጣቸው 4,220 የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርትቤቶች መካከል 107 ወይም 2.5% ደረጃ 3 ሆነዋል፡፡ ይህም ከታቀደው አፈፃፀሙ 50.7% ነው፡፡

በኢንስፔክሽን ደረጃ 3 የደረሱ የአንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርትቤቶችን ብዛት እስከ አመቱ መጨረሻ 20% ለማድረስ የታቀደ ሲሆን አጠቃላይ የኢንስፔክሽን አገልግሎት ካገኙ እና ደረጃ ከተሰጣቸው 8,467 የአንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርትቤቶች መካከል 1,099 ወይም 13.0% ትምህርትቤቶች ደረጃ 3 ሆነዋል፡፡ ይህም ከታቀደው 64.9% ነው፡፡በተመሳሳይ በኢንስፔክሽን ደረጃ 3 የደረሱ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርትቤቶችን ብዛት እስከ አመቱ መጨረሻ 30% ለማድረስ የታቀደ ሲሆን አጠቃላይ የኢንስፔክሽን አገልግሎት ከአገኙ እና ደረጃ ከተሰጣቸው 573 ሁለተኛ

ደረጃ ትምህርትቤቶች መካከል 146 ወይም 25.5% ትምህርትቤቶች ደረጃ 3 ሆነዋል። ይህም ከታቀደው 84.9% ሆኗል።

## የትምህርት ቤት ምገባ እና አትክልትና ፍራፍሬ ልማት

የትምህርትቤት ምገባ መርሀ ግብር ተጠቃሚ የሆኑ የቅድመ አንደኛ፣አንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርትቤት ተማሪዎች ብዛት በቁጥር 1,000,000 (ወንድ 500,000፣ ሴት 500,000) ለማድረስ የታቀደ ሲሆን በቅድመ አንደኛ እና አንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርትቤት በበጀት አመቱ በመማር ላይ ከሚገኙ ተማሪዎች መካከል የምገባ መርሃ ግብር ተጠቃሚ የሆኑት 214,820 (ወንድ 106,545፣ሴት 108,275) በማድረስ ከእቅዱ 21.5% (ወንድ 21.3%፣ሴት 21.7%) ሆኗል።አፈፃፀሙ ከተያዘው እቅድ ጋር ሲነጻጸር አነስተኛ ነው። ለአፈጻጸሙ ዝቅተኛ መሆን እንደ ምክንያት የሚወሰደው አንዳንድ ፕሮግራሞች መቋረጣቸው፣በታቀደው መሰረት በንቅናቄ በህብረተሰቡ ተሳትፎ ወደ ስራው ያልተገባ በመሆኑ እና በፀጥታ ችግሮች ነው። በመሆኑም የተማሪዎች ምገባ የተማሪዎችን መማር ለማሻሻል ከአለው አስተዋጽኦ አንጻር ከክልሉ መንግስት እና አጋር አካላት ጋር በመሆን ተጠቃሚዎቸን ማሻሻል በቀጣይ በጀት አመት ትኩረት ይደረግበታል። ከዚሁ ጎን ለጎን አትክልትና ፍራፍሬ ልማት የተገበሩ ትምህርትቤቶች ብዛት በቁጥር 1,836 ለማድረስ የታቀደ ሲሆን የተገበሩት ብዛት 2,576 የደረሰ ሲሆን ከእቅዱ 140.3% መፈጸም ተችሏል።

## የተማሪዎችን ተሳትፎ ማሳደግ

የትምህርት ዘመን የተማሪዎችን ተሳትፎ ለማሳደግ ከቅድመ አንደኛ እስከ ሁለተኛ ደረጃ ድረስ 6,292,241 (ወንድ 3,095,327፣ሴት 3,196,914) ተማሪዎችን ለመመዝገብ ታቅዶ 3,673,250 (ወንድ 1,787,453፣ ሴት 1,885,797) መመዝገብ ተችሏል።ይህም ከታቀደው ጋር ሲነጻጸር 58.38% (ወንድ 57.75%፣ ሴት 58.99%) ነው።ለአፈፃፀሙ ዝቅተኛ መሆን ዋነኛው ችግር በክልላችን የተከሰተው የፀጥታ መደፍረስ ሲሆን ከተመዘገቡት ተማሪዎች መካከል የምዝገባ ምጣኔው ከፍተኛ ሆኗል። ከላይ በተገለጹት ችግሮች ምክንያት ከ3,000 በላይ ትምህርትቤቶች ባለመከፈታቸው ነው። ወደ 3 ሚሊዮን የሚጠጉ ተማሪዎችም ከትምህርት ውጭ ሲሆኑ በጸጥታ ችግሩ ምክንያት በየጊዜው የሚዘጉና የሚከፍቱ ትምህርትቤቶች በርካታ ናቸው።

## የተማሪ ሴክሽን ጥምርታን ማሻሻል

በአንደኛ ደረጃ (ከ1ኛ - 6ኛ ክፍል) ትምህርት 1፡50 ለማድረስ ታቅዶ በአመቱ መጨረሻ 2,108,188 ተማሪዎች በ59,254 ሴክሽኖች ለመማር የተመዘገቡ ሲሆን ጥምርታው 1፡36 ሆኗል፡፡በመሆኑም የእቅድ አፈጻጸሙ 140.5% ነው፡፡ የተማሪ ሴክሽን ጥምርታውን በመካከለኛ ደረጃ 1፡40 ለማድረስ ታቅዶ በአመቱ መጨረሻ 497,186 ተማሪዎች በ16,019 ሴክሽኖች ለመማር የተመዘገቡ ሲሆን ጥምርታው 1፡ 31 ሆኗል፡፡በመሆኑም የእቅድ አፈጻጸሙ 128.9% ነው፡፡ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት የተማሪ ሴክሽን ጥምርታ 1፡40 ለማድረስ ታቅዶ 545,400 ተማሪዎች በ11,187 ሴክሽኖች ለመማር በመምዝገባቸው ጥምርታው 1፡49 ደርሷል፡፡በመሆኑም የእቅድ አፈጻጸሙ 82.0% ነው፡፡ ይሁንና ይህ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪ ሴክሽን ጥምርታ በአለፈው አመት መጨረሻ ከነበረበት 1፡54 በፍጥነት ማሽቆልቆሉ በደረጃው የተማሪ ቁጥር ምን ያህል እንደቀነሰ የሚያሳይ እንጂ ስታንዳርዱን ለመጨመር በተሰራው የክፍል ግንባታ ብቻ የመጣ እንዳልሆነ መገንዘብ ይገባል፡፡

## የስርዓተ-ትምህርት ትግበራ

በክልል ደረጃ የሚሰጠውን የአዲሱ ስርዓተ ትምህርት ትውውቅ የተሳተፉ የአንደኛና መካከለኛ እንዲሁም ቅድመ-አንደኛ ደረጃ መምህራን ብዛት በቁጥር በበጀት አመቱ መጨረሻ 20,317 (ወንድ 14,397፣ሴት 6,900) ለማድረስ ታቅዶ በትውውቅ የተሳተፉ ብዛት 6,359 (ወንድ 2,701፣ሴት 3,658) ደርሷል፡፡ይህም ከታቀደው ጋር ሲነፃፀር 39.8% (ወንድ 25.0%፣ሴት 70.7%) እንደተፈጸመ ያሳያል፡፡በክልል ደረጃ የሚሰጠውን የአዲሱ ስርዓተ ትምህርት ትውውቅ የተሳተፉ የሁለተኛ ደረጃ መምህራን ብዛት፣ በቁጥር በበጀት አመቱ መጨረሻ 44,850 (ወንድ 32,762፣ሴት 11,488) እንዲሆን ታቅዶ በትውውቅ የተሳተፉ ብዛት 26,152 (ወንድ 19,815፣ሴት 6,337) ደርሷል፡፡ይህም ከታቀደው ጋር ሲነፃፀር 58.3% (ወንድ 60.5%፣ሴት 55.2%) እንደተፈጸመ ያሳያል፡፡

## አዲስ ስርዓተትምህርት በሙሉ ትግበራ ደረጃ ማካሄድ

በአለፉት አመታት ወደ ሙሉ ትግበራ የገቡትን ጨምሮ በአዲሱ ስርዓተ-ትምህርት ሙሉ ትግበራ የሚደረግባቸው የአንደኛና መካከለኛ ደረጃ መማሪያና ማስተማሪያ መጽሃፍት ብዛት በቁጥር 396 ለማድረስ ታቅዶ የሚተገበርባቸውን መማሪያና ማስተማሪያ መጽሃፍት 396 በማድረስ የእቅዱን 100% መፈጸም ተችሏል፡፡ በተመሳሳይ በአዲሱ ስርዓተ ትምህርት በ2016

ዓ.ም ሙሉ ትግበራ የሚደረግባቸው የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ማስተማሪያ መጽሐፍት ብዛት 2 ለማድረስ ታቅዶ የሚተገበርባቸውን ማስተማሪያ መጽሃፍት 2 በማድረስ የእቅድ አፈጻጸሙ 100% ሆኗል፡፡በአዲሱ ስርዓተ-ትምህርት 2016 ዓ.ም ሙሉ ትግበራ የሚደረግባቸው የሁለተኛ ደረጃ መማሪያና ማስተማሪያ መጽሃፍት ብዛት በቁጥር 80 ለማድረስ ታቅዶ የሚተገበርባቸውን መማሪያና ማስተማሪያ መጽሃፍት 92 ማድረስተ ችሏል፡፡

## የመጽሃፍት አቅርቦት

የቅድመ-አንደኛ ደረጃ የማስተማሪያ መጻሕፍት መምህር ጥምርታ 1፡1 ለማድረስ ታቅዶ በደረጃ አንድና ሁለት ህትመቱ በመጠናቀቅ ላይ የሚገኘው መፅሀፍ ብዛት 58,092 (ለእርከን አንድ 28,137፣ለእርከን ሁለት 29,955) የደረሰ ሲሆን የማስተማሪያ መጽሃፍት መምህር ጥምርታው ከ1፡1 የተሻለ (ከታቀደው 100%) ይሆናል፡፡በአማርኛ ቋንቋ ለሚማሩ ተማሪዎች በክልሉ መንግስት በጀት የመጽሃፍት ህትመት ያልተካሄደላቸው እና በበጀት አመቱ የሚታተሙ የአንደኛና መካከለኛ ደረጃ የትምህርት አይነቶችን መጽሃፍት አይነት እስከ አመቱ መጨረሻ 12 እንዲሆን ታቅዶ በሁሉም አይነቶች (100%) ታትሟል፡፡

የአንደኛና መካከለኛ ደረጃ መጻሕፍት ተማሪ ጥምርታ 1፡2 ለማድረስ ታቅዶ ለተማሪዎች አገልግሎት በመስጠት ላይ የሚገኘው መጽሃፍት ብዛት 8,394,714 (የአንደኛ ደረጃ መጽሃፍት 5,998,915፣የመካከለኛ ደረጃ መጽሃፍት 2,395,799) የደረሰ ሲሆን አሁን ተመዝግበው በመማር ላይ ለሚገኙ ተማሪዎች በሁሉም የትምህርት አይነት መድረስ የሚገባው መጽሃፍ ብዛት (በትምህርት አይነት በየክፍሉ ተማሪ ብዛት ተባዝቶ) 18,658,539 የደረሰ በመሆኑ የተማሪ መጽሃፍት ጥምርታው ከ1፡2.22 ደርሷል፡፡ይህም ከታቀደው ጋር ሲነጻጸር 90% ተፈጽሟል፡፡ይሁንና ይህ አፈጻጸም በርካታ የክልሉ ህጻናት ትምህርት ስላልጀመሩ የተገኘ ሲሆን ሁሉም ተማሪዎች ወደ ትምህርት ቤት ከተመለሱ አማካኝ ጥምርታው አንድ መጽሃፍ ለ3 ተማሪ እና ለ4 ተማሪ እንደሚሆን መረጃው ያሳያል፡፡



የመፅሐፍት ህትመትና አቅርቦት -ባህር ዳር

## የተማሪ ሴክሽን ጥምርታ

ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት የተማሪ ሴክሽን ጥምርታ 1:40 ለማድረስ ታቅዶ 534,709 ተማሪዎች በ11,185 ሴክሽኖች ለመማር በመምዝገባቸው ጥምርታው 1:48 ደርሷል፡፡በመሆኑም የእቅድ አፈጻጸሙ 83.7% ነው፡፡ ይሁንና ይህ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪ ሴክሽን ጥምርታ በአለፈው ዓመት መጨረሻ ከነበረበት 1:54 በፍጥነት ማሽቆልቆሉ በደረጃው የተማሪ ቁጥር ምን ያህል እንደቀነሰ የሚያሳይ እንጂ ስታንዳርዱን ለመጨመር በተሰራው የክፍል ግንባታ ብቻ የመጣ እንዳልሆነ መገንዘብ ይቻላል፡፡

## የስርዓተ-ትምህርት ግምገማ

በ2016 ዓ.ም ስርአተ ትምህርቱን ውጤታማ ለማድረግ የተደረጉ ጥናትና ምርምር (ተግባራዊ እና መሠረታዊ) ብዛት 3,363 እንዲሆን ታቅዶ 4,327 (ተግባራዊ 3,516፣መሠረታዊ 811) የደረሱ በመሆኑ የእቅድ አፈጻጸሙ 165.0% ሆኗል፡፡



ስርዓተ ትምህርት ትግበራ በቴክኖሎጅ እርማት -ባህር ዳር

## የፈተና ውጤትን ከማሻሻል

በ2016 ዓ.ም የ6ኛ ክፍል ክልላዊ ፈተና ለመውሰድ ተመዝነው 50 በመቶ እና በላይ አምጥተው ያለፉ ተማሪዎች ብዛትን፣ የ8ኛ ክፍል ክልላዊ ፈተና ለመውሰድ ተመዝነው 50 በመቶ እና በላይ አምጥተው ያለፉ ተማሪዎች ብዛትን፣ የ12ኛ ክፍል ሀገራዊ ፈተና ለመውሰድ ተመዝነው 50 በመቶ እና በላይ አምጥተው ያለፉ ተማሪዎች ብዛትን፤በአንደኛና መካከለኛ ደረጃ እንዲሁም በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በሁሉም የትምህርት ዓይነት 50% እና በላይ፣75% እና በላይ፤85% እና በላይ ያመጡ ተማሪዎች ብዛትን ለማሻሻል ግብ ተቀምጦ እንቅስቃሴ የተደረገ ሲሆን ፈተናዎች በቀጣይ የሚሰጡ በመሆናቸው ውጤት እንደደረሰ ትንተናዎች እየተዘጋጁ የሚገመገም ይሆናል፡፡ይሁን እንጅ በ2015 ዓ.ም የ8ኛ ክፍል ክልላዊ ፈተና ለመውሰድ ተመዝነው ፈተና ከወሰዱ 321,183 (ወንድ 143,159፣ሴት 178,024) ተማሪዎች መካከል 50 በመቶ እና በላይ ያመጡ 153,651 (ወንድ 70,406፣ሴት 83,245) ተማሪዎች ሲሆኑ ከተፈተኑት 47.84% ነው፡፡የመቁረጫ ነጥቡን አሟልተው ወደ 9ኛ ክፍል የተዛወሩ 222,434 (ወንድ 98,254፣ሴት 124,180) ተማሪዎች ሲሆን ከተፈተኑት 69.25% ሆኗል፡፡በተመሳሳይ በ2015 ዓ.ም የ12ኛ ክፍል ሀገር አቀፍ ፈተና ከወሰዱ 210,323 (ወንድ 99,556፣ሴት 110,767) ተማሪዎች መካከል 50 በመቶ እና በላይ ያመጡ 8,434 (ወንድ 6,417፣ሴት 2,017) ተማሪዎች ሲሆኑ ከተፈተኑት 4.01% ነው፡፡ በተወሰነው የመቁረጫ ነጥብ መሰረት እንደገና ተምረው (Remedial) እንዲፈተኑ ያለፉ ተማሪዎች ተፈጥሮ ሳይንስ 14,995 (ወንድ 8,196፣ሴት 6,354) ወይም 17.01%፣ማህበራዊ ሳይንስ 13,542 (ወንድ 7187፣ሴት 6354) ወይም 11.91% ሲሆኑ በአጠቃላይ 28,702 (ወንድ 15,493፣ሴት 13,208) 14.2% ናቸው፡፡

## መጠነ ማቋረጥን ለመቀነስ የተደረገ ክትትል

መጠነ ማቋረጥን ለመቀነስ በተሰራው ስራ በአንደኛ ደረጃ በአመቱ መጀመሪያ ከተመዘገቡ ተማሪዎች መካከል እስከ አመቱ መጨረሻ ድረስ በተሰበሰበ መረጃ 532,327 (ወንድ5 274,501፣ሴት 256,928) ወይም ከተመዘገቡት 25.52% (26.18% ወንድ፣ 24.76% ሴት) ከትምህርት ቤት ቀርተዋል፡፡ይህ መረጃ ከፍተኛ ቁጥር ያለው የተመዘገበ ተማሪ በመማር ላይ እንዳልሆነ የሚያሳይ ሲሆን አቋራጭን ለመቀነስ ከተያዘው እቅድ አንጻር አፈጻጸሙ ዝቅተኛ ነው፡፡ለዚህ ዝቅተኛ አፈጻጸም ዋና ምክንያቱ የፀጥታ ችግር ነው፡፡በተመሳሳይ በመካከለኛ ደረጃ በአመቱ መጀመሪያ ከተመዘገቡ ተማሪዎች መካከል እስከ አመቱ መጨረሻ ድረስ በተሰበሰበ

መረጃ 142,497 (ወንድ5 66,343፣ሴት 76,154) ወይም ከተመዘገቡት 28.83% (ወንድ 29.84%፣ሴት 28.06%) ከትምህርት ቤት ቀርተዋል፡፡ በተመሳሳይ ይህ መረጃ ከፍተኛ ቁጥር የሆነው የተመዘገበ ተማሪ በመማር ላይ እንዳልሆነ የሚያሳይ ነው፡፡ በተመሳሳይ ይህ መረጃ ከፍተኛ ቁጥር ያለው የተመዘገበ ተማሪ በመማር ላይ እንዳልሆነ የሚያሳይ ሲሆን አቋራጭን ለመቀነስ ከተያዘው እቅድ አንጻር አፈጻጸሙ ዝቅተኛ እንዲሆን አድርጎታል፡፡ለዚህ ዝቅተኛ አፈጻጸምም ዋና ምክንያቱ የፀጥታ ችግር ነው፡፡ በመሆኑም በቀጣይ አመት ይህን ለማሻሻል በዞንና ወረዳ ደረጃ ከትምህርት ቤቶች ተከታታይ መረጃ በማሰባሰብ አስፈላጊውን ድጋፍ ማድረግ ይገባል፡፡

በሁለተኛ ደረጃ በአመቱ መጀመሪያ ከተመዘገቡ ተማሪዎች መካከል እስከ አመቱ መጨረሻ ድረስ በተሰበሰበ መረጃ 154,931 (ወንድ5 68,846፣ሴት 86,085) ወይም ከተመዘገቡት 28.41% (ወንድ 29.27%፣ሴት 27.75%) ከትምህርት ቤት ቀርተዋል፡፡ በተመሳሳይ ይህ መረጃ ከፍተኛ ቁጥር ያለው የተመዘገበ ተማሪ በመማር ላይ እንዳልሆነ የሚያሳይ ሲሆን አቋራጭን ለመቀነስ ከተያዘው እቅድ አንጻር አፈጻጸሙ ዝቅተኛ እንዲሆን አድርጎታል፡፡ለዚህ ዝቅተኛ አፈጻጸምም ዋና ምክንያቱ የፀጥታ ችግር ነው፡፡በመሆኑም በቀጣይ ሩብ አመት ይህን ለማሻሻል በዞንና ወረዳ ደረጃ ከትምህርትቤቶች ተከታታይ መረጃ በማሰባሰብ አስፈላጊውን ድጋፍ ማድረግ ይገባል፡፡

## የጎልማሶች መሰረታዊ ትምህርት

በጎልማሶች መሰረታዊ ትምህርትና መደበኛ ያልሆነ ትምህርት መስክ የተቋቋሙ መማማሪያ ጣቢያዎች ብዛት በአመቱ መጨረሻ 28,155 ለማድረስ ታቅዶ 5,350 ጣቢያዎች የተቋቋሙ በመሆኑ የእቅድ አፈጻጸሙ 19.0% ሆኗል፡፡በተመሳሳይ በስታንዳርዱ መሰረት የተቋቋሙ የማህበረሰብ መማማሪያ ማዕከላት ብዛት እስከ አመቱ መጨረሻ 60 ለማድረስ ታቅዶ 42 ማዕከላት የተቋቋሙ በመሆኑ የእቅድ አፈጻጸሙ 76.4% ሆኗል፡፡የተቋቋሙ የተፋጠነ ትምህርት መስጫ ተቋማት ብዛት በበጀት አመቱ መጨረሻ 184 ለማድረስ ታቅዶ 100 ማዕከላት የተቋቋሙ በመሆኑ የእቅድ አፈጻጸሙ 54.3% ሆኗል፡፡ቅጥር የተፈጸመላቸው አመቻቾች ብዛት በአመቱ መጨረሻ 9,385 (ወንድ 4,692፣ ሴት 4,693) ለማድረስ ታቅዶ 2,738 (ወንድ 1,142፣ ሴት 1,596) አመቻቾች የተቀጠሩ በመሆኑ የእቅድ አፈጻጸሙ 29.2% (ወንድ 24.3%፣ ሴት 34.0%) ሆኗል፡፡ በዚሁ የሴት አመቻቾች ድርሻ 50.0% እንዲሆን ታቅዶ 58.3% በመሆኑ የእቅድ አፈጻጸሙ 116.6% ሆኗል፡፡ ከስራና ገበያ ፍላጎት ጋር

የተሳሰረ የጎልማሶች ትምህርት ፕሮግራም ተሳትፎን ሲታይ ማንበብ፣ መጻፍና ማስላት እንዲችሉ የተደረጉ ጎልማሶች ብዛት በአመቱ መጨረሻ 844,654 (ወንድ 413,684፣ ሴት 430,669) ለማድረስ ታቅዶ 43,926 (ወንድ 26,463፣ ሴት 17,463) የደረሰ ሲሆን የእቅድ አፈጻጸሙ 5.2% (ወንድ 6.4%፣ ሴት 4.1%) ሆኗል፡፡

በጉልማሶች መሰረታዊ ትምህርትና መደበኛ ያልሆነ ትምህርት መስክ የተቋቋሙ መማማሪያ ጣቢያዎች ብዛት በአመቱ መጨረሻ 28,155 ለማድረስ ታቅዶ 5,350 ጣቢያዎች የተቋቋሙ በመሆኑ የእቅድ አፈጻጸሙ 19.0% ሆኗል፡፡በተመሳሳይ በስታንዳርዱ መሰረት የተቋቋሙ የማህበረሰብ መማማሪያ ማዕከላት ብዛት እስከ አመቱ መጨረሻ 60 ለማድረስ ታቅዶ 42 ማዕከላት የተቋቋሙ በመሆኑ የእቅድ አፈጻጸሙ 76.4% ሆኗል፡፡ የተቋቋሙ የተፋጠነ ትምህርት መስጫ ተቋማት ብዛት እስከ አመቱ መጨረሻ 184 ለማድረስ ታቅዶ 100 ማዕከላት የተቋቋሙ በመሆኑ የእቅድ አፈጻጸሙ 54.3% ሆኗል፡፡ቅጥር የተፈጸመላቸው አመቻቾች ብዛት በአመቱ መጨረሻ 9,385 (ወንድ 4,692፣ ሴት 4,693) ለማድረስ ታቅዶ 2,738 (ወንድ 1,142፣ ሴት 1,596) አመቻቾች የተቀጠሩ በመሆኑ የእቅድ አፈጻጸሙ 29.2% (ወንድ 24.3%፣ ሴት 34.0%) ሆኗል፡፡ በዚሁ የሴት አመቻቾች ድርሻ 50.0% እንዲሆን ታቅዶ 58.3% በመሆኑ የእቅድ አፈጻጸሙ 116.6% ሆኗል፡፡ከስራና ገበያ ፍላጎት ጋር የተሳሰረ የጎልማሶች ትምህርት ፕሮግራም ተሳትፎን ሲታይ ማንበብ፣ መጻፍና ማስላት እንዲችሉ የተደረጉ ጎልማሶች ብዛት በአመቱ መጨረሻ 844,654 (ወንድ 413,684፣ ሴት 430,669) ለማድረስ ታቅዶ 43,926 (ወንድ 26,463፣ ሴት 17,463) የደረሰ ሲሆን የእቅድ አፈጻጸሙ 5.2% (ወንድ 6.4%፣ ሴት 4.1%) ነው፡፡



የጎልማሶች መሰረታዊ ትምህርት ሞጁል ዝግጅት -ባህር ዳር

## የትምህርት ብርሀን ምዘና የወሰዱ ጎልማሶች

የትምህርት ብርሀን ምዘና የወሰዱ ጎልማሶች እና ታዳጊዎች ብዛት በአመቱ መጨረሻ 250,000 (ወንድ 125,000፣ሴት 125,000) ለማድረስ ታቅዶ 22,743 (ወንድ13,080፣ሴት 9,662) የደረሰ ሲሆን የእቅድ አፈጻጸሙ 9.1% (ወንድ 10.5%፣ ሴት 7.7%) ነው፡፡በትምህርት ብርሃን ምዘና ከተሳተፉ ጎልማሶችና ታዳጊዎች መካከል ስታንዳርዱን ያሟሉት ብዛት በአመቱ መጨረሻ 205,000 (ወንድ 102,500፣ሴት 102,500) ለማድረስ ታቅዶ 8,408 (ወንድ 5,740፣ሴት 2,668) የደረሰ ሲሆን የእቅድ አፈጻጸሙ 4.1% (ወንድ 5.6%፣ሴት 2.6%) ሆኗል፡፡እስከ አመቱ መጨረሻ በአለፈው አመት ስታንዳርዱን ከአሟሉ መካከል የገቢ ማስገኛና አጫጭር የሙያ ክህሎት ስልጠናዎች የወሰዱ ወጣቶችና ጎልማሶች ብዛት 50.0% (ወንድ 50.0%፣ሴት 50.0%) ለማድረስ ታቅዶ በ2015 መጨረሻ በምዘናው ስታንዳርዱን ያሟሉ ብዛት 89,261 (ወንድ 23,021፣ሴት 66,240) የነበረ ሲሆን አመታዊ እቅዱ 44,631 (ወንድ 11,511 ፣ሴት 33,120) ሆኗል፡፡በ2016 ዓ.ም ስልጠናውን የወሰዱ 6,009 (ወንድ 4,095፣ሴት 1,914) ወይም ከእቅዱ 13.5% (ወንድ 35.6% ፣ሴት 5.8%) ደርሷል፡፡

## በመደበኛ ያልሆነ ትምህርት በርቀት እና በማታ ፕሮግራሞች

በመደበኛ ያልሆነ ትምህርት በርቀት እና በማታ ፕሮግራሞች የሚሳተፉ ወጣቶችንና ጎልማሶችን በርቀት እና ተከታታይ ትምህርት ማሳተፍ የአገልግሎት ፈላጊዎችን በሙሉ ወይም 100% እንዲሆን ተደርጓል፡፡በመሆኑም በየአካባቢው ፍላጎት ያላቸው እየተሳተፉ ይገኛሉ፡፡በተፋጠነ ትምህርት ተሳታፊዎችን ማሳደግ የተሳታፊዎችን ቁጥር በበጀት አመቱ መጨረሻ 5,250 (ወንድ2,640፣ሴት 2,610) ለማድረስ ታቅዶ 4,668 (ወንድ 2,529፣ሴት 2,139) ደርሷል፡፡በመሆኑም የእቅድ አፈጻጸሙ 88.9% (ወንድ 95.8%፣ሴት 82.0%) ሆኗል፡፡

## የከፍተኛ ትምህርትና ምርምር

የከፍተኛ ትምህርትና ምርምር አግባብነትና ጥራት፣ ፍትሀዊነት እና ተደራሽነትን በሚመለከት በዚህ ዋና ተግባር ስር የመጀመሪያው የሚጠበቅ ውጤት ኮርስ መፅሀፍ የተዘጋጀላቸው የመምህራን ትምህርት ኮሌጅ የ2ኛ ዓመት ኮርሶች ብዛትን የሚመለከት ሲሆን በኮሌጆች በየትምህርት ክፍሉ የሁለተኛ አመት በ1ኛ እና በ2ኛ ሰሚስተር የሚወስዱ ኮርሶች በሙሉ (100%) ኮርስ መፅሀፍ ለማዘጋጀት የታቀደ ሲሆን በዲግሪ ፕሮግራም የ2ኛ አመት አንደኛ እና የሁለተኛ ወሰነ ትምህርት ኮርስ ሲለበሶችና ኮርስ ፕላኖች በፌደራል ትምህርት ሚኒስቴር ደረጃ

ተሰርተው ያልተላኩ ቢሆንም በሁሉም ኮሌጆች ደረጃ እንዲዘጋጅ ተደርጓል፡፡ከዚህ በተጨማሪ የቅድመ አንደኛና የአንደኛ ደረጃ የዲፕሎማ ፕሮግራም ሥርዓተ ትምህርት ኮርስ ሲለበሶችና ኮርስ ሞጁሎች የተዘጋጁ ሲሆን አፈፃፀሙ 100% ደርሷል፡፡

## ክልላዊ የመምህራን ትምህርት ኮሌጆች የሥርዓተ ትምህርት ሂደታዊ ግምገማ

በአመት ሁለት ጊዜ ክልላዊ የመምህራን ትምህርት ኮሌጆች የሥርዓተ ትምህርት ሂደታዊ ግምገማ ለማካሄድ ታቅዶ የመጀመሪያው ዙር ጥቅምት ወር ላይ የተካሄደ ሲሆን የሚቀጥለው ዙር በቀጣይ 2016 በጀት ዓመት ማጠቃላያ ምዕራፍ ላይ እንደሚደረግ የታቀደ ቢሆንም ግምገማው አልተካሄደም፡፡ ስለሆነም የስርዓተ ትምህርት ግምገማ መድረክ አፈፃፀም 50% ነው፡፡ ነገር ግን በኮሌጅ ደረጃ ኮሌጆች የሥርዓተ ትምህርት ሂደታዊ ግምገማ በትምህርት ክፍልና በአካደሚክ ኮሚሽን ደረጃ በመገምገም የአፈፃፀም ክፍተቶችን በመለየትና የማስተካከያ አቅጣጫ በማስቀመጥ ከሥርዓተ ትምህርት ጋር ተያያዥ የሆኑ ተግባራት ተከናውነዋል፡፡

## በኮሌጆች ሁለተኛ ዲግሪና በላይ መምህራንን ማሟላት

ለደረጃው የተቀመጠውን (ሁለተኛ ዲግሪና በላይ) የትምህርት ደረጃ የሚያሟሉ የኮሌጅ አሰልጣኝ መምህራን ብዛት በመቶኛ ለማሻሻል በተያዘው እቅድ መሰረት የአሰልጣኝ መምህራንን ብቃት በማሻሻል የስልጠናውን ጥራት ለማስጠበቅ እንዲቻል ኮሌጆች የአዳዲስ መምህራንን ቅጥር በሚፈጽሙበት ጊዜ ለደረጃው የሚመጠኑትን ብቻ እንዲቀበሉ መደረጉ አንዱ ሲሆን መምህራንን በደረጃ ማሳደግ ስልጠና ደረጃቸውን ማሻሻል ሌላው ስልት ነው፡፡ ይህንም ጥረት ለመደገፍ እንዲቻል በ2016 ዓ.ም በሁሉም ኮሌጆች ከሚያስተምሩ መምህራን መካከል 94% ያህሉ የኮሌጅ አሰልጣኝ መምህራን ለደረጃው የተቀመጠውን የትምህርት ደረጃ የሚያሟሉ ይሆናሉ በሚል ግብ የተጣለ ሲሆን አፈፃፀሙም 90.24% ደርሷል፡፡

## ደረጃ 3 የደረሱ የመምህራን ትምህርት ኮሌጆችን ብዛት ማሻሻል

በ2016 ዓ.ም ደረጃ 3 የደረሱ የመምህራን ትምህርት ኮሌጆች ብዛት ለማሻሻል በአመቱ 80% ያህሉ ኮሌጆች በኢንስፔክሽን ግምገማ ደረጃ 3 ይደርሳሉ በሚል ግብ ተይዞ ምንም እንኳ የመምህራን ትምህርት ኮሌጆች በውጭ ኢንስፒክሽን የተመዘኑ ባይሆኑም

የውስጥ ኢንስፒክሽን አጠናቀው ሪፖርት ካደረጉ ስምንት ኮሌጆች መካከል ስድስቱ (ጎንደር፣ ወልድያ፣ ደብረብርሃን፣ ደብረማርቆስ፣ እንጅባራ፣ በጌምድርና ጎንደር) ደረጃ 3 (ደረጃውን ያሟሉ) እንዲሁም ሁለት ኮሌጆች (ሰቆጣ እና ከሚሴ) ደግሞ ደረጃ 2 (በመሻሻል ላይ ያሉ) ናቸው፡፡

## ባህልና ቱሪዝም

### የቅርስ ጥበቃና እንክብካቤን ማሳደግ

በበጀት ዓመቱ ውስጥ በቢሮው እና በሁሉም ዞኖችና ከተማ አስተዳደሮች በ295 ቅርሶች ላይ የጉዳት መጠን ልየታ በማካሄድ ለ32 ቋሚ ቅርሶች የጥገና ስራ እንዲሰራ ክትትል ለማድረግ ታቅዶ በ164 ቅርሶች ላይ የጉዳት ልየታ ስራ የተሰራ ሲሆን ለ87 ቋሚ ቅርሶች የጥገናና ክትትል ስራ በመስራት አፈጻጸሙን ከተያዘው የጉዳት ልየታ ዕቅድ አንጻር 55.6 በመቶ ከቅርስ ጥገና ዕቅድ አንጻር ከዕቅድ በላይ ለማከናወን የተቻለ ሲሆን ከቅርስ ጉዳት ልየታ አንጻር ግን አፈጻጸሙ ያነሰበት ነው፡፡ ለአፈፃፀሙ ማነስም ስራው ከቦታ ቦታ በመንቀሳቀስ የሚሰራ ከመሆኑ አኳያ በክልላችን ያለው የጸጥታ ችግር ነው፡፡ እንዲሁም ለ956 ተንቀሳቃሽ ቅርሶች የጥገና ስራ ለመስራት ታቅዶ ለ994 ተንቀሳቃሽ ቅርሶች የጥገና ስራ ተሰርቷል፡፡ በዚህም አፈጻጸሙን ከተያዘው ዕቅድ አንጻር ከዕቅድ በላይ መፈፀም ተችሏል፡፡ በ6 ጥንታዊ የስዕል ቅርስ ተቋማት የጥገና ስራ ለማከናወን ታቅዶ 2 ቅርሶችን ማለትም የዑራ ኪዳነ ምህረት እና አዝዋ ማርያም ገዳም ከኢትዩጵያ ቅርስ ጥበቃ ባለስልጣን ጋር በመሆን የስዕል ጥገና ስራ እየተከናወነ ይገኛል፡፡

በሁሉም ዞኖች እና ከተማ አስተዳደሮች ለ295 ቋሚና ለ11,807 ተንቀሳቃሽ ቅርሶች እንክብካቤ እና የጽዳት ስራ ለመስራት ታቅዶ ለ958 ቋሚ እና ለ22,101 ተንቀሳቃሽ ቅርሶች የጽዳት እና የእንክብካቤ ሥራ ተሰርቷል፡፡

### የክልሉን የባህልና ቋንቋዎች ልማትና አጠቃቀምን ማሳደግ

በ2016 በጀት ዓመት መጀመሪያ ላይ በክልሉ የሚከበሩ ሻዳይ ፣አሸንድዬ፣ ሶለል፣ ቡሄና እንግጫ ነቀላ ክብረ-በዓላት ማጠቃለያ በዓልን ከነሀሴ 16 ጀምሮ በየአካባቢው በማከበር ለህዝብ ተደራሽ ሆኗል፡፡

“አዲስ ዓመትን በአዲስ መንፈስ “በሚል የአዲስ ዓመት ዋዜማ ዝግጅት ማስፈጸሚያ ሰነድ ተዘጋጅቶ ፕሮግራሙ ጳጉሜ 6 የክልሉ ርዕሰ-መስተዳድርን ጨምሮ ከፍተኛ አመራሮች እና የባህርዳር ከተማ ነዋሪዎች በተገኙበት በድምቀት ተከብሯል፡፡

የ18ኛው የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ቀን በዓል “ብዝሃነትና እኩልነት ለሃገራዊ አንድነት” በሚል መሪ ቃል በሶማሌ ክልል ጅግጅጋ ከተማ ከህዳር 25 እስከ 29/2016 ዓ.ም ሲከበር የበአሉ አስተባባሪዎችንና ከየዞኑና ከብሄረሰብ ዞኖች የተውጣጡ ወንድ 55፣ ሴት 37 በድምሩ 92 የአማራ ክልል የባህል አምባሳደሮች / የባህል ትርኢት አቅራቢዎች/ በማስተባበር ለማሳተፍ ተችሏል፡፡




የክልሉ ሉዕኳን ቡድን ጅግጅጋ ላይ የነበረው ገፅታ የሚያሳይ ምስል

በሀገር አቀፍ ደረጃ ለሚካሄደው የቋንቋ ሲምፖዚየምና ኢግዚቪሽን የሚውል በክልሉ ያሉ ብሄረሰብ ዞኖች ቋንቋ የተዘጋጁ የመዝገበ ቃላት፣ የሰነድና መዛግብት ስራዎችን የማሰባሰብ ስራ ተሰርቷል፡፡

የአለባበስና አጊያጊያጥ ስርዓትን ለማጉላት፣ ለማስተዋወቅ የጎንደር ከተማ የሴቶች ጸጉር አሰራር እና ታሪካዊ አመጣጥ የሚያሳይ በጎንደር በስዕል እና በፎቶግራፍ ኢግዚቪሽን ተዘጋጅቶ ለእይታ እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡

በበጀት ዓመቱ የጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን ለመቀነስ የሚያስችሉ በ4500 መድረኮች ለ900 ሽህ የህብረተሰብ ክፍሎች (50 በመቶ የሴቶች፣20 በመቶ የወጣቶች፣3 በመቶ የህጻናት እና ቀሪው 77 በመቶ የአዋቂዎች ድርሻ) የግንዛቤ ፈጠራ ስራ ለመስራት ታቅዶ በ781 መድረኮች

በማዘጋጀት ለ191 ሽህ (210 ሴቶች እና ለ183 ሽህ 712 ወንዶች በድምሩ ለ374 ሽህ 922 ) የህብረተሰብ ክፍሎች የግንዛቤ ፈጠራ ስራ ተሰርቷል፡፡






### በጎጂ ልማዳዊ ድርጊት እና በግጭት አፈታት ዙሪያ  ስልጠና ላይ ኮምቦልቻ

127ኛው የአድዋ ድል በዓል የካቲት 23/2016 ዓ.ም በተለያዩ ዝግጅቶች ማለትም አባት አርበኞች፣ የሀይማኖት አባቶች፣ የኪነ-ጥበብ አማተሮች፣ ተማሪዎች፣አጠቃላይ የከተማው ህብረተሰብ በተገኙበት በፉከራና በቀረርቶ በዋና ዋና ጎዳናዎች በደመቀ ሁኔታ የተከበረ ሲሆን በሙዚቃ፣ በድራማ፣ በግጥም፣ በፉከራና ቀረርቶ እና የፓናል ውይይት በማድረግ በዓሉ በተለያዩ ከተሞች በደመቀ ሁኔታ ተከብሮ ውሏል፡፡




የአድዋ በአል አከባበር በከፊል ደብረ ብርሃን

## የክልሉን የስነ-ጥበብና የኪነ-ጥበብ ስራዎችን ማጎልበት

"ባህላችን ለሰላማችንና ለአንድነታችን "በሚል መሪ ቃል የባህልና ኪነ-ጥበብ ፌስቲቫል ተከናውኗል፡፡ በፌስቲቫሉ ላይ ከዞኖችና ከተማ አስተዳደሮች የተሳተፉ 19 የባህል ሙዚቃ ቡድኖች  ዝግጅታቸውን ያቀረቡ ሲሆን 14 የዕደ-ጥበብ አምራቾች የተለያዩ ባህላዊ ምርቶችን ለኤግዚቢሽን እና ለሽያጭ ሲያቀርቡ የተመረጡ  የስዕልና ቅርጻ ቅርጽ ስራዎችም ለኤግዚቢሽን

ቀርበዋል በዚህም ፕሮግራም ላይ የላቀ የኪነ -ጥበብ አስተዋጽኦ ያበረከቱ 9 ሞዴል ከያንያን ተሸላሚ ሆነዋል፡፡

"የባህል ጥበባት ለማህበረሰብ ትስስርና ለህገረ መንግስት ግንባታ " በሚል መሪ ቃል ሁሉም ክልሎች በተሳፉበት በሀገር አቀፍ የኪነ-ጥበብና ስነ-ጥበበ ፈጠራ ውድድርና ትዕይንት ላይ በስነ - ስዕል /ቀለም ቅብ/፣ በባህላዊ አልባሳት ፋሽን ሾው፣ በባህላዊ ሙዚቃና ውዝዋዜ ውድድር ተሳትፎ ተደርጓል፡፡

## የዕደ-ጥበብ ምርትን ማስፋፋትና ገበያን ማጎልበት

በክልላችን የሚገኙ በአካል ለሁለት የዕደጥበብ አምራቾች ማህበራት እና ለአራት ማህበራት በስልክ ድጋፍ ተደርጓል፡፡ ለ3 ቀን በቆየው በሀገር አቀፍ የኪነ-ጥበብና ስነ-ጥበበ ፈጠራ ውድድርና ትዕይንት ላይ 2 የዕደ ጥበብ አምራቾች የክልሉን የዕደጥበብ ውጤት ይዘው እንዲሳተፉ ተደርጓል፡፡ በሁሉም ዞኖችና ከተማ አስተዳሮች በባህል ኢንዱስትሪ ለተሰማሩ ለ108 ተቋማት እና ማህበራት ገበያ ትስስር በመፍጠር 200 አባላትን ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ ለ218 ተቋማት ትስስር በመፍጠር 451 አባላትን ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡
ለ200 በባህል ኢንዱስትሪ ልማት (ዕደ-ጥበባት) ለተሰማሩ ባለሙያዎች የሥራ አመራርና የፈጠራ ክህሎት ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ ለ163 አባላት ስልጠናውን መስጠት የተቻለ በመሆኑ አፈፃፀሙ ከበጀት አመቱ እቅድ አንፃር 81.5 ፐርሰንት ነው፡፡





የዕደ-ጥበብ አውደ ርዕይ ሲካሄድ

## የሀገር ውስጥ ቱሪዝም ልማት ማስፋፋት

በበጀት አመቱ ከቢሮ እስከ ወረዳ ድረስ በቱሪዝም ማህበራዊ፤ባህላዊ፤ኢኮኖሚያዊ እና አካባቢያዊ ጠቀሜታዎች ዙሪያ ግንዛቤ ለመፍጠር ታቅዶ በ83 መድረኮች ለ22,334 ሴቶችና ለ21,905 ወንዶች በድምሩ ለ44,239 የህብረተሰብ ክፍሎች ግንዛቤ ለመፍጠር ተችሏል፡፡

የሀገር ውስጥ ቱሪስት ፍሰትን 8,150,016 ለማድረስ ታቅዶ 7,095,510 በማድረስ አፈጻጸሙ 87 በመቶ ነው፡፡ የውጭ ሀገር ቱሪስት ፍሰትን 93,366 ለማድረስ ታቅዶ 19,196 የተፈፀመ ሲሆን በመቶኛም 20.56 ነው፡፡ጠቅላላ የቱሪስት ፍሰትን 8,243,382 ለማድረስ ታቅዶ 7,114,706 ማድረስ የተቻለ ሲሆን አፈጻጸሙ 86.31 በመቶ ነው፡፡ ከገቢ አንፃርም ከሀገር ውስጥ ጎብኝዎች 3,642,229,788፣ከውጭ ሀገር ቱሪስቶች 93,295,641 ብር በጠቅላላ 735,525,429 ገቢ ተገኝቷል፡፡ከዕቅድ አንጻርም 87.06 በመቶ ማድረስ ተችሏል፡፡

### ህብረተሰብ ተጠቃሚነት መተመለከተ

በዘርፉ በአገልግሎት ሰጭ ተቋማት፣በቅርስ ጥገናና እንክብካቤ በባህል ኢንዱስትሪ ዘርፍ በሚሰሩ ስራዎች ለዜጎች የስራ ዕድል መፍጠር የተቻለ ሲሆን በበጀት አመቱ ለ25,000 ሴቶች እና ለ25,000 ወንዶች በድምሩ 50,000 ለሚሆኑ ዜጎች ቋሚ የሥራ ዕድል ለመፍጠር ታቅዶ ለ7,959 ሴቶች እና ለ5,608ወንዶች በድምሩ ለ13,567ዜጎች ቋሚ የሥራ ዕድል ተፈጥሯል፡፡

## ጤና

### የህፃናት ጤና አገልግሎት

ከአምስት አመት በታች የሆኑ ህፃናት የሳምባ ምች ታመው የታከሙ ሽፋን 78 ለማድረስ ታቅዶ ክንውን 533,225 /62%/ እንዲሁም በክልላችን ታመው የአፍ ውስጥ የውሃ ፈሳሽ መፍትሄዎች (ORS) እና ዚንክ የታከሙ ህፃናት ሽፋን እቅድ 30% ክንውን 757,469 /24%/፣ የጨቅላ ፃናት ኢንፌክሽን በሽታ ይያዛሉ ተብለው ከሚጠበቁት እቅድ 60% ክንውን 89142 /49%/፣ ጨቅላ ህፃናት ፅኑ ህሙማን ክፍል ውስጥ ታክመው አገግመው /ድነው/ የወጡ ህፃናት 27400 /77%/ በተመሳሳይ የቀዳማዊ ልጅነት እድገትና መዳበርን 313670 /25%/ ለሚሆኑ ጨቅላ ህፃናት የህክምና አገልግሎት መስጠት ተችሏል፡፡

### የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራሙን ማጠናከር

የጤና ኤክቴንሽን ፕሮግራሙን ለማጠናከር በሮድማፑ መሰረት የጤና ኬላዎችን በሶስት ምድብ በመለየት ከጤና ጣቢያ ጋር የሚዋሀዱ 635 ተለይተው 353 ተዋህደው ስራ የጀመሩ ሲሆን መሰረታዊ አገልግሎቶችን የሚሰጡ 2242 ጤና ኬላዎች ተለይተው 133 መስፈርት ያሟሉ ሲሆን 30 ጤና ኬላዎች ከጤና ጣቢያ ነርስ እና ሚድዋይፈሪ ተመድቦላቸው አገልግሎት በመስጠት ላይ ሲሆኑ የተቀናጀ ሙሉ የህክምና አገልግሎት የሚሰጡ ጤና ኬላዎች 518

ተለይተው 26 ግንባታው ተጠናቆ 12 ጤና ኬላዎች ከጤና ጣቢያ ባለሙያ ተመድቦ የተቀናጀ ሙሉ የህክምና አገልግሎት እየሰጡ ነው፡፡ ሌሎች መሰረታዊ አገልግሎቶችን የተቀናጀ ሙሉ ህክምና አገልግሎት መስጠት ያለባቸው 117 ጤና ኬላዎች ሲቪል ሰርቪስ ፎረም 15 ስላልተፈቀደ አገልግሎት አልጀመሩም፡፡

## የእናቶች ጤና አገልግሎት

የቅድመ ወሊድ፣ የወሊድ እና የድህረ ወሊድ አገልግሎት ተጠቃሚ እናቶች ነፍሰጡር መሆናቸውን ካወቁበት ቀን ጀመሮ በጤና ተቋም ከጤና ባለሙያ ጋር በመመካከር ጤናማ የሆነ ከእርግዝና ጊዜ እና ጤናማ ፅንስ እንዲኖር እንዲሁም ከወሊድ በኋላ ጤነኛ እናትና ልጅ እንዲቀጥል በጥቅሉ ከእርግዝና እና ከወሊድ ጋር በተያያዘ የሚከሰተውን የእናቶችና ወጣቶች ሞት እና ህመም የምንከላከልባቸው አገልግሎቶች ዋናዎቹ ናቸው፡፡

በ2016 ዓ.ም በአመት ውስጥ የቅድመ ወሊድ ክትትል -1 /ANC-1/ አገልግሎት ያገኛሉ ተብሎ ከታቀደ 98% እናቶች ውስጥ 658674 /83%/ አንድ ጊዜ አገልግሎት የገኙ ሲሆን ከ12 የእርግዝና ሳምንት በፊት የቅድመ ወሊድ ክትትል እንዲጀምሩ ከታቀደው 35% መካከል 178051 /22%/ እናቶች ክትትል ጀምረዋል፡፡ በመሆኑም የነፍሰጡር እናቶች ልየታ እና ምዝገባ እንዲሁም የቅድመ ወሊድ ክትትል ቀድሞ የማስጀመር ስራ በሚፈለገው ደረጃ ባለመሆኑ ቀድሞ ክትትል መጀመርንም ሆነ በተከታታይ የሚከናወኑ አገልግሎቶች አፈፃፀም ዝቅቀተኛ እንዲሆን አድርጉታል፡፡ ቅድመ ወሊድ-4 አገልግሎት /ANC-4/ 82% ሽፋን ይኖራል ተብሎ ታቅዶ 519874 /65%/ ተከናውኗል፡፡ ቅድመ ወሊድ ክትትል-1 እና አራት መካከል ያለው የአቋራጭ መጠን ወደ 10% ለመቀነስ ታቅዶ አፈፃፀሙ 21 ፐርሰንት ነው፡፡የቅድመ ወሊድ አገልግሎት -8 (ANC-8) አፈፃፀሙ 18% ለማከናወን ታቅዶ 122516 /15%/ ተፈፅሟል፡፡ በመሆኑም የነፍሰጡር ልየታ እና ተከታታይ አገልግሎቶች በቀጣይ የበለጠ ተጠናክሮ መቀጠል እንዳለበት ያመላክታል፡፡

በጤና ተቋም በሰለጠነ ባለሙያ በመታገዝ የወሊድ አገልግሎት ሽፋን 77% ለማድረስ ታቅዶ የአመቱ አፈፃፀም 460708 /58%/ ሲሆን በጤና ተቋም በሰለጠነ ባለሙያ የወሊድ አገልግሎት በቀጣይ መሻሻል ያለበት እንደሆነ ያሳያል፡፡ በአለም አቀፍ ጤና ድርጅት መስፈርት መሰረት በጠቅላላ የጤና ተቋማት ከሚወልዱ እናቶች መካከል ከ5-15% የሚሆኑ እናቶች በቀዶ ጥገና

ይወልዳሉ ተብሎ ይገመታል፡፡ በዚህ መሰረት በክልላችን በቀዶ ጥገና የወለዱ እናቶች 9% ለማድረስ ታቅዶ የተከናወነው ግን 45057 /6%/ ነው፡፡

የድህረ ወሊድ አገልግሎት በተመለከተ እናቶች ከወለዱ በኂላ ከ48 ሰዓት ውስጥ የድህረ ወሊድ አገልግሎት እንደሚያገኙ ይጠበቃል፡፡ በዚህ መሰረት በበጀት ዓመቱ አገልግሎት ያገኛሉ ተብሎ ከታቀደው 85% ከወለዱ እናቶች መካከል አገልግሎት ያገኙ 448946 /57%/ ናቸው፡፡ በተጨማሪም እስከ 7 ቀን ድረስ የድህረ ወሊድ አገልግሎት ያገኛሉ ተብሎ ከታቀዱ 85% እናቶች መካከል 580729 /73%/ የአገልግሎቱ ተጠቃሚ ሆነዋል፡፡በበጀት አመቱ የጤናማ እናትነት ወርን ማክበር ተችሏል፡፡



*የጤናማ እናትነት ወር ሲከበር*

## የእናቶች ሞት እና ሞተው የተወለዱ ጨቅላ ህፃናት

የእናቶችን ሞት በተመለከተ በተባበሩት መንግስታት ድርጅት ጥናት መሰረት በሀገር ደረጃ በእርግዝና እና ከወሊድ ጋር በተያያዘ 267/100,000 በህይወት ከሚወለዱ ህፃናት ውስጥ ህይወታቸው ያልፋል ተብሎ ይገመታል፡፡ በመሆኑም በክልላችን በ2016 ዓ.ም ይወልዳሉ ተብለው ከሚገመቱ 793918 ነፍሰጡር እናቶች መካከል 2090 እናቶች ከወሊድ ጋር በተያዘ ህይወታቸው ያልፋል ተብሎ ይገመታል፡፡ በዚህ መሰረት በ2016 ዓ.ም 193 እናቶች በጤና ተቋም 127 እናቶች ደግሞ በማህበረሰብ ውስጥ በድምሩ 320 እናቶች ህይወታቸው አልፏል፡፡ ይህም ከሚጠበቀው ሞት በላይ የተከሰተ በመሆኑ ሰፊ ስራ የሚጠይቅ ተግባር ነው፡፡

የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ጥናት መሰረት (Still Birth) 15/1000 በህይወት ከተወለዱ ህፃናት ህይወታቸው አልፎ ይወለዳሉ ተብሎ ከሚገመቱ 793918 ጨቅላ ህፃናት ውስጥ 11115 ህይወታቸው አልፎ ተወልደዋል፡፡ ይህም ሲሰላ ከአንድ ሽህ የተወለዱ ህፃናት መካከል 14 /14/1000 በህይዎት ከተወለዱ ህፃናት / ሞተው የተወለዱ ናቸው፡፡

## የጨቅላ ህፃናት እና ህፃናት ጤና

በ2016 ዓ.ም ታፍነው የተወለዱ ጨቅላ ህፃናት 7011 (82%) አገልግሎት በመስጠት ህይወታቸውን ለማዳን ተችሏል፡፡ ዝቅተኛ ክብደት ያላቸው ወይም ከመወለጃ ቀናቸው ቀድመው የተወለዱ ጨቅላ (የKMC) 7261 (80%) አገልግሎት አግኝተዋል፡፡በሰምባ ምች ታመው የታከሙ ከ5 ዓመት በታች የሆኑ ህፃናት ሽፋን 533225 /62%/ ሲሆኑ በተቅማጥ በሽታ ታመው በORS እና ዚንክ የታከሙ ከ5 አመት በታች የሆኑ ህፃናት 757,469 (24%) ናቸው፡፡

የጨቅላ ህፃናት ኢንፌክሽን በሽታ ይያዛሉ ተብሎ ከሚጠበቁት 89142 /49%/ ህፃናት መካከል ጨቅለ ህፃናት ጽኑ ህሙማን ክፍል ውስጥ ታክመው አገግመው /ድነው/ የወጡ 27404 /77%/ ናቸው፡፡ ከዚህ በጨማሪ የቀዳማዊ ልጅነት እድገትና መዳበርን ለ3136670 /25%/ ለሚሆኑ ጨቅላ ህፃናት እና ህፃናት የህክምና አገልግሎት ለመስጠት ተችሏል፡፡ በመሆኑም ምንም እንኳን ክልሉ በችግር ውስጥ ቢሆንም በአጠቃላይ ውጤቱ ከባለፈው ዓመት ጋር ሲነፃፀር ከሳንባ ምችና ከተቅማጥ በስተቀር በሌሎች አመልካቾች የተሻለ ውጤት ተመዝግቧል፡፡ በበጀት አመቱ የጨቅላ ህፃንትን ቀን ማክበር ተችሏል፡፡



*የጨቅላ ህጻናት ቀን ሲከበር*

## ፍትሃዊ የጤና አገልገሎት

የጤናው ዘርፍ ለክልሉ ኢኮኖሚ እድገት በአማካይ የ3.35 ቢሊየን ብር እሴት ጭማሪ አበርክቶ አለው፡፡ ስለሆነም በበጀት አመቱ ልክ እንደሌላው ዘርፍ ሁሉ ለጤናው ሴክተር ትኩረት ተሰጥቶት እየተሰራ ይገኛል፡፡በክልሉ ጥራት ያለው ፍትሃዊ የጤና አገልገሎትን ለማሳለጥ እና ማህበረሰቡን ለማርካት የተጀመሩ ሰባት አዳዲስ ተግባራት አፈጻጸም ሲታዩ በጤና ጣቢያ ደረጃ አልትራሳውንድ አገልግሎት የጀመሩ በቁጥር 132፣ጤና ጣቢያዎችን የቀዶ ህክምና አገልግሎት ማስጀመር 19፣ኢዲቴብል የሆነ የፋርማሲ አገልግሎት የሚሰጡ ጤና ተቋማትን ቁጥር 144፣የሙሉ ኤሌክትሮኒክ የህክምና መረጃ አያያዝ ስርዓት የተገበሩ ጤና እና ሆስፒታል ቁጥር

6 እና የማህበረሰብ መድሃኒት ቤት አገልግሎት በወረዳ/ከተማ አስተዳደር በቁጥር 27 ለማድረስ 5 በዝግጅት ላይ ናቸው፡፡

## የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት

የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት ተጠቃሚዎች 1,369,519(38.3%) ወጣቶችና አፍላ ወጣቶች ሲሆኑ ከ 548,301 አዲስ የቤተሰብ እቅድ አጠቃላይ ተጠቃሚዎች ውስጥ 310,610 (56.6%) እድሜያቸው ከ10-24 የሆኑ ወጣቶች ሲሆኑ ከ15-19 እድሜ ያሉት አፍላ ወጣቶች ደግሞ 131868(24%) ተጠቃሚ ናቸው፡፡አጠቃላይ ከ1049 ዓመት ከወሊድ በኋላ ወዲያውኑ በ48 ስዓት ውስጥ የሚሰጥ የቤተሰብ እቅድ አገልግሎት ተጠቃሚዎች 9716 (2.1%) ሲሆኑ ከእነዚህም ውስጥ የአፍላ ወጣቶች እና ወጣቶች(10-24 ዓመት) ደግሞ 3733 (38.4%) ናቸው፡፡

## የቤተሰብ እቅድ

የቤተሰብ እቅድ 85% ለማድረስ ታቅደ 3,578,920 (75%) ለሚሆኑ በመውለድ እድሜ ክልል ላሉ ሴቶች መስጠት ተችሏል፡፡ የልጅነት እርግዝናን ወደ 7% ለማውረድ ታቅዶ 8.8% ከፍ ብሏል፡፡ የቅድመ ወሊድ ክትትል ለመጀመሪያ ጊዜ (ANC1) አገልግሎት ለ90% ለማድረስ ታቅዶ 658,674 (82.7%) ለሚሆኑ ነፍሰጡር እናቶች የአንድ ጊዜ አገልግሎት ያገኙ ሲሆን 22.4% የሚሆኑት የእርግዝና ጊዜቸው ከ12 የእርግዝና ሳምንት በፊት የቅድመ ወሊድ ክትትል እንዲጀምሩ ከታቀደው 35% ውስጥ 178,051(22%) እናቶች ክትትል ጀምረዋል፡፡የቅድመ ወሊድ አገልግሎት (ANC4) 82% ለማድረስ ታቅዶ 519,874 ( 65.3%) ያገኙ ነፍሰ ጡር እናቶች ሲሆኑ አራት ጊዜ ክትትል አግኝተዋል፡፡

## በሰለጠነ ባለሙያ በመታገዝ የወሊድ አገልግሎት መስጠት

በሰለጠነ ባለሙያ በመታገዝ የወሊድ አገልግሎት 77% ለማድረስ ታቅዶ 460,708 (58%) የሚሆኑ እናቶች በጤና ተቋም አገልግሎቱን ያገኙ ሲሆን ከነዚህ ውስጥ 10.2% የሚሆኑት በቀዶ- ጥገና ህክምና የወለዱ ሲሆን በወለዱ በመጀመሪያው 7 ቀን የድህረ ወሊድ አገልግሎት ያገኙ እናቶች ሽፋን 580,729 (73%) ናቸው፡፡ በሌላ በኩል ከእርግዝና እና ከወሊድ ጋር በተያያዘ ህይወታቸው ያለፈ እናች 320 ሲሆን 193 በጤና ተቋም እና 127 በማህበረሰቡ ውስጥ ሲሆን ህይወታቸው አልፎ የተወለዱ ጨቅላ ህጻናት 6,531(14/1000 በህይወት

ከተወለዱት ህጻናት) ነው፡፡ለ35,668 ጨቅላ ህፃናት በክልሉ ውስጥ በሚገኙ ሆስፒታሎች በጨቅላ ህፃናት ፅኑ ህክምና ክፍል ተኝተው የታከሙ ሲሆን 27,404 (77%) የሚሆኑት በተሰጣቸው ህክምና ሙሉ በሙሉ ድነዋል፡፡

## የክትባት አገልግሎት መስጠት

በ2016 ዓ.ም ውስጥ ከ1 ዓመት በታች ለሆኑ ህጻናት ፔንታቫለንት አንድ፣ ፔንታ ቫለንት ሦስት እና የኩፍኝ አንድ ክትባት 100% ለማድረስ ታቅዶ በቅደም ተከተል ክትባቱን ይወስዳሉ ተብሎ ከሚጠበቁት 98% ህፃናት መካከል በቅደም ተከተል 93%፣ 89% መከተብ ችለዋል፡፡





*ክትባት በተመለከተ እቅድ ክንውን ግምገማ*

## የህፃናት የምግብ እጥረትና አለመመጣጠን ልየታ ስራ

ከአምስት ዓመት በታች ህፃናት የምግብ እጥረትና አለመመጣጠን ልየታ ስራ 75% ለማድረስ ታቅዶ 66% ለሚሆኑ ህፃናት የተሰራላቸው ሲሆን ከነዚህ መካከል 56.2% የሚሆኑት መካከለኛ የምግብ እጥረት የተገኘባቸው ሲሆን 148,899 (9.5%) ከፍተኛ የምግብ እጥረት ያለባቸው ናቸው፡፡ የምግብ እጥረት ተገኝቶባቸው ወደ ህክምና ከገቡት 81% ህፃናት መካከል 47,757 (81%) የሚሆኑት በህክምና ጋይድላይኑ መሰረት ታክመው ድነው መውጣት ችለዋል፡፡በተመሳሳይ ለሚዲያ ባለሙያዎችና አመራሩ በስርዓተ ምግብ ዙሪያ ስልጠና መስጠት ተችሏል፡፡



*ለሚዲያ አካላት ስርዓተ ምግብ ስልጠና ሲሰጥ*

## ኤች አይ ቪን መከላከል እና መቆጣጠር

በበጀት አመቱ ተላላፊ የሆኑ እና ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎችን መከላከል እና መቆጣጠር ስራ የተሰራ ሲሆን ኤች አይ ቪን ከመከላከል እና ከመቆጣጠር አንፃር ሶስቱን 95 ኢላማዎች ለማሳካት ጠቅላላ ኤችአይቪ በደማቸው መኖሩን ያወቁት ቁጥር ይኖርባቸዋል ተብለው ከሚጠበቁት 173,416 መካከል 157,401 ራሳቸውን አውቀዋል፡፡በመሆኑም የመጀመሪያው 95 ኢላማ 91% ማድረስ ተችሏል፡፡ሁለተኛውን 95 ለማሳካት የፀረ ኤች አይ ቪ መድሃኒት በመጠቀም ላይ ያሉ ህሙማን መጠን 156,091 (99.1%) የሚሆኑ ሰዎችን የፀረ ኤች አይ ቪ መድሃኒት ተጠቃሚ ማድረግ የተቻለ ሲሆን ከዚህ ውስጥ 3,066 ህጻናት ናቸው ፡፡ በተጨማሪ ሶስተኛውን 95 ኢላማ ለማሳካት ከጸረ-ኤች አይቪ መድሃኒት ተጠቃሚዎች 145,336 (96%) የሚሆኑት በደማቸው ያለው የኤች አይ ቪ ቫይረስ መጠን በሚሊ ሊትር ከ1000 ኮፒ በታች ነው፡፡



*የአለም የኤድስ ቀን ሲከበር*

## የቲቢ ሕክም

በበጀት አመቱ የቲቢ ሕክምና ሽፋን(ሁሉም አይነት) 22,085(65%) የቲቪ መዳን ምጣኔ 91% እና የህክምና ስኬት 96% መድሃኒት የተላመደ ቲቪ ህክምና ሽፋን 52% ሲሆን ስኬቱም 86% ሲሆን ባለፈው በጀት አመት ከነበረው 77% ዝቅተኛ አፈጻጸም ተመዝግቧል፡፡

## የወባ በሽታ ህክምና

በ2016 በጀት ዓመት 4,263,698 የሚሆኑ የወባ ተጠርጣሪዎች በየደረጃው ባሉ ጤና ተቋማት የላቦራቶሪ ምርመራ የተደረገላቸው ሲሆን ከነዚህም ውስጥ 1,480,996 (34.7%) ወባ የተገኘባቸው ሲሆን በክልላችን ውስጥ ባሉ ጤና ተቋማት ውስጥ 25 ሰዎች በወቅቱ ህክምና ባለማግኘታቸው በወባ በሽታ ምክንያት የሞቱ ናቸው፡፡



*ወባን መከላከል በተመለከተ ከጤና ትምህርትና ተግባቦት ባለሙያዎች ጋር የተደረገ ውይይት*

## የማህጸን ጫፍ ቅድመ ካንሰር ልየታ

የማህፀን በር ካንሰር በሁለተኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ በጣም የተለመደ የካንሰር ዓይነት ሲሆን ምልክት ሳያሳይ የሴቶችን ጤና አደጋ ላይ የሚጥል በሽታ ነው፡፡ በቀን ውስጥ 14 የሚያህሉ ሴቶች በማህፀን በር ካንሰር ይሞታሉ፡፡ ስለዚህ የተሻለ መፍትሄ እና ህክምናን ለማግኘት እንዲሁም ችግሩ የከፋ ደረጃ ላይ ሳይደርስ ለማወቅ የማህጸን ካንሰር ምርመራ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡በመሆኑም በ2016 ዓ.ም 400,890 ሴቶች የማህጸን ጫፍ ቅድመ ካንሰር ልየታ ተደረገው 81,100 (20%) ምርመራ ተደርጎላቸው 2,966 (3.7%) የማህፀን ጫፍ ቅድመ ካንሰር ምልክት ተገኝቶባቸው 1,954 (66%) ህክምና ተደርጎላቸዋል፡፡

## ትራኮማ በሽታ መከላከል

የትራኮማ በሽታ ካላሚዲያትራኮሚቲስ በተባለ ህዋስ (ባክቴሪያ) የሚመጣ ሲሆን ተገቢው ህክምና ካልተደረገለት ወደ ዓይነስውርነት ሊያመራ ይችላል፡፡ በሽታው ቀስ በቀስ ዓይንን በመቆርቆር የስሜት እንባን በማንባት፣ በማቅላትና የፀሐይ ብርሃን በመፍራት ይታወቃል፡፡

በመጨረሻ ደረጃ ላይ የደረሰ ትራኮማ ደግሞ የዓይን ቆብ ሽፋሽፍት ወደ ውስጥ እንዲቀለበስ በማድረግ ከፍተኛ የሆነ የመቆርቆር ስሜትና ስቃይን ያስከትላል፡፡ የዓይን ቆብ ሽፋሽፍት ወደ ውስጥ ሲቀለበስ የሽፋሽፍት ፀጉሩ የዓይን መስታወቱን (ኮርኒያ) አዘውትሮ ስለሚፍቀው የዓይን መስታወቱ ይቆስልና ጠባሳን ይፈጥራል፡፡ ይህም ሁኔታ ብርሃን ወደ ዓይናችን ውስጠኛው ክፍል መግባት እንዳይችል ስለሚያደርግ አይነስውርነትን ያስከትላል፡፡ በመሆኑም በ2016 በጀት አመት በትራኮማ ምክንያት ለሚከሰት የአይን ቆብ ፀጉር ወደ ውስጥ መቀልበስ ችግር ለገጠማቸው 83,887 የህብረተሰብ ክፍሎች አገልግሎት እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡



*የትራኮማ በሽታ መከላከል -ጎንደር ከተማ (አይራ ሆስፒታል)*

## የተሻሻለ የመጸዳጃ ቤት አገልግሎት

የተሻሻለ የመጸዳጃ ቤት አገልግሎት (basic + limited sanitation facilities) የሚጠቀሙ አባወራዎች በቁጥር 3,114,195 ሲሆን ሽፋኑን 753,321 (24.18%) ማድረስ ተችሏል፡፡ከአይነ ምድር የጸዳ ቀበሌ ከመፍጠር አንጻር እንደ ክልል ይደረስበታል ተብሎ ከታቀደው 635 ቀበሌዎች 260 (41%) ነጻ ሲሆኑ አፈጻጸሙም ዝቅተኛ ስለሆነ በቀጣይ 2017 ዓ.ም በልዩ ትኩረት መሰራት እናዳለበት ያሳያል፡፡

## የኮሌራ በበሽታ

በክልሉ ውስጥ በተለያዩ ዞኖች በኮሌራ በበሽታ ወረርሽኝ 5,874 ሰዎች ተይዘው የነበሩ ሲሆን ከእነዚህ መካከል ከበሽታው ያገገሙ 5,775 (98.3%) ሲሆኑ የሞቱት ደግሞ በቁጥር 99 መሆናቸው ሪፖርት ተደርጓል፡፡ 33,885,622 ሰዎች ለተመላላሽ ህክምና፣ 318,007 ሰዎች ለተኝቶ ህክምና እና 726,900 ለድንገተኛ ህክምና በክልሉ ውስጥ በሚገኙ ጤና ተቋማት ጎብኝተዋል፡፡ከዚህ በተጨማሪ 81,073 ሰዎች ከፍተኛ ቀዶ-ህክምና አገልግሎት አግኝተዋል፡፡



*የኮሌራ በሽታ መከላከያ ክትብት ማስጀመሪያ መርሀ ግብር*



*የኮሌራ በሽታ መከላከያ ክትብት ማስጀመሪያ መርሀ ግብር*

## የጤና ተቋማት ቁጥጥር

በጤና ቢሮ እና በስሩ ባሉ የቁጥጥር ባለሙያዎች በተመረጡ 8,397 የተለያዩ አገልግሎት ሰጭ ጤና ነክ ተቋማት (ድርጅቶች) ላይ የቁጥጥር ስራ ተሰርቷል፡፡በተጨማሪ ከኢትዮጵያ ምግብና መደሃኒት ቁጥጥር ባለስልጣን ጋር በመሆን በ333 ጤና ተቋማት የቁጥጥር ስራ በማድረግ አስተዳዳራዊ እርምጃ እንዲወሰድ ተደርጓል፡፡በዚህም ድንገተኛ ቁጥጥር 13.8 ሚሊዮን ብር ዋጋ ያላቸው ህገወጥ መድሀኒቶች ተሰብስበው እንዲወገዱ ተደርጓል፡፡

## የመድሀኒት አቅርቦት

በበጀት አመቱ ከመንግስት፣ከጤና ሚኒስቴር እና ከተለያዩ አጋር አካላት ጋር በመተባበር በድምሩ 3,321,154,023.27 ብር የሚያወጣ የመድኃኒት፤የህክምና መሳሪያዎች፤የህክምና መገልገያ መሳሪያዎች፤እና ኬሚካሎች በመድኃኒት አቅራቢ አገልግሎት ቅርንጫፎች እና በጤና ቢሮ በኩል ስርጭት ተከናውኗል፡፡በ2016 ዓ.ም የማህበረሰብ ጤና አባል ይሆናሉ ተብለው ከተገመቱት 4,576,373 አባወራ/እማወራ መካከል 2,827,458(62%) አባል ማድረግ ተችሏል፡፡ከከፋይ አባላት 2,072,602,115 ብር የተሰበሰበ ሲሆን 2,043,506,977.00(99%) ወደ ጤና መድህን አካውንት ገብቷል፡፡የ2016 ዓ.ም የተናጥል ድጎማ 30 ፐርሰንት የወረዳን ድርሻ ያስገቡ ወረዳዎች 171(93%) ሲሆኑ ከዚህ ውስጥ የሚጠበቅባቸውን በትክክል ያስገቡ ወረዳዎች 146(79% ናቸው፡፡የውስጥ ገቢን በተመለከተ የተመደ በጀት 1,743,571,039.00 ሲሆን ስራ ላይ የዋለ 730,153,115.40 (42%) ነው፡፡

## ሲቪል ሰርቪስና የሰው ሀብት አስተዳደር

### ሰው ሃብት ግንባታ

የሲቪል ሰርቪስና ሰው ሃብት ልማት ኮሚሽን በበጀት ዓመት በክልሉ እስከ ቀበሌ ድረስ በሚገኙ ከ7000 በላይ የመንግስት ተቋማትና በስራቸው በሚገኙ ከ450,000 በላይ ቋሚ የመንግሰት ሰራተኞች አማካኝነት የሚሰጠውን የመንግስት ተቋማት አገልግሎት አሰጣጥ ውጤታማነት ለማሳደግ የሚያስችሉ ስራዎችን ለማከናወን ትኩረት ሰጥቶ እየሰራ ይገኛል ፡፡

በመሆኑም የፈጻሚዎችን አቅም በመገንባት የሲቪል ሰርቪሱን አገልግሎት ከማሳለጥ አኳያ በተለያዩ ተቋማት የሚገኙ የመንግሰት ሰራተኞችን ለረዥም ጊዜ ስልጠና መልምሎ በተለያዩ የከፍተኛ የትምህርት ተቋማት በመደበኛ / በበጋ /የትምህርት መርሃ ግብር ለማስተማር የበጀት እጥረት በማጋጠሙ በክረምት መርሃ ግብር ማስተማር የተሻለ አማራጭ መሆኑን በመገንዘብ ለማስተማር የተያዘ እቅድና አፈፃፀም ሲታይ በመጀመሪያ ድግሪ 149 ፤ በ2ኛ ዲግሪ 629 በድምሩ በሁለቱ መርሃ ግብሮች 778 የመንግሰት ሰራተኞችን ወደ ተለያዩ የከፍተኛ የትምህርት ተቋማት በመስፍረቱ መሰረት ተመልምለው የተላኩ ቢሆንም ከጊዜ መጣበብ ጋር

በተያያዘ ትምህርት እንደማይኖር የፌደራል ትምህርት ሚኒስቴር በማሳወቁ ምክንያት ትምህርታቸውን መከታተል አልቻሉም፡፡ ከክረምቱ መርሃ ግብር በተጨማሪ የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርስቲ ለ2017 ዓ.ም በ2ኛ ዲግሪ በመደበኛው መርሃ ግብር ለመማር መስፈርቱን የሚያሟሉ 162 እንዲሁም በ3ኛ ዲግሪ 3 ተወዳዳሪዎች ተመልምለው የተላኩ ሲሆን በድምሩ- 1,500 ለማስተማር ታቅዶ ክንውኑ 943 አፈጻጸሙ ደግሞ (62%) እንደሆነ ተመላክቷል፡፡

ሌላው የአጫጭር ጊዜ ስልጠናዎችን በመስጠት ፈጻሚውን ማብቃት ሲሆን በዚህም በሰው ሃይል አስተዳደር መመሪያዎችና በተለያዩ ተያያዥ ርዕሶች ዙሪያ በበጀት ዓመቱ ለ35,000 በየደረጃው ለሚገኙ አመራርና ሰራተኞች የአጭር ጊዜ የአቅም ማጎልበቻ ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ በልዩ ልዩ ነባር የሰው ሃይል አስተዳደር መመሪያዎች፣በአዲሱ የመንግሰት አገልግሎትና አስተዳደር ፖሊሲና በተቋማዊ አካቶ ትግበራ ዙሪያ፣ለ17,863 (68%) አመራርና ሰራተኞች ስልጠና በመስጠት በአሰራር ላይ የሚስተዋሉ ክፍተቶችን ለማረምና ወጥ አሰራር በመዘርጋት ጥራት ያለው አገልግሎት ለመስጠት ጥረት ተደርጓል፡፡



የቀጥታ ኮርስ ስልጠና ሪጂስተሬሽን

## የአሰራር ማንዋል እና መመሪያዎችን ማሻሻል

የተሻሻለውን የመንግስት ሰራተኞች አዋጅ ቁጥር 253/2010 መሰረት በማድረግ በተገልጋዮች ጥያቄ የሚቀርብባቸውንና ለአፈፃፀም ያስቸገሩ የሰው ሃይል አስተዳደር መመሪያዎችን 8 (2 አዳዲስ መመሪያዎች ለማዘጋጀት እና 6 ነባር በስራ ላይ ያሉ መመሪያዎችን በማሻሻል) ጥቅም ላይ ለማዋል በእቅድ ተይዞ 7 ነባር እና 3 አዲስ በድምሩ 10 (>100%) የሰው ሃይል አስተዳደር መመሪያዎችን የማሻሻልና የማዘጋጀት ስራ በመሰራትና ጥቅም ላይ እንዲውሉ በማድረግ በተገልጋዮችና ተቋማት ለሚቀርቡ ቅሬታዎች ምላሽ መስጠት እና የጋጠሙ ክፍተቶችን መሙላት ተችሏል፡፡



በመመሪያዎች  ዙሪያ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ሲሰጥ -ባህርዳር

## የሰው ሀይል ስምሪት ክትትል እና ግምገማ

በተቋማት የሰው ሃይል እንዲሟሉ የሚጠየቁ ክፍት የስራ መድቦችን በየደረጃው ባሉ የሰው ሃይል አስተዳደሮች አማካኝነት ለማሟላት 33,956 የሰው ሃይል ስምሪቶችን ለመፈፀም በእቅድ ተይዞ ክንውኑ 22,941 አፈጻጸሙ ደግሞ (67.5%) ነው፡፡በመሆኑም የተፈፀሙ ስምሪቶች አግባብነትን አስመልክቶ መደበኛ የክትትልና ቁጥጥር (ኦዲት) ስራ ለማከናወን (ለ32 የክልልና ለ21 የዞን ተቋማት) በድምሩ 53 ተቋማት ለመከታተል ታቅዶ በክልል ደረጃ 21 መስሪያ ቤቶችን ለማየት ሲቻል አፈጻጸሙ (60.3%)፣ በተዋረድ የሚገኙ የዞን ተቋማትን ደግሞ 11 ማየት ተችሏል አፈጻጸሙም (52%) ነው ፡፡

በተጨማሪም በዞን ተቋማት አማካኝነት በተፈፀሙ ክትትሎች  የ18,049 ሰራተኞች የግል ማህደሮችን መመርምር የተቻለ ሲሆን  በተፈጸሙ ስምሪቶች  የተገኘ የግድፈት መጠን 166 (0.9%) መሆኑን ከማሳየቱ በተጨማሪም አላግባብ የተከፈለ (የባከነ) ገንዘብ መጠን ብር 1,126,546 እንደሆነ እና ከዚህ ውስጥ ተመላሽ የሆነው 32,568 ብር ብቻ መሆኑ በሪፖርቱ ተመላክቷል ፡፡

ከዚሁ ጋር ተያይዞ የተደረገውን የድጋፍ፣ክትትልና ቁጥጥር (ኦዲት) ስራ  መሰረት በማድረግ ጥንካሬና ድክመትን የሚያሳይ ግብረ መልስ የተሰጠ ሲሆን የሚፈፀሙ የሰው ሃይል ስምሪት ግድፈቶችን ለመቀነስ ባለሙያውን ማብቃት፣ክትትል፣ድጋፍና ቁጥጥር (ኦዲት) ስራን ማጠናከር እንዲሁም ከሚመለከታቸው የፍትህ ተቋማት ጋር በቅንጅት በመስራት የተጠያቂነት ስርዓትን ማጎልበት ይገባል፡፡

## የሲቪል ሰርቪስ ሪፎርም አፈፃፀም

የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ፖሊሲ ከዚህ በፊት ያልነበረ ነጻ እና ገለልተኛ የሲቪል ሰርቪስ ሪፎርም ቢሆንም እስከአሁን ባለው አፋጻጸም ውጤታማ ነው፤ ማለት አይቻልም በመሆኑም በሀገር ደረጃ የተሻሻለ ፖሊሲ ተዘጋጅቶ በረቂቅ ሰነዱ ላይ በየደረጃው ከሚገኙ ባለድርሻ አካላት ጋር ውይይት ተደርጎበት የጸደቀና በሙከራ ላይ ያለ ሲሆን የክልሉን ነባራዊ ሁኔታ ከግምት ውስጥ ያስገባ ክልላዊ የተቋማት አስተዳዳር፣አሰራርና አደረጃጀት ለመፍጠር የማስፈጸሚያ እቅድ ተዘጋጅቶ ለክልል ርዕሰ መሰተዳድር እና የበላይ አመራሮች ቀረቦ ይሁንታን አግኝቶ ወደ ተግባር ለመግባት አስፈላጊ ሁኔታዎችን የማመቻቸት ስራ እየተሰራ ይገኛል፡፡በቀጣይም በሁሉም ዘርፍ የሲቪል ሰርቪስ ሪፎርሙን ትራንስፎርም ሊያደርግ የሚችል ከክልል እስከ ቀበሌ ያለውን አመራርና ሰራተኛ ግንዛቤ ለማስጨበጥ የሚያስችል ጥራት ያለው የስልጠና ሞጅሎች እንደሚዘጋጁ እና እስከ ታችኛው መዋቅር ያሉ የአሰራር ስርዓትና አገልግሎት አሰጣጦችን በማዘመንና በቴክኖሎጅ እንዲታገዙ በማድረግ ወደ ስራ ለመግባት የሚያስችል ዝርዝር የማስፈጸሚያ ሰነድ በማዘጋጀት ወደ ስራ የሚገባ መሆኑ የተገለጸ ሲሆን ለኮሚሽኑ አመራርና ሰራተኞች በአዲሱ የመንግሰት አገልግሎትና አስተዳደር ፖሊሲ ዙሪያ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ተሰጥቷል፡፡

## የለውጥ መሳሪያዎች አተገባበር

የመንግስት ተቋማት የአገልግሎት አሰጣጥ ችግር የሚፈታው በተቋማዊ ሪፎርም መሆኑን በማመን ተቋማት የአገልግሎት አሰጣጥ ስታንዳርድ (የዜጎች ቻርተር) በማዘጋጀት በስታንዳርዱ መሰረት አገልግሎት ለመስጠት ጥረት የተደረገ ሲሆን፤ሙሉ በሙሉ በስታንዳርዱ መሰረት አገልግሎት ተሰጥቷል ለማለት የሚቀር ነገር እንዳለ በተደረገው የክትትል እና ግምገማ ስርዓት ተስተውሏል፤ በመሆኑም በበጀት አመቱ 48 የክልል ተቋማትን ድጋፍና ክትትል ለማድረግ ታቅዶ ለ45 (94%) ተቋማት ድጋፍ በማድረግ የተደረጀ ግብረ- መልስ የየተቋማቱ የማኔጅመንት አባላት በተገኙበት ተሰጧል፡፡ በመሆኑም አብዛኞቹ ተቋማት ለሪፎርሙ ትኩረት በመስጠትና አገልግሎትን ለማሻሻል ትኩረት ሰጠው ወደ ስራ መግባት እንደቻሉ ተረጋግጧል፡፡በዞን እና ወደታች ባሉ የሲቪል ሰርቪስ መዋቅሮች የሪፎርም አፈጻጸም ግምገማ በኮር አመራሮች እየተገመገመ የሚመራ በመሆኑ የተሻለ አፈጻጸም እንዲኖረው አድርጎታል፡፡ከዚሁ ጋር ተያይዞ አንጻራዊ ሰላም ባለባቸው 6,762 በሚሆኑ ወደ ታች ባሉ

ተቋማት የድጋፍና ክትትል ስራ ለመስራት ታቅዶ ለ3,236 (48%) ተቋማት የድጋፍና ክትትል ስራ የተሰራ በመሆኑ የመነቃቃት ሁኔታ ፈጥሮላቸዋል ፡፡

## ሴቶች፣ህጻናትና ማህበራዊ ጉዳይ

### የሴቶች፣ህፃናት፣አካል ጉዳተኞች እና አረጋውያንን መብት ማስከበር

የሴቶች፣ህፃናት፣አካል ጉዳተኞች እና አረጋውያንን መብትና ሁለንተናዊ ደህንነት ማስጠበቅ አንዱ በቢሮው ታቅዶ ሲፈጸም የነበረ ተግባር ነው፡፡የሴቶችን መብትና ሁለንተናዊ ደህንነት ማስጠበቅ በሚመለከት በመደራጀት ጥቅምና አስፈላጊነት ዙሪያ 4,944,013 ሴቶች ግንዛቤ እንዲያገኙ ታቅዶ 2,313,044(47%) ሴቶች ግንዛቤ ተፈጥሯል፡፡ግንዛቤ ከተፈጠረላቸው 276,485 ሴቶች በተለያዩ አደረጃጀቶች ተደራጅተው መብታቸውን እንዲያስከብሩ ተደርጓል፡፡በተመሳሳይ ለ3,792,367 የህብረተሰብ ክፍሎች በሴቶች ላይ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችና ሥርዓተ ጾታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች እንዲቀንሱ ብሎም እንዲወገዱ በተለያዩ ዘዴዎች ግንዛቤ ለመፍጠር በእቅድ ተይዞ 2,747,294 (74%) ሰዎች ግንዛቤ መፍጠር ተችሏል፡፡




የሴት አመራሮች ፎረም የግምገማ መድረክ

### የአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጠት

በበጀት ዓመቱ የአንድ ማዕከል አገልግሎት አሰጣጡን የተሻለ ለማድረግ 4 የአንድ ማእከል አገልግሎት ለማጠናከር በእቅድ ተይዞ 22 (100%) የአንድ ማዕከላትን ከተለያዩ አጋር አካላት በተገኘ የገንዘብ እና የአይነት ድጋፍ ማጠናከር የተቻለ ሲሆን በማዕከላቱ 1058 ሴቶች የህክምና፣የስነልቦና ድጋፍና ሌሎች አገልግሎቶች ተጠቃሚ መሆን ችለዋል፡፡ በተመሳሳይ የተለያዩ ጥቃት(የኢኮኖሚ፣የስነ ልቦና እና ፆታዊ ጥቃት) ለደረሰባቸው 18,190 ሴቶች የንግድ ክህሎት ስልጠና በመስጠት፣የመስሪያና የመሸጫ ቦታዎች በማመቻቸት ከተለያዩ ባለድርሻ

አካላት ሀብት በመሰብሰብ 13,556,016 ብር ድጋፍ እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡ሴቶችን የሰላሙ ባለቤት ለማድረግ ከሴቶች አደረጃጀት ጋር በመሆን በተሻለ ንቅናቄ የሰላም ኮንፈረንሶችን በማካሄድ 900,000 የሚሆኑ ሴቶችን ለማሳተፍ ታቅዶ 783,788 ሴቶችን ማሳተፍ ተችሏል፡፡

## የሴቶችን የኢኮኖሚ ተጠቃሚነት ማሳደግ

በበጀት አመቱ የሴቶችን የኢኮኖሚ ተጠቃሚነት ለማሳደግ በተሰራው ስራ 700,000 ሴቶች በልማት ቡድንና ራስ አገዝ እንዲቆጥቡ ለማድረግ በተሰራው ስራ 700,000 ሚሊዩን ብር እንዲቆጥቡ በዕቅድ ተይዞ 371,232 (53%) ሴቶች ብር 501,281,256 (64%) እንዲቆጥቡ ማድረግ ተችሏል፡፡እንዲሁም 3,522,738 ሴቶች፣1,268,000,000 ብር እንዲበደሩ በእቅድ ተይዞ 429,556 ሴቶች፣ 444,723,909 ብር ብድር ወስደው በተለያዩ የስራ መስኮች እንዲሰማሩ ማድረግ ተችሏል፡፡

## የልማት ህብረቶችን በአዲስ ማቋቋም

የልማት ህብረት ማደራጀት በኢኮኖሚ ተጠቃሚ ከማድረጉ በተጨማሪ የእርስ በእርስ ግንኙነትን ያጠናክራል በመሆኑም በበጀት ዓመቱ 9,040 የልማት ህብረቶችን በአዲስ ለማቋቋም እና 164,555 የልማት ቡድኖችን ለማጠናከር ታቅዶ 10,210 የልማት ቡድኖችን በአዲስ በማቋቋም እንዲሁም 50,115 የልማት ህብረቶችን የማጠናከር ስራ ተሰርቷል፡፡

## የህፃናትን መብትና ደህንነት ማስጠበቅ

በ2016 ዓ.ም 1,538,020 (ሴት 769,010) ለሚሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች በህጻናት ላይ በሚፈጸሙ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችና የሃይል ጥቃቶች ዙሪያ ግንዛቤ ለመፍጠር በዕቅድ ተይዞ 1,274,458 (83%) ((ሴት.689, 974) ለሚሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች ግንዛቤ እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡እንዲሁም 724 ቀበሌዎችን ከህጻናት ጋብቻ ነጻ ለማድረግ ታቅዶ 178 የሚሆኑ ቀበሌዎች ከልጅነት ጋብቻ ነጻ ማድረግ ተችሏል፡፡

## የህጻናትን ተሳትፎ ማረጋገጥ

በ2016 ዓ.ም 596,125(ሴት 290,691) የሚሆኑ ህጻናትን በማደራጀት ጥቅምና አስፈላጊነት ዙሪያ ግንዛቤ እንዲያገኙ በማድረግ ግንዛቤ ከተፈጠረላቸው መካከል 613,618(ሴት.306,809) የሚሆኑትን ህፃናት በአዲስ የህፃናት ፓርላማና በክበባት እንዲደራጁ ታቅዶ 342.746(ሴት.179,881) (56%) የሚሆኑ ህፃናትን በልዩ ልዩ አደረጃጀቶች ማስገባት ተችሏል፡፡ 3,648 የሚሆኑ በየደረጃው የሚገኙ የህዝብ ምክርቤቶች የህፃናት ተወካዮችን በማሳተፍ 10,944 (ሴት.5472) የሚሆኑ የህጻናት ፓርላማ አባላትን በመወከል በየደረጃው በሚገኙ የህዝብ ምክር ቤቶች እንዲሳተፉ ለማድረግ በተያዘው እቅድ መሰረት 884 በሚሆኑ ምክርቤቶች 3,798 (ሴት.1,730) የሚሆኑ የህጻናት ፓርላማ ተወካዮች እንዲያሳትፉ ተደርጓል፡፡

## የህጻናትን ተጠቃሚነት ማረጋገጥ

በጀት ዓመቱ 451,610 (ሴት.226, 919) ህጻናትን በተለያዩ አማራጭ የህጻናት ድጋፍና እንክብካቤ ፕሮግራሞች ተጠቃሚ ለማድረግ በእቅድ ተይዞ 348,444 (ሴት.186, 560) ህፃናትን በተለያዩ አማራጭ የህጻናት ድጋና እንክብካቤ ፕሮግራሞች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ ተችሏል፡፡






የህጻናት ማዕከል ግንባታ ምርቃት

## የህፃናት ማዋያዎችን ማቋቋም

በበጀት አመቱ 62 የህፃናት ማዋያዎችን በአዲስ በማቋቋም እንዲሁም በአዲስ በተቋቋሙና በነባሮች 2,380(ሴት.1,190) ህፃናት የአገልግሎቱ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ በእቅድ ተይዞ 26 ማቋቋም ተችሏል፡፡በአዲስ በተቋቋሙና በነባሮች 3,875 (ሴት.1,937) የሚሆኑ ህጻናት በማቆያው ገብተው የአገልግሎቱ ተጠቃሚ እንዲሆኑ መድረግ ተችሏል፡፡

## የማህበራዊ ጥበቃ ሥርዓትን መዘርጋትና በማስፋፋት

በበጀት አመቱ የማህበራዊ ጥበቃ ሥርዓትን በመዘርጋትና በማስፋፋት የዜጎችን ተጠቃሚነት ለማሳደግ በተሰራው ስራ በማህበረሰብ ድጋፍና እንክብካቤ ጥምረቶች አማካኝነት ከነባርና ከአዲስ የጥምረቱ አባላት በጥሬ ገንዘብ እና በዓይነት 144,705,402 ብር ሀብት ለመሰብሰብ ታቅዶ በጥሬ ገንዘብ 82,620,260.00 በዓይነት 42,132,339 በድምሩ 124,765,449 (86%) ብር ተሰብስቧል፡፡በማህበረሰብ አቀፍ ድጋፍና እንክብካቤ ጥምረቶች አማካኝነት በተሰበሰበ ኃብት 201,717 ለማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግር ተጋላጭ የህብረተሰብ ክፍሎች ድጋፍ ለማድረግ ታቅዶ 165,641 (ሴት 88,450) ድጋፍ የተደረገላቸው ሲሆን አፈፃፀሙም 82% ነው፡፡



በክልል ደረጃ የማህበራዊ ጥበቃ ምክር ቤት ሲመሰረት

## ልማታዊ ሴፍቲኔት

በገጠርና በከተማ ልማታዊ ሴፍቲኔት የቋሚ ቀጥተኛ ድጋፍ ተጠቃሚዎችን ጉዳይ አያያዝ ከተሰራላቸው ውስጥ 196,176 ተጠቃሚዎች የማህበራዊ አገልግሎት ትስስር ለመፍጠር ታቅዶ 107,296 ተጠቃሚዎች ትስስር እንዲፈጠርላቸው ተደርጓል፡፡አፈፃፀሙም 55% ሆኗል፡፡

## የከተማ ምግብ ዋስትና ፕሮግራም

በ2016 ዓ.ም በከተማ ምግብ ዋስትና ፕሮግራም 1910 ውሎና አዳራቸውን ጎዳና ላይ ያደረጉ ዜጎች ከጎዳና በማንሳት ወደ ማዕከል ለማስገባት የስነ ልቦና፣የህክምና፣ የምግብ እና የሙያ ስልጠና በመስጠት ወደ ማህበረሰቡ ለመቀላቀል እና ለማቋቋም ታቅዶ 1,910 (ሴት 286) የሚሆኑትን በተለያዩ አማራጮች ተጠቃሚ በማድረግ ማቋቋም ተችሏል፡፡ከመቀላቀል አኳያ አፈፃፀሙ 100% ነው፡፡

## በተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋ ተጋላጭ ለሆኑ ዜጎች ሰባዊ ድጋፍ ማድረግ

በተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋ ተጋላጭ ሆነው የሰብዓዊ ድጋፍ የተደረገላቸው ሴቶች፣ ህፃናት እና ሌሎች የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግር ተጋላጭ ዜጎች በተመለከተ ዕቅድ 452,252 ክንውን 430,967 (ሴት 260,003) ሲሆን አፈፃፀሙን 95% ማድረስ ተችሏል፡፡

## የአረጋውያን እና አካል ጉዳተኞችን መብትና ሁለንተናዊ ደህንነት ማስጠበቅ

የአረጋውያን እና አካል ጉዳተኞችን መብትና ሁለንተናዊ ደህንነት ለማስጠበቅ በተሰራው ስራ ለ9595 ለሚሆኑ አስፈፃሚ አካላት በአረጋዊያን እና በአካል ጉዳተኞች ዙሪያ በወጡ ፖሊሲዎች፣ አዋጆች፣ መመሪያዎች፣ ደንቦች፣ ዓለም አቀፍ ስምምነቶች የአድቮኬሲ ስራዎችን ለማከናወን ታቅዶ ለ7319 (ሴት 3146) ማከናወን የተቻለ ሲሆን አፈጻጸሙ 76.3 ፐርሰንት ሆኗል፡፡



አለም አቀፍ አካል ጉዳተኞች ቀን ክልላዊ  የማጠቃለያቃለ ፕሮግራም

## አረጋዊያን እና አካል ጉዳተኞች  የሕግ ጥበቃ እንዲያገኙ ማድረግ

የመብት ጥሰት የደረሰባቸውን 1744 አረጋዊያን እና 1176 አካል ጉዳተኞች  የሕግ ጥበቃ እንዲያገኙ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን መብታቸው እንዲከበር ለመሥራት በዕቅድ

ተይዞ 788 ( ሴት 466) አረጋውያን እና 595 (ሴት 295) አካል ጉዳተኞች መብታቸው የተከበረ ሲሆን ከዕቅዱ አኳያ 45.2% እና 50.6% እንደ ቅደም ተከተላቸው መፈጸም ተችሏል፡፡ በተመሳሳይ ለ1177 የአካል ጉዳተኞች ማህበራት ፌደሬሽን አመራር አባላት ፍላጎታቸውን መሰረት ያደረገ የአቅም ግንባታ ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ ለ702 (ሴት 229) ስልጠና በመስጠት 59.7% መፈጸም ተችሏል፡፡

## የአረጋዊያን እና አካል ጉዳተኞችን ተሳትፎና ውክልና ማረጋገጥ

የአረጋዊያን እና አካል ጉዳተኞች ተሳትፎና ውክልና ለማረጋገጥ በተሰራው ስራ በየደረጃው የሚገኙ 311 የአረጋዊያን እና 402 የአካል ጉዳተኛ ማህበራትን  ያልተቋረጠ ድጋፍና ክትትል በማድረግ ለማጠናከር በዕቅድ ተይዞ 182 የአረጋውያን እና 394 የአካል ጉዳተኞች ማህበራትን ማጠናከር ተችሏል፡፡በተመሳሳይ ለ1177 የአካል ጉዳተኞች ማህበራት ፌደሬሽን አመራር አባላት ፍላጎታቸውን መሰረት ያደረገ የአቅም ግንባታ ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ ለ702 (ሴት 229) በመስጠት 59.7% መፈጸም ተችሏል፡፡

## የአረጋውያን እና አካል ጉዳተኞችን ገቢ ማሳደግ

በ2016 ዓ.ም 12,303 አረጋውያን እና 2394 አካል ጉዳተኞችን  በቋሚ የገቢ ማስገኛ ሥራ እንዲሠማሩ ድጋፍ ለማድረግ ታቅዶ 5,758 (47%) አረጋዊያን እና 2,449 (102.3%) አካል ጉዳተኞችን ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡ እንደዚሁም 94,446 አረጋውያን ቋሚ እና 76,618 አረጋውያን ጊዜያዊ ድጋፍ እንዲያገኙ ታቅዶ ለ158,937 አረጋዊያን ቋሚ እና 138,210 ልዩ ልዩ ጊዜያዊ ድጋፍ እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡ለ12011 አካል ጉዳተኞች የአካል ተሃድሶ አገልግሎት ለመስጠት በተያዘው እቅድ መሰረት ለ10,416 (ሴት 3632) አካል ጉዳተኞች የተጠቀሰውን አገልግሎት በመስጠት የእቅዱን 86.7 ማከናወን ተችሏል፡፡በበጀት ዓመቱ በአምስት ዞኖች (ደብረ ብርሃን፣ሰሜን ጎንደር፣ጎንደር ከተማ እና ኮምበልቻ) ለአረጋዊያን ገቢ ማስገኛ ማዕከል ግንባታ የሚውል ቦታ ለመረከብ እና አራት (ዋግህምራ፣ ደቡብ ጎንደር፣ ደሴ እና ምዕራብ ጎጃም) ግንባታ ለመጀመር ታቅዶ 1 (ደብረ ብርሃን) ቦታ መረከብ እና ሶስት (ዋግህምራ፣ ደቡብ ወሎ እና ደሴ ማዕከል ግንባታ መጀመር ተችሏል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የባህር ዳር አካል ተሃድሶ ማዕከል እድሳት ማድረግ ተችሏል፡፡



የባህር ዳር አካል ተሃድሶ ማዕከል የእድሳት ምርቃት

## የሴቶች፣ ህፃናት፣ አካል ጉዳተኞችና አረጋዊያንን ተጠቃሚነትና ተጠያቂነት ማጎልበት

በበጀት ዓመቱ ነባርና አዲስ የሴት አመራር ፎረሞች ለማጠናከር 202 የምክከር መድረክ ለማካሄድ ታቅዶ 152 የምክከር መድረኮችን መፍጠር ተችሏል፡፡ የሴቶች፣ ህፃናት፣ አካል ጉዳተኞችና አረጋዊያን ተቋማዊነትና ተጠያቂነት ስርዓት ለማጎልበት በተሰራው ስራ በየደረጃው ለሚገኙ ለ5169 አመራሮች፣ዳይሬክተሮችና ቡድን መሪዎች በአካቶ ትግበራ የአቅም ግንባታ ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ ለ4581 (88.62%) ተቋማት አመራሮች፣ ዳይሬክተሮችና ቡድን መሪዎች የአቅም ግንባታ ስልጠና ተሰጥቶል፡፡ እንዲሁም በየደረጃው ለሚገኙ ለ5245 የተቋማት ባለሙያዎች በአካቶ ትግበራ እና በአዲሱ የተቋማት መመዘኛ ማዕቀፍ ዙሪያ ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ ለ 4203 የተቋማት ባለሙያዎች ስልጠና የተሰጠ ሲሆን አፈፃፀሙ 80.13% ሆኗል፡፡

## ክትትል እና የምክክር መድረክ

በ2016 ዓ.ም ከክልል እስከ ወረዳ አደረጃጀት ለሚገኙ ለ4783 ተቋማት ክትትልና ድጋፍ ለማድረግ ታቅዶ ለ4009 (83.8%) ተቋማት ክትትልና ድጋፍ ተደርጓል፡፡እንዲሁም ከክልል እስከ ወረዳ ባለው አደረጃጀት በድምሩ 201 በአካቶ ትግበራ ዙሪያ የምክክር መድረኮችን ለማካሄድ ታቅዶ በድምሩ 72 የምክክር መድረኮች በአካቶ ትግበራ አፈፃፀም ዙሪያ በየደረጃው ከሚገኙ የመንግስት ተቋማት አመራሮችና ባለሙያዎች ጋር ውይይቶችን በማካሄድ የአካቶ ትግበራ ስራው ያለበትን ደረጃ የመገምገም ስራ ተሰርቷል፡፡

## ወጣቶች እና ስፖርት ልማት

### የወጣቶችን የመደራጀት መብት ማስጠበቅ

በበጀት አመቱ 1,189,800 (ወንድ 594,900 ሴት 594,900) ወጣቶችን በማደራጀት ጥቅምና አስፈላጊነት ግንዛቤ በመፍጠር 1,076,921 (ወንድ 538,461 ሴት 538,461) ወጣቶችን በአዲስና በነባር ልዩ ልዩ አደረጃጀቶች (በሊግ፣ በማህበራት፣ በክበባት፣ ወዘተ) እንዲደራጁ ለማድረግ ታቅዶ 554,263 (ወንድ 308,076 ሴት 246,187) ወጣቶችን በማደራጀት ጥቅምና አስፈላጊነት ዙሪያ ግንዛቤ በመፍጠር 277,982 (ወንድ 183,950 ሴት 94,032) በአዲስና በነባር ልዩ ልዩ አደረጃጀቶች እንዲደራጁ ማድረግ የተቻለ ሲሆን አፈጻጸሙም በቅደም ተከተላቸው መሰረት 47% እና 26% ሆኗል፡፡ ከዚህ ውስጥ ለ11,898 (ወንድ 5,949 ሴት 5,949) አካል ጉዳተኛ ወጣቶች ግንዛቤ እንዲፈጠርላቸው በማድረግ 10,769 (ወንድ 5,385 ሴት 5,384) አካል ጉዳተኛ ወጣቶች በልዩ ልዩ አደረጃጀት እንዲገቡ ታቅዶ 3,951 (ወንድ 2,184 ሴት 1,767) አካል ጉዳተኛ ወጣቶች ግንዛቤ እንዲፈጠርላቸው በማድረግ 3,991 (ወንድ 2,465 ሴት 1,526) አካል ጉዳተኛ ወጣቶች በአዲስና በነባር ልዩ ልዩ አደረጃጀት (በሊግ፣ በማህበራት፣ በክበባት፣ ወዘተ) እንዲደራጁ ተደርጓል፡፡

### የአቅም ግንባታ ስልጠና

በ2016 ዓ.ም 438,742 (ወንድ 285,182 ሴት 153,560) ወጣቶችና 87,507 (ወንድ 56,880 ሴት 30,627) የአደረጃጀት መሪዎች በአመራር ጥበብ ዙሪያ ስልጠና ለመስጠት በእቅድ ተይዞ ለ23,739 (ወንድ 13,631 ሴት 10,108) ወጣቶች እና ለ448 (ወንድ 344 ሴት 104) የአደረጃጀት መሪዎች ስልጠና የተሰጣቸው ሲሆን አፈጻጸሙም በቅደም ተከተላቸው መሰረት 5% እና 1% ነው፡፡ ከዚህ ውስጥ ለ3,290 (ወንድ 1,645 ሴት 1,645) አካል ጉዳተኛ ወጣቶች ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ 179 (ወንድ 105 ሴት 74) አካል ጉዳተኛ ወጣቶች ስልጠና እንዲያገኙ የተደረገ ሲሆን አፈጻጸሙ 4% ሆኗል፡፡

## ለወጣት አደረጃጀቶች የተለያዩ ድጋፎችን ማድረግ

በበጀት ዓመቱ 836 የወጣት አደረጃጀቶችን በሙያ፣ በቁሳቁስ እና በገንዘብ ለመደገፍ በእቅድ ተይዞ በሙያ (1,631)፣ በቁሳቁስ (461) እና በገንዘብ (433) አደረጃጀቶችን ለመደገፍ የተቻለ ሲሆን አፈጻጸሙም በቅደም ተከተላቸው መሰረት 195%፣ 165% እና 155% ሆኗል፡፡

## የሰላም ግንባታና ግጭትን መከላከል

በሰላም ግንባታና ግጭትን ለመከላከል በተሰራው ስራ ለ2,099,176 /ወንድ 1,049,588 ሴት 1,049,588/ ወጣቶች በሰላም አስፈላጊነት ዙሪያ ግንዛቤ ለመፍጠር ታቅዶ ለ1,021,784 /ወንድ 585,376 ሴት 396,408/ ወጣቶች ግንዛቤ የመፍጠር ስራ የተሰራ ሲሆን አፈፃፀሙ 48.7% ነው፡፡ይሁን እንጅ በሰላም ዙሪያ የተሰራው ስራ ዝቅተኛ በመሆኑ በቀጣይ በጀት አመት ትኩረት ሰጥቶ መስራት ያስፈልጋል፡፡

## የወጣቶችን ተሳትፎና ውክልና ማረጋገጥ

የወጣቶችን ተሳትፎና ውክልና ለማረጋገጥ፤ 13,056 (ወንድ 8,705፣ ሴት 4,351) የወጣት አደረጃጀት አመራሮች በየደረጃው ባሉ የህዝብ ምክር ቤቶች ወጣቶች ያለ ድምጽ ተሳታፊ ለማድረግ ታቅዶ 13,056 (ወንድ 8,705 ሴት 4,351) ውክልናቸውን ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

## የወጣቶች የንቅናቄ ተሳትፎ ኮንፈረንስ

በ2016 ዓ.ም በወጣቶች የንቅናቄ ተሳትፎ ኮንፈረንስ በቅድመ ዝግጅት ምዕራፍ የማስፈሚያ እቅድና ማወያያ ሰነድ በማዘጋጀት በክልል ደረጃ በሶስት ክላስተር ለ138 አሰፈፃሚዎች ፤በዞን ደረጃ ለ881፤ለወረዳ ሃላፊዎችና ለ529 የወጣት አደረጃት አመራሮች በ103 ወረዳዎች/ከተሞች/ክፍለከተሞች፤2,807 የቀበሌ አመራሮችና 1,477 የቀበሌ የወጣት አደረጃጀት አመራሮች ኦሬንቴሽን በመስጠት ወደ ተግባር እንዲገቡ ተደርጓል ፡፡

## የወጣቶችን ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት ማረጋገጥ

የወጣቶችን ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ በተሰራው ስራ 616,927 (ወንድ 308,464 ሴት 308,464) ወጣቶች በቁጠባ እንዲሳተፉ በማድረግ 3,000,000,000 ብር እንዲቆጥቡ ለማድረግ ታቅዶ 92,456 (ወንድ 52,187 ሴት 40,269) ወጣቶች በቁጠባ እንዲሳተፉ በማድረግ 832,243,990 ብር እንዲቆጥቡ ማድረግ ተችሏል፡፡ አፈጻጸሙም በወጣቶች ተሳትፎ ደረጃ 15% ሲሆን በመቆጠብ ደረጃ ደግሞ 28% ነው፡፡ ከዚህ ውስጥ 6,169 (ወንድ 3,085 ሴት 3,085) አካል ጉዳተኛ ወጣቶች በቁጠባ እንዲሳተፉ ታቅዶ 283 (ወንድ 138 ሴት 145) አካል ጉዳተኛ ወጣቶችን ተሳታፊ ማድረግ ተችሏል፡፡

## ወጣቶችን የብድር አገልግሎት ተጠቃሚ ማድረግ

በ2016 ዓ.ም ለ269,936 (ወንድ 134,968 ሴት 134,968) ወጣቶች የብድር አገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ ታቅዶ 51,855 (ወንድ 29,848 ሴት 22,140) ወጣቶች የብድር አገልግሎት ተጠቃሚ ማድረግ የተቻለ ሲሆን አፈጻጸሙም 19% ነው፡፡ ከዚህ ውስጥ 2,706 (ወንድ 1,354 ሴት 1,354) አካል ጉዳተኛ ወጣቶች የብድር ተጠቃሚ እንዲሆኑ ታቅዶ 179 (ወንድ 80 ሴት 99) አካል ጉዳተኛ ወጣቶችን የብድር ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡በአጠቃላይ ከብድር ጋር በተያያዘ በበጀት ዓመቱ 3,000,000,000 ብር ብድር ለመስጠት ታቅዶ 573,846,557 ብር ብድር መስጠት የተቻለ ሲሆን አፈጻጸሙ 19% ሆኗል፡፡ በመሆኑም የወጣቶች የብድር አገልግሎት ተጠቃሚነት ዝቅተኛ በመሆኑ በቀጣይ በጀት አመት ትኩረት ሰጥቶ መስራት ያስፈልጋል፡፡

## ከስደት ተመላሽ ወጣቶችን የኢኮኖሚ ተጠቃሚ ማድረግ

በበጀት ዓመቱ 10,580 (ወንድ 3,174 ሴት 7,406) ከስደት ተመላሽ ወጣቶችን በገቢ ማስገኛ ተሰማርተው ተጠቃሚ እንዲሆኑ በእቅድ ተይዞ 4,179 (ወንድ 1,749 ሴት 2,430) ከስደት ተመላሾችን ተጠቃሚ ማድረግ የተቻለ ሲሆን አፈጻጸሙ 39% ነው፡፡

## የወጣቶችን ማህበራዊ ተጠቃሚነት ማረጋገጥ

የወጣቶችን ማህበራዊ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ በተሰራው ስራ የክረምት ወራት በጎ ፈቃድ አገልግሎት የአስተባባሪ ተቋም በየደረጃው ያለው አጋር ተቋማትና አደረጃጀቶች አቅደው በክልል 16 (88.9%)፣ በዞን 370 (90%)፣ በወረዳ ደረጃ 3400 (74%) ዕቅድ አቅደው ወደ ስራ ገብተዋል፡፡በክልላችን 5,218,244 ወጣቶችን ወደ ንቅናቄ ለማስገባት ታቅዶ 4,304,679 (ወንድ 2,654,132፣ ሴት 1,650,547) (82.5%) ወጣቶችን ማሳተፍ ተችሏል፡፡ በተጨማሪም 12,521,544 (ወንድ 6,260,772፣ ሴት 6,260,772) የህብረተሰብ ክፍሎችን ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ 10,397,059 (ወንድ 5,629,437፣ ሴት 4,767,622) (83%) የህብረተሰብ ክፍሎች ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡

## የበጋ ወራት በጎ ፈቃድ አገልግሎት

የበጋ ወራት የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ለመስጠት በታቀደው መሰረት በበጋ በጎ ፈቃድ አገልግሎት ለ2,525,250(ወንድ 1262625 ሴት 1262625) ወጣቶች ለማሳተፍ ታቅዶ ለ1,264,567 (ወንድ 737055 ሴት 527417) ወጣቶችን ማሳተፍ የተቻለ ሲሆን አፈጻጸሙ 50.1 ሆኗል፡፡የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ተጠቃሚ 4,084,000/ ወ 2,042,000 ሴ 204,2000/ የህብረተሰብ ክፍሎች ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ 2,994,647 /ወንድ 1,516,381 ሴ 1478,266 / የህብረተሰብ ክፍሎች ተጠቃሚ ሆነዋል፡፡አፈፃፀም 74% ነው፡፡የተሰጠው አገልግሎት በገንዘብ ሲተመን እቅድ 2.5 ቢሊዮን ክንውን 1.35 ቢሊዮን አፈፃፀም 54% ነው፡፡



የበጋ ወራት በጎ ፈቃድ አገልግሎት

## የወጣት የሰብዕና ልማት ማዕከላት መገንባት

በ2016 ዓ.ም 238 የወጣት ሰብዕና ልማት ማዕከላት መገንቢያ ቦታ ርክክብ በመፈጸም 238 የወጣት ስብዕና ልማት ማዕከላት የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ እንዲኖራቸው በማድረግ 30 የወጣት ሰብዕና ልማት ማዕከላትን በአዲስ ለመገንባት በዕቅድ ተይዞ 17 የወጣት ሰብዕና

ልማት ማዕከላት መገንቢያ ቦታ ርክክብ በመፈጸም 21 ወጣት ሰብዕና ልማት ማዕከላትን የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ በማስጠት 2 የወጣት ስብዕና ልማት ማዕከላትን በአዲስ መገንባት የተቻለ ሲሆን አፈጻጸሙም በቅደም ተከተላቸው መሰረት 7%፣ 9% እና 7% መሆን ተችሏል፡፡

## የስፖርት ማህበራትን ማደራጀትና ማጠናከር

የስፖርት ማህበራትን ለማደራጀትና ለማጠናከር በተሰራው ስራ በየደረጃው 19,005 ፌዴሬሽኖችና ከሚቴዎችን ለማደራጀትና ለማጠናከር ታቅዶ 7,233 ፌዴሬሽኖችና ከሚቴዎችን ማጠናከር ተችሏል፡፡ አፈጻጸሙም 38.06% ነው፡፡376 የአሰልጣኞች ማህበር በተለያዩ የስፖርት አይነቶች ለማደራጀትና ለማጠናከር ታቅዶ 235 የአሰልጣኞች ማህበር ማደራጀት ተችሏል፡፡ አፈፃፀሙም 62.5% ነው፡፡ 378 የዳኞች ማህበር በተለያዩ የስፖርት አይነቶች ለማደራጀትና ለማጠናከር ታቅዶ 239 የዳኞች ማህበር ማደራጀት ተችሏል፡፡ አፈፃፀሙም 63.2% ነው፡፡ በበጀት አመቱ 272 የሙያ ማህበር በክልል፣ በዞን እና በወረዳ ለማደራጀትና ለማጠናከር ታቅዶ 148 የሙያ ማህበር ማደራጀት ተችሏል፡፡ አፈፃፀሙም 54.41% ነው፡፡ በተለያዩ የስፖርት አይነቶች 376 የቴክኒክ ከሚቴዎችን ለማደራጀትና ለማጠናከር ታቅዶ 281 የቴክኒክ ከሚቴዎችን ማጠናከር የተቻለ ሲሆን አፈጻጸሙ 75% ሆኗል፡፡



የስፖርት ማህበራት ማደረጀትና ማጠናከር ውይይት

## የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎችና የስልጠና ማዕከላት ማስፋፋትና ማሳደግ

የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎችና የስልጠና ማዕከላትን ለማስፋፋትና ለማሳደግ በተሰራው ስራ 73 አገር አቀፍ ስታንዳርዱን ያሟሉ የማዘውተሪያ ስፍራዎች ለመለየትና ለመገንባት ታቅዶ 35 መለየት ተችሏል፡፡ አፈፃፀሙም 50 % ነው፡፡ በሌላ በኩል በአመቱ 850 ጥርጊያ ሜዳዎችን ለማስፋፋት ታቅዶ 383 ማከናወን ተችሏል፡፡አፈፃፀሙ 45.3 % ሆኗል፡፡



የስፖርት ማዘውተርያ እና የስልጠና ማዕከላት

## የአማራ ክልል ህዝቦች ሰማዕታት መታሰቢያ

የአማራ ክልል ህዝቦች ሰማዕታት መታሰቢያ የአማራ ህዝብን ታሪክ ለማስረጽ በሙዚየም፣ በኪነቅርስ፣በንባብቤት፣በመዝናኛ ጋርደን፣በመልዕክቶች፣በኢንተርኔት ቴክኖሎጅ፣በስዕል ጋለሪ እና በመዝናኛ ቤቶች ማሕበረሰቡን እያስተማረ የታሪኩ ባለቤት እንዲሆን በመገንባት የቱሪስት መዳረሻ ማድረግ ነው፡፡ከዚህ አንፃር የአማራ ሕዝብ የዝክረ-ታሪክ ማዕከል የአስር ዓመት ስትራቴጅክ ዕቅድ በመንደፍ በየአመቱ የተቀመጡ ግቦችን ክልላዊ ነባራዊ ሁኔታው ጋር በማጣጣም ዕቅድ አቅዶ ወደ ተግባር ገብቷል፡፡

### የታሪክ መረጃ ስብስብን ማሳደግ

በ2016 ዓ.ም በአማራ ህዝብ ታሪክ ውስጥ ጉልህ አሰተዋጽኦ የሚያሳየውን የአፄ ቴድሮስ ሴፓስቶፖል መድፍ ኪነ-ቅርጽ በፋይበር ተሰርቶ በግቢው ውስጥ ማስቀመጥ ተችሏል፡፡ ከአርት ጋላሪ የጣራ ቅብ በኃላ ስዕሎችን ወደ ቦታቸው የመመለስና የአማራን ታሪክ፣ተፈጥሮአዊ ገጽታ፣ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ዘርፍ የማደራጀት ስራ ተሰርቷል፡፡በሙዚየም ውስጥ ላሉ ነባር ባለታሪክ ቅርሶች ካፕሽን የማስተካከልና 29 ካፕሽኖችን በአዲስ የመስራት ስራ ተከናውኗል፡፡የውጭ እና የውስጥ የታሪክ ሙዚየም ቅርስ ጥበቃና ክትትል እየተደረገና በየጊዜው ካፕሽናቸውን በየቅርሶች ፊት ለፊት የማድረግ ስራ ተሰርቷል፡፡የታሪክ ሙዚየም፣ የስዕል ጋላሪ፣የቤተ-መጽሃፍት፣የኢንተርኔት ክፍሉና የቤተ-መዘክር ውስጣዊ ደህንነትና ንጽህና መጠበቅ ተችሏል፡፡አጠቃላይ የጉብኝት አገልግሎት ክፍል ስዕሎችን፣የታጋይ ሰማዕታት ቁሳቁሶችን እና መጣጥፎችን እንዲሁም ታሪካዊ ፎቶዎችን፣ቅርሶችንና አልባሳት ክትትል ተደርጓል፡፡የቅርሶችን ፎቶዎች ባህላዊ አልባሳቶችን እና የስነ-ጥበብ ስራዎች ፎቶ ቡክ ለማዘጋጀት /ለህትመት/የቅርስ ምዝገባ/ ከቅርስ ክብደት ውጭ አጠቃላይ መረጃ በሶፍት ኮፒ ተዘጋጅቷል፡፡ሙዚየም ለገቡ የአማራ ነገስታቶች ታሪክ በሶፍት ኮፒ ታሪካቸው

ተዘጋጅቷል፡፡ለ58 የታሪክ መጽሃፍት አስፈላጊውን ግብዓት በማሟላት ለአገልግሎት እንዲውሉ ተደርጓል፡፡በቤተ-መዛግብቱ ያሉ ስዕሎችን በፎቶ በማንሳት በስዕል ጋላሪው ውስጥ በፕላዝማ ለጎብኝዎች ለማስጎብኘት የምስል /ቪዲዮውን /ማስቀጠል ተችሏል፡፡አጠቃላይ የማዕከሉ መግለጫ ሊሆን የሚችል ሰነድ ተዘጋጅቶ በማኔጅመንት በማጸደቅና ኢዲት በማድረግ እንዲታተም ለህዝብ ግንኙነት ተሰጥቷል፡፡የዛጉየ ስርወ- መንግስትና የመካከለኛውን ዘመን ታሪክ ነገስታትና ያስተዳደሩበትን ዘመን የማዘጋጀት ስራ ተሰርቷል:: በሙዚየሙና ቤተ-መጽሃፍቱ ውስጥ ያሉ ንብረቶችና ቅርሶችን ደህንነት ለመጠበቅ የተለያዩ ቦታዎች ላይ የጥንቃቄ መልዕክቶች ተለጥፈዋል ፡፡ስለ አጼ ቴዎድሮስ የህይወት ታሪክና የሴፓስቶፖል መድፍ አሰራር ሙሉ ሰነድ በማዘጋጀት ለህዝብ ግንኙነት ተሰጥቷል፡፡በቅርሶች ዙሪያ የተሰሩ በቁጥር 34 ጥናታዊ ጽሁፎችና የቅርስ መመዝገቢያ ማንዋሎችን ማምጣት ተችሏል፡፡





ቅዱስ ላልይበላ----1171-1213 ዓ.ም አጼ ፋሲለደስ -----1624-1659 ዓ.ም





አጼ ቴዎድሮስ---1847-1860 ዓ.ም ዳግማዊ ሚኒሊክ …1881-1905 ዓ.ም





ንጉሥ ተክለሓይማኖት--1839-1893 ዓ.ም ንጉሥ ሚካኤል---1842-1910 ዓ.ም





እትጌ ምንትዋብ ---1723-1767 ዓ.ም ንግስት ዘዉዲቱ-----1818-1922 ዓ.ም

## የአገልግሎት ሽፋንን ማሳደግ

በ2016 ዓ.ም የጎብኝዎችን ቁጥር ለማሳደግ ለ70,000 የሀገር ውስጥ ጎብኝዎች የጉብኝት አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ ክንውን 21,857 ሲሆን አፈጻጸሙ 31.3% ነው፡፡በተመሳሳይ ለ500 የውጭ ሀገር ጎብኝዎች የጉብኝት አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ ክንውን 59 ሲሆን አፈጻጸሙ 12.9% ሆኗል፡፡

በበጀት አመቱ ለ70,000 ቤተ-መጽሃፍት አንባቢ የንባብ አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ ክንውን 36,071 ሲሆን አፈጻጸሙ 51.5% ነው፡፡ በሌላ በኩል ለ1,931 ዓይነት ዲጅታል /ኤሌክትሮኒክስ/ የታሪክ መጽሃፎችን በዓይነት 148 በኮፒ ብዛት 552 የማንዋል ለአንባቢዎች ማቅረብ ተችሏል፡፡ እንዲሁም ለ20,000 የኢንተርኔት ተጠቃሚዎች አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ ክንውን 16158 ሲሆን አፈጻጸሙ 80% ነው፡፡በአጠቃላይ ለ82,961 በማንዋል፣በዲጅታልና በኢንተርኔት አንባቢና ተመራማሪዎች የንባብ አገልግሎት ለማስጠት

ታቅዶ ክንውን 40,916 ሲሆን አፈጻጸሙ 49.3% ነው፡፡ከ125 በላይ የሆኑ በአማተርና በፕሮፌሽናል ሰዓሊ የተሳሉ የአማራ ክልልና አጠቃላይ የኢትዮጵያ ታሪክን፣ ተፈጥሮን፣ ባህልን፣ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ኩነቶችን የሚያሳዩ የስዕል ስብስቦችን በመደበኛ የስዕል ጋላሪው ውስጥና በቤተ-መዛግብቱ የማስጎብኘት ስራውን ማስቀጠል ተችሏል፡፡

## የቱሪስት መዝናኛ አገልግሎቶችን ማስፋፋት

በ2016 ዓ.ም የቱሪስት መዝናኛ አገልግሎቶችን ለማስፋፋት፣ የኪነ ህንጻውን የአዳራሹንና የጋላሪውን ደህንነት ለመጠበቅ እንዲሁም የውጭውን ግድግዳ በፍሳሽ የተጎዳን ቀለም ለመቀባት በቅድ ተይዞ 7,850 ካሬ ሜትር ቀለም ቅብ ተከናውኗል፡፡ልዩልዩ አገልግሎት መስጫ ክፍሎች የሙዚየሙን፣አዳራሽ፣ ቤተመጽሐፍቱ፣ጋላሪ፣የጋርደን፣የጽዳት፣የውሃና የመብራት መስመሮች--ወ.ዘ.ተ ተገቢ የሆነ አገልግሎት እንዲሰጡ ተደርጓል፡፡ለቅርሶች፣ ጀኔሬተሮች፣ መጽሐፍትና ኮምፒውተሮች ደህንነትና ክትትል ተደርጓል፡፡ወደ ሴቫስቶፖሉ የሚወስድ እግረኛ መንገድ 116 ሜትር ተሰርቷል፡፡በመሆኑም በበጀት አመቱ የተለያዩ ቱሪስቶች የአማራ ክልል ህዝቦች ሰማዕታት መታሰቢያ ሀውልትን መጎብኘት ችለዋል፡፡



የሀገር ውሥጥ ጎብኝ

## የሥራ ዕድል ፈጠራ

በበጀት አመቱ ለ10,000 ሰራተኞች ጊዚያዊ የስራ እድል ለመፍጠር ታቅዶ ወንድ 5578 ሴት 3637 በድምሩ ለ 9216 ሰራተኞች ጊዚያዊ የስራ እድል ተፈጥሮላቸዋል፡፡

## የቴክኖሎጅ አጠቃቀም አቅም ማሳደግ

በ2016 ዓ.ም የሀርድ ኮፒ የወረቀት ብክነትን ለመቀነስ የተለያዩ የእቅድ ሪፖርቶችና ሌሎች የመረጃ ልውውጦችን በላን ሜሴንጀር ማስተሳሰርና ማስቀጠል ተችሏል፡፡ ለመስሪያቤቱ ባለሙያዎችና ለአገልግሎት መስጫ ክፍሎች ማለትም ለዲጅታልና ለኢንተርኔት ክፍሎች ልዩ ልዩ አፕሊኬሽኖችን ሶፍትዌር መጫን፣ኔትወርክና ሲስተም የማስተካከል ስራ ተሰርቷል፡፡

ለዲጅታል ንባብ የተዘጋጁ ኮምፒውተሮችን በተደራቢነት አንባቢያን ኢንተርኔት እንዲጠቀሙባቸው የኢንተርኔት አክሰስ አፕልኬሽ ሶፍትዌር ተጭኖ ዋይፋይ እንዲጠቀሙ ተደርጓል ፡፡

አጠቃላይ በበጀት አመቱ በመስሪያቤቱ ውስጥ የኮኔክሽን እና ሌሎች ችግሮች ሲከሰቱ በፍጥነት የማስተካከል ስራ ተሰርቷል፡፡80 ሜጋባይት ኢንተርኔት ብሮድባንድና ዋይፋይ ተሟልቶ ለአንባቢዎችና ጎብኝዎች አገልግሎት ውሏል፡፡ለዲጅታል ንባብ የተዘጋጁ ኮምፒውተሮችን በተደራቢነት ኢንተርኔት እንዲጠቀሙባቸው የኢንተርኔት አክሰስ አፕልኬሽ ሶፍት ዌር ተጭኖ ዋይፋይ እንዲጠቀሙ ተደርጓል፡፡ ሌላው የሰርቨር ኮምፒውተር የዲጅታል ቤተ-መጽሃፍቱን 31,062 ኢ- ቡክስ ሙሉ መረጃ ባክአፕ በመያዝ ከጉዳት መጠበቅ ተችሏል፡፡ ወደ ኮሃ ላይበራሪ ሲስተም የገቡትን አጠቃላይ የቤተ-መጽሃፍቱን ከ8000 በላይ የመጽሃፍት መረጃዎች ባካአፕ መያዝ ተችሏል፡፡45 የመገልገያ ኮምፒውተሮች የጥገናና የአፕሊኬሽን ሶፍትዌሮችን በመጫን እንዲሁም የሲስተም ማስተካከያ ስራዎችን በመስራት ለተጠቃሚዎች ቀልጣፋና ምቹ አገልግሎት ተሰጥቷል፡፡ፕሪንተሮችን ሸር የማድረግ ስራ ተከናውኗል፡፡ደረጃውን የጠበቀ የኢንስታሌሽን ስራ እንዲሰራ የፕሮጀክት ስራ ተሰርቶ ተሰጥቷል፡፡ለካፌ፣ ለቤተ-መጽሃፍት ተጠቃሚዎችና ለማዕከሉ ሰራተኞች ዋይ ፋይ ተደራሽ ማድረግ ተችሏል፡፡ አጠቃላይ የአማራ ክልል ጥንታዊ ነገስታትን ታሪክ በትረካ መልክ በማዘጋጀት በፕላዝማ ተጭኖ በድምጽ አገልግሎትን እንዲሰጥ ተደርጓል፡፡ በተጨማሪም ዲስፕሊይ ያልተደረገ የስዕል ጋላሪ የምስል ቢዲዮ በአርት ጋላሪው ውስጥ በፕላዝማ ለጎብኝዎች የማሳየት ስራ ተሰርቷል፡፡ ለተቋሙ ሰራተኞችና ለአገልግሎት መስጫ ክፍሎች ልዩ ልዩ አፕሊኬሽኖችን ሶፍት ዌር መጫን፣ ኔትወርክና ሲስተም የማስተካከያ ስራ ተሰርቷል፡፡ኢንተርኔት ክፍል ውስጥ የነበሩትን የላፕቶፕ ተጠቃሚዎች የሚያነሱትን የክፍል ጥበት ቅሬታ ለመፍታት ተጨማሪ ክፍል ተዘጋጅቶ አገልግሎት እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡






የማዕከሉ ሰራተኞች የቴክኖሎጂ አጠቃቀም ስልጠና ሲሰጥ

## የሙያ ብቃት ምዘናና ማረጋገጫ

### የምዘና ተደራሽነትን ማስፋት

በ2016 ዓ.ም በአዲስ እውቅና ያገኙ ማዕከላትን ለማፍራት በተሰራው ስራ 320 የምዘና ማእከላትን አዲስ እውቅና ለመስጠት ታቅዶ ለ17 የምዘና ማእከላት አዲስ እውቅና የተሰጠ ሲሆን አፈፃፀሙም 53.13% ሆኗል።እንዲሁም 243 ነባር የምዘና ማዕከላትን እውቅና ለማደስ ታቅዶ ክንውን 55(22.63%) ነባር የምዘና ማዕከላትን እውቅና ማደስ ተችሏል።

### የሰልጣኞችን ብቃት ለማረጋገጥ

በጀት አመቱ የሰልጣኞችን ብቃት ለማረጋገጥ ትክክለኛ፣ አስተማማኝና አካታች የሆነ የምዘና ስርዓት ለመፍጠርና ለማጠናከር በተሰራው ስራ 22,000 በመንግስትና በግል ድርጅቶች በመካከለኛና ዝቅተኛ ደረጃ የተቀጠሩ ባለሙያዎችን ብቃት በምዘና ለማረጋገጥ ታቅዶ ለምዘና የተቀመጡ 2,932 ሲሆኑ አፈፃፀሙም 13.33% ነው።ተመዝነው ብቁ የሆኑ1,164 ሲሆኑ አፈፃፀሙም 39.7 ደግሞ 0% ነው።

### የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት ድጋፍ

በ2016 ዓ.ም የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ አንቀሳቃሾችን የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት ድጋፍ አግኝተው ብቃታቸውን በምዘና ለማረጋገጥ በተሰራው ስራ ለ26,982 የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ አንቀሳቃሾችን የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት ድጋፍ አግኝተው ብቃታቸውን በምዘና እንዲረጋገጥ ለማድረግ ታቅዶ ለምዘና የተቀመጡ 2,628 ሲሆን አፈፃፀሙም 9.74%

ነው፡፡ተመዝነው ብቁ የሆኑ ደግሞ 1,452 ሲሆኑ አፈፃፀሙም 55.25% ነው፡፡መደበኛ ስልጠና አጠናቃቂዎች ብቃታቸው በምዘና ለማረጋገጥ ታቅዶ ለምዘና የተቀመጡ 14,500 ሲሆኑ አፈፃፀሙም 61.03% ነው፡፡ተመዝነው ብቁ የሆኑ 4,881 ናቸው፡፡ አፈፃፀሙም 55.15 % ነው፡፡

## የገበያ-ተኮር አጫጭር ስልጠና አጠናቃቂዎችን ብቃት በምዘና ማረጋገጥ

በ2016 ዓ.ም የገበያ-ተኮር አጫጭር ስልጠና አጠናቃቂዎችን ብቃት በምዘና ለማረጋገጥ በተሰራው ስራ ለ136,659 በምዘና ለማረጋገጥ ታቅዶ ለምዘና የተቀመጡ 34,419 ሲሆኑ አፈፃፀሙም 25.19% ነው፡፡ተመዝነው ብቁ የሆኑ ደግሞ 29,613 ናቸው፡፡አፈፃፀሙም 86.04% ነው፡፡

# IV.መልካም አስተዳደር ዘርፍ

## ርዕሰ መስተዳደር

ጽ/ቤቱ በአዋጁና በሌሎች ህጎች መሠረት ለርዕሰ-መስተዳድሩ ተጠሪ የሆኑ አስፈፃሚ መስሪያ ቤቶችንና ተቋማትን ለይቶ በመያዝ ከርዕሰ-መስተዳድሩ ጋር የሚኖራቸውን የሥራ ግንኙነት ቀልጣፈ እንዲሆን የሚያደረግ ተልዕኮ ይዞ ከመፈፀም በተጨማሪ በክልሉ ለሚካሄዱ የልማትና የመልካም አስተዳደር ስራዎች የበኩላቸውን እንዲወጡ ለተመደቡ ለክልሉ ከፍተኛ አመራሮች ከሥራ ኃላፊነታቸው ጋር በተያያዘ ሁለገብ አገልግሎት እና የፕሮቶኮል ሽፋን እየሰጠ የሚገኝ ተቋም ነው፡፡

## አገልግሎት አሰጣጥን በማሻሻል የደንበኞችን እርካታ ማሳደግ

ከቀረቡ አቤቱታዎች ውስጥ ደረጃቸውን ጠብቀው የቀረቡ አቤቱታዎች ብዛት 4160 (9.17%) ደረጃውን ሳይጠብቁ የቀረቡ 24919 (54.95%) ሲሆን በብዛት የቀረበባቸው ምዕራብ ጎንደር፣ ሰሜን ጎንደር፣ ማዕከላዊ ጎንደር፣ ደቡብ ጎንደር፣ ምዕ/ጎጃም፣ ደቡብ ወሎ፣ማዕ/ጎንደር ዋግኽምራ እና ባህርዳር ከተማ ናቸው፡፡

በበጀት ዓመቱ ከፍተኛ ቅሬታ/አቤቱታ የታየባቸው የዞን አስተዳደር ጽ/ቤቶች ስንመለከት ማዕከላዊ ጎንደር 10,707፣ ምዕራብ ጎጃም 7,404፣ ሰሜን ጎንደር 5416፣ ደቡብ ወሎ 4197፣ ደቡብ ጎንደር 3,613 እና ዋግኽምራ ብሔረሰብ ዞን 3,425 ናቸው፡፡

## የሚሰጡ በውሳኔዎችን ሚዛናዊነት፣ውሳኔ ጥራት ክትትል

በየደረጃው በወረዳ፣ በዞንና በክልል ደረጃ ከተሰጡ ውሳኔዎች ይግባኝ አፈፃፀም በየደረጃው ስንመለከት ወደ ወረዳ፤ ከተማ ወይም ክፍለከተማ አስተዳድር- ይግባኝ የተባለ 60፣ የፀደቁ 49/81.6% የተሻሩ 7 በሂደት ላይ ያሉ 4 ናቸው፡፡

| ተ.ቁ | የአቤቱታ የቀረበባቸው የሥራ ዘርፎች | የቀረበ | ሽፋኑ % |
|---|---|---|---|
| 1 | ከከተማ ቦታ አገልግሎት አሰጣጥ ጋር | 2877 | 6 |
| 2 | ከአስተዳደራዊ አገልግሎት አሰጣጥ ጋር | 8622 | 19 |
| 3 | ከፍትህ አገልግሎት አሰጣጥ ጋር | 256 | 1 |
| 4 | ከፖሊስና ሚሊሻ (ከፀጥታ ኃይሉ) አገልግሎት አሰጣጥ ጋር | 187 | 0 |
| 5 | ከሰው ሀይል ስምሪት አገልግሎት አሰጣጥ ጋር | 693 | 2 |
| 6 | ከሴፍትኔት ምልመላና መረጣ አገልግሎት አሰጣጥ ጋር | 9397 | 21 |
| 7 | ከሥራ እድል ፈጠራ አገልግሎት አሰጣጥ ጋር | 2026 | 4 |
| 8 | ከንግድና ገበያ ልማት አገልግሎት አሰጣጥ ጋር | 1175 | 3 |
| 9 | ሌሎች(ከላይ ከተገለፁ ተቋማት ውጭ የቀረቡ) | 20110 | 44 |
| | ጠቅላላ ድምር | 45343 | 100 |

## የማህበራዊ አሃዝ ካርድ አሰራር ስርዓትን ተግባራዊነት ማጠናከር

በነባር የተለዩ ችግሮች ለመፍታት እቅድ የያዙ ወረዳዎች 53 ሲሆን አፈፃፀሙ 60% ነው፡፡ በቀበሌ ደረጃ ደግሞ ችግሮችን ለመፍታት እቅድ የያዙ ቀበሌዎች 69 ሲሆን ክንውን 35 አፈፃፀሙ 50.72 ነው፡፡ ለመፍታት የተለዩ ችግሮች ብዛት ደግሞ 281 ክንውን 59 (20.99%) ነው፡፡

## የግልፀኝነትና ተጠያቂነት አሰራር ስርዓትን ማጎልበት

በክልል ደረጃ ማህበራዊ ተጠያቂነት ሄሎ ገበርን መንት ግንዛቤ የተፈጠረላቸው 332 87.13% ለአመራሩ፤ ለመንግስት ሰራተኛው ለተለያዩ የህሰብ ክፍሎች ግንዛቤ

ተፈጥሯል፡፡ከዞን እስከ ቀበሌ የተቋሙን የአሰራር ህግ ደንብ ቁጥር 179/2011፣ መመሪያ ቁጥር 2/2012ዓም እና የተለያዩ የስራ ማንዋል መሰረት በማድረግ ለተዋረድ የመንግስት ተቋማት ሙያተኞችና አመራሮች ገጽ ለገጽ ግንዛቤ ለመፍጠር በተያዘው እቅድ መሰረት ለ477,398 ግንዛቤው ተፈጥሯል፡፡

### የአጭር ጊዜ ስልጠና

በክልል ደረጃ ለሚመለከታቸው አካላት በቅሬታ ማስተናገጃ ስርዓቱና በይድረስ ለመንግስት የስልክ አገልግሎት ዙሪያ ላይ ስልጠና ለመስጠት በተያዘው እቅድ መሰረት 191 ወንድ፣ 123 ሴት በድምሩ 314 ያህሉ ስልጠና ወስደዋል፡፡በዞኖች ደረጃም ለሚመለከታቸው አካላት በማህበራዊ ተጠያቂነትና በቅሬታ ስርዓቱ ላይ ስልጠና ለመስጠት በተያዘው እቅድ መሰረት ለ186 ወንዶችና ለ53 ሴቶች በድምሩ ለ234 ሰዎች ስልጠናው ተሰጥቷል፡፡

## ክልል ምክር ቤት

ምክር ቤቶች የህዝብ ሉዓላዊነት የስልጣን ባለቤት መገለጫ በመሆናቸው በሕገ-መንግስቱ የተሰጣቸውን ሕግ የማውጣት፤የክትትልና ቁጥጥር ስራዎችን በአግባቡ ለመፈጸምና የተሰጣቸውን የህዝብ ውክልና በመወጣት የመረጣቸውን ህዝብ ተሳታፊነትና ተጠቃሚነት የማረጋገጥ፣የመንግስት አሰራር ግልፅነትና ተጠያቂነት በተላበሰ አግባብ መፈፀሙን የማረጋገጥ እና ውክልናቸውን በአግባቡ የሚወጡበት ምክር ቤት ነው፡፡

### የሚወጡ ህጎችን ጥራትና ተደራሽነትን ማሻሻል

ሕገ-መንግስቱ ለምክርቤቱ በሰጠው ሕግ የማውጣት ስልጣን መሰረት በህግ አወጣጥ ሂደት ላይ በ79% ለማሻሻል ግብ ተጥሎ ለክልል ምክር ቤት በሚቀርቡ ረቂቅ ሕጎች ላይ የህዝብ አስተያየት በማሰባሰብ የውሳኔ ሃሳቦችን ማቅረብ እንዲቻል በምክር ቤቶች የአሰራር እና የስነ-ምግባር ደንብ መሰረት ቀደም ብለው ከአንድ ወር በፊት ለጽ/ቤቱ እንዲላኩ በታቀደው መሰረት 6 (100%) ማከናወን ተችሏል፡፡እነርሱም አዋጅ ቁጥር 287/2015 ዓ.ም. በአብክመ የዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤትን ተግባርና ኃላፊነት መወሰኛ አዋጅ እንደገና ለማሻሻል የወጣ አዋጅ፤አዋጅ ቁጥር 288/2015 ዓ.ም የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የ2015 በጀት ዓመት ለመንግስት ሥራዎች ማስፈጸሚያ ተጨማሪ በጀት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ እና አዋጅ ቁጥር

289/2014 ዓ.ም በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የ2016 በጀት ዓመትን በጀት ለማጽደቅና የበጀት አስተዳደሩን ለመወሰን የወጣ አዋጅና ሌሎች ናቸው፡፡

## የህዝብ ውክልናን የመወጣት አሰራርን ማሻሻል

የህዝብ ውክልናን የመወጣት አሰራርን በ100% ለማሻሻል በታቀደው መሰረት ከካሳ ክፍያ፣ ከይዞታ የባለቤትነት፣ከአገልግሎት አሰጣጥ እና በተለያዩ ጉዳዮች ጋር በተያያዘ ቅሬታዎችና አቤቱታዎች ይዘው ለአማካሪዎች እና ለቋሚ ኮሚቴዎች ያቀረቡ በቡድን የመጡ ወንድ 16 ሴት - ድምር 16፣ በተናጠል የመጡ ወንድ 6፣ ሴት 6 ድምር 12 በአጠቃላይ 28 ቅሬታዎችና አቤቱታዎች አቅራቢዎችን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመነጋገር 100% መፍትሔ እንዲሰጣቸው ተደርጓል፡፡

ተቋሙ ባወጣው መርሃ ግብር መሰረት የምክር ቤት አባላት በየምርጫ ክልላቸው የመራጭ ተመራጭ መድረክ በሚሄዱበት ጊዜ ከላይ በሚወርደው አቅጣጫና ቼክ ሊስት መሰረት መራጩን ህዝብ ለማወያየት በተቀመጠው ፕሮግራም መሰረት በተወሰኑ አካባቢዎች ወደ መረጣቸው ህዝብ ወርደው መራጩን ማወያየት ችለዋል፡፡

## ምክር ቤቶችን የጉባኤ አፈፃፀም ማሻሻል

በበጀት ዓመቱ የምክር ቤቶች የጉባኤ አፈፃፀም 100% ለማሻሻል በተጣለው ግብ መሰረት በህገ-መንግስቱ በተደነገገው የክልል ምክርቤት ቢያንስ በዓመት 2 ጊዜ፤ የብሔረሰብ አስተዳደር ምክርቤቶች 3 ጊዜ የወረዳና ከተማ ምክርቤቶች 4 ጊዜና የቀበሌ ምክርቤቶች 12 ጊዜ ጉባኤ ለማካሄድ በታቀደው መሰረት የክልል ምክርቤት 2 ጊዜ መደበኛና 1 አስቸኳይ ጉባኤዎች 100% በተሳካ ተካሂዷል፡፡ እንዲሁም በምክር ቤት ጉባኤ የህዝብ ክንፍ 2 ጊዜ ማሳተፍ ታቅዶ 2 ጊዜ (100%) የተከናወነ ሲሆን በሦስቱም ጉባኤዎች ለተሳታፊ የምክር ቤት አባላትና ተጋባዥ እንግዶች በቼክሊስቱ መሰረት ድጋፍ የማድረግ ስራ 100% ተከናውኗል፡፡






ምክር ቤቱ ጉባኤ ሲያካሂድ

## የህገ-መንግስት ተርጓሚ ኮሚስዮንና አጣሪ-ጉባኤ አሰራር ማሻሻል

የምክር ቤት ጽ/ቤቱ የህገ-መንግስት ተርጓሚ ኮሚስዮንና አጣሪ-ጉባኤ አሰራር በ85% ለማሻሻል በተጣለው ግብ መሰረት በዜጐችና በተቋማት የሚቀርቡ የህገ-መንግስት ትርጉም ጥያቄዎችን በመቀበል በአጣሪ ጉባኤ በበጀት ዓመቱ 11 እንዲታዩ ለማድረግ ታቅዶ በአጣሪ ጉባኤ ውሳኔ እንዲሰጥባቸው ለማድረግ ፋይል ተከፍቶላቸውና አስፈላጊው የሆኑ መረጃዎች ተሟልተው መዝገቦቹ በሰብሳቢው አማካኝነነት የውሳኔ አስተያየት እንዲቀርብባቸው ለሚመለከታቸው የህግ ባለሙያዎች ተመርተው ከታዩ በኋላ 10(90.9%) ጉዳዮች የውሳኔ አስተያየት ተሰጥቶባቸው ተመልሰው በአጣሪ ጉባኤ ታይተው ውሳኔ ተሰጥቶባቸዋል፡፡

## የምክር ቤቶችን አሰራርና አደረጃጀት ማሳደግ

ተቋሙ የምክር ቤቶችን  አሰራርና አደረጃጀት የነበረውን በ95% ለማከናወን ግብ ተጥሎ ህብረተሰቡ ስለምክር ቤቶች በአግባቡ እንዲረዳ ለማድረግ በተቋቋመው ነፃ የስልክ ጥሪ ማዕከል አማካኝነት የህዝብ ጥያቄዎችን፣ ጥቆማዎችን፣ቅሬታና አቤቱታዎችን በመቀበል 100% ምላሽ እንዲሰጥባቸው ለማድረግ ታቅዶ በእቅዱ መሰረት ተከናውኖ ለሚመለከታቸው አመራሮችና አማካሪዎች እንዲደርስ ተደርጓል፡፡

## የመንግስት ኮሙዩንኬሽን

በ2016 በጀት ዓመት በአማራ ክልል የተፈጠረውን የሠላም መደፍረስ ወደ ነበረበት ሠላማዊ ሁኔታ ለመመለስ በርካታ እልህ አስጨራሽና ከፍተኛ መስዋእትነት ተከፍሎ አንፃራዊ ሠላም እንዲገኝ ተደርጓል፡፡ ይህንን አንፃራዊ ሠላም ወደ ዘላቂ ሰላም ለመመለስ በሁሉም ዘርፎች በተለይም በህዝብ ግንኙነትና በህዝቡ ሁሉን አቀፍ ተሳትፎ ለማረጋገጥ ተከታታይ ስራ እየተሰራ ይገኛል፡፡የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ የመንግሥት ኮሙዩኒኬሽን ቢሮ የክልሉን መንግሥትና የተቋሙን የ10 ዓመት የልማትና የመልካም አስተዳደር ዕቅድ መነሻ በማድረግ የ2016 በጀት ዓመት ዕቅድ አዘጋጅቶ ወደ ሥራ በመግባት ውጤታማ ስራ ሰርቷል፡፡

## ኘሮጀክት መቅረፅ

ለአካባቢ ሚዲያዎች ማቋቋሚያ፣ ቁሳቁስ ማሟያ እና ለክትትልና ድጋፍ ማስፈጸሚያ የሚሆን 149 ፕሮጀክት ለመቅረጽ ታቅዶ 129 በማከናወን አፈፃፀሙ 86.5% ሲሆን ከተቀረፁ ፕሮጀክቶች 2,636,427.46.00 ብር በማግኘት ስራ ላይ ማዋል ተችሏል፡፡

## የአጭር እና የረጅም ጊዜ ስልጠናዎች

የረጅም ጊዜ የስልጠና እድሎችን በማመቻቸት የኮሚዩኒኬተሩን፣ የህዝብ ግንኙነት ባለሙያውንና ሌሎች የሚዲያ ሙያተኞችን የመፈፀም አቅም ለማጎልበት ታቅዶ 1 ወንድ አመራር እና 1 ሴት ባለሙያ በውጭ አገር እየተማሩ ሲሆን 2 ወንድ እና 1 ሴት ደግሞ በአገር ውስጥ በሚገኙ ዩንቨርስቲዎች በመማር ላይ ይገኛሉ፡፡ አጫጭር ስልጠናዎችን በተመለከተ ደግሞ በዓመት 2 ጊዜ ለመስጠት ታቅዶ ክንውን 1 አፈፃፀም 50% መፈጸም ተችሏል፡፡ በዞን፣በከተማ አስተዳደር ደረጃ 388 ያህል ስልጠና መድረኮችን ለማመቻቸት ታቅዶ 256 የስልጠና መድረኮችን ተካሂደዋል፡፡

## የኮሙዩኒኬሽን፣ የሚዲያና የሴክተር ሕዝብ ግንኙነቶች ፎረሞች

የሚዲያ ቴክኒክ ፎረም በክልሉ የሚንቀሳቀሱ የሚዲያ አመራሮችና ተወካዮች ከኮሙዩኒኬሽን አመራሮች ጋር በጋራ አጀንዳዎች ላይ እየተገናኙ የሚመክሩበትና ክፍተቶችን በመለየት የቀጣይ አቅጣጫዎችን የጋራ የሚያደርጉበት ነው፡፡ በ2016 በጀት ዓመትም እቅድ 12 ክንውን 13 ሲሆን አፈፃፀሙም 108% ነው፡፡ ሌላው ደግሞ የሚዲያ እና የኮሙዩኒኬሽን የከፍተኛ አመራር ፎረምን ሲሆን የብልፅግና ፓርቲ የአማራ ክልል ቅርጫፍ ጽ/ቤት ኃላፊ የሚመሩት የአማራ ሚዲያ ኮርፖሬሽን እና የመንግስት ኮሙዩኒኬሽን ኮር አመራሮች ብቻ የተገኙበት የስራ ግምገማ

የሚካሄድበት ፎረም ነው፡፡ በየሩብ ዓመቱ አንድ ጊዜ ለመገናኘት እና ለመገምገም ታቅዶ ከእቅድ በላይ በየወሩ ለማካሄድ ተችሏል፡፡ ሌላው የኮሙዩኒኬሽን፣ የህዝብ ግንኙነትና የሚዲያ ተቋማት የጋራ ፎረም ሲሆን የኮሙዩኒኬሽን ቢሮ ኃላፊ የሚመሩት በየሩብ ዓመቱ የሚካሄድ የተቋማት የህዝብ ግንኙነት የስራ አፈጻጸም ግምገማ የሚካሄድበትና አቅጣጫ የሚሰጥበት ፎረም ነው፡፡ በዚህም መሰረት በ2016 በጀት ዓመት 4 ጊዜ የጋራ ፎረም ለማካሄድ ታቅዶ 5 ተከናውኗል፡፡

## የማስታወቂያ እና ፕሮሞሽን ምስክር ወረቀት መስጠትና ማደስ

የኢንፎርሜሽንና ሚዲያ ዘርፉን ለማሳደግ ይቻል ዘንድ ኮሙዩኒኬሽን ግለሰቦችና ድርጅቶች በሚዲያው ዘርፍ አቅማቸው እንዲጠናከር ድጋፍ ይሰጣል፡፡ የማስታወቂያና ኘሮሞሽን ምስክር ወረቀት ለማውጣት የሚመጡ ግለሠቦችና ድርጅቶች የሙያ ምስክር ወረቀት ለማውጣት የሚያስፈልጉ መስፈርቶችን ላሟሉ ደንበኞች ለ6 ወንድ የሙያ ምዝገባ ፈቃድ ዕድሣት መስጠትና ለ1 ወንድ ደግሞ የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ተሰጥቷል፡፡ በተጨማሪም ለ5 ወንዶች ደግሞ በሙያ ፈቃድ አሰጣጥ ዙሪያ መረጃ ተሰጥቷል፡፡

## የፓናል ውይይት ማካሄድ

ከክልል እስከ ወረዳ ባሉ የኮሙዩኒኬሽን መዋቅሮች በልዩ ልዩ አገራዊ፣ ክልላዊና አካባቢያዊ ጉዳዮች ዙሪያ የፓናል ውይይቶች ተካሂደዋል፡፡ በክልል ቢሮ ደረጃ ከዕዳ ወደ ምንዳ በሚል ወቅታዊ ርዕሰ ጉዳይ ላይ 1 ፓናል ውይይት ተደርጓል፡፡ በተጨማሪም በክልሉ የተፈጠረውን ቀውስ ለማስቆም በርካታ የህዝብ የውይይት መድረኮችን በተለያዩ ዞኖች፣ ከተሞችና ወረዳዎች ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር በማመቻቸትና በመምራት የማረጋጋትና የግንዛቤ ፈጠራ ስራ በ464 መድረኮች ተሰርቷል፡፡

## ምርጥ ተሞክሮ በመቀመር ማስፋት

በየደረጃው በሚገኙ የዘርፉ ተቋማት በክልሉ ልዩ ልዩ አካባቢዎች በልማትና በዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ውስጥ የሚከናወኑ ምርጥ ተሞክሮዎችን ቀምሮ በማስፋት ልምዶች እንዲሰፉ ይደረጋል፡፡ ከዚህ አንጻር በክልል ቢሮ ደረጃ 2 ታቅዶ 2 ተከናውኗል፡፡ በዞኖችና በከተማ አስተዳደሮች ደግሞ 399 ተሞክሮዎችን ቀምሮ የማስፋት ስራ የተሰራ ሲሆን ፈፃፀሙም 45% ነው፡፡

## የአካባቢ ሚዲያ ከማስፋፋት እና ከማጠናከር አንፃር

በወረዳዎችና በከተሞች የአካባቢ የሚዲያ አውታሮች ማስፋፋትና ማጠናከር በዕቅድ የሚመራ ተግባር ሲሆን እነዚህን ሚዲያዎች በመጠቀም በአካባቢው የተከናወኑ የልማትና የመልካም አስተዳደር ተግባራትን እና ወቅታዊ መረጃዎችን ለአካባቢው ህብረተሰብ በማቅረብ የሚዲያ አሰራሮችን ብቃትና የአካባቢውን ህብረተሰብ ግንዛቤ ማጎልበት ይጠይቃል፡፡ በመሆኑም በ2016 በጀት ዓመት 8 አዲስ ሚኒ ሚዲያ፣15 ማስታወቂያ ሰሌዳዎች፣17 መረጃ ማዕከሎችና 12 ቲቪ ፓርኮች በአዲስ የተቋቋሙ ሲሆን ለ1255 ነባር ሚኒ ሚዲያ፣ለ1827 ማስታወቂያ ሰሌዳ፣1441

ነባር መረጃ ማዕከልና ለ185 ቲቪ ፓርኮች ክትትልና ድጋፍ ተደርጓል፡፡





አዲስ የተቋቋመ ሚኒ ሚዲያ (ደቡብ ወሎ) ነባር መረጃ ማዕከል ድጋፍ (ማዕከላዊ ጎ

## መልዕክት መቅረፅ

እንደ ክልል 2,384 መልዕክት ለመቅረፅ ዕቅድ ተይዞ በክልል ቢሮ ደረጃ እቅድ 16 ክንውን 21 በመከናወኑ አፈፃፀሙ 131% ለማድረስ የታቀደ ቢሆንም 1,812 በመሰራቱ አፈፃፀሙም 76% ሆኗል፡፡በዞንና በከተማ አስተዳደሮች ደግሞ 2,368 መልዕክቶችን ለማዘጋጀት ታቅዶ 1,791 መልዕክቶች ተዘጋጅተው ለጋራ መግባባት ሥራ የዋሉ ሲሆን አፈፃፀሙም 76.6% ነው፡፡

## ፎቶ ግራፍ ኤግዚቢሽን

በዘርፉ በልማትና በመልካም አስተዳደር የተከናወኑ ሥራዎችን በቋሚ የፎቶ ግራፍ ኤግዚቪሽን ለማሣየት 2,074 እቅድ ተይዞ 1,172 በማከናወን አፈፃፀሙ 57% ነው። በክልል ቢሮ ደረጃ 12 ታቅዶ 6 ተከናውኗል።

## ሚዲያ ጥቆማን (ዘገባ ጥቆማ)

ሚዲያ ጥቆማን በሚመለከት እንደ ክልል እቅድ 2,386 ክነውን 2,421 ጥቆማ በማድረግ የእቅዱን 101% መፈጸም ተችሏል። በክልል ቢሮ ደረጃ እቅድ 24 ተይዞ 37 በመከናወኑ አፈፃፀሙ 154% በላይ ነው። አፈጻጸሙ ከፍ ያለበት ምክንያት በክልሉ የሚገኙ ሁሉም የመንግስት ተቋማት የሚዲያ ጥቆማ በተቋማችን እንዲሰጥ በመደረጉና በወቅታዊ ጉዳይ ምክንያት ነው። በተመሳሳይም በዞንና ከተማ አስተዳደሮች 2,362 የሚዲያ ጥቆማዎችን ለመስጠት ታቅዶ 2,384 ጥቆማዎችን ለተለያዩ ሚዲያዎች በመስጠት 101% ማከናወን ተችሏል።

## ሚዲያዎች ሞኒተሪንግ

ክልላችንን አስመልክቶ በህትመትና ኤሌክትሮኒክስ ሚዲያ፣ በመንግስት እና በግል ሚዲያዎች ውስጥ የተዘገቡ መረጃዎችን በመዳሰስ እና ከሚመለከተው ዞንና ከተማ አስተዳደሮች በማጣራት ለሚመለከተው አካል በወቅቱ የማድረስ ስራ ተሰርቷል። በመሆኑም በአጠቃላይ በዓመቱ 1464 ዘገባዎች ተዘግበዋል። እነዚህም ከማህበራዊ 199፣ ከኢኮኖሚያዊ 370 እና ከፖለቲካዊ 895 ጉዳዮች ጋር የተያያዙ ናቸው።

## መረጃ መሰብሰብ፣ የማደራጀት፣ የመተንተን እና ማሰራጨት

በዘርፉ የመረጃ ትንተና ሥራ በመሥራት ለተጠቃሚ በማቅረብ ህብረተሰቡ በትክክለኛ መረጃ ሙሉ እንዲሆን የማድረግ ስራ ይሰራል። በመሆኑም መረጃ ከመሰብሰብና ከማደረጃት አኳያ በበጀት ዓመቱ ዕቅድ 138,446 ክነውን 66,910 አፈፃፀም 48% ተከናውኗል። የተሰበሰቡና የተደራጁ መረጃዎች የ2016 ዓ.ም እቅድ፣መጽሄቶች፣በራሪ ወረቀት፣2015 ዓ.ም ሪፖርት፣ ፎቶግራፎች፣ጋዜጦች፣ ዜናዎች፣ የህዝብ አስተያየት መረጃዎች፣የገበያ መረጃ ወዘተ ናቸው። የተሰበሰበውን መረጃ በማደራጀት ለተመራማሪዎች፣እቅድ ለሚያቅዱ እና ለፖሊሲ አውጭዎች

ወቅታዊ ተግባራትን ለማከናወን ጥቅም ከመስጠቱም ባሻገር ለቀጣይ አመታት የተለያዩ ተግባራት ለሚሰሩ ባለሙያዎች በመረጃ ምንጭነት ያገለግላል፡፡ በተጨማሪም ወቅታዊ መረጃዎችን ተንትኖ ለደንበኞች ማድረስ ህብረተሰቡ በኢኮኖሚ፣በማህበራዊና በመልካም አስተዳደር ዘርፍ በየወቅቱ የሚከናወኑ ተግባራትን በቀላሉ እንዲረዳ ለማድረግ በበጀት ዓመቱ 822 ለመተንተን ታቅዶ 345(42%) መረጃዎችን በመተንተን ጥረት ተደርጓል፡፡

## የአማራ ክልል የመረጃ መፅሐፍ ዝግጅት

በበጀት አመቱ አመታዊ የመረጃ መፅሀፍ ለመስራት በታቀደው መሰረት የ35 ተቋማት የተገመገመ የ2015 ዓ.ም ሪፖርት እና ከተለያዩ ተቋማት የተለያዩ የፎቶ መረጃዎችን በመሰብሰብ ለአመታዊ የመረጃ መፅሀፍ ግብዓት ማድረግ ተችሏል፡፡ እንዲሁም የተተነተነውንና ጥሬ ሀቆችን በማረጋገጥ በ500 ቅጅ ታትሞ ለተለያዩ አካላት በመረጃ ምንጭነት እንዲያገለግል ተደርጓል፡፡

## ህትመት ዝግጅትና ስርጭት

በቢሮ ደረጃ ሐዲስ መጽሄት በየሩብ ዓመቱ በማዘጋጀት ለማሰራጨትና በዌብ ሳይት ከመልቀቅ አኳያ በበጀት ዓመቱ 4 እትም ሐዲስ መጽሄት እያንዳንዱን በ2,000 ቅጅ በድምሩ በ8 ,000 ቅጅ ለማሳተም እና ለማሰራጨት ታቅዶ በእትም 4(100%) ማዘጋጀት የተቻለ ሲሆን በቅጂ 2,000 (25%) አሳትሞ ማሰራጨት ተችሏል፡፡

በዞን፣ ወረዳና ከተማ አስተዳደር ደረጃም ተግባሩ በየወሩ የሚከናወን ሲሆን ነባራዊ ሁኔታውን መሰረት በማድረግ ወቅታዊ ይዘት ተመርጦ በየአካባቢው ልምድ ለማለዋወጥ በሚያስችል አግባብ በዘርፉ 2,820 እትም በራሪ ወረቀት በ705,000 ቅጂ ለማሳተም ታቅዶ 1,846 (65%) እትም አዘጋጅቶ 554,444 ቅጅዎችን በማሰራጨት የእቅዱን 79% ማከናወን ተችሏል፡፡ በተመሳሳይ በበጀት ዓመቱ 4 እትም ፖስተር በ12,000 ቅጅ ለማዘጋጀትና ለማሰራጨት ታቅዶ በእትም 4(100%) ማዘጋጀት የተቻለ ሲሆን በቅጅ 2000 (17%) ማከናወን ተችሏል፡፡

በሌላ መልኩ በቢሮ ደረጃ ለዌብ ሳይት የሚመጥኑና የተለያየ ይዘት ያላቸው 12 አርቲክሎችን በማዘጋጀት የእቅዱን 100% መፈፀም ተችሏል፡፡



የሐዲስ መጽሄት እትሞች

## ዜናና ፕሮግራም ማዘጋጀት

በቢሮው፣ በዞኖችና ከተማ አስተዳደሮች 11,479 የጽሑፍ ዜናዎችን ለማዘጋጀትና ለማስራጨት ታቅዶ 9,969(87%) ተከናውኗል፡፡በተመሳሳይ 9,485 የምስል ዜናዎች ለማዘጋጀት ታቅዶ 4,714(50%) ተፈፅሟል፡፡በሌላ መልኩ በዞንና ከተማ አስተዳደር ደረጃ 2,384 የአካባቢ ማስተማሪያ ፕሮግራም ለመስራት ታቅዶ 1,367(57%) ተዘጋጅቷል፡፡በተጨማሪም በቢሮ ደረጃ 12 የቴሌቪዥን ፕሮግራም ለማዘጋጀት ታቅዶ 19 በመከናወኑ አፈጻጸሙ 158% ነው፡፡ እንዲሁም 3,276 የሚኒ ሚዲያ ፕሮግራሞችን ለማዘጋጀት ታቅዶ 1,563 በማከናወን የእቅዱን 47 በመቶ በመፈፀም ህብረተሰቡ መረጃ ተደራሽ እንዲሆን ጥረት የተደረገ ከመሆኑም ባሻገር በስምንቱ ሪጆዮ ፖሊቲያን ከተሞች 384 የሬድዮ ፕሮግራም ለማዘጋጀትና ለማስተላለፍ ታቅዶ 192(50%) የሬድዮ ፕሮግራም በማዘጋጀት መረጃ ማሰራጨት ተችሏል፡፡

## ማህበራዊ ሚዲያ

የአማራ ክልል መንግስት ኮሙዩኒኬሽን ቢሮ የፌስቡክ ገፅ Amhara communications- ከ380 ሺህ በላይ ተከታይ ያለው ገፅ ነው፡፡ በዚህ የፊስቡክ ገፅ ሌሎች ሚዲያዎች የዘገባ ግብዓት ሊሆኑ የሚችሉ ክልል አቀፍ ፓለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ይዘት ያላቸው 500 ዜናዎችን በፌስ ቡክ ገፁ ለመልቀቅ እቅድ ቢያዝም ከእቅድ በላይ በወቅታዊ የክልሉ ሁኔታ ምክንያት 1000 ዜናዎች ተጭነዋል፡፡ ከእነዚህም ውስጥ ወቅታዊ ፓለቲካን የተመለከቱ 475 ዜናዎች ኢኮኖሚን የተመለከቱ 78 በክልሉ ያሉ በማህበራዊ ልማት እንቅስቃሴዎች ላይ ያተኮሩ 157 ዘገባዎች በፌስ ቡክ ገፁ መልቀቅ ተችሏል፡፡

## መደበኛ የሆነ የህዝብ አስተያየት ጥናትን

በበጀት ዓመቱ ህብረተሰቡ የሚያነሳቸውን የተለያዩ ጥያቄዎች በተደራጀ ሁኔታ መረጃዎችን በመሰብሰብ ለሚመለከታቸው አካላት በማቅረብ የመልካም አስተዳደር ችግሮችን ለመፍታት የሚያስችል መደበኛ የህዝብ አስተያየት ጥናት ማድረግን በተመለከተ ዕቅድ 1,211 ክንውን 579(48%) ነው፡፡

## ወቅታዊ የህዝብ አስተያየት

ወቅታዊ የህዝብ አስተያየት ጥናት እቅድ 5 ክንውን 5 አፈፃፀሙ 100% ነው፡፡ የተለያዩ ወቅታዊ ርዕስ ጉዳዮችን ወደ ዞኖች እና ከተማ አስተዳደሮች በመላክ የመሰብሰብ እና የማጠናቀር ስራ በመስራት ለሚመለከታቸው አካላት ማድረስ ተችሏል፡፡

## የአካባቢ ሚዲያ ዳሰሳ ጥናትን

የአካባቢ ሚዲያዎች ላይ ጥናት በማድረግ ያሉበትን ደረጃ ለማወቅና ክፍተቶቻቸውን ለመሙላት እንዲሁም ጠንካራ ጎናቸው ተጠናክሮ እንዲቀጥል ለማስቻል 212 የአካባቢ ሚዲያ ጥናት ለማድረግ ታቅዶ 90(42%) ተከናውኗል፡፡

# ጠቅላይ ፍርድ ቤት

በ2016 ዓ.ም የዳኝነት ዘርፉ በሀገር ግንባታ ሂደት ውስጥ ህግና ሥርዓትን በማስከበር እንዲሁም የዜጎችን ሰብአዊ እና ዴሞክራሲያዊ መብቶችን በማስከበር ጤናማ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ እንዲኖር፣ ማህበራዊ ፍትህ እንዲረጋገጥ እና የዳበረ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት እንዲገነባ በማድረግ ረገድ ያለውን የማይተካ ሚና ለመወጣት እንዲችል ሰፊ ጥረት ተደርጓል፡፡

## የፍርድ ቤቶችን ተደራሽነት ማሻሻል

የፍርድ ቤቶችን ተቋማዊ ተደራሽነት ማስፋት ዜጎች የዳኝነት አገልግሎትን በቅርበት እንዲያገኙ በማስቻል ረጅም ርቀት በመሄድ ሊያወጡት ይችሉት የነበረውን የገንዘብ፣ የጊዜ እና የጉልበት ወጪን በመቀነስ የፍትህ ተደራሽነትን ለማረጋገጥ የጎላ አስተዋጽኦ አለው፡፡ይህንን በመረዳት በባለፉ ዓመታት የፍርድ ቤቶችን ተደራሽነት ለማስፋት በርካታ ስራዎች ተሰርተዋል፡፡ በዋናነትም የዳኝነት አገልግሎቱን ተደራሽነት ለማሳደግና ፍትህ ፈላጊውን ማህበረሰብ ፍትህን በቅርበት እንዲያገኝ ለማድረግ በየጊዜው የጉዳዮችን ፍሰት መሰረት ያደረገ ፍርድ ቤቶች

እንዲከፈቱ ሲደረግ ቆይቷል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ በ2016 በጀት ዓመትም ተገቢውን ጥናት በማድረግ ተደራሽነትን ለማስፋት ትኩረት የተሰጠው በመሆኑ ይህን ግብ ለማሳካት በበጀት ዓመቱ ልዩ ልዩ ተግባራት ተከናውነዋል፡፡በዚህም በክልሉ ካሉን 152 የወረዳ ፍርድ ቤቶች በተጨማሪ 4 የወረዳ ፍርድ ቤቶችን በመጨመር ወደ 156 የወረዳ ፍርድ ቤቶች ለማሳደግ እና የነበሩን 40 የወረዳ ፍርድ ቤት ምድብ ችሎቶች በ2016 በጀት ዓመት ወደ 41 የወረዳ ፍርድ ቤት ምድብ ችሎቶች የማሳደግ እቅድ ተይዞ እንቅስቃሴ ተደርጓል፡፡ ሆኖም ግን ይህንን ግብ ለማሳካት ከዚህ በጀት ዓመት በፊት የሚመለከታቸው የፍትሕ አካላት ማለትም ፍርድ ቤት፣ ፖሊስና ዐቃቢ ህግ በጋራ በመሆን ጥናት በማካሄድ ለክልሉ ርዕሰ መስተዳድር ጽ/ቤት ባቀረቡት የውሳኔ ሃሳብ ላይ ከክልሉ ነባራዊ ሁኔታ ጋር በሚነሳ ምክንያት ውሳኔ ስላልተሰጠበት ተግባራዊ ሳይደረግ የቆየ ሲሆን በክልላችን ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 281/2014 አንቀጽ 6(2) መሰረት የወረዳ ምድብ ችሎቶችን የማቋቋም ኃላፊነት ለጠቅላይ ፍርድ ቤት የተሰጠ ቢሆንም በክልላችን በተከሰተው የጸጥታ ችግር ምክንያት የታሰበውን የማስፋፋት ስራ ለመስራት አስቻይ ሁኔታዎች ባለመኖራቸው ምክንያት ተግባራዊ ማድረግ አልቻልንም፡፡

በሌላ በኩል ተቋማዊ ተደራሽነት ከማስፋት አንፃር ሊጠቀስ የሚገባው ከመጋቢት 01 ቀን 2016 ዓ.ም ጀምሮ በወልቃይት ጠገዴ ሰቲት ሁመራ፣ በሰሜን ጎንደር፣ በዋግኽምራ ብሄረሰብ አስተዳደር እና በሰሜን ወሎ ዞኖች ከፍተኛ የሆነ ፍትህ የማግኘት መብት ጥያቄ ምላሽ ያገኘበት ተግባር ነው፡፡ በዚህም መሠረት በድምሩ አንድ ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና 10 ወረዳ ፍርድ ቤቶች ተደራጅተው ሥራ ጀምረዋል፡፡ 30 ዳኞች፣ 24 የጉባኤ ተሿሚዎችና 306 የአስተዳደር ሠራተኞች በድምሩ 360 አስቀድመው የነበሩ እና በአዲስ የተሟሉ ሠራተኞች የዳኝነት አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛሉ፡፡ በዚህም በከፍተኛ ፍርድቤቱ 224 ጉዳዬች ቀርበው 183 ጉዳዬች እልባት አግኝተዋል፡፡ በወረዳ ፍርድ ቤቶች ደግሞ 2,608 ጉዳዮች የቀረቡ ሲሆን ከእነዚህ መዛግብት መካከል ለ2,163 መዛግብት ያህል እልባት መስጠት ተችሏል፡፡ በመሆኑም ይህ ተግባር የዳኝነት አገልግሎት ተደራሽነትን መፍታት ብቻ ሳይሆን ፍትህ የማግኘት መብት ጭምር የተረጋገጠበት ነው፡፡ይሁን እንጂ በክላስተር የተደራጁ ፍርድ ቤቶች በሁሉም ወረዳዎች በማስፋት እንዲሁም የሰው ኃይላቸውን በማሟላት በሚቀጥለው የበጀት ዓመት የበለጠ የዳኝነት አገልግሎት ተደራሽነትን ማረጋገጥ ይጠበቅበታል፡፡

## ቴክኖሎጂ በመጠቀም የርቀት ሙግት ስርዓትን ማጠናከር

የዘመኑን ቴክኖሎጂ በመጠቀም የርቀት ሙግት ስርዓትን ማጠናከር አንዱ ተደራሽነትን የምናሰፋበት መንገድ ሲሆን በ2015 በጀት ዓመት አገልግሎት በመስጠት ላይ ከነበሩ 11 የቪዲዮ ኮንፈረንስ ጣቢያዎችን በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ወደ 25 ለማድረስ በእቅድ የተያዘ ቢሆንም በክልላችን በተፈጠረው የጸጥታ ችግር ምክንያት በተለይም በምዕራብ አማራ አካባቢ የሚገኙ ፍርድ ቤቶች መደበኛ ስራቸውን መስራት የማይችሉበት ሁኔታ የተፈጠረ ከመሆኑም በተጨማሪ በፍርድ ቤቶቻች በደረሰ ጉዳት ምክንያት በቴክኖሎጅ መሳሪያዎች ላይ ከፍተኛ ጉዳት የደረሰ በመሆኑ በእቅዱ ልክ ተግባራዊ ማድረግ አልቻለም፡፡

## የእስልምና እምነት ተከታዮች የዳኝነት አገልግሎት

የእስልምና እምነት ተከታይ የማህበረሰብ ክፍሎች የዳኝነት አገልግሎትን ተደራሽ ለማድረግ በየደረጃው የሸሪያ ፍርድ ቤቶች ተቋቁመው አገልግሎት እየሰጡ ሲሆን በጠቅላይ ሸሪያ 22 ጉዳዮች ቀርበው ለ22 መዛግብት ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡በከፍተኛ ሸሪያ ፍርድ ቤቶች ደግሞ 202 ጉዳዮች ቀርበው 186 ጉዳዮች ውሳኔ አግኝተዋል 16 ጉዳዮች በቀጠሮ ተላልፈዋል፡፡ በወረዳ ሸሪያ ፍርድ ቤቶች ደግሞ 11,865 ጉዳዮች ቀርበው 11,353 መዛግብት ውሳኔ ሲያገኙ 512 ጉዳዮች ወደ ሚቀጥለው የበጀት ዓመት ተላልፈዋል፡፡ በአጠቃላይ በሸሪያ ፍርድ ቤቶች 12,089 ጉዳዮች ቀርበው 11,561 (95.63%) ጉዳዮች ውሳኔ አግኝተው 528 ጉዳዮች ተላልፈዋል፡፡

## በተዘዋዋሪ ችሎት የፍትህ አገልግሎት ተደራሽነት

የተዘዋዋሪ ችሎት አገልግሎት ፍርድ ቤቶች ወደ ህብረተሰቡ ቀረብ ብለው አገልግሎት የሚሰጡበት እና የፍትህ ተደራሽነትን ለማረጋገጥ ተግባራዊ ከሚደረጉ መንገዶች አንዱ ነው፡፡ በመሆኑም በ533 የጠቅላይ ፍርድ ቤት፣የዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና የወረዳ ፍ/ቤት የተዘዋዋሪ ችሎት ጣቢያዎች አማካኝነት 5,624 መዛግብት ቀርበው 2,822 መዛግብት እልባት/ውሳኔ እንዲያገኙ በማድረግ ወንድ 14,145 ሴት 4,130 በድምሩ 18,275 ባለጉዳዮች አገልግሎት እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡ ስለሆነም በየደረጃው የሚገኙ ፍርድ ቤቶች በቀጣዩ በጀት ዓመት የክልሉ ፀጥታ ሁኔታ በፈቀደ መጠን ተዘዋዋሪ ችሎት ጣቢያዎችን በማስፋትና እና የዙር ድግግሞሽን ወደ ስምንት ከፍ በማድረግ እና ልዩ ትኩረት ሰጥቶ በመስራት የዳኝነት አገልግሎት ተደራሽነትን ማስፋት ይጠበቅበታል፡፡

## በምድብ ችሎቶች የፍትህ አገልግሎት ተደራሽነት ማረጋገጥ

በበጀት አመቱ በየደረጃው በሚገኙ ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ተደራሽነትን በማስፋት የተገልጋዩን ህብረተሰብ ጊዜና ወጭ በመቀነስ የፍርድ ቤቶችን የአገልግሎት ተደራሽነትን አስፍቶና አጠናክሮ ለማስቀጠል ጠቅላይ ፍርድ ቤቱ በባህርዳር ካለው መደበኛ ችሎት በተጨማሪ በጎንደር፣ ደሴና ደብረ-ብርሃን ቋሚ ምድብ ችሎቶችን በማደረጀትና ተገቢውን ድጋፍና ክትትል በማድረግ አገልግሎት አሰጣጣቸው ተጠናክሮ እንዲቀጥል ተደርጓል። በመሆኑም በእነዚህ ቋሚ ምድብ ችሎቶች የተከናወኑ ተግባራት፡-በደሴ ምድብ ችሎት ከቀረቡ 4,201 የሰበር ጉዳዩች መካከል በእቅዱ መሰረት 78% ማለትም ለ3,277 መዛግብት እልባት ለመስጠት አቅዶ ለ3,659 (87.1%) መዛግብት ያህል እልባት በመስጠት አበረታታች ውጤት ማስመዝገብ ችሏል።እንዲሁም ከቀረቡ 2,843 የወንጀልና የፍትሃብሔር ጉዳዩች ውስጥ በእቅዱ መሰረት 82% ማለትም ለ2,331 መዛግብት እልባት ለመስጠት አቅዶ ለ2,170 (76.32%) መዛግብት ያህል እልባት መስጠት ችሏል።

በአጠቃላይ በምድብ ችሎቱ ለስራ ከቀረቡ 7,044 ጉዳዩች ውስጥ በእቅዱ መሰረት 78/82% ማለትም ለ5,608 መዛግብት እልባት ለመስጠት ታስቦ ለ5,829 (82.75%) መዛግብት እልባት በመስጠት እንደ ምድብ ችሎት ከእቅድ በላይ መፈጸም ተችሏል።በደብረ ብርሃን ምድብ ችሎት ከቀረቡ አጠቃላይ 1,202 ጉዳዩች ውስጥ በእቅዳችን መሰረት 82% ማለትም ለ967 መዛግብት እልባት ለመስጠት ታስቦ ለ1,114 (92.68%) መዛግብት እልባት በመስጠት ከእቅድ በላይ መፈጸም ችሏል።በጐንደር ምድብ ችሎት ከቀረቡ አጠቃላይ 2,335 ጉዳዩች ውስጥ በእቅዱ መሰረት 82% ማለትም ለ1,915 መዛግብት እልባት ለመስጠት አቅዶ ለ2,126 (91.05%) መዛግብ እልባት በመስጠት አበረታታች በሆነ ሁኔታ ከእቅድ በላይ መፈጸም ተችሏል።አጠቃላይ በ3ቱ ምድብ ቋሚ ችሎቶች 10,581 ጉዳዮች ለሥራ ቀርበው በእቅዱ መሰረት 78/82% ማለትም ለ8,490 መዛግብት እልባት ለመስጠት ታስቦ ለ9,069 (85.71%) ያህል በማስመዝገብ በምድብ ችሎቶች ደረጃ የበጀት ዓመቱን ግብ በአጥጋቢ ሁኔታ ማሳካት ችሏል።

### በጠቅላይ ፍርድ ቤት ባህርዳር ምድብ ችሎት

በጠቅላይ ፍርድቤት ባህርዳር ምድብ ችሎት በሰበር የቀረቡ መዛግብት ብዛት 8,387 ሲሆኑ የዚህን 78% ማለትም 6,542 መዛግብት ለመስራት በእቅድ ተይዞ 5,600 (66.77%) መዛግብት እልባት መስጠት ተችሏል።በፍትሃብሄር የቀረበ መዛግብት ብዛት 2,549 ሲሆን የዚህን 82%

ማለትም 2,090 መዛግብት ለመስራት በእቅድ ተይዞ 1,839 (72.15%) መዛግብት እልባት መስጠት ተችሏል፡፡

በጠቅላይ ፍርድቤት ባህርዳር ምድብ ችሎት በወንጀል የቀረበ መዛግብት ብዛት 1,197 ሲሆኑ የዚህን 82% ማለትም 982 መዛግብት ለመስራት በእቅድ ተይዞ 887 (74.1%) መዛግብትን ያህል እልባት መስጠት ተችሏል፡፡በአጠቃላይ በጠቅላይ ፍርድ ቤት ባህርዳር ምድብ በሶስቱም የስራ ሂደቶች በበጀት ዓመቱ የቀረቡ መዛግብት ብዛት 12,133 ሲሆኑ የዚህን 78/82% ማለትም 9,614 መዛግብት ለመስራት በእቅድ ተይዞ 8,326 መዛግብትን መስራት የተቻለ ሲሆን አፈጻጸሙም 68.62% መሆኑን መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ወደ ሚቀጥለው በጀት ዓመት የተላለፈ አጠቃላይ ብዛት 3,807 መዛግብት ናቸው፡፡

ከአሃዛዊ መረጃው መረዳት እንደሚቻለው የባህር ዳር ምድብ ችሎት ዕቅዱን ማሳካት አልቻለም፡፡ ለዚህም መሠረታዊ ምክንያቶቹ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ባህርዳር ምድብ ችሎት ከተለያዩ የክልሉ አካባቢዎች በተለይም ከደቡብ ጎንደር ከፍተኛ ፍርድ ቤት፣ ከባህርዳርና አካባቢው ከፍተኛ ፍርድ ቤት፣ ከአዊ ብሔረሰብ አስተዳደር ከፍተኛ ፍርድ ቤት፣ ከምስራቅ ጎጃም ከፍተኛ ፍርድ ቤት፣እንዲሁም ከምዕራብ ጎጃም ከፍተኛ ፍርድ ቤቶች በይግባኝና በሰበር የሚመጡ መዛግብት የሚታዩበት ምድብ ሲሆን፤ ባለው ግጭት ምክንያት ከእነዚህ አካባቢዎች ባለጉዳዮች በቀጠሯቸው ቀን ወደ ፍርድ ቤቱ መምጣት ባለመቻላቸው ምክንያት መዛግብት የተከራካሪ ወገኖች በሌሉበት አከራክሮ መወሰን ባለመቻሉ፤እንዲሁም እልባት የተሰጣቸውም መዛግብት ውሳኔውን ሁለቱም ወገኞች በተገኙበት ይፋ ማድረግ ካለመቻሉም በተጨማሪ በተዘዋዋሪ ችሎት ተደራሽ ወደ ሚደረጉ ዞኖች በመሄድ አገልግሎቱን መስጠት ባለመቻሉ የደብረ-ማርቆስ፣ የእንጅባራና የደብረታቦር ከተማ ተዘዋዋሪ ችሎት ቀጠሮ ይዘው የነበሩ መዛግብትን በተመለከተ ወደ ባለጉዳዮች ወደ ባህርዳር እንዲመጡ በማድረግ ለመስራት ጥረት የተደረገ ቢሆንም በተሟላ ሁኔታ ባለጉዳዮች መቅረብ የማይችሉባቸው ሁኔታዎች በመከሰታቸው ምክንያት እና የፍኖተ ሰላም መዛግብት ወደ ባህርዳር ማምጣት ባለመቻሉ ምክንያት በተዘዋዋሪ ችሎት መስራት የሚገባቸው መዛግብት አለመስራታቸው በምድብ ችሎቱ አፈጻጸም ላይ የራሱን ተጽዕኖ አሳድሯል፡፡ከዚህም በላይ ዳኞች በተረጋጋ ሥነ ልቦናዊ ሁኔታ ውስጥ ሆነው ሥራዎችን መፈጸም አለመቻል፣ በተለያዩ ምክንያቶች ለምሳሌ በወሊድ፤ በህመም በመሳሰሉት ሥራ ላይ በተሟላ ሁኔታ ያልተገኙ ዳኞች መኖራቸው፣ እንዲሁም የዳኞች የግል መዝገብ አፈፃፀም ከዳኛ ዳኛ መለያየት ለአፈፃፀሙ ማነስ የበኩላቸውን አስተዋፅዖ ያደረጉ ምክንያቶች ናቸው፡፡

## የፍርድ ቤቶችን አሰራር ማሻሻል

የፍርድ ቤቶችን የዳኝነት አገልግሎት ለማሻሻል ልዩ ልዩ አሰራሮችን መዘርጋት ተገቢነት ይኖረዋል፡፡በዚህ ረገድ አሰራርን በማሻሻል ረገድ ጥቅም ላይ ሲውሉ የሚችሉ ዋና ዋና ስልቶችም እርቅ ተኮር የፍትህ አስተዳደር፣ ነጻ የህግ ድጋፍ አገልግሎት እና ልዩ ልዩ ህጎችን አውጥቶ ተግባራዊ ማድረግ ተችሏል፡፡ ስለሆነም እነዚህን አሰራሮች ውጤታማ በሆነ አግባብ ስራ ላይ በማዋል የዳኝነት አገልግሎቱን ማሻሻል ስለሚገባ ይህንን ግብ ለማሳካት በበጀት ዓመቱ የተለያዩ ተግባራት ተከናውነዋል፡፡በመሆኑም የእርቅና ድርድር ስርዓትን በመዘርጋት አለመግባባትን በስምምነት የመፍታት ባህሉን የበለጠ ለማጠናከር በጥናት ላይ የተመሰረተ ፍርድ ቤት መር አስማሚነት ሥርዓት መዘርጋት እንዳለበት በአዋጅ ቁጥር 281/2014 ተደንግጓል፡፡ በዚህም መሠረት ጠቅላይ ፍርድ ቤት የፍርድ ቤት መር አስማሚነት አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 1/2016 በማውጣት በተወሰኑ ፍርድ ቤቶች በሙከራ ደረጃ እንዲጀመር አድርጓል፡፡ በሙከራ ደረጃ የተጀመረው ተግባር አፈፃፀሙ ሲታይ ለአስማሚዎች 1,020 መዛግብት ቀርበ ውላቸው 591 መዛግብት በስምምነት የተቋጩ ሲሆን በ359 መዛግብት ላይ ስምምነት ላይ መድረስ ባለመቻሉ ወደ መደበኛው የክርክር ስርዓት ተመልሰዋል፡፡70 መዛግብት ደግሞ በአስማሚነት ስርዓቱ በመታየት ላይ ናቸው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በመደበኛው የክርክር ስርዓት ጉዳያቸው እየታዩ ያሉ ባለጉዳዮች ጉዳያቸውን ህብረተሰቡ በሚጠቀምባቸው የተለመዱ የአለመግባባት መፍቻ ስርዓትን በመጠቀም በስምምነት ወይም በእርቅ ሊጨርሱ የሚችሉበትን ሁኔታ በመፍጠር 15,365 መዛግብት በእርቅ ታይተው ጉዳያቸው በስምምነት እንዲያልቅ ተደርጓል፡፡በዚህም መሰረት የሚዘጉ የፍትሃብሄር መዛግብትን መጠን ጠቅላላ ውሳኔ ካገኙ የፍትሃብሄር መዛግብት ውስጥ በ2015 ከነበረው 5.51% ድርሻ ባለበት ለማስቀጠል በእቅድ ተይዞ በ2016 በጀት ዓመት 322,064 እልባት ካገኙ የፍትሃብሔር ጉዳዬች መካከል በድምሩ 15,976 መዛግብት በእርቅና በስምምነት እልባት እንዲያገኙ በማድረግ አፈጻጸሙን 4.96% ማድረስ ተችሏል፡፡ስለሆነም አለመግባባትን በግራቀኙ ስምምነት መፍታት አሸናፊና ተሸናፊ የሌለበት ዘላቂ አለመግባባት መፍቻ መንገድ መሆኑን በመረዳት በየደረጃው የሚገኙ ፍርድ ቤቶችን የመፈፀም አቅም በማሻሻል አጠናክሮ ማስቀጠል ይጠበቅበታል፡፡

### ነጻ የህግ ድጋፍ አገልግሎት ተደራሽ ማድረግ

በየደረጃው የሚገኙ ፍርድ ቤቶች የተከላካይ ጠበቆችን አደረጃጀትና የሰው ሃይል በማጠናከር በራሳቸው ጠበቃ ለማቆም ለማይችሉ ተከሳሾች በነጻ የህግ ድጋፍ አገልግሎት ተደራሽ ለማድረግ በእቅድ ተይዞ በ2,975 መዛግብት በወንጀል ለተከሰሱ ጠበቃ ማቆም ለማይችሉ 3,988 ተከሳሾች ነጻ የሕግ ድጋፍ እንዲያገኙ በማድረግ ከእነዚህ ውስጥ በ1,547 መዛግብት የ1,917 ተከሳሾች ጉዳይ ውሳኔ እንዲያገኙ ማድረግ ተችሏል።ነጻ የህግ ድጋፍ ማግኘት የሚገባቸው ባለጉዳዮች ቁጥር ቀላል ባለመሆኑ የተከላካይ ጠበቆችን አደረጃጀት በማጠናከርና በግል ጥብቅና ከሚሰሩ አካላት ጋር ትስስር በመፍጠር አገልግሎቱን ማቅረብ ይጠበቃል። በዚህ ረገድ ጥናቱ ተጠናቋል። የበጀት አቅም ካልገደበም ወደ ተግባር የሚገባ ይሆናል።

### በወንጀል ፍትህ አካላት መካከል ቅንጅታዊ አሰራር መፍጠር

በወንጀል ፍትህ አካላት መካከል ቅንጅታዊ አሰራር ለመፍጠር በተደረገ ጥረት ዕቅድ ማቀድ፣ በቴክኒክ ኮሚቴ ችግሮች ላይ መነጋገር፣ ይህ አደረጃጀት እስከ ታችኛው መዋቅር ተደራጅቶ ችግሮችን እየፈታ እንዲሄድ ጥረት እየተደረገ ነው።ይሁን እንጂ ይህ የምክክር መድረክ በክልሉ ባለው የፀጥታ እና ደራሽ ሥራ ምክንያት በየጊዜው እየተገናኙ መምራት አልቻለም።

### የፍርድ ቤቶችን አሠራር ለማሻሻል

በስትራቴጅክ እና ዓመታዊ እቅድ ላይ በመመስረት ብቻ የፍርድ ቤቶችን አሠራር ለማሻሻል የሚደረገው ጥረት በተጠቃለለ የፍርድ ቤቶች ማሻሻያ ፕሮግራም መደገፍ እንዳለበት ታምኖ አገራዊ እና ክልላዊ የፍትህ ሥርዓት ማሻሻያ እንቅስቃሴን በተለይም የክልሉን የፍትህ ትራንስፎርሜሽን እቅድ መሰረት በማድረግ የሶስት ዓመት የተደራጀ የፍርድ ቤት ማሻሻያ እቅድ (ከ2016 — 2018 ዓ/ም) እና እቅዱን ለማስፈጸም የሚያስችል የአደረጃጃት እና የአሰራር መመሪያ ተዘጋጅቶ ከክልሉ የትራንስፎርሜሽን ስተሪንግ ኮሚቴ እና ከክልሉ ፍርድ ቤቶች የለውጥ (የማሻሻያ) አስተግባሪ ኮሚቴ ጋር የጋራ ተደርጎ እና በዳኞች አስተዳደር ዐቢይ ጉባኤ ጸድቆ ተግባሩ ወደ ትግበራ ገብቷል። እቅዱን ይበልጥ ለማዳበር አስፈላጊ የሆኑ ውይቶችን የማድረግ፣የማሻሻያውን አስፈላጊነት በተመለከተ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር የጋራ መግባባት እና ግንዛቤ እንዲያዝባቸው የማድረግ ስራ ተከናውኗል።

በተደረጉ የተለያዩ ውይይቶች የተነሱ መሰረታዊ ጉዳዬችን ግምት ውስጥ በማስገባት የማሻሻያ ፕሮግራሙን ከልሶ የሚያቀርብ ኮሚቴ እንደገና በማደራጀት የተከለሰውን እቅድ በአመራር ደረጃ የጋራ በማድረግ የመጨረሻውን እቅድ ለዳኞች አስተዳደር ዓቢይ ጉባዔ በማቅረብ ውይይት በማድረግ የጋራ የማድረግ ስራ ተሰርቷል። የፍርድ ቤቶች የለውጥ ፕሮግራም እቅድን ለክልሉ

ምክር ቤት አባላት በማቅረብ ውይይት ተደርጓል፣ ከምክር ቤት አባላት በውይይቱ የተነሱ እቅዱን የሚያዳብሩ ሃሳቦችም በግብዓትነት ተወስደዋል፡፡ በማሻሻያ ፕሮግራሙ ላይ በየደረጃው ከሚገኙ ፍርድ ቤቶች ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ውይይት ማካሄድ ተችሏል፡፡ በጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ደረጃ ደግሞ ከከፍተኛ ፍርድ ቤት አመራሮች፣ ምድብ ዳኞች እና አመራሮች፣ ከጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኞች እና ሰራተኞች ጋር ውይይት ማድረግ ተችሏል የተገኙ ግባቶችም የማሻሻያ ፕሮግራሙ አካል ተደርገዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በክልሉ ፍርድ ቤቶች የማሻሻያ ፕሮግራም የአደረጃጃት እና የአሰራር መመሪያን ለሚመለከታቸው ፍርድ ቤቶች የማስተዋወቅ ስራ ተሰርቷል፡፡

በምስራቅ አማራ ከሚገኙ ከፍተኛ ፍርድ ቤቶች እና ከጠቅላይ ፍርድ ቤቱ የደሴ እና ደብረብርሃን ምድብ ችሎች እንዲሁም ከባህርዳር ምደብ ችሎት የስራ ክፍል ሀላፊዎች ጋር መድረክ በማዘጋጀት የማሻሻያ ፕሮግራሙ ያለበትን ደረጃ እያንዳንዱ ፍርድ ቤት ሪፖርት እንዲያቀርብ በማድረግ የመገምገም እና ንቅናቄ የመፍጠር ስራ ተሰርቷል፡፡ የማሻሽያ እቅዱን እና እቅዱን ለማስፈጸም የወጣውን የአደረጃጀት እና የአሰራር መመሪያ በማዳበር እና በእነዚህ ላይ እውቅና በመፍጠር ከተከናወኑት የዝግጅት ተግባራት ባሻገር የማሻሻያው አካል የሆኑ የተለያዩ ተግባራት የተከናወኑ ሲሆን ዋና ዋናዎቹን ለመግለጽ ያክል፡-ከማሻሻያ እቅዱ ውስጥ የዳኝነት ነጻነትን፣ ግልጽነትን እና ተጠያቂነትን እውን ለማድረግ ከተቀረጸውን ፕሮግራ ውስጥ የስነ-ምግባር ተጠያቂነትን ለማረጋገጥ የታሰበበትን ስልት ሰነድ በማዘጋጀት በየደረጃው ከሚገኙ የፍርድ ቤት አመራሮች እና ከጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኞች እና የጉባዔ ተሿሚዎች እንዲሁም በክልሉ የፍትህ ሥርዓት ማሻሻያ ስትሪንግ ኮሚቴ ደረጃ ውይይት በማድረግ በክልሉ ፍርድ ቤት አመራሮች፣ ዳኞች እና ባለሙያዎች ላይ ከስነ-ምግባር እና ከችሎታ ማነስ ጋር ተያይዞ የሚነሱ ችግሮችን በውይይት፣ የቅሬታ መቀበያ አሰራር፣ የዳኝነት ኮንፈረንስ በማካሄድ እና ጥናት መሰረት በማድረግ መለየት እና ተገቢውን ማጣራት በማድረግ በህጎቹ አግባብ ተጠያቂነትን በማረጋገጥ የማጥራት ስራ ለመስራት የጋራ መግባባት ላይ ተደርሷል፡፡ ይህንን ተግባርም ከሌሎች የፍትህ ተቋማት ጋር በመቀናጀት ተግባራዊ ማድረጉ አፈጻጸሙን ውጤታማ ስለሚያደርገው በቅንጅት የሚሰራበት ስልት ሊነደፍ እንደሚገባ የጋራ ግንዛቤ ተወስዶበታል፡፡ በዚህም መሰረት የጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኞችን እና የጉባዔ ተሿሚዎችን የስነ ምግባር ሁኔታ በተመለከተ የዳሰሳ ጥናት በማድረግ የስነ ምግባር ማሻሻያ ስራዎችን ተግባራዊ ለማድረግ እና ተጠያቂነትን እውን ለማድረግ የሚያስችል መጠይቅ እና የጥቆማ መስጫ ሰነዶችን ለሚመለከታቸው አካላት በመስጠት መረጃዎችን ለዚሁ ዓላማ በተቋቋመ ኮሚቴ

አማካኝነት መሰብሰብ ተችሏል፡፡ ከባህርዳር ዩኒቨርሲቲ በኩል እየተደረገ ያለውን የስነ-ምግባር ጥናት ለሪፎርሙ ግብዓትነት ለመውሰድ እንዲቻል በጠቅላይ ፍርድ ቤቱ በኩል ለጉዳዩ ትኩረት በመስጠት ተገቢውን እገዛ እያደረገ ይገኛል፡፡

አሰራርን ለማሻሻል የሚያግዝ የህግ ማእቀፍ እንዲኖር ለማድረግ በ2015 በጀት ዓመት ከፀደቁትና በመተግበር ላይ ካሉት የፍርድ ቤቶች የማቋቋሚያ ማሻሻያ አዋጅ እና የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ማቋቋሚያ ማሻሻያ አዋጅ የሚመነጩ ደንቦችንና መመሪያዎችን በማውጣት ተግባራዊ ለማድረግ በእቅድ ተይዞ ወደ ተግባር የተገባበት ሁኔታ ያለ ሲሆን በዚህም የጉዳዮች ፍሰት አስተዳደር መመሪያ፣ የዳኝነት ስነ ምግባር እና ተጠያቂነት ደንብ ዝግጅት ተጠናቋል፡፡ እንደጸደቁም ተግባራዊ የሚደረጉ ይሆናል፡፡ በሌላ በኩል የዳኞችና ጉባኤ ተሿሚዎች የስራ አፈጻጸም ምዘና፣ የዳኞችና ጉባኤ ተሿሚዎች የፈቃድ አሰጣጥ እና የህክምና ማሰረጃ አቀራረብ መመሪያ፣ የፍርድ ቤት መር አስማሚነት መመሪያዎች ፀድቀው ወደ ሥራ ገብተዋል፡፡

## ውሳኔ የሚያገኙ መዛግብትን ብዛት መጨመር

በየደረጃው በሚገኙ ፍርድ ቤቶች የተሻሉ አሰራሮችን በማስፋት፣የስራ አፈጻጸም ምዘና ስርአትን በመተግበርና ተጨማሪ ዳኞችን በማሾም እንዲሁም የዳኞችን ውሳኔ የመስጠት አቅም በማጎልበት፣ በፍርድ ቤቶች ውሳኔ የሚሰጥባቸው መዛግብት ብዛት እንዲጨምር በማድረግ በበጀት ዓመቱ ማጠናቀቂያ በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት 72.31% የነበረውን አፈፃፀም ወደ 78%፣ በጠቅላይ ፍርድ ቤት 82% የነበረውን አፈፃፀም ባለበት ለማስቀጠል፣ በከፍተኛ ፍርድ ቤቶች 83.41% የነበረውን አፈፃፀም ወደ 90%፣ በወረዳ ፍርድ ቤቶች 95.66% የነበረውን አፈፃፀም ወደ 96% ከፍ ለማድረግ ታቅዶ በጠቅላይ ፍርድ ቤት የሚታዩ 22,714 የሰበር፣ የወንጀልና ፍትሐብሔር ጉዳዮች የቀረቡ ሲሆን ከእቅዱ (78/82%) 18,104 መዛግብት መካከል ለ17,395 (76.58%) እልባት መስጠት ተችሏል፡፡

በከፍተኛ ፍርድ ቤቶች ደረጃ ሊታዩ 48,415 የወንጀልና ፍትሐብሔር ጉዳዮች የቀረቡ ሲሆን ከእቅዱ (90%) 43,105 መዛግብት መካከል ለ38,349 (79.21%) እልባት መስጠት ተችሏል፡፡

በወረዳ ፍርድ ቤቶች ደረጃ ሊታዩ 363,956 ጉዳዮች የቀረቡ ሲሆን ከእቅዱ(96%) 349,398 መዛግብት ውስጥ 331,928 (91.2%) የሚሆኑት መዛግብት ውሳኔ ማግኘት ችለዋል፡፡ በአጠቃላይ በየደረጃው በሚገኙ ፍርድ ቤቶች ሊታዩ የቀረቡ ጉዳዮች 435,085 ሲሆን ከቀረቡ መዛግብት ውስጥ በእቅዱ መሰረት ለ410,606 መዛግብት እልባት ለመስጠት በእቅድ ተይዞ ለ387,672 መዛግብት እልባት መስጠት የተቻለ ሲሆን ከእቅድ 94.41% እና ከአቅርቦት ደግሞ

89.1% መፈጸም ተችሏል፡፡ይህ አፈጻጸምም ከክልሉ ነባራዊ ሁኔታ አኳያ ሲታይ እጅግ አበረታች አፈጻጸም እንደሆነ መውሰድ ይቻላል፡፡

የመዛግብት የማጣራት አቅምን ማሳደግን

የመዛግብት ማጥራት ማለት ፍርድ ቤቶች አዲስ ከሚቀርቡና ከመዝገብ ቤት ከተንቀሳቀሱ መዛግብት ውስጥ ምን ያህሉን እንደወሰኑና ከሚንከባለሉት ወይም ካለፈው ከተላለፉት ደግሞ ምን ያህሉን እያጠሩ ወይም እየወሰኑ እንደሆነ የሚያመላክት የቅልጥፍና መለኪያ ነው፡፡ በመሆኑም የስራ አፈጻጸም ምዘና ስርአትን በመተግበር፣ተጨማሪ ዳኞችን በማሾም እና የዳኞችን ውሳኔ የመስጠት አቅም በማጐልበት የመዛግብት የማጣራት አቅም ከፍ እንደሚል ይጠበቃል፡፡በዚሁ መሠረት በየደረጃው በሚገኙ ፍርድ ቤቶች በበጀት ዓመቱ ማጠናቀቂያ በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት 87.4% የነበረውን አፈፃፀም ወደ 107% ከፍ ማድረግ፣ በጠቅላይ ፍርድ ቤት 100.57% የነበረውን አፈፃፀም ወደ 101% ከፍ ማድረግ፣ በከፍተኛ ፍርድ ቤቶች 98.89% የነበረውን አፈፃፀም ወደ 101% ከፍ ማድረግና በወረዳ ፍርድ ቤቶች 100.29% የነበረውን አፈፃፀም ባለበት ለማስቀጠል ታቅዶ በሰበር ሰሚ ችሎት 8,072 በአዲስ የተከፈቱና ከመዝገብ ቤት የተንቀሳቀሱ ሲሆን 9,685 መዛግብት ያህል እልባት መስጠት የተቻለ ሲሆን አፈጻጸሙም 119.98% ደርሷል፡፡በጠቅላይ ፍርድ ቤት ደግሞ 7,157 በአዲስ የተከፈቱና ከመዝገብ ቤት የተንቀሳቀሱ ሲሆን 7,710 መዛግብት እልባት መስጠት የተቻለ ሲሆን አፈጻጸሙም 107.73% ሆኗል፡፡ በከፍተኛ ፍርድ ቤት አፈጻጸሙ 109.22% እና በወረዳ ፍርድ ቤት ደግሞ 98.68% መድረስ ችሏል፡፡በጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበርና መደበኛው እንዲሁም በከፍተኛ ፍርድ ቤቶች ደረጃ ግቡን ያሳካ ሲሆን በወረዳ ፍርድ ቤቶች ለግቡ የተቃረበ ቢሆንም ክልሉ ከአለፈበት ነባራዊ ሁኔታ አኳያ ሲታይ አበረታታች አፈጻጸም ማስመዘገብ ተችሏል፡፡

የፋይሎችን የመጨናነቅ መጠን መቀነስ

የፋይሎች መጨናነቅ መጠን ማለት በአጠቃላይ የቀረበው መዛግብት ክምችት ውሳኔ ካገኘው መዝገብ ጋር ሲነፃፀር ማለት ሲሆን ለዳኞች የተለያዩ የአቅም ግንባታ ስልጠናዎችን በመስጠት፣ ልዩ ልዩ የአሰራር ማሻሻያዎችን ተግባራዊ በማድረግ የፋይሎች መጨናነቅ ምጣኔ እንደሚቀንስ ይገመታል፡፡በዚህ መሠረት በየደረጃው በሚገኙ ፍርድ ቤቶች በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት 1ለ1.38 የነበረውን አፈፃፀም ባለበት ለማስቀጠል፣ በጠቅላይ ፍርድ ቤት 1ለ1.23 የነበረውን አፈጻጸም ወደ 1ለ1.2፣ በከፍተኛ ፍርድ ቤቶች 1ለ1.2 የነበረውን አፈጻጸም ወደ 1ለ1.05፣ በወረዳ ፍርድ ቤቶች 1ለ1.05 የነበረውን አፈጻጸም ወደ 1ለ1.01 ለማድረስ ታቅዶ ወደ ተግባር ተገብቷል፡፡በመሆኑም በየደረጃው የሚገኙ ፍርድ ቤቶች በበጀት ዓመቱ

የነበረውን አፈጻጸም ሲታይ በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት 1 መዝገብ እልባት ሲያገኝ 1.35 መዛግብት ሲከፈቱ፣ በጠቅላይ ፍርድ ቤቱ 1 መዝገብ እልባት ሲያገኝ 1.25 መዛግብት ሲከፈቱ፣ የከፍተኛ ፍርድ ቤቶች 1 መዝገብ እልባት ሲያገኝ 1.24 መዛግብት የተከፈቱ ሲሆን የወረዳ ፍርድ ቤቶች 1 መዝገብ እልባት ሲያገኝ 1.05 መዛግብት የተከፈቱ መሆኑን መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ስለሆነም በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ግቡን ያሳካ ሲሆን በቀሪ በየደረጃው በሚገኙ ፍርድ ቤቶች በበጀት ዓመቱ ግቡን ማሳካት ባለመቻሉ መዛግብት በከፍተኛ መጠን ያደሩ መሆኑን በመረዳት በቀጣዩ በጀት ዓመት የክልላችን የሰላም ሁኔታው በፈቀደ መጠን ልዩ ትኩረት በመስጠት ግባችንን ሊያሳክ በሚችል አግባብ መዛግብት ውሳኔ እንዲያገኙ ማድረግ ተገቢ ነው፡፡

## የዳኝነት አገልግሎት ጊዜን መቀነስ

በበጀት ዓመቱ ውሳኔዎችን በአጭር ጊዜ ውስጥ እልባት ለመስጠት የሚያስችሉ በርካታ እርምጃዎች የተወሰዱ ሲሆን ለአብነት ተከላካይ ጠበቃ ማቆም ለማይችሉና በከባድ ወንጀል ተጠርጥረው ለቀረቡ ተከሳሾች የተከላካይ ጠበቃ አገልግሎት እንዲያገኙ በማድረግ፣አማራጭ የሙግት መፍቻ ሥርዓት በመጠቀም፣የተፋጠነ የወንጀል ዳኝነት ስርዓት ተግባራዊ በማድረግ፣የምስክር ቃል እና ሌሎች ክርክሮችን በሪከርዲንግና ትራንስክራይቢንግ ማሽን በመታገዝ በመቅረጽ እና ወደ ጽሁፍ በመገልበጥ፣ትኩረት የሚሹ ጉዳዮችን በልዩ ችሎት በማስተናገድ፣የቀጠሮ ፖሊሲ ተግባራዊ በማድረግ እንዲሁም የዳኞችን ቁጥር በመጨመርና ክህሎታቸውን በስልጠና በማሳደግ ወደ ተግባር በመግባት በየደረጃው በሚገኙ ፍርድ ቤቶች የዳኝነት አገልግሎት ጊዜን የመቀነስ ስራ ተሰርቷል

በየደረጃው የሚገኙ ፍርድቤቶች የዳኝነት አገልግሎት ጊዜን የመቀነስ ስራ

| ተ.ቁ | የፍርድ ቤቱ ስም | ውሳኔ ያገኙ መዝገቦች | ከቀረቡ ከ30 ቀን በታች | ከቀረቡ ከ1 ወር እስከ 20 ወር | ከቀረቡ ከ2 ወር እስከ 6 ወር | ከ6 ወር እስከ አንድ አመት | ከ1-3 አመት | ከ3 አመት በላይ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ጠቅላይ ፍርድ ቤት | 17395 | 3733 | 2017 | 6595 | 4210 | 776 | 64 |

| | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 2 | ከፍተኛ ፍ/ቤቶች | 38349 | 16239 | 4811 | 8066 | 5723 | 3255 | 255 |
| 3 | ወረዳ ፍ/ቤቶች | 331928 | 236265 | 55067 | 34010 | 6129 | 444 | 13 |
| ድምር | | 387672 | 256237 | 61895 | 48671 | 16062 | 4475 | 332 |

## የዳኞችን መዝገብ ጥምርታ ስታንዳርድ ማሳደግ

ዳኞች የሚወስኑት መዝገብ እንደ ጉዳዩ ውስብስብነትና የክርክር ደረጃ የተለያየ ቢሆንም በበጀት ዓመቱ አንድ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኛ በአማካይ በወር 45 መዛግብት በአመት 450 መዛገብትን፣ አንድ የከፍተኛ ፍርድ ቤቶች ዳኛ በወር 30 በአመት 300 መዛግብት እና አንድ የወረዳ ፍርድ ቤት ዳኛ በወር በአማካይ 40 በአመት 400 መዛግብት ለመወሰን በእቅድ ደረጃ ተይዞ ወደስራ የተገባ ቢሆንም ሁሉም ፍርድ ቤቶች በክረምቱ ነሐሴና መስከረም ወር ላይ ለእረፍት ዝግ በመሆናቸው እና በክልሉ ውስጥ ባለው አለመረጋጋት ምክንያት በእቅዱ ልክ መስራት ባይችልም በጠቅላይ ፍርድ ቤት በአንድ ዳኛ በአማካይ በወር 23 መዛግብትን፣ በከፍተኛ ፍርድ ቤቶች በአንድ ዳኛ በአማካይ በወር 17 መዛግብትንና በወረዳ ፍርድ ቤቶች በአንድ ዳኛ በአማካይ በወር 24 መዛግብት ተወስነዋል፡፡

## የመጽናት ምጣኔን ማሳደግ

በየደረጃው በሚገኙ ፍርድ ቤቶች የዳኞችን አቅም እና ክህሎት ለማሳደግ በተሰራው ስራ በይግባኝ ቀርበው የሚፀኑ መዛግብት ቁጥር ከአመት አመት እየጨመረ መጥቷል፡፡ በዚህ መሰረት በጠቅላይ ፍርድ ቤት ታይቶ በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የመፅናት ምጣኔ 81.73% የነበረውን በዚህ በጀት ዓመት ወደ 87.5% ለማድረስ ታቅዶ አፈጻጸሙ 81.08%፣ በከፍተኛ ፍርድ ቤት ታይቶ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የመፅናት ምጣኔ 76.12% የነበረውን በዚህ በጀት ዓመት ወደ 84% ለማድረስ ታቅዶ አፈጻጸሙ 74.19%፣ በወረዳ ፍርድ ቤት ታይቶ በከፍተኛ ፍርድ ቤት የመፅናት ምጣኔ 65.77% የነበረውን በዚህ በጀት ዓመት ወደ 78.5% ከፍ ለማድረግ ታቅዶ አፈጻጸሙ 65.19% ላይ በመሆን በሁሉም ደረጃ በሚገኙ ፍርድ ቤቶች ግቡን ማሳካት አልተቻለም፡፡

## የመሻር ምጣኔን መቀነስ

በጀት ዓመቱ በተጠናከረ ሁኔታ ለዳኞች የተለያዩ ሥልጠናዎችን በመስጠት ክህሎታቸውንና ስነ-ምግባራቸውን በማሳደግ እንዲሁም የፍርድ ምርመራ ስራን አጠናክሮ በማስቀጠል በይግባኝ ቀርበው የሚሻሩ መዛግብት በጠቅላይ ፍርድ ቤት ታይቶ በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የመሻር ምጣኔ 11.61% የነበረውን ወደ 8% ዝቅ ለማድረግ ታቅዶ አፈጻጸሙ 11.35%፣ በከፍተኛ ፍርድ ቤት ታይቶ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የመሻር ምጣኔ 15.26% የነበረውን ወደ 10% ዝቅ ለማድረግ ታቅዶ አፈጻጸሙ 18.19%፣ በወረዳ ፍርድ ቤት ታይቶ በከፍተኛ ፍ/ቤት የመሻር ምጣኔ 22.98% የነበረውን ወደ 14% ዝቅ ለማድረግ ታቅዶ አፈጻጸሙ 27.27% ሆኗል፡፡

## የመሻሻል ምጣኔን መቀነስ

በየደረጃው በሚገኙ ፍርድ ቤቶች የዳኞችን አቅም እና ክህሎት በሥራ ላይ ሥልጠና በማሳደግ የውሳኔ ጥራትን በማሻሻል በይግባኝ ቀርበው የሚሻሻሉ መዛግብት በተጠናከረ ሁኔታ ለዳኞች የተለያዩ ሥልጠናዎችን በመስጠት ክህሎታቸውንና ስነ-ምግባራቸውን በማሳደግ እንዲሁም የፍርድ ምርመራ ስራን አጠናክሮ በማስቀጠል በይግባኝ ቀርበው የሚሻሻሉ በጠቅላይ ፍርድ ቤት ታይቶ በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የመሻሻል ምጣኔ 6.65% የነበረውን ወደ 4.0% ዝቅ ለማድረግ ታቅዶ አፈጻጸሙ 7.56%፣ በከፍተኛ ፍርድ ቤት ታይቶ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የመሻሻል ምጣኔ 8.626% የነበረውን ወደ 6% ዝቅ ለማድረግ ታቅዶ አፈጻጸሙ 7.6%፣ በወረዳ ፍርድ ቤት ታይቶ በከፍተኛ ፍርድ ቤት የመሻሻል ምጣኔ 11.25% የነበረውን ወደ 7.5% ዝቅ ለማድረግ ታቅዶ አፈጻጸሙ 7.54% ደርሷል፡፡

# ፍትህ

### ሰነድ ምዝገባና ማረጋገጥ ስራን በተመለከተ

በበጀት አመቱ ሰነድ ምዝገባና ማረጋገጥ ስራ ለመስራት በታቀደው መሰረት ወንድ 240,785 ፣ሴት 115,358 ድምር 368,875 ተገልጋዮች 226,946 ጉዳይ ይዘው መጥተው አገልግሎት አግኝተዋል፡፡ ከቴምብር፣ በጥሬ ከንዘብና ከአገልግሎት በጥቅሉ 880,180,692.90 ብር ገቢ ሆኗል፡፡

## ለመንግስት ተቋማት የተሰጠ አገልግሎት

የሕግ ምክር አገልግሎትን በተመለከተ በ12 ወራት ውስጥ 2,473 የሚሆኑ ጉዳዮች የያዙት የገንዘብ መጠን 42,771,797.00 ቀርበው ሁሉም ውሳኔ አግኝተዋል፡፡ለተቋማቱ የህግ ክትትል ማድረግን በተመለከተ ደግሞ ለ21 የመንግስት ተቋማት ክትትልና የህግ ምክር አገልግሎት እንዲሰጥ ተደርጓል፡፡

## ነፃ የህግ አገልግሎት

ነፃ የህግ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው 304 አረጋውያን፣ 307 ህፃናት፣ 253 ወጣቶች፣ 387 ገልማሶች፣ 95 አካል ጉዳተኞች፣ 3 የወንጀል ጥቃት ሰለባዎች፣ 25 ኤች.አይ.ቪ ህሙማን ና 411 ድሃ ይገኙበታል፡፡ድጋፍ ለማግኘት ፈልገው ለመጡ 100% አገልግሎቱን እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡

## የመንግስትን ንብረት ማስመለስና ገቢ ማድረግ

ከኦዲት፣ ከክስ፣ ከድርድር፣ከኪሳራ፣ ከሰነድ ምዝገባና ማረጋገጥ ስራወች ፣ከሲቪል ማህበረሰብ ምዝገባ ፣ ከጠበቆች ምዝጋባና ከሌሎች ልዩ ልዩ ጉዳዮች ገቢ የተደረግ ገንዘብ ተጠቃሎ ሲታይ ለመንግስት ብር 2,152,0183,010.03 በመሬት ደግሞ 22,995.033 ሄክታር እንዲሁም ከግለሰቦች ብር 10,391,284 በመሬት ደግሞ 8,488.2 ሄክታር ነው፡፡

## የሰብዓዊ መብት ጉዳዮች

የህፃናት ጋብቻና በሴቶችና በህፃናት ላይ የሚደርሰውን የኃይል ጥቃት በመከላከልና ምላሽ በመስጠት ዙሪያ እንዲሁም በፖሊስ ጣቢያ በጥበቃ ስር የሚገኙ ተጠርጣሪዎችን እና በማረሚያ ቤት የሚገኙ ተከሣሾችን እንዲሁም የፍርደኞችን አያያዝ ህግን የተከተለ ስለመሆኑ ማረጋገጥን በተመለከተ ስራዎች ተሰርተዋል፡፡

## በወንጀል ጉዳይ ዘርፍ የተከናወኑ ተግባራት

በ2016 በጀት ዓመት 16,910 መዛግብት ለአቃቢ ህግ ቀርበዋል፡፡ ከቀረቡት ውስጥ በ15,822 መዛግብት ላይ በዐቃቤ ሕግ ውሳኔ ያገኙ ሲሆን 368 መዛግብት ደግሞ በዐቃቤ ህግ እጅ የሚገኙ ናቸው፡፡ ስለሆነም መዛግብት የማጣራት ምጣኔ 97.73% ነው፡፡

## የፍርድ ቤት ክርክር በማድረግ የማሸነፍ ምጣኔ

በ2016 በጀት ዓመት 17,732 መዛግብት ለፍርድቤት ቀርበዋል፡፡ ከእነዚህ መካከል 8,633 መዛግብት ውሳኔዎች አግኝተዋል::በ7,637 መዛግብት ላይ ጥፋተኛ የሆኑ ሲሆን 996 መዛግብት ላይ ደግሞ ተከሳሾች በነጻ ተሰናብተዋል፡፡ የማስቀጣት ምጣኔ 88.46% ነው፡፡

## የተዘጉ መዛግብትና የመቋረጥ ምጣኔ

በበጀት ዓመቱ የተዘጉ መዛግብትና የመቋረጥ ምጣኔን በተመለከተ ለፍርድ ቤት ከቀረቡ 17,732 መዛግብት ውስጥ ተከሳሽ እና ምስክር ባለመቅረቡ የተዘጉ መዛግብት ቁጥር 2,787 ነው፡፡ የማቋረጥ ምጣኔ 15.72%ነው፡፡

## በወንጀል ጉዳይ ላይ ተከራክሮ የማሸነፍ ምጣኔ

የአማራ ክልል ፍትህ ቢሮ የፌዴራል ፍትህ ሚኒስቴርን ወክሎ በሚከራከርባቸው የወንጀል ጉዳዮች በ2016 በጀት ዓመት 706 መዛግብት ለዐቃቤ ህግ ቀርቦ 682 መዛግብት ውሣኔ አግኝተዋል፡፡ 24 መዛግበት በዐቃቤ ህግ እጅ የሚገኙ ናቸው፡፡ በዚህ ረገድ ያለው የማጥራት ምጣኔም 96.6 በመቶ ነው፡፡

## በዐቃቤ ሕግ ይግባኝ መዛግብትን ተከራክሮ ማሸነፍ

አጠቃላይ በ2016 በጀት ዓመት 661 መዛግብት የቀረቡ ሲሆን ከእነዚህም ውስጥ በ300 መዛግብት ውጤትን የሚለኩ ውሳኔዎች የተሰጡ ሲሆን በ252 መዛግብት ላይ ማሸነፍ የተቻለ ሲሆን በ48 መዛግብት ማሸነፍ አልተቻለም፡፡ የማሸነፍ ምጣኔ 84.0% ነው፡፡

## በፍርደኛ ይግባኝ ተከራክሮ ማሸነፍ

በ2016 በጀት ዓመት በወንጀል ጉዳዮች 1,356 መዛግብት የቀረቡ ሲሆን ከእነዚህ ውስጥ በ932 መዛግብት ላይ ውጤትን የሚለኩ ውሳኔ የተሰጠ ሲሆን በ826 መዛግብት ላይ በአሸናፊነት የተወሰነ ሲሆን በ106 መዛግብት ደግሞ ማሸነፍ አልተቻለም፡፡ የማሸነፍ ምጣኔ 88.63 በመቶ ነው፡፡

## ዐቃቤ ህግ  የሰበር አቤቱታ መዛግብት ተከራክሮ ማሸነፍ

በበጀት ዓመቱ በወንጀል ጉዳዮች የዐቃቤ ህግ ሰበር አቤቱታ ክርክር መዛግብት በተመለከተ 164 መዛግብት የቀረበ ሲሆን ከእነዚህም ውስጥ በ59 ውጤትን የሚለኩ ውሳኔዎች ተሰጥቷል፡፡ በ36 መዛግብት ማሸነፍ የተቻለ ሲሆን 23 ማሸነፍ አልተቻለም፡፡ የማሸነፍ አቅም 61.02% ነው፡፡

## በፍርደኛ ሰበር አቤቱታ መዛግብት ተከራክሮ ማሸነፍ

በፍርደኛ ሰበር አቤቱታ 599 የቀረበ ሲሆን ከእነዚህ ውስጥ በ249 መዛግብት ውጤትን የሚለኩ ውሳኔዎች ተሰጥቷል፡፡ በ214 መዛግብት በአሸናፊነት፣ በ35 መዛግብት በተሸናፊነት ተወስኗል፡፡ የማሸነፍ ምጣኔ 85.94% ነው፡፡

## እጅ ከፍንጅ ወንጀልን በተመለከተ

በ2016 ዓ.ም እጅ ከፍንጅ ወንጀልን በተመለከተ  በዞንና በወረዳ 608 መዛግብት የቀረቡ ሲሆን 500 መዛግብት ውሳኔ ሲያገኝ 108 መዛግብት ደግሞ በቀጠሮ ተላልፈዋል፡፡ አፈፃፀም 82.0% ነው፡፡

## በወንጀል አቤቱታ መልስ አሰጣጥና አፈጻፀም በተመለከተ

በበጀት አመቱ ከክልል እስከ ወረዳ ባሉ የዐቃቤ ህግ መስሪያቤቶች ውስጥ ከሚሰጣቸው አገልግሎቶች ጋር በተያያዘ በወንጀል ብቻ 6,382 አቤቱታዎች ቀርበው 6,356 ውሳኔ አግኝተዋል፡፡

## የወንጀል ዋስትናን በጥራት መስራት

በበጀት አመቱ የወንጀል ዋስትናን በጥራት ለመስራት በታቀደው መሰረት በአቃቤ ሕግ 10,132 አስተያየት እንዲሰጥበት ታዝዞ በ9,802 ላይ አስተያየት ተሰጥቷል፡፡ አፈጻጸም 96.74 % ነው፡፡

## የቀዳሚ ምርመራ ማድረግ

የምስክሮችን ቃል ለመጠበቅ ሲባል ህጉ የቀዳሚ ምርመራ ሊደረግባቸው ይገባል ባላቸው ጉዳዮች ላይ 100 % የቀዳሚ ምርመራ በማድረግ የምስክሮችን ቃል ለመጠበቅ ተችሏል፡፡

## የክስ አይቀርብም ዉሳኔ ጥራን ማስጠበቅ

በስር ዐቃቤ ህግ የክስ አይቀርብም የተሰጠባቸውን መዝገቦች ጥራት ማስጠበቅን በተመለከተ የወረዳን ውሳኔ የዞን አቃቤ ህግ ፣የዞንን ውሳኔ የክልል ዐቃቤ ህግ በመመርመር የውሳኔ አፈጻጸሙን 98% ማድረስ ተችሏል፡፡

## ስነ- ምግባርና ፀረ-ሙስና

የአብክመ የስነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን በክልሉ ውስጥ የፀረ-ሙስና ትግሉን ለማስተባበር እና ለመምራት የተቋቋመ መንግስታዊ ተቋም ነው፡፡ ዋነኛ ተልዕኮውም አግባብነት ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር የስነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ትምህርት ማስፋፋት፤ በተደራጀ የህዝብ ተሣትፎ ሙስናና ብልሹ አሠራርን በመከላከል ሙስናን የሚጠየፍ፤ አጥብቆ የሚቃወምና የሚታገል ህብረተሰብ መገንባት እና የግልፅነትና ተጠያቂነት አሠራርን ማረጋገጥ ነው፡፡

## ስልጠናና ግንዛቤ ፈጠራ ተግባራትን በተመለከተ

በ2016 በጀት ዓመት የስልጠናና ግንዛቤ ፈጠራ ዕቅድ 1,073,590፣ ክንውን ወንድ 323,359 ፣ሴት 311,064 ድምር 634,423 አፈፃፀም 59.09% ማድረስ ተችሏል፡፡ የሥነ ምግባር ሞራል ዕሴቶችን የሚገነባ መልዕክት በሬድዮ 4 ፣በቴሌቪዥን 2 ስፖቶችን ማስተላለፍ ተችሏል፡፡ ህዝባዊ በዓላትን ተጠቅሞ በሬዲዩ በእንኳን አደረሳችሁ መልዕክት ኮሚሽኑን ራዕይ ማስተዋወቅ ተችሏል፡፡ መልዕክቶች በማህበራዊ ሜዲያ በስራ ቀናት በቀን አምስት መልዕክት ቀመር የዓመቱ ዕቅድ 1,224 ክንውን 248 ወይም 20.26% ተከናውኗል፡፡እንዲሁም 16 የሬዲዮ ፕሮግራም እና 1 የሬዲዬ ጭውውት ማከናወን ተችሏል ፡፡በተጨማሪም በበኩር ጋዜጣ የመጣጥፍ መልእክቶችና ምስሎች 9 እንዲሁም በራሪ ወረቀቶችን ለአዋቂዎች13 እና ለህፃናትና ለወጣቶች 17 ማዘጋጀትና ግንዛቤ መፍጠር ተችሏል፡፡






በሥነ ምግባር ግንባታና ሙስና መከላከል ዙሪያ የተሰጠ ስልጠና (ኮምቦልቻ)

## የሙስና ተጋላጭነት ስጋት ጥናት

ለኮሚሽኑ በአዋጅ ከተሰጡት ተግበራት እና ሀላፊነት አንዱ ከፍተኛ በጀት እና ሰፊ የሠው ሀይል የሚያስተዳድሩ ተቋማትን አሰራር በመፈተሽ የአሰራር ክፍተት የሚታይባቸውን ተቋማት የአሰራር ሥተርዓታቸውን በጥናት በማረጋገጥ የመፍትሄ ሀሳብ ማቅረብ እና ከተቋሙ ጋር የምክክር መድረክ አዘጋጅቶ በመግባባት ወደ ትግበራ ማስገባት ነው፡፡ በመሆኑም በ2016 ዓ.ም ተግባሩን ለማከናወን 8 ታቅዶ 9 በማከናወን ከክልል እስከ ወረዳ ያለውን አደረጃጀት በመጠቀም በተከታታይ ድጋፍና ክትትል በማድረግ ዕቅድን ከ100% በላይ ማሳካት ተችሏል ፡፡

## የሀብት ማሳወቅና ምዝገባ ተግባራት

በአዎጅ ቁጥር 187/2003 የሀብት ማሳወቅና ምዝገባ ተግባራት የህዝብ ተመራጭ፣የመንግስት ተሿሚዎች እና የማስመዝገብ ግዴታ የተጣለባቸው ሠራተኞች እንዲያስመዘግቡ በሚደነግገው መሰረት በ2016 ዓ.ም 15,000 ታቅዶ 10,749 (71.66%) የተከናወነ ቢሆንም ከአለው ወቅታዊና ነባራዊ ሁኔታ ጋር ሲነፃፀር የተሻለ ነው ብሎ መውሰድ ይቻላል፡፡

## በትምህርት ተቋማት የስነ ምግባር እና የፀረ-ሙስና ክበባትን ማቋቋም

የሙስና ወንጀል እና ብልሹ አሰራር መበራከት የሥነ ምግባር ሞራል መሸርሸር ነው ተብሎ ይታመናል በመሆኑም የነገው የሀገራችን ተረካቢዎች ተስፋ ከሆኑ ህፃናትና ወጣቶች ላይ መስራት አማራጭ የሌለው ተግባር በመሆኑ በየትምህርት ቤታቸው በሥነ ምግባር ክበባት በማደራጀት ማብቃት ነው፡፡በመሆኑም በክልላችን በሚገኙ የመንግስትና የግል ትምህርት ቤቶች የሥነ ምግባር ክበባትን ለማቋቋም በተሰራው ስራ 9,253 መቋቋሙን ተክትሎ ቀሪውን ለማቋቋም የዓመቱ ዕቅድ 1,117 የክንውን 32 (2.86%) ነው፡፡

## አስቸኳይ መከላከልን በተመለከተ

አስቸኳይ መከላከል ዕቅድ እንደቀረበ ሲሆን የቀረበ ጥቆማ 399 ሲሆን ለፖሊስ ተጨማሪ ምርመራ የተላከ 36፣ በአስተዳደራዊ የተፈታ 200፣ በአስቸኳይ መከላከል የተፈታ 77 ወደ ሚቀጥለው የዞረ 86 ከብክነት የዳነ ሀብት በዓይነት 2,928.33 ካሬ ሜትር የከተማ ቦታ፣59.5 ኩንታል ማዳበሪያ ፣12 ዴስክቶኘ ፣ 48 ላኘቶኘ፣1 ኤልሲዲ፣ 1 ፎቶ ኮፒ፣7 ታብሌት ስልክ፣1 ጅፒኤስ፣1 ፕሪንተር፣1 ጀኔሬተር፣2 ሞተር ሳይክል፣1 ፍሪጅ፣100 ሊትር ነዳጅ እና 16 የቤት

ክዳን ቆርቆሮ እንዲመለስ ተደረጓል፡፡ አስቀድሞ ከተመዘበረው ውስጥ ከኦዲት ግብረ ሀይል ጋር በመተባበር ብር 3,483,249.28 ማስመለስ ተችሏል ፡፡

## አማራ ሚዲያ ኮርፖሬሽን

የአማራ ሚዲያ ኮርፖሬሽን በ2016 በጀት ዓመት የምልክት ቋንቋን ጨምሮ በአስራ አንድ ቋንቋ ዘገባዎችን በአራት ቋንቋዎች ጋዜጦችን፣ በሁለት የቴሌቪዥን እና በሰባት የኤፍ ኤምና የራዲዮ እንዲሁም በዲጂታል ሚዲያ ከባሕርዳር ዋናው ቢሮ፣ከደሴ፣ደብረብርሐን፣ አዲስ አበባ፣ ጎንደር እና ደብረ ማርቆስ በተጨማሪ በማቀነባበሪያ ቴክኖሎጂ በመታገዝ በክልሉ በሚገኙ ዞኖች በተመደቡ ዞን ሪፖርተሮች ከአራቱ አቅጣጫ ዘገባዎችን ለታዳምያን ከትላንት በተሻለ ለማድረስ በጥረት ውስጥ ይገኛል፡፡

## የሚዲያ ተደራሽነት

ከሚዲያ ተደራሽነት አንጻር በሚዲያ መሰረተ ልማት ተደራሽነት ካስቀመጣቸው ግቦች መካከል የጎንደርና ደብረ ማርቆስ ኤፍኤም ግንባታ አጠናቆ ርክክብ ማድረግ የተቻለ ሲሆን የኦቪቫን ግዥንም በማጠናቀቅ የተሟላ ርክክብ ለማድረግ የሚያስችል ስራዎች ላይ ይገኛል፡፡የደሴ ሚዲያ ኮምሌክስ ግንባታ በጥሩ ደረጃ 32.4 በመቶ የደረሰ ሲሆን የአዲስ አበባ ስቲዲዮና ራዲዮ ማሰራጫ ስራዎችም በጥሩ ደረጃ ይገኛሉ፡፡ሰቆጣ ኤፍኤም ግንባታ በወቅታዊ ሰላም ችግር ምክንያት ማጠናቀቅ ባይችልም በሚቀጥለው በጀት ዓመት የሚከናወኑ ተግባራትን ቅድመ ዝግጅት ማጠናቀቅ ተችሏል፡፡አዲስ አበባ ለሚገነባው የአሚኮ ሚዲያ ኮምፕሌክስ የቦታ ካሳ ክፍያ በክልሉ መንግስት እንዲሸፈን የተደረገ ሲሆን ቦታውን በተሟላ ደረጃ ተረክቦ በሚቀጥለው በጀት ዓመት ወደ ስራ የሚገባበትን ሁኔታ የማመቻቸት ስራ ተሰርቷል፡፡

## የይዘት ተደራሽነት

በይዘት ተደራሽነት አንጻር ሲታይ የአማራ ሚዲያ ኮርፖሬሽን የዘገባ ይዘቶች በአብዛኛው ፖለቲካዊና ማህበራዊ ይዘቶች ላይ ያተኮሩ ሲሆን በስፖርታዊና ምጣኔ ሀብት ይዘቶች ላይም መሻሻሎች የታዩበት ሲሆን መዝናኛ ዘገባዎች ላይ ዘርፈ ብዙ ስራዎችን መስራት እንደሚገባ ሪፖርቱ ያመላክታል፡፡አማራ ሚዲያ ኮርፖሬሽን በአማርኛ ቋንቋ 30,589 ዘገባዎችን ለማሰራጨት አቅዶ የተሰራ ሲሆን 30,705.5 ወይም 100.2 ማሳካት ተችሏል፡፡በተመሳሳይ በአሚኮ ኀብር ማሰራጫ ስምንት ቋንቋዎች 17,148 ዘገባዎችን በማዘጋጀት በአራቱም

የማስራጫ አማራጮች ለማስራጨት ታቅዶ 18,859 ወይም 109.9 በመቶ ማሳካት ተችሏል፡፡178 ወቅታዊ ጉዳዮችን የሚዳስሱ ፕሮግራሞችን አዘጋጅቶ ለማስራጨት ታቅዶ 168 ወይም 94 ዘገባዎችን ለማስራጨት ተችሏል፡፡

## የታዳምያንን እርካታና ተሳትፎ ማሳደግ

የታዳምያንን እርካታና ተሳትፎ የሚያሳድጉ ዘርፈ ብዙ ዘገባዎች የተሰሩ ሲሆን ከቀረቡት 1373 ጥቆማዎች በዜና ጉባኤ በማስወሰን 1331 ጥቆማዎችን ለስርጭት ማብቃት የተቻለ ሲሆን ከተለያዩ የኮሙኒኬሽንና ተቋማት የሚመጡ 1140 ዘገባዎችን አርትዎት በመስራት ለስርጭት ለማብቃት ታቅዶ 1872 ዘገባዎችን እሴት በመጨመር ለስርጭት ማብቃት ተችሏል፡፡በዚህም አሚኮ ከፍተኛ የሆነ የጥቆማ ዘገባዎችን በማስተናገድ ከደንበኞች ጋር የነበረው ቁርኝት ከፍተኛ መሆኑን ያመላክታል፡፡በተጨማሪም ከቀረቡት 26 ቅሬታዎች 24 የዘገባ ሽፋን በመስጠት እንዲፈቱ በማድረግ የታዳምያንና የህብረተሰቡን ችግሮችን ለመፍታት ጥረት ተደርጓል፡፡የአሚኮ ዘገባዎችን በአሚኮ ዲጂታል ሚዲያዎች ለህብረተሰቡ እንዲደርሱ በማድረግ የእርከታና ዲጂታል ሚዲያ መስተጋብርን እንደ አንድ አመላካች በመውሰድ በሁሉም የዲጂታል ሚዲያ አማራጮች 775,000 ታዳምያን የአሚኮን ዲጂታል ሚዲያ ቤተሰብ እንዲሆኑ ለማድረግ በተሰራው ስራ 333,080 ወይም 43.6 እድገት እንዲኖር የሚያስችሉ ዘገባዎች መሰራታቸውን ያመላክታል፡፡በዚህም ከአሚኮ ዘርፈ ብዙ የሚዲያ አማራጭነት አንጻር ብዙ መስራት የሚጠበቅ ሲሆን በወቅታዊው ችግርም ዘርፈ ብዙ ተግዳሮቶች ውስጥ ሆኖ እድገት መታየት መቻሉ አበረታች ስራ ነው፡፡

## የአሚኮን የገቢ አቅም ከማሳደግ

